
# ዮቶር

## ኮብላይ ካህን

5ተኛ ዕትም



ዓለማየሁ ደመቀ

Scanned with CamScanner

# ዮቶር

## (ኮብላይ ካህን)

ዓለማየሁ ደመቀ

2008 ዓ.ም

Scanned with CamScanner

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
© All Rights Reserved

© ዓለማየሁ ደመቀ
የመጀመሪያ ህትመት: (ሐምሌ 2008 ዓ.ም)
ሁለተኛ ህትመት: (ሐምሌ 2008 ዓ.ም)
ሦስተኛ ህትመት: ( ነሐሴ 2010 ዓ.ም)
አራተኛ ህትመት: ( መጋቢት 2011 ዓ.ም)
አምስተኛ ህትመት: (ሚያዝያ 2011 ዓ.ም)

ስልክ፡- +251 911 654598
ኢ-ሜይል፡- alexdemeke1@gmail.com
ድረ-ገፅ /facebook.com/ alexdyotor999
ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 30,261
አዲስ አበባ Addis Ababa
ኢትዮጵያ Ethiopia

ዲዛይን፡- መስፍን አድነው
ኮምፒውተር ጽሁፍ፡- ፍሬሰናይ ሽታዬ

የዚህን ምድር ህይወት አልፈው
ወደ ሌላኛው ዓለም ለተሻገሩት
ለወላጅ እናቴ ለወ/ሮ ጋረደች በቀለ ( አልሚ )
እና
ለወላጅ አባቴ ለአቶ ደመቀ ነጊያ
መታሰቢያ ይሁንልኝ

Scanned with CamScanner

## መግቢያ

"ይሄ ድርሰት እኔን የቃላቱ መፍሰሻ ቦይ ያደረገ ሌላ ጸሐፊ አለው።" ብዬ ለቅርብ ወዳጆቼ መናገር የጀመርኩት ገና ድርሰቱን መጻፍ በጀመርኩበት ሰሞን ነበር ። ከዘጠኝ ዓመት በፊት።

ልናገረው የፈለግኩትን ሀሳብ ያልገለፁልኝን፣ ያወሳሰቡብኝን ወይም ያቃለሉብኝን ምዕራፎች አስቀድደው ያስጣሉኝ ፤ በምትካቸውም ከሕይወት ትዕይንት መዝዘው ሀሳቦቼን የኳሏቸውና ያስመረቹቸው ተደጋጋሚ ግጥምጥሞሾች ነበሩ ።

ሀሳብ አልገለፅ ሲል ያማል ። ከዚህ ህመሜ ለመደበቅ ከምሸጊ ወጥቼ የወዳጆቼን ዓለም እቀላቀላለሁ ። በመሃል ታዲያ ስላለሁበት ሁኔታ አንድም ግንዛቤ ካልነበራቸው ወዳጆቼ አንደበት አንዲት ቃል አሊያም አንድ ታሪክ ይፈልቃል ። ወረቀት ላይ ትቼው የወጣሁትን ሀሳብ ብርሃን አልብሶ ፤ ድምፅ አበጅቶለት ፊት ለፊት የሚታይ ትዕይንት የማድረግ አቅም ያለው አንድ ገጠመኝ እሸለማለሁ።

ግጥምጥሞሹ መጀመሪያ ያስደንቀኝ ነበር ። የኋላ ኋላ ግን እኔው ራሴ በማየውና በምሰማው ነገር ውስጥ እንደሚከሰት የምጠብቀው ነገር መሆን ጀመረ ። ስለዚህም ነው "ይሄ ድርሰት እኔን የቃላቱ መፍሰሻ ቦይ ያደረገ ሌላ ጸሐፊ አለው።" ያልኩት ። ወዳጆቼን ከርዕሳቸው አውጥቶ የኔ ርዕስ ውስጥ የሚነከራቸው ፤ ለሌላ ጉዳይ በሄድኩበት ሀገር ፥ የአንድ ምዕራፌን ጉዳይ ከለበሱ እንግዶች ጋር የሚያውል ጸሐፊ ። ለዓመታት እኔ ጋር መኖሩን እንኳ ያላወቅኩትን ፤ ጸሐፊው ያልተገለፀበት አንድ ገፅ ታሪክ የያዘ ወረቀት ፤ የሱን ሀሳብ ከታጠቀ ምዕራፌ ጋር ቀጠሮ ያላቸው ይመስል በሰበብ መዝዞ ፊቴ የሚያስቀምጥ ጸሐፊ... በእነዚህ ሁላ ድንቅ ግጥምጥሞሾች ውስጥ እያሳለፈ ስለ ሕይወት የዕጣ ፈንታ ግጥምጥሞሽ ያስገፈኝ ጸሐፊ ።

እና ደግሞ የቀደሙ የሀገሬ እና የዓለሜ ደራሲዎች ከልጅነት እስከ እውቀት ውስጤ የዘሩት የጥበብ ዘር ፤ ጥበብ እንዲዘራበት የፈቀደው ልቤ ውስጥ አሻራና ተፅኗቸውን ማተማቸው ነውና እዚህ ድርሰት ውስጥ አሻራቸውም ተፅኗቸውም በሰፊው ይታያል ።

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

*ሆሣቤም እግር ባይኖረው*
*ሀልሜንም እክል ቢገጥመው*
*ምኞቴም እንደጉም በናኘ*
*ሥጋዬም የከፋው መናኛ*
*ቢሆንም...*
*እኔ አልተውም ዛሬም*
*ዳግም ሰማይ መንካትን ማለም*



# ክፍል አንድ

## ከብላይ ካህን

- 1 -

"ነፍስና ስጋችን የሚያዜሙት ዜማ ህብር ካልሆነ ውበትም ስምረትም ሆነ የተቃኘ መልዕክት ሊኖረው አይችልም።"

የሰው ልጅ አብዝቶ የሚያስበው ሁለት ነገሮችን ይመስለኛል። የመጀመሪያው ሊያገኘው የሚመኘውንና የራቀበትን፣ ሁለተኛው ደግሞ የሚሳሳለትንና እንዳያጣው የሚሰጋውን ነገር ነው ብዬ አስባለሁ።

እኔም የአዳም ልጅ ነኝና አብዝቼ እጨነቃለሁ። የምሳሳለትና እንዳላጣው የምሰጋውም ነገር አለኝ። የምመኘውና ላገኘው ያልቻልኩት ነገርም አለኝ።

ዛሬ ከባዱን ጭንቀቴን ይበልጥ አከብጄ ልጨነቅበት ከተማዩን ሸሽቼ፣ ሰው ከማይደርስበት ጫካ መሃል፣ ከአንዲት ትንሽ ጅረት አጠገብ ድንጋይ ላይ ተቀምጫለሁ።

ከ30 ዓመታት በላይ እዚህች ምድር ላይ ኖሬያለሁ። የምፈልገውንም ለማግኘት ብዙ ወጥቼ ወርጃለሁ፤ ግን በመንገዴ ላይ እንዳለሁ ቢሰማኝም የተጓዝኩት ቅርብ ነው፤ ያለመጓዝን ያህል የቀረበ መንገድ። ያሰብኩት ሩቅ ለመጓዝ ነበር። ለመድረስ ያሰብኩበት ሥፍራ ከአድማሱም በላይ ርቆ ይታየኛል። አንዳንዴ ትንፋሽ ለመሰብሰብ መንገዴ ላይ ቁጢጥ ብዬ "የሆነ አቋራጭ መንገድ ይኖር ይሆን?" እላለሁ። አቋራጭ መንገድ ገጥሞኝ ባያውቅም።

Scanned with CamScanner

ብዙ የምቀናባቸው ሰዎች አሉ:: አንዳንዶቹ መድረሻቸው ላይ በቀላሉ ቆመው ያየኋቸው ናቸው:: ሲሎቹ ደግሞ መድረሻም ሆነ መነሻ ያላቸው ሳይመስል እጅጉን በገዘፈ ሰላም የሆነ ቦታ እንደተደላደሉ ቆመው ያገኘኋቸው ናቸው፤ ግን ሰላም አላቸው:: ሰላም ካላቸው ደግሞ ወይ ደርሰዋል አሊያም የሚሄዱበት የላቸውም ማለት ነው::

የእኔ ነፍስ ግን ሰላም የላትም:: መንገደኛ ናት:: የወደደችው የራቀባት፣ የተመኘችው ያልሆነላት ስደተኛ ነፍስ:: ለመሆኑ ይሄ መንገድ ካሰብኩበትስ ያደርሰኝ ይሆን?... እውነት ግን ባያደርሰኝስ?...ካለምኩበት ጭራሽ የሚያርቀኝ መንገድ ቢሆንስ?.... ለመሆኑ ይሄንን መንገድ ለስንት ዓመት ያህል ተጓዝኩበት?.. ለምንድነው ከአስር ዓመት ያላነሰ ተጉገዤ ሳለ፤ ዛሬም በመንገዴ ላይ የማየው ነገር ሁሉ ተመሳሳይ የሚሆንብኝ? መንገድ ሁሉ በተመሳሳይ ነገሮች የተሞላ ሆኖ ነው? ወይስ እኔው ራሴ ወደፊት ከመጓዝ ይልቅ መላልሼ እየሄድኩባቸው?...

ዛሬ እዚህ ጅረት አጠገብ ያስቀመጠኝ ይሄ ሀሳቤ አሳስቦኝ ነው:: መልስ የሚሻ ከባድ ጥያቄ ገጥሞኝ:: ነፍሴ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ የማይኖራት ከሆነ እዚያ ሩቅ ለመሄድም አቅሙ የላትም ማለት ነው:: ይሄ ትንሽ ነገር ካልተገለፀልኝ እንደምን የከበደውን ነገር ማግኘት ይቻለኛል?

ዛሬ ከዚህ ጅረት ያለምንም የብርሃን ፍንጣቂ አልነሳም:: ከተነሳሁ ወይ ብርሃን ተገልፆልኛል፤ አሊያም የምሄድበትም ሆነ መድረሻ የለኝም ብዬ እጄን አርፎ ለመቀመጥ ሰጥቻለሁ ማለት ነው::

ለሰዓታት አሰላሰልኩ፤ ግን ምንም የሚረባ ሀሳብ አልመጣልኝም:: ተስፋ ወደመቁረጡ ነኝ:: ለባከኑት የወጣትነቴ አስር ዓመታት እርሜን አውጥቼ የምመለስበት ሰዓት ደረሰ:: ሐዘን ይሁን ፍርሃት ያልለየሁት ስሜት ተጫነኝ:: ለመሆኑ ከዚህ በኋላ እኔ ማን ነኝ? ከዚህ በፊት የገነባሁት እኔነቴስ ምን ሲባል ነው?...



ይሄን እያሰላሰልኩ ሳለ ጭነት የተጫነ አህያ ከጀርባዬ በኩል መጥቶ በስተቀኜ አልፎኝ ከጅረቱ ውሃ መጠጣት ጀመረ::... እንግዲህ ይሄንንም ጨርሼ አስብ ዘንድ አልተፈቀደልኝም ማለት ነው:: ሰው አይደርስበትም ያልኩት ዱር እንዳሰብኩት ሰው አልባ አልሆነም:: ጭነት የጫነ አህያ ካለ ባለቤቱም ቅርቤ አለ ማለት ነው:: ወዲያውም የእርምጃ ኮቴ ተሰማኝና ወደ ኋላዬ ዞሬ ተመለከትኩ:: አንድ ፀጉሩና ፂሙ የሸበተ ሰው በፈገግታ ተሞልቶ ወደ እኔ መጣና:-

"እንዴት ውለሃል?" ብሎኝ ከጎኔ ተቀመጠ::

"ደህና_" አልኩት ደህንነት በተራበ ባዶ ድምፅ:: እናም ፀጥ ያለ የነበረውን ዱር ትቼ ወደተመሳቀለው ከተማዬ ልመለስ ብድግ አልኩኝ:: ሰውየው ከተቀመጠበት ሆኖ ሽቅብ ተመለከተኝና...

"ብቸኝነትህን ወሰድኩብህ መሰል" አለኝ ፈገግ ብሎ:: ፈገግታው ውስጥ የተመለከትኩት ጥልቅ ሰላምና እርካታ አስቀናኝ::

'ይሄስ ከየትኞቹ ወገን ይሆን?... ያለመበት ደርሶ የተገኘ ሰላም ይሆን? ወይንስ የሚሄድበት የሌለውና በእርጋታ ውስጥ ያለ ሰላም?' ብዬ አሰብኩኝ::

"እኔ ረጅም መንገድ ተጉገዤ ነው እዚህ የደረስኩት፤ ገና ደግሞ ረጅም መንገድ ይጠብቀኛል:: በዚህ መሃል ትንሽ አረፍ ብሎ ቀልብን መሰብሰብ ደግሞ መልካም ነው::... አንተ መመለስህ ነው መሰል፤ እስቲ ትንሽ አረፍ በልና እንጫወት::" ብሎ ሰላማዊ ፈገግታውን በድጋሚ ጋበዘኝ::

ሀሳቤና ንግግሩ ተምታቱብኝ:: 'አሁን ስለሱ ያሰብኩትን ነው የመለሰልኝ? ወይንስ በአጋጣሚ እሱ ራሱ ከአህያው ጋር ስለሚያደርገው ጉዞ ነው ያወራኝ? እንደዚያ ከሆነ 'አንተ መመለስህ ነው መሰል' ሲል ምን ማለቱ ነው? ወደ ቤትህ ማለቱ ነው?... ከየት አቅጣጫ እንደመጣሁ ምን አውቆ ነው መመለስህ ነው ማለቱ?.... ለምን 'መሄድህ ነው' አላለም?...

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ወይንስ ከረጅሙ ጉዞዬ ማፈግፈጌን ነው የነገረኝ?
ለማንኛውም ተመልሼ ቁጭ አልኩኝ:: አንድም የምሄድበት የለኝም፤
ሌላም የሰውየው ፈገግታ ያረጋጋል::
"ከከተማው ይልቅ እዚህ ሰላም አለ:: ለምን ይመስልሃል?" አለኝ ገና ከመቀመጤ::

"ከተማው ግርግር ስለሆነና ብዙ ድምፅ ስለሚበዛበት ነው::"

"ከተማው ግርግር ስለሆነና ብዙ ድምፅ ስለሚበዛበት ነው::"

"ከተማው ግርግር ስለሆነና ብዙ ድምፅ ስለሚበዛበት ነው::" "እዚህም ብዙ ድምፅ አለ:: በእርግጥ አላስፈላጊ ግርግር እዚህ የለም:: እዚህ ያለው ድምፅ የማይረብሸው ሥርዓት ያለውና ህብር ሆኖ የሚፈስ ተፈጥሯዊ ድምፅ ስለሆነ ነው:: ለመሆኑ ብዙ ጊዜ ወደዚህ ትመጣለህ?"

"ዛሬ ገና መምጣቴ ነው::"

"አንተ ብቻ ሳትሆን ዓለም ሁሉ ከተፈጥሮ እየራቀ ነው:: እዚህ ለምን ያህል ሰዓት ተቀመጥክ?"

ሰዓቴን ተመለከትኩና "ከሦስት ሰዓት በላይ::" ብዬ መለስኩለት::

"ታዲያ ምን አየህ? ምን ሰማህ?"

"ምንም:: በራሴ ሀሳብ ሰማስን ነበር::"

"ሀሳብ የሚያበዙ ሰዎች ነፍሳቸውንም ሆነ ተፈጥሮን አያዳምጡም:: በሰመረ ህብር የድምፅ ቃና ውስጥ የሙዚቃን ውበት ማድመጥ እንደሚቻል ሁሉ፤ ህብር ባለው ከንውን እና እንቅስቃሴ ውስጥ ውበትና ስኬት አለ::

"ነፍስና ስጋችን የሚያዜሙት ዜማ ህብረት ከሌለው ውብትም ሆነ መልዕክት ሊኖረው አይችልም:: ንጋት ላይ ተጋድመህ የወፎችን ዝማሬ ስትሰማ፤ ዛፉ፣ ሳር ቅጠሉ፣ ወንዙ ሁሉ በልቦናህ እብሮ የሚታይህ፤ተፈጥሮ በተቆራኘችበት ምትሃታዊ ኃይል ሳቢያ ነው:: የሰመረና የተዋበ የነገሮች ውህደት የመሰረተው ምትሃታዊ ኃይል..." ብሎ ጨዋታውን አቋረጠና ሩቅ መመልከት ጀመረ::



'ይሄ ሰው ምንድን ነው?... ራሴን የወቀስኩት እንሶ በማላውቀው ሰው መወቀሴ ቢያናድደኝም፤ የሚናገረው ነገር ጥልቅና እውነት ነው:: ደግሞም መልዕክቱ በቀጥታ እኔን የሚመለከትም መሰለኝ::

"ቅድም ገና ሩቅ እጓዛለሁ ብለኸኝ ነበር:: ወዴት ነው የምትሄደው?" ብዬ ጠየኩት::

"ሰዎች ወደማይደፍሩት ሥፍራ::" አለኝና ዘወር ብሎ ተመለከተኝ::

"ሰዎች ወደማይደፍሩት ሥፍራ የሚጓዝ ሰው ወይ ደንታ ቢስ አሊያም ሰዎች የሰጉትን ነገር ለመቀበል የቆረጠ ጀብደኛ መሆን አለበት:: አንተ ከየትኛው ነህ?"

"እኔ ከሁለተኛው ወገን ነኝ:: ሰዎች የፈሩትን ነገር ለመቀበል የቆረጥኩና ደጋግሜም የተጋፈጥኩ ነኝ:: አንተስ ወዴት ነው የምትሄደው?"

"እኔ... እንጃ! እስካሁን አንድ መሄጃ ያለኝ ይመስለኝ ነበር፤ አሁን ግን ተጠራጠርኩኝ::" አልኩት ተስፋ መቁረጤን በሚያሳብቅ ድምፅ::

"ለምን?" አለኝ የአዛኝነት ቃና ባለው ድምፅ::

"ከመቅረብ ይልቅ እየራቅኩ መሄዴ ታወቀኝ::"

"እና የትም አልደረስኩም ብለህ አሰብክ?"

"አዎ::" ብዬ መለስኩለትና 'ለምንድነው እዚህ ቁጭ ብዬ ከማያገባው ሰው ጋር የምዘበዝበው?' ስል አሰብኩ:: እንግዳው ሰው ግን አልለቀቀኝም::

"አንድ ቦታማ ደርሰሃል:: ምናልባት ካለምከው አልደረስክ ይሆናል:: ከተነሳህበት ግን ተንቀሳቅሰሃል:: ያ ማለት ደግሞ አንድ ቦታ ደርሰሃል:: ያንተ ጥያቄ 'ካለምኩበት ቶሎ አልደረስኩም' ከሆነ ለምን ቶሎ እንዳልደረስክ ውስጥህን መፈተሽ ብቻ ነው የሚጠበቅብህ:: ምናልባትም ከነፍስህ ዋና ዓላማ ይልቅ ይበልጥ ትኩረት የሰጠኸው ለሌላ ጉዳይ ሊሆን ይችላል:: በዚህ መንገድ አስበኸው ታውቃለህ?... በህይወትህ ውስጥ ከሁሉም የሚበልጥብህ ነገር የቱ ነው?... ያንን ከመለስክ ሌላውን ነገር

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ሁሉ ለዚያ ታላቅ ነገር መስዋዕት ለማድረግ መጨከን ይኖርብሃል:: ይሄንን መስዋዕትነት ሳይከፍል ማንም ታላቅ መሆን አይችልም::"

የሰውየው ንግግር እስከዛሬ እየኖርኩት ግን ያላስተዋልኩትን የሕይወቴን አንኳር ምስጢር በግልፅ የሚጠቁም ሆነብኝ:: 'ስለምንድነው እያወራን ያለነው? እንዴት ጨዋታችን ውስጤ ባመቅኩት ምስጢር ላይ ሊያጠነጥን ቻለ?... ስለግል ሕይወቴ ምንም ነገር ሳልነግረው እሱ እንዴት የእኔን ታሪክ የሚያውቅ ያህል ምስጢሬን ይጠቁመኛል?' ግርም አለኝና ማንነቱን ለማወቅ ጓጉሁ::

"አሁን ያወራኸኝ ነገር በቀጥታ የእኔን ሕይወት የሚመለከት ነው:: ስለኔ ሕይወት ምንም ሳልነግርህ የልቤን እየነገርከኝ መሆኑ ደንቆኛል:: እንዴት ታሪኬን ሳታውቅ ምስጢሬን እንዲህ ልትገልፀው ቻልክ?... ይቅርታ አድርግልኝና አንተ ማን ነህ?" ጠንከር አድርጌ ጠየቅኩት::

"የእኔን ማንነት ማወቅህ የራስህን ማንነት የማወቅን ያህል አርባና የለውም:: ስለ እኔ ማወቅ ከፈለግክ ግን እኔ ካህን ነኝ:: ገበሬም ነኝ:: እንዲሁም መንገደኛ ነኝ:: ዮቶር ብለህም ጥራኝ::

"የእኔን ማንነት መጠየቅህ ግን አንድ ነገር አስታወሰኝ:: ብዙ ሰዎች የራሳቸውን ማንነት ከመረዳት ይልቅ የሌሎችን ማንነት በመጠየቅና በመመርመር ዕድሜያቸውን ያባክናሉ:: እነዚህ ሰዎች የራሳቸውን የታሪክ አሻራ ትተው ከማለፍ ይልቅ ጥቂቶች ታሪካቸውን ሰርተው እንዲያልፉ መሰላል በመሆን ያገለግላሉ:: ራሳቸው ሊፅፉት የሚችሉት ታሪክ አፍንጫቸው ስር ሳለ፤ ሌሎች ያንን ታሪክ እንዲፅፉት መረማመጃ መንገድ ይሆናሉ:: እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ:: የኢትዮጵያ ታሪክ የማን ታሪክ ነው ትላለህ?"

"ማለት?... ያው የኢትዮጵያ ታሪክ ነዋ!" ጥያቄው ግራ አጋባኝ::

"ኢትዮጵያ ማን ናት?"



"ኢትዮጵያማ ኢትዮጵያውያን የሚኖሩባት መሬት ናት::" እሁንም የጥያቄው አካሄድ ግራ አጋብቶኝ መለስኩለት::

"ጥያቄዬ ከዚህም በላይ ሰፋ ተደርጎ ሊመለስ ይችላል:: ግን ለነጥባችን የሚሆነውን መልስ ሰጥተኸኛል:: እንግዲህ የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት በነዋሪዎቿ የተሰራ ታሪክ ማለት ነው:: በህዝቧ:: ግን ያ የተፃፈው ታሪክ በትክክል ህዝቡን ይወክላል?"

"ጥያቄው አልገባኝም::" ብዬ በገረሜታ ተመለከትኩት::

"እንግዲያው ቁም ነገሩን እኔ ላብራራልህ:: የአድዋ ድል ሲነሳ ሁሌም አብረው የሚነሱ ሁለት ስሞች አሉ:: አፄ ምኒልክና እቴጌ ጣይቱ:: ከዚያ ቢቀጥል ጥቂት ራሶች፣ ጥቂት ፊታውራሪዎች፣ ጥቂት ደጃዝማቾች እና የመሳሰሉት ያንን ታሪክ ይጋሩታል:: የተረፈው ሕዝብ ግን እንዲሁ በደፈናው "ጀግና ህዝብ" ተብሎ ይታለፋል:: በስሙም በቅርፁም ታሪኩ ሳይፃፍ ተደፋፍኖ ይኖራል::

ያ ሁሉ ጀግና፣ ስንት ጠላት የጣለ ያ ሁሉ የቁርጥ ቀን ጀግና ስሙ እንኳ በዚያ የታሪክ መዝገብ ላይ አልሰፈረም:: ስለዚያ እኒያ ጀግኖች፣ ጥቂቶች ለትውልድ የሚተላለፍ ታሪካቸውን እንዲፅፉ ደማቸውን ቀለም፤ አጥንታቸውን ብዕር፣ ቆዳቸውን ብራና አድርገው አልፈዋል:: ያ ማለት ግን የታሪክ መዝገቡ ባያውቃቸውም ወደዚህች ዓለም የመጡበትን የሕይወት ተልዕኮ ከግብ ያደረሱ ከመካከላቸው የሉም ማለት አይደለም:: በስም ከተጠቀሱትም መሳፍንት ይበልጥ የነፍሳቸውን ጥሪ እውን ያደረጉ ጥቂት ጀግኖችም ነበሩ::... ሆነም ቀረም አብላጫው የዓለም ታሪክ ብዙሃኑን የገበረ የጥቂት ግለሰቦች ታሪክ ነው::

"ይሄንን ጨዋታ ስናጠቃልለው እግዚአብሔር አንተንም ሌሎች የነፍስ ጥሪያቸውን ያሳኩ ዘንድ መንገድ እንድትሆን ሰርቶሃል:: የሰው ልጅ ሁሉ አንዱ ለሌላው መልካም መንገድ እንዲሆን ጭምር ነው የተፈጠረው::

መረዳት ያለብህ ቁም ነገር ግን ለሌሎች መንገድ ከመሆንም በላይ ራስህ ወደዚህች ምድር የመጣህበትን የሕይወት ተልዕኮ አሳክተህ እንድትረካ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ አንተ ለሌሎች መንገድ እንደሆንከ ሁሉ፣ አንተ ሳታስተውለው ሌሎችም ወደ ነፍስህ ተልዕኮ እንድታቀና መንገድ ሆነውልሃል፡፡ ወደፊትም ቢሆን ሰዎችም ሆኑ መላው ተፈጥሮ ወደ መንገድህ እንድታቀናና ካለምከበት እንድትደርስ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡" አለና ፊቱን ከጅረቱ ውሃ እየጠጣ ወዳለው አህያው መለሰ፡፡

"አሁን የነገርከኝ ነገር እውነት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ግን አስቤው አላውቅም ነበር፡፡" አልኩትና የነገረኝን ማብሰልሰል ያዝኩኝ፡፡ ጥቂት በሀሳብ እንደተዋጥኩ ዋናውን ጥያቄዬን እንዳልመለሰልኝ አስታወስኩ፡፡

"ግን ምንም ሳልነግርህ ጉድለቴንና ምስጢሬን እንዴት ልትነግረኝ ቻልክ?" አልኩት መለስ ብዬ፡፡

"አንተ እንድታውቅና እንድታደርግ የተፈቀደልህ ነገር እንዳለ ሁሉ እኔም ይሄን፣ ይሄን ጭምር እንዳውቅ የተፈቀደልኝ ነኝ፡፡ ረጅም መንገድ ተጉገለሁ አልኩህ እኮ፡፡" ብሎኝ ፈገግ አለ፡፡

"ይሄ ማለት የሆንኩትን፣ያደረግኩትንና የፈለግኩትን ታውቃለህ ማለት ነው?" አልኩት ተገርሜ፡፡

"አዎ፡፡ እጅ ሰጥተህ ልትመለስ ስትል ነው ትንሽ ላወራህ የመጣሁት፡፡ አላስታወስከኝም እንጂ ከዚህ በፊትም አግኝተኸኛል እኮ፡፡"

ግራ ተጋብቼ "እኔ'ንጃ ምንም ትዝ አላልከኝም፡፡" .እያልኩ ማብሰልሰል ያዝኩኝ፡፡

"ለማስታወስ አትቸገር፡፡ ወደፊት ታስታውሰኝ ይሆናል፡፡"

"እስቲ ስለራሴ ሌላም ነገር ንገረኝ፡፡ ያልከኝን ዓይነት ሰው መሆንህን እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፡፡"

"አንተ ጥበብን ለመረዳት የምትባዝን ሰው ነህ፡፡ ከፍቅረኛህ ከዕድላዊት



ጋር ባለህ ግንኙነት ራስህን እያስቃየህ ያለህም ነህ፡፡ አባትህ ለጥበብ ተጠርቶ ከጅማሬው ያፈነገጠ ሰው ነበር፡፡ ይሄ ይበቃሃል፡፡"

የሰማሁት አስገረመኝ እንጂ አላስደነገጠኝም፡፡ በተለይ አባቴ ለጥበብ የተፈጠረ ሰው እንደነበር ከእኔ ሌላ ማንም አያውቅም፡፡ እኔም ያወቅኩት እሱ ከሞተ በኋላ ከዚህ በፊት የፃፈውን አግኝቼ ሳነብ ነው፡፡ 'እውነትም ይሄ ሰው፣ ነኝ ያለውን የሆነ ሰው ነው' ብዬ ደመደምኩኝ፡፡

"ግን ከዕድላዊት ጋር ባለኝ ግንኙነት ራሴን እያሰቃየሁ እንደሆነ ነግረኸኛል፡፡ እኔ የማውቀው ደሞ እሷ እያሰቃየችኝ እንደሆነ ነው፡፡"

"እተያይህ ነው፡፡ እስቲ 'ራስህን እያሰቃየህ ነው' ባልኩህም መንገድ ተመልከተውና ትክክል መሆኑን አሊያም መሳሳቴን ራስህ ተረዳው፡፡ እንዲህ ያለውን ነገር ራስህ ካልተረዳኸው በቀር ሌላው ሊያስረዳህ አይችልም፡፡ ቢችልም ሕመምህን ከውስጥህ ለመንቀል መድኃኒት አይሆንህም፡፡ ነፍስህን ማድመጥ ስትጀምር ግን እያንዳንዱን ቁስል ራስህ ለማከም ትችላለህ፡፡... አንድ ቁም ነገር ግን ልንገርህ፡፡ በሕይወትህ ውስጥ እጅጉን አብልጠህ የምትፈልገው ነገር ብቻ ነው መተኪያ የሌለው፡፡ ሌላው ነገር ሁሉ ለጊዜው ባይመስልህም በቀላሉ ሊተካ የሚችልና ከተተካም በኋላ እስኪገርምህ ድረስ የምትረሳው ነገር ነው፡፡... አሁን መሄጃዬ ደርሷል፡፡ አንድ ስምምነት ላቅርብልህ፡፡ ከእኔ ጋር ለጥቂት ቀናት ጉዞ ለማድረግ ፈቃደኛ ነህ?"

" ማለት?!... ዛሬ?" ያልተጠበቀ ጥያቄው አስደነገጠኝ፡፡

"ዛሬ ሳይሆን አሁን፡፡ ጨርቄን፣ ስንቄን ሳትል ከአንድ ሁኔታ ለመውጣት የሚጎትቱህን ነገሮች ሁሉ መስዋዕት አድርገህ ስትነሳ ብቻ ነው ካለምከበት መድረስ የምትችለው፡፡

'ጓዙ ሸከሙ ያነሰ

ቀድሞ ካለመው ደረሰ' ይባላል፡፡ ለጥቂት ቀናት ይሄን ሞክረውና

ውጤቱን እየው፡፡ ግን ልብህ የፈቀደውን አድርግ እንጂ ልገፋፋህ አልፈልግም፡፡" አለኝና ብድግ አለ፡፡

ከራሴ ጋር ሙግት ገባሁ፡፡ እስከዛሬ ጉዞ ለማድረግ እስቢ ለአፍታም ልርቃቸው የማልችላቸው ብዙ ነገሮች ገትተውኛል፡፡ በተለይ ደግሞ ዕድላዊት፡፡ ከእርሷ ለቀናት ለመራቅ አቅሙ ይኖረኝ ይሆን?... እንጃ! ከእርሷ መራቅ ስቃይ ነው፡፡ ይሄን ስቃይ ደግሞ ደጋግሜ ቀምሼዋለሁ-በጣም ያማል፡፡ በእነዚያ ጊዜያት ሁሉ ግን እኔ ርቄያት ሳይሆን እሷ ደጋግማ እየራቀችኝ ነው ያሰቃየችኝ፡፡ ዛሬ በራሴ ውሳኔ ያንን ስቃይ ለመቀበል ፈቃደኛ ነኝ?... ግን ደግሞ፤ ከእርሷስ ጋር መሆን የደስታ ምንጬ መሆኑ ከቀረ ስንት ዓመታት ተቆጠሩ? አብሬያት ሆኜስ የተረፈኝ ስቃይ አይደለም እንዴ?... ታዲያ መራቁም ሆነ አብሮ መሆኑ ያለፈቃዴ የሚያሰቃየኝ ከሆነ ቢያንስ ዛሬን እንኳ በራሴ ፈቃድ የስቃዬን መንገድ ብመርጥ ጀግንነት አይደለም? ደሞስ ካሰብኩበት ለመድረስ መስዋዕትነት መክፈል ካለብኝ ከዕድላዊት ጋር ሆኜ የምቀበለውን ስቃይ ተለይቻትስ ብቀበለው ምን ይመጣል? ሁለቱም ስቃይ ከሆነ ለምን ስቃዬን ወደ ነፍሴ ጥሪ እያዘነበኩ አላስታምመውም?... መቁረጥ አለብኝ፡፡ አሁኑኑ... ቀና ብዬ ወደ ሰውየው ተመለከትኩኝ፡፡ ዞር ብሎም ሳያየኝ መንገዱን ቀጥሏል፡፡ ከተቀመጥኩበት ተፈናጥሬ ተነሳሁና በሩጫ ተከተልኩት፡፡

ምንም ሳልናገር ጎን ጎኑ መራመድ ስጀምር በቅድሙ ፈገግታ ተቀበለኝ፡፡ አንዳችንም አንዳች ሳንተነፍስ ጉዟችንን ቀጠልን፡፡

'ጓዙ፣ ሸከሙ ያነሰ

ቀድሞ ካለመው ደረሰ' የሚለውን የካህኑን ቅኔ መላልሼ እየተቀኘሁ፡፡



- 2 -

"እውነትን ይበልጥ እየተረዳህ በመጣህ ቁጥር ከነአካቴው ስቃይ የሚባል ነገር አያውቅህም፡፡"

ይሄ የጥቂት ሰዓታት ጉዞ ላለፉት አሥር ዓመታት በሁካታ መሃል ከተጓዝኩት ጉዞ የበለጠ ድንቅ ሆነብኝ፡፡ እስካሁን በሁካታው መሃል ያላስተዋልኳቸው የገዘፉ ቁም ነገሮች ፍንትው ብለው አፈጠጡብኝ፡፡ ተራ በተራ እየወጡ 'ታውቀናለህ ወይ?.... ታስታውሰናለህ ወይ?...' እያሉ እናትና ጅራት አውጥተው ፊቴ ይንጎማለሉ ገቡ፡፡

ለመሆኑ ማነው ዝምታን 'ዝም-እታ' ነው ብሎ የተረጎመው? እስከዛሬ ለካ እኔ የሌሎችን፣ ሌሎችም የእኔን ስሜት ነው ትርጉም ስንሰጥ የነበርነው፡፡ እኔም የራሴን፣ እነሱም የራሳቸውን ስሜት ትርጉም ሰጥተነው ቢሆን ኖሮ ከመጀመሪያው ትርጉሙ በተቃረነ ነበር፡፡

'የእኔ ዝምታ፣ ዝም-እታ'ነቱ ለሌላው ተመልካች ነው፡፡ ለእኔ ግን ተሰምቶ የማያውቅ ታላቅ የነፍስ ኡኡታ ነው፡፡ እናትን በሁለት እጅ ጠፍረው የሚያስነኩት ዓይነት ኡኡታ፡፡ ማነው ታዲያ 'ምነው ዝም አልክ?' ብሎ ጠይቆኝ ትክክል የሚሆን?

ያንን፣ አሥር ዓመታትን ያህል የረዘመ የኑሮ መንገድ፣ በደቂቃዎች ዕድሜ ከለስኩት፡፡ ከአሥር ዓመታት በፊትም ቢሆን፣ ልጅ እያለሁ፣ የጥበብን መንገድ ፈልፍዬ ለመረዳትና ለማጣጣም፣ የራሴንም የታሪክ

Scanned with CamScanner

አሻራ በዚያ ውስጥ ለመተውና የስጋዬን ሞት ላሸንፈው ታላቅ ህልም ነበረኝ፤ ግን ከተፈጠርኩለት ተልዕኮ ይልቅ በአጋጣሚ ያገኘኝን ዕድል ተከትዬ ከመንገዴ ወጣሁ:: ለዓመታት ልቤ ባልወደደው መንገድ ላይ ስቅበዘበዝ ከቆየሁ በኋላ እኔ የዘነጋሁትን የነፍሴን ተልዕኮ የሚያስታውስ ሁኔታ ተፈጠረና ተዓምር ሊባል በሚችል መልኩ ወደ መንገዴ ተመለስኩ:: ይኸው ላለፉት አሥር ዓመታት መንገዴ ነው ባልኩት ጎዳና ላይ መውጣትና መውረድ ያዝኩኝ::

ወደ መንገዴ የመለሰኝን ሰው ወደ ነፍስ ሲጀመር ሳላስበውና ሳያስበው ጥሪው በጥልቀት እንዲገባና ስኬትን እንዲያጣጥም አግዤው ከአዲሱ መንገዴ ጋር መላመድ ያዝኩኝ:: ከሁለትና ሦስት ዓመታት በኋላ እኔም መንገድ ብቻ ሳልሆን ውጤትም ስኬትም፣ ታሪክም መሆን እንዳለብኝ ገባኝና ራሴን 'ተነስ! ኮርቻህን ጫን' ብዬ ለጉዞ መዘጋጀት ጀመርኩኝ:: እንግዲህ ለጉዞዬም እየተሰናዳሁ፤ ለሌሎች ተጓዦችም ድልድይ እየሆንኩ በዕድሜ ጅረት ላይ ሽቅብ መቅዘፍ ስቀጥል ነው ዕድላዊት የተከሰተችው:: እሷም፣ እንደኔው ሩቅ መንገድ ለመጓዝ የተነሳች ነበረች:: ከመጀመሪያው ጀምሮ ሌሎችን ሴቶች ባየሁበት ዓይኔ እንዳላየኋት መካድ አልችልም:: እንዳገኘኋት ልዩ ስሜት ተሰማኝ፤ ግን ቃል አልወጣኝም ነበር:: የተሰማኝን ስሜት ውጬ አስቀረሁት::

የተገናኘነው በሆነ አጋጣሚ ነበር:: እሁን ሳስተውለው ግን ለአጋጣሚው ሌላ ትርጉም ሰጠሁት:: እሷም ግቧን ለመምታት ትፍጨረጨር ነበርና የእኔ እዚያ ቦታ ላይ በዚያ ሰዓት መገኘት ተራ አጋጣሚ አለመሆኑን አሁን ነው የተረዳሁት:: የነፍስ ጥሪዋን እውን ታደርግ ዘንድ ተፈጥሮ በራሷ ምስጢራዊ መንገድ እየረዳቻት ነበርና እኔን አንከውክዋ ፊቷ ጣለችላት::

እኔም በምፈራውና እንደደመና በማይጨበጠው እሰጨናቂ ስሜት ውስጥ ወደቅኩ:: የምመርጠው ከዚያ ስሜት መሸሽ፣ መፈርጠጥ ነበር::



እሷ ግን እንድሸሽ ዕድሉን አልሰጠችኝም:: እዘናግታ እቅፏ ውስጥ ጣለችኝ:: ቃላቶቿ ሙሉ ብርሃን አልነበሩም:: መንገዱን ጠቁመው እንደሚሰወሩ ተወርዋሪ ከዋከብት ዓይነት ነበሩ:: አሷው በጠቆመችኝ መንገድ ጠልቄ ወደ ሕይወቷ መግባቴን ስታረጋግጥ ደሞ እኔን ብቻ እንደተሸናፊ፣ እርሷን እንደ አሸናፊ በሚያስቆጥር ፍቅር ውስጥ ዘፈቀችኝ::

በራሴ እውን ላደርገው ያሰብኩት ታሪክ፣ ውጤት እና ስኬት ሁሉ እንደጉም በኖ፤ ድልድይ ብቻ ሳልሆን እኔው ራሴ በሩቅ እያየሁ ከጓጓሁለት መድረሻ ላይ አደረስኳት::

በእርግጥ የትኛውም መድረሻ ቢሆን ለሌላ ጉዞ መነሻ ነው:: ግን እዚያ ስትደርስ ሁሉም ነገር የውሸት ሆነ:: በጨለማውና በሚያስጨንቀው ግርዶሽ ስር አብረን አልፈናል:: ግን በጠራው ፀሐይ ላይ ቆማ ስታበራ ያገኟትን ሰዎች ከእኔ ይልቅ መረጠች::

"አብረን ያፈካነው ቀን እኮ ነው አንቺን የገለፀሽ:: እነዚህ ሰዎች የዚህ ቀን ፀሐይ ሲያበራሽ ነው የተመለከቱሽ:: እንደኔ በጨለማ ውስጥ አብረውሽ ሲጓዙ የሚችሉ አይደሉም!!" እያልኳት ይኸው እስከዛሬ በሌሎች የድል አጥቢያ አርበኞች ዳር እየወጣሁ፤ እንዳፈቀርኳት አለሁ:: ታዲያ ለእርሷ ጉዞ መስዋዕት ያደረግኩት የእኔ የነፍስ ጥሪ እንቅልፍና ሰላም መች ሰጠኝ?

አሁን ግን በዚህ የነፍስ 'ኡኡታ' ውስጥ አንድ ነገር ተገለጠልኝ:: እያንዳንዱ መድረሻ ለቀጣዩ ታሪክ መነሻ ከሆነ፤ በእሷ በኩል የእኔ እድራሽነት አብቅቷል::

ለቀጣዩ

የጉዞ እርምጃዋ ሌላ ድልድይ እየገነባች ቢሆንስ? እንደውም ልብ ስለው እያደረገች ያለችው ይሄንን ነው:: ግን የግድ እኔን ገሸሽ በማድረግ መሆን ነበረበት?... እኔ ላይ የደረሰው ተገቢ ነው ባልልም እሷ መንገዷን ለማቅናት የምትከብ የምታፈርሰው ነገር ጀግና ሲያሰኛት እንደሚገባ

ጥሩም ይሁን መጥፎ ያው ጀግና ነው:: ብቻ
ተረዳሁ:: ደግሞ እኮ ጀግና ጥሩም ይሁን መጥፎ ያው ጀግና ነው:: ብቻ ጥሩና መጥፎውን የት ቦታ ቆሜ አይቼው ነው ለዳኝነት የምቀመጠው? ታዲያ ይሄ ካህን መቸ ተሳሳተ? "በሕይወትህ ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊው ነገር ብቻ ነው መተኪያ የሌለው:: ሌላው ነገር ሁሉ ለጊዜው ይተካል::" ነበር ያለኝ ቅድም:: ከእኔ አይመስልህ ይሆናል እንጂ በቀላሉ ይተካል::" ነበር ያለኝ ቅድም:: ከእኔ ይልቅ እርሷ ይሄንን በቀላሉ ተግባራዊ አድርጋዋለች ማለት እኮ ነው:: ገረመኝ:: በብዙ መልኩ እኔ ከእሷ የተሻልኩ እንደሆንኩ አስብ ነበር:: አሁን ግን እሷ ከእኔ በብዙ መልኩ የተሻለች እንደሆነች ተገለፀልኝ::

ከመጻሕፍት ውስጥ የቃረምኩት ያ ሁሉ እውቀት፤ ያንን ሁሉ ዝባዝንኬ ባላነበበችው ዕድላዊት መረታቱ ገባኝ:: ከዚህ ሁሉ ሃሳቤ መሃል ለስቃዬ እሷን ተጠያቂ ማድረጌን ልፍቀው አልቻልኩም:: ሕመሜ ግን በመጠኑ ሲቀንስ ታወቀኝ:: ይሄ ደግሞ እሷን የሕይወቴ አካል ካደረግኩበት ጊዜ ጀምሮ ገጥሞኝ የማያውቅ ነገር ነው:: እስከዛሬ ድረስ ስቃዬን በደንብ አድርጌ ሰሰቃይበት፤ ከመጠን በላይ ስታመመው ኖርኩ እንጂ፤ የአንድ ጣትን ያህል ቀንሼው አላውቅም ነበር:: አሁን ግን ባልጠበቅኩት መልኩ ስቃዬ ሲቀንስ ታወቀኝ:: 'እንዴት?' ብዬ ራሴን ጠየቅኩት::

"በፊት ያልተገለፁልህ እውነታዎች እየገቡህ ስለመጣህ ነው:: እውነትን ይበልጥ እየተረዳህ በመጣህ ቁጥር ከእነአካቴው ስቃይ የሚባል ነገር እያውቅህም- ሁሉም ነገር የሚሆነው በምክንያት ነውና::" አለኝ ከልቤ ጥልቀት ውስጥ የፈለቀ ረቂቅ ድምፅ::

ይሄን ካህን ተከትዬ መሄዴ በሕይወቴ የወሰድኩት ትልቅ ውሳኔ ነው:: ይሄን ለመወሰን ደግሞ የደቂቃ ዕድሜን ያህልም ቢሆን፤ ከልቤ ጋር በሚገባ ተማክሬ፣ ግራና ቀኙን አይቻለሁ:: ውሳኔዬ አስደስቶኛል:: ከተደሰትኩ ደግሞ ትክክለኛ ውሳኔ ነው ማለት ነው::

ለመሆኑ ዕድላዊት "የያዝከውን ሁሉ አራግፈህና እኔን ብቻ ተሸከመህ



ያለምኩበት አድርሰኝ::" ብላኛለች እንዴ? ... ፈፅሞ ! እኔው ነኝ በፍቅር ስም የያዝኩትን ሁሉ መስዋዕት አድርጌ እሷን ብቻ ተሸክሜ የመሄዱን ስህተት የፈፀምኩት:: እኔ ለጣልኩት ነገር ሁሉ እሷን ተጠያቂ በማድረጌ ምን ያህል ስቃይ ነው የተቀበልኩት?... እኔንም፣ እሷንም በአንድነት ይገፍ ለመሄድ አቅሙ አልነበረኝም ወይ?... አሁን ሳስበው አቅሙ ነበረኝ፤ ስለሆነም ይሄን ያለማድረጌ ስህተት ሙሉ በሙሉ የእኔ ነው:: እኔ ግን 'ያን ሁሉ ውለታ ውዬላት እንዴት እንዲህ ታደርገኛለች?' ብዬ ጠጠር ውለታዬ ላይ ተራራ ስህተቴን ከምሬ፤ በአንድ ስም ውለታዬን አግዝፌ በማየቴ ነው ለዚህ የበቃሁት:: አደረኩላት ያልኩት ካደረገችብኝ ጋር የተዛባ የንፅፅር ውጤት በማምጣቱ ነው ራሴን በሚያቃጥል ስቃዬ ውስጥ የዘፈቅኩት:

አሁን ስህተቴን ከውለታዬ ነጥዬ ሳየው የውለታዬ ግዝፈት ቀንሶ ተመለከትኩት:: ዋልኩ ላት ያልኩት ውለታ ባነሰ ቁጥር የሀጢአቷ ክብደትም እየቀለለ መጣ:: የሀጢአቷ ክብደት እየቀነሰ በመጣ ቁጥር ስቃዬም በዚያው መጠን እየቀነሰ ሄደ:: እነዚህን እውነታዎች እየተረዳሁ ስለመጣሁ በዚህ አጭር ጉዞ ውስጥ ሁለት ጊዜ ስቃይን መቀነስ መቻሌ አስደሰተኝ:: በሀሳብ የተቋጠረው ፊቴ ታላቅ ፈገግታ ነገሰበት:: ነፍሴም ደስታዬ ተጋባባት መሰል:-

"አይዞህ!... በጉዞህ በርታ ብቻ:: እውነትን ይበልጥ እየተረዳህ በመጣህ ቁጥር ስቃይ ውስጥህ ይሞታል" ብላ ሹክ ስትለኝ ሰማኋት:: ድምጿ ውስጥ የደስታዬ ሺህ እጥፍ የሆነ የደስታ ሲቃ ሲሰማኝ_

"እኔና አንቺ ምንና ምን ነን?" ብዬ ነፍሴን ጠየቅኳት::

"እኔና አንተ እረኛና በግ ነን:: እኔ ነፍስህ፣ እረኛህ ነኝ:: አንተ ደግሞ የጠፋኸኝ በጌ ነህ:: አሁን በሩቅ ላይህ ስለቻልኩ ነው እንዲህ የፈነደቅኩት:: አንተስ አልታወቀህም? በሩቁ

Scanned with CamScanner

ሊታየኝ ስለቻልክ እኮ ነው እንዲህ የፈነጠዝከው:: አንተም ወደ እኔ ና:: እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ:: ልክ ስንገናኝ የጠፋህ በግ አትሆንም- እረኛ አለህና:: ቀብሮም እያሰጋህም- እኔ እረኛህ ነቅቼ እጠብቅሃለሁና:: ግን በድጋሚ አትቅበዝበዝ- ላገኝህ ቀርቤያለሁና::" ብላ መለሰችልኝ::

"ፈፅሞ አልቅበዘበዝም:: በመካከላችን ያለውን መሰናከል ሁሉ አልፌ እንድንገናኝ አበረታለሁ::" ብዬ ቃል ገባሁላት::

ዞር ብዬ አጠገቤ መኖሩን የዘነጋሁትን ካህን ተመለከትኩት:: ከነፍሱ ጥልቀት ስር በመነጨ ፈገግታ ተመለከተኝ:: እኔም እስካሁን የነፈግኩትን ፈገግታ አቀበልኩት::

ከነፍሴ ጋር የጀመርኩትን ጨዋታ እንድቀጥል የፈለገ ይመስል፣ ትኩረቱን ወደ መንገዳችን አደረገ:: እኔም ወደ ደስታዬ ምንጭ ወደ ውስጤ ተመለስኩ::

ወደ እኔና ዕድላዊት ጉዳይ ተመለስኩ:: ሁሉንም ነገር በዕሞና ማጤን አለብኝ:: ለመሆኑ ዕድላዊት ማን ናት?... ይሄን ጥያቄ ከዚህ በፊት ለራሴ አቅርቤ ቢሆን ኖሮ፣ ያስደሰተችኝ ዕለት 'ሕይወት' ያስከፋችኝ ዕለት ደግሞ 'ሬት' ብዬ በአንድ ቃል እገልፃት ነበር:: አሁን ግን ሚዛኔን ማስተካከል እንዳለብኝ ተረድቻለሁ:: እስቲ በተስተካከለ የሕሊና ሚዛን ልመልከታትና ውጤቱን ልሞክረው::

ዕድላዊት፥ የነፍስ ጅረት የሚፈስባት፣ የነፍስ አበባ የሚፈካባት፣ የነፍስ ዜማ የሚደመጥባት፣ የነፍስ ብርሃን የነፍስን ዛፎች እያሸኮረመመ የጮራዎች ህብር ሆኖ የሚዳስሳት፣ እጥር ምጥን ያለች ውብ የነፍስ ከተማን ትመስላለች::

በሰማዩዋ፣ ዐሐይና ጨረቃዋ ታርቀውላት፤ ቀንና ሌቷ አብረው የሚኖሩባት፤ ኮረዳ ከዋክብቷ ዓይናቸውን ተኳኩለው፣ ዐጉራቸውን አዘናፍለው፣ ዳሌያቸውን እየነቀነቁ ሽቅብ ሆኖ የሚመለከቷቸውን እዛውንት ዐሐይ እያማለሉ 'ምነው የጥንቱ ጉልበቴ ዛሬም በኖረና ተንደርድሬ ሄጄ በሙቀታቸው በቀለጥኩ፣ በመዓዛቸው በሰከርኩ፣ ግልድማቸውንፈትቼበፍቅራቸውጦገበሰከንኩ፤በትንፋሻቸውበበነንኩ' እያሰኙ፤ ከጎረምሳ ከዋክብቷ ጋር እየተላፉና እየተሳሳቁ፣ ተቆላልፈው የሚደንሱባት፤ ሲያሻቸውም ወደ አንዱ ስርጥ ተያይዘው ከንፈው በፍቅር የሚያብዱባት፤ እጥር ምጥን ያለች ውብ የተረት ከተማን ትመስላለች:: ጫካዎቿና ኮረብታዎቿ ቅኔ እየተቀኙ፣ ድንቅ ዜማ እያዜሙ፣ ሳቅና ዕልልታቸውን ከዳር እስከዳር እየተቀባበሉ የሚያስነኩባት፤ በተረት ውስጥ የምትገኝ ውብ የነፍስ ከተማን ትመስላለች::

በእኔ ዓይን ዕድላዊት ይሄን የመሰለች ውብ ናት:: ስለዚህ ውስጧ ለመኖር መጓጓቴም ሆነ፤ በውስጤ ላኖራት መፍቀዴ ጤነኛ አዕምሮ ያለው ሁሉ የሚያደርገው ነውና እኔም አልተሳሳትኩም::

ግን ደግሞ፤ ሳቅና ዕንባዋ አብረው ይኖራሉ:: ደስታና ሐዘኗ፣ ውዳሴና ወቀሳዋ፣ ሙገሳና ቁጣዋ፣ ጨዋታና ኩርፊያዋ፣ ትዕግስቷና ጥድፊያዋ፣ ደግነቷና ክፋቷ፣ ፍቅሯና ጥላቻዋ... ሁሉም አብረው ይኖራሉ:: አንዳቸውን ብቻ መኖር አትችልም:: ሁለቱንም ተግራሪ ስሜቶች ጥግ ድረስ ትኖራቸዋለች::

ይሄንን የስሜት ማዕበል ነው እንግዲህ የእኔ ያደርግኩት:: የትና መች እንደሚናወጥ፤ የትና መች እንደሚረጋ የማይታወቅ የስሜት ማዕበል ውስጥ ነው ገብቼ የተዘፈቅኩት::

ከስሜታዊነት ውጪ ሆኜ ለማጤን እየሞከርኩኝ ነው ያለሁት:: ያንን ውበት የእኔ ለማድረግ መሞከሬ፤ ወይንም ራሴን የዚያ ውበት ለማድረግ መጣሬ ስህተት ላይሆን ይችላል:: ግን በዚያ እንደጉድ በሚገላበጥ

የስሜት ማዕበል ውስጥ ለመኖር አቅሙ አለኝ?... ኸረ ለመሆኑ ፈቃደኛስ ነኝ?... በራሴ ላይ ያነጣጠሩ ቆንጆ ጥያቄዎች::

በእኔ ውስጥ እነዚህ ተፃራሪ ስሜቶች አንዳቸው ሌላቸውን ጨቁነው ይኖራሉ እንጂ የልቤን ውቅያኖስ በተደጋጋሚ ማዕበል አይንጡትም:: በአመዛኙ ስመለከተው እኔ የረጋ ውቅያኖስ ነኝ:: እሷን የስሜት ማዕበሏ ባናወጣት ቁጥር ከፍና ዝቅ ያደርገኛል፤ ያንገላታኛል፤ እርጋታዬን ይነጥቅና ያስጨንቀኛል::እንዲህ ባለው ማዕበል ውስጥ መቅዘፍ እችላለሁ ወይ?... አልችልም:: ፈፅሞ አቅሙ የለኝም:: በመሞከሬም ነው ይሄን ያህል ዓመት ስሰባበር የኖርኩት:: ደግሞም ያቺ ትንሽዬ ውብ የተረት ከተማ የእኔ እንድትሆን ያለኝ ፍላጎት አይሎ ነው እንጂ በዚያ ማዕበል ውስጥ ለመኖር ፈቃደኛም አይደለሁም::

ታዲያ በዚህ ነውጥ ውስጥ ለመኖር አቅሙም ፈቃዱም ከሌለኝ፤ ዕድላዊት ጥላኝ ሌላ ሰው ጋር በከነፈች ቁጥር የማዝነውና የምሰቃየው ለምንድን ነው?... የዚህን መልስ ለማግኘት ውስጤን መቆፈር ያዘኩኝ:: ጥቂት ካሰላሰልኩ በኋላ መልሱ ተገለፀልኝ:: ለካስ መልሱን ቀድሜ መልሼዋለሁ:: የዕድላዊት ውበት፣ እጥር ምጥን ያለችው ውብ የተረት ዓለም ከተማ የእኔ እንድትሆን ያለኝ ታላቅ ፍላጎት፣ ያንን ውበት እንዳልነጠቅ ያለኝ ለቃላት የገዘፈ ጥልቅ ስጋት- በቃ ይሄ ነው ለሐዘንና ለስቃይ የዳረገኝ::

በማዕበሏ ውስጥ ለመኖር አቅሙም ፈቃዱም ሳይኖረኝ፤ በዚያ ውበት ላይ ባለኝ ፍላጎት ሳቢያ ብቻ ስቃዬን እያበቀልኩ እጭዳለሁ:: ምን የሚሉት ነገር ነው?

አንድ ሰው፣ አንድን ቤት ወዶ ገዝቶት፤ ግን ሊኖርበት ባይፈቅድ፣ ያ ሰው ሊኖርበት የሚፈቅደው ሌላ ቤት አለው ማለት ነው::

እኔስ ሌላ ቤት አለኝ? የለኝም:: ስለዚህ ምንም ብወደው፣ ልኖርበት



በማልፈቅደው ቤት ውስጥ እየተላተምኩና እየተፈጠፈጥኩ ከምኖር፣ ልኖርበት የምፈቅደውን ሌላ ቤት መስራት አለብኝ::

ለመሆኑ የዕድላዊት ውበት ላይ ወስዶ የጣለኝ ዓይኔ በዘመኑ ስንት ውበት አይቶ ያውቃል? መቶ፣ ሺ፣ አሥር ሺ... ይኸው የዕድላዊት ውበት እየቀጠነ ወይም እየወፈረ፣ እያጠረ አሊያም እየረዘመ አልፍ ሴቶች ላይ በየቤቱ፣ በየመንደሩና በየአደባባዩ ሲመላለስ ዓይኔ አይቷል:: ልቤ እሷ ጋር ስላለ በሩን ዘግቶ ነው እንጂ ያንን ውበት በአልፍ ሴቶችም ላይ አይቼዋለሁ:: ምናልባትም እኮ አንዲት ሌላ ውብ ልቤ ገብታ ቢሆን፣ ኖሮ ልኖርበት ከማልፈቅደው ማዕበል ያናወጠው ውቅያኖስ ውስጥ ከንፌ በወጣሁ ነበር:: ይሄ ሊሆን ስላልቻለ ብቻ ነው ስቃዬን በጀርባዬ እዝዬ 'እሹሩሩ' ስለው የኖርኩት::

በአንዲት ቀላል እርምጃ ስንት ነገር ሊለወጥ እንደሚችል አሰብኩና በረጅሙ ተነፈስኩ:: ያኔ በጣም ቀለለኝ:: ዕድሜ ጭንቀቴን ይበልጥ ልጨነቅበት ለተሰደድኩበት ጫካ፤ ዕድሜ ለድንገተኛው ኩብላይ ካህን፤ ዕድሜ የት እንደሆነ ለማላውቀውና ግን እየሄድኩበት ላለሁበት ሥፍራ፤ ተዓምር በሆነ መንገድ ከበሽታዬ እየተፈወስኩ ነው::

Scanned with CamScanner

## - 3 -

"የትኛውም ጨለማ በተጠጋኸው አርምጃ ቁጥር ልክ ወደ ኋላው ያፈገፍጋል።"

ለመሆኑ ስንቶቻችን ነን የሌሊቱን ውበት፣ የሌሊቱን ግርማ፣ የሌሊቱን ሕይወት በቅጡ አይተነዋል የምንል? ስንቶቻችንስ ነን የጨለማን ትርጉም የምናውቅ?... ጥቂቶች ብቻ ይመስሉኛል። ጥቂት የተመረጡ ሰዎች፣ አሊያም ይሄንን እውቀት ለመረዳት የመረጡ ጥቂት ሰዎች ብቻ።

የቀን ጉዟችንን አጠናቅቀን፣ በምሽቱ ውልደት ስር አልፈን፣ ጨለማውን ሰንጥቀው በሚያልፉት በጨረቃዋ ውብ ብርሃንና በከዋክብቱ ስልምልም ጥቅሻዎች ስር ተጉዘን ሁሉ ያለነው የሰው ዘር የሌለበት በሚመስል ጫካ ውስጥ ነው። አንድ ዋርካ ስር ስንደርስ ካህኑም እህያውም ቆሙ። ካህኑ አህያው ላይ የተጫነውን ሸከም ለማውረድ ጠፍሩን መፍታት ሲጀምር አገዝኩት።ሸከሙን አውርደን ስንጨርስ ምንም ሳይናገር ዋርካው ስር ቁጭ አለ። እኔም ጎኑ ተቀመጥኩ። ልቤ በፍራቻ መምታት ከጀመረች ቆይታለች። ዞር ብዬ የካህኑን ፊት በጨረቃዋ ብርሃን ለማጤን ሞከርኩ። ምንም አይነበብበትም። ይግረምህ ብሎ፦

"ለምን ዞር ዞር ብለህ ጭራሮ አትለቅምም?" አለኝ።

"በዚህ ጨለማ?!" ደነገጥኩ።



"ይሄ ጨለማ ምን አለበት?"

"ጨለማው እኮ ብቻውን አይደለም። ጫካውና አራዊቱ ሁሉ አብረውት አሉ። አንተ ምንም አትፈራም ማለት ነው?... ወይንስ ቅድም ስንገናኝ 'ሰዎች ሊያደርጉት የሚፈሩትን የምጋፈጥ ጀብደኛ ነኝ' ያልከኝ ይሄንንም ይጨምራል?"

"አንተ የፈራኸው ጫካውን ነው ወይንስ አራዊቱን?"

"አራዊቱን ነው እንጂ። ለነገሩ አራዊት ባይኖሩበትም ጫካው በጨለማ ያስፈራል።"

"ስለዚህ የፈራኸው ሁለቱንም ነው ማለት ነው?"

"አዎ ሁለቱም ያስፈራሉ።"

"ጫካው አራዊት ከሌለው እንዴት ያስፈራል?"

"እንጃ!... ምናልባት አራዊት እንደማይኖሩበት በእርግጠኝነት ስለማላውቅና አውሬ ሊገጥመኝ ይችላል ብዬ ስለምሰጋ ይሆናል።"

"ግን አውሬ የሚባል ነገር ከእነአካቴውም እኮ ላይኖርበት ይችላል። አይደል እንዴ?"

"አዎ። ላይኖርበትም ይችላል።"

"በጫካው ውስጥ ምንም አውሬ ከሌለ ፍራቻህ ከንቱ መሆኑ ነው።"

"አውሬ ያለመኖሩን እኮ በምንም መልኩ እርግጠኛ መሆን አልችልም።" ብዬ ተጋፈጥኩት።

"እዚህ ጫካ ውስጥ ብዙ አራዊት አሉ። አንዳቸው ሌላቸውን ይፈራሉ። ግን ይሄን ፍራቻቸውን ሰበብ አድርገው ምግባቸውን ለመፈለግም ሆነ ለሌላ ጉዳያቸው ከጎሬያቸው ሳይወጡ አይቀሩም። ፍራቻ የሚሰማቸው በሁለት መልኩ ብቻ ነው። አንደኛው በደመ-ነፍሳቸው ጠላታቸው በአቅራቢያቸው እንዳደባ ሲሰማቸው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጠላታቸውን በአቅራቢያቸው ሲያዩትና ሲያጠቃቸው

Scanned with CamScanner

እንደሆነ ሲገነዘቡ ነው:: በተረፈ ግን ይሄ ጫካ የአጥቂያቸውም መኖሪያ በመሆኑ ብቻ በከንቱ አይፈሩም:: ስለዚህ ሦስተኛውና 'ከንቱ ፍራቻ' ብለን የጠራነው የሰው ልጅ ደመ-ነፍሱን ከማዳመጥ ስለቦዘነ በራሱ ላይ የፈጠረው የፍራቻ ስሜት ነው::

"እርግጥ አንድ ሌላ ነገርም አለ:: የእኔና ያንተ እዚህ ቦታ መገኘት የጫካውን አራዊትም ትንሽ ያስፈራቸዋል እኮ:: ጀግና የምትለው አውሬም ቢሆን ያልለመደው ነገር ሲገጥመው በመጠኑም ቢሆን መፍራቱ አይቀርም:: ስለዚህ ራስህን ብቸኛው ፈሪ አድርገህ አትቁጠር::.... አሁንስ ጭራሮውን ለመልቀም ዝግጁ ነህ?"

'ዝግጁ አይደለሁም' አልኩ በልቤ:: እሱ ቀላል ነው ብሎ ያሰበው ነገር ለእኔ ከባድ ነው:: አሁንም እዚህ ጫካ መሃል በጨለማ ያስቀመጠኝ በዚህ ሰው ላይ የጣልኩት እምነት እንጂ፤ እንጃ! ምን ይውጠኝ እንደነበር::

ብቻ መልስ ሳልሰጠው ለአፍታ ማሰላሰል ያዝኩኝ:: 'መቼም አደጋ የሚገጥመኝ ቢሆን ኖሮ ይሄን አድርግ ብሎ አይልከኝም ነበር::' ብዬ ራሴን ሳረጋጋው ሞከርኩ:: አልተረጋጋሁም:: ከዚህ ይልቅ የት ድረስ አካባቢዬን በግላጭ ማየት እንደምችል ዓይኖቼን ልኬ መተርኩ:: ብዙም ርቄ ሳልመለከት ዓይኖቼ ከጨለማ ግድግዳ ጋር ተላተሙ:: ከጨለማው ግድግዳ እስከ ተቀመጥንበት ቦታ ድረስ ያለው ርቀት ከአሥር እርምጃ አይበልጥም:: በዚህ አሥር እርምጃ ውስጥ ምንም የሚያሰጋ ነገር አልታየኝም::

'ካለሁበት ተነስቼ አንድ እርምጃ ወደፊት በተራመድኩ ቁጥር፣ የጨለማው ግድግዳም በአንድ እርምጃ ወደ ኋላው ይሸሻል:: የጨለማው ግድግዳ አሁን የቆመበት ሥፍራ ላይ ስደርስ፣ እሱም አሁን ካለበት አሥር እርምጃን ያህል ወደ ኋላ ሸሽቶ ይጠብቀኛል:: ከዚህ ካለሁበት ደግሞ ሃያ እርምጃን ያህል



ማለት ነው:: ምክንያቱም ተጨማሪ አሥር እርምጃን ያህል አጥርቼ ማየት እችላለሁና::'

ምንም ሳልናገር ብድግ አልኩና በእያንዳንዱ እርምጃዬ ማየት የቻልኩበት ርቀት ድረስ አካባቢዬን እያስተዋልኩ ተራመድኩ:: የጨለማው ግድግዳ ቆሞ የነበረበት ቦታ ስደርስ በአሥር እርምጃ ወደኋላ አፈግፍጎ ጠበቀኝ:: አሥራ አንደኛ እርምጃዬን ስቀጥል እግሬ ደረቅ ጭራሮ ሲረግጥ ታወቀኝ:: አጎንብሼ ጭራሮውን ከማንሳቴ በፊት ዙሪያዬን በጥንቃቄ ተመለከትኩ:: ከዚያም ዓይኖቼን ወደ መሬት ላኳቸው:: አንድ ብቻ ሳይሆን የተበታተኑ ጭራሮዎች አየሁ:: ብዙም ሳልርቅ የምፈልገውን በማግኘቴ ተደሰትኩ:: ግን ደስታዬ አስተውሎቴን እንዳይነጥቀኝ ፈርቼ አካባቢዬን መቃኘትንና ጭራሮዎቹን መልቀምን በአንድነት ስራ አደረኳቸው::

ለጨለማው ጀርባ ሰጥቼ ወደ ቦታዬ ከመመለሴ በፊት አንድ ጊዜ ጨለማውን በጥልቀት መረመርኩና እርጋታ ሲሰማኝ ዞሬ ወደመጣሁበት አቅጣጫ እርምጃ ጀመርኩኝ:: ወዲያው ግን አንድ ሀሳብ አዕምሮዬ ውስጥ ገባ::

'የጀርባህንስ አስተውለሃል? የመጣህበትንስ መንገድ?... አንተ ተራምደኸው ካለፍከ በኋላ ምን እንደገባበት ምን ታውቃለህ?' የሚል ሀሳብ:: እርምጃዬን ገታሁና የመጣሁበትን መንገድ በሚገባ ቃኘሁት:: ሰላም ነው:: ጀርባዬንም ምንም የሚከብድ ስሜት አልተሰማኝም:: ካሁኑ ጓደኛዬም ቁጭ ብሎ ይታየኛል:: ጭራሮዬን ተሸክሜ እርምጃዎቼን በድል ጨርሼ እጠገቡ ደረስኩ:: ፊቱ ላይ ያቺን የወደድኳትን ፈገግታ ስመለከት ጭራሮ ለመልቀም መወሰኔን ወደድኩት:: ጭራሮዎቹን ፊት ለፊታችን አስቀምጬ፣ አስተካከልኩና ስጨርስ ቀና ብዬ ተመለትኩት:: እሱም በዝምታ ተመለከተኝ::

"ከብሪት..." ብዬ ጀመርኩና በድንገት ንግግሬን አቋረጥኩኝ:: ከብሪት

Scanned with CamScanner

ይዟል! አልያዘም የሚል ሀሳብ አዕምሮዬ ውስጥ ሳይከሰት፣ ድምጼ ውስጥ ግን ጥርጣሬዬን ሰማሁት:: ድምጼ ውስጥ የሰማሁት ጥርጣሬ ከባዶ ስሜት የመነጨ እንደማይሆን እርግጠኛ ሆንኩ:: 'ይሄ ሰው ክብሪት አልያዘም ማለት ነው:: መቼም ትክክል ከሆንኩ ይገርመኛል' እያልኩ

"ክብሪት ይዘሃል?" አልኩት ለመልሱ ጓጉቼ::

"አልያዝኩም" አለኝ እንደፈገገ:: ለአፍታ በአትኩሮት ተመለከትኩትና ፊቴን ወደ ዱሩ መልሼ ማሰብ ያዝኩኝ::

'ይሄ ሰው ክብሪት ያለመያዙን እንዴት ድምጼ ሊነግረኝ ቻለ?' ይሄ መቼም ድንቅ ነገር ነው:: ዛሬ ገና ለጥያቄዬ ምላሽ ከመስማቴ በፊት በራሴ ድምፅ ውስጥ ምላሹን አገኘሁ:: ደመ- ነፍሴ በድምጼ ውስጥ ራሱን ገልጾ ምላሽ እንደሰጠኝ አልተጠራጠርኩም:: ግርም አለኝ::

ደግሞም ይሄ ሰው ክብሪት ሳይኖረው ወይንም እኔን እሳት ማቀጣጠያ እንዳለኝ ሳይጠይቀኝ ጭራሮ ልቀም ብሎ እንዴት ላከኝ?... ቆይ ቆይ!... የካህኑ ነጥብ ይሄ አይሆንም:: ያለምንም ምክንያት ይሄንን አላደረገም:: እኔ ራሴ ጭራሮ ለመልቀም ከመሄዴ በፊት መቹ ይሄንን ጥያቄ አነሳሁበትና?

"እስቲ ልትነግረኝ የፈለግከውን ልስማው:: መቼም ያለአንዳች ምክንያት ክብሪት እንደሌለን እያወቅክ ጭራሮ እንድለቅም አልላከኝም:: " አልኩት ፊቴን ወደእሱ መልሼ::

"ራስህ ብትረዳው መልካም ነበር:: ግን... ጭራሮ ለቅመህ በመምጣትህ ምን አጣህ?... ምንስ አገኘህ? ይሄ ነው ትልቁ ቁም ነገር:: ክብሪት ባለመኖሩ ምክንያት ይሄንን ጭራሮ እሳት አድርገን ልንሞቀው የመቻላችን ጉዳይ አብቅቶ ሊሆን ይችላል:: ግን... ጭራሮ ለመልቀም ባትሄድም ኖሮ እኮ እሳት አንሞቅም ነበር:: ስለዚህ ለመልቀም በመሄድህ ያጣኸው ነገር የለም:: ስላገኘኸው ነገር ብቻ ነው



ማውራት ያለብን:: እስቲ ምን እንዳገኘህ ንገረኝ?" አለኝ እንደፈገገ:: ለአፍታ አሰላሰልኩና...

"ልክ ነህ:: ያጣሁት ምንም ነገር የለም:: ያገኘሁት ግን ብዙ ነው:: አንደኛ፣ ፍራቻዬን በድርጊት አሸንፌዋለሁ:: ሁለተኛ፣ የትኛውም ጨለማ በተጠጋኹት ቁጥር የዚያኑ ያህል ሸሽቶ እንደሚያፈገፍግ ተረድቻለሁ:: ሦስተኛ፣ በራሴ የደመ-ነፍስ ስሜት ላይ እምነት ጥያለሁ:: እንደውም በደመ-ነፍሴ ላይ የጣልኩት እምነት ክብሪት እንዳለህ ልጠይቅህ ስጀምር ድምጼ ውስጥ በሰማሁት ጥርጣሬ እንዳልያዝክ እንድረዳ ረድቶኛል:: አራተኛው፣ አንድን ነገር ለመሰብሰብ እርምጃ ከመጀመሬ በፊት፤ ያንን ነገር ባገኘው ወደምፈልገው ውጤት ልለውጥበት የሚያስችለኝ ሌላው ኃይል እጄ ላይ መኖሩን ማረጋገጥ እንዳለብኝ ተረድቻለሁ::" ጭራሮ ለቀማዬ ከንቱ ልፋት እንዳልነበረ እንደተገነዘብኩ ዘረዘርኩለት::

"ጥሩ ተረድተሃል:: አሁን ያደረግከው የአሥር እርምጃ ጉዞ በዕድሜህ ውስጥ ያደረግከውን የአሥር ዓመት ጉዞ ይወክላል:: ያመጣኸውን ጭራሮ ያለማቀጣጠልህ ጉዞህን ውጤት አልባ አያደርገውም:: ትልቁ ቁም ነገር በዚህ ጉዞ ውስጥ ብዙ አዲስ ነገሮችን መማር መቻልህ ነው::

"በጉዞህ ውስጥ ያገኘኸው እውቀት ለወደፊት የታላላቅ ስኬቶች ቁልፍ በመሆን ያገለግልሃል:: በእነዚያ አሥር ዓመታት ያጣኸውን እየቆጠርክ ስትሰቃይ ኖረሃል:: እስቲ ያገኘሃቸውን አዳዲስ እውቀቶች አሰባቸውና ከአሁን በኋላ ላለው ጉዞህ እንዴት የስኬት ቁልፍ ሊሆኑህ እንደሚችሉ አስተውል:: አሁን አገኘሁት ካልከው እውቀት ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ምንም ስህተት የለባቸውም:: በአራተኛ ደረጃ የጠቀስከውን ግን ላርምህ::

"'አንድን ነገር ለመሰብሰብ እርምጃ ከመጀመሬ በፊት፤ ያንን ነገር ባገኘው ወደተፈለገው ውጤት ልለውጥበት የሚያስችለኝ ሌላው ኃይል እጄ ላይ

Scanned with CamScanner

መኖሩን ማረጋገጥ አንዳለብኝ ተረድቻለሁ፡፡' ብለሃል፡፡ የሰበሰብከውን ነገር ወደ ውጤት የምትለውጥበት ኃይል እውቀት ነው፡፡ ያ እውቀት የሚገኘው ደግሞ ልክ እንዳሁኑ፣ ጭራሮ ለመልቀም ባደረግከው ጉዞ ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ እውቀቱ እጄ ውስጥ ሳይኖር እግሬን አላነሳም ማለት አትችልም፡፡ እውቀቱ የሚገኘው በእያንዳንዱ የጭራሮ ለቀማ እርምጃ ውስጥ ነውና፡፡ ተረድተኸኛል?"

"በሚገባ፡፡ በደንብ ተረድቼሃለሁ፡፡" ብዬ ፈገግኩ፡፡ 'የሚገርም ገለፃ ነው' አልኩ በልቤ፡፡

"ባለፉት አሥር ዓመታት ያደረግከው ጉዞ ያንተን የታሪክ አሻራ በትልቁ ለመፃፍ የሚረዳህ ቁልፍ ነው፡፡ ይሄንን በቀጣዩ ጉዟችን ወቅት በጥልቀት መርምርና እንዴት እንደምትጠቀምበት አብሰልስለው፡፡" አለኝና በዝምታ ተመለከተኝ፡፡ ውስጤ 'ልክ ነህ' እያለ እሥሬ ሲያስተጋባ እሰማዋለሁ፡፡

"ደግሞም ሌላም ነገር አለ፡፡" አለና ከውስጤ የገደል ማሚቶ አነቃኝ፡፡ ዞር ብዬ ተመለከትኩት፡፡ "በአስተዋይ ልቦና ካየኸው እኮ ይሄንን ጭራሮ አሁንም ቢሆን እሳት ማድረግ ይቻላል፡፡"

"እንጨትና እንጨት አፋትገን ማለትህ ነው?" አልኩት፡፡

"የቀድሞ ዘመን ሰዎች እሱን አድርገው አሳይተውናል፡፡ ለእነሱ ከተቻለ ላንተ የማይቻልበት ምክንያት ምንድን ነው?"

"ምንም፡፡" አልኩት በአንገቴና በትከሻዬ ጭምር፡፡

"እንግዲያውስ አድርገውና እሳቱን እንሙቃ፡፡" አለኝና የዋርካውን ስር ትራስ አድርጎ በጀርባው ተጋደመ፡፡

እንዴት ነው እንጨትና እንጨት አፋትጌ እሳት የምፈጥረው?... ከዚህ በፊት ሰዎች እንጨት አፋትገው እሳት ሲፈጥሩ ፊልም ላይ ተመልክቻለሁ፡፡ ትዕይንቱን በዓይነ ሕሊናዬ ከለስኩት፡፡ መሞከር አለብኝ፡፡ ከኪሴ የጥፍር መቁረጫ አወጣሁና አንዱን ስለት መዝጌ መካከለኛ ውፍረት ያለውን



ጭራሮ እንስቼ መሃሉን መቦርቦር ያዝኩኝ፡፡ ከዚያም፤ ሌላ ጭራሮ አንስቼ ጫፉን ከቦረቦርኩት ጉድጓድ ጋር እንዲመጣጠን ቀረፅኩት፡፡ የቦረቦርኩትን እንጨት ከጭራሮዎቹ ስር አደላደልኩና የቀረፅኩትን እንጨት ከትቼበት በሁለት እጆቼ መዳፎች አፈትገው ገባሁ፡፡

ከብዙ ደቂቃዎች በኋላ የእጆቼ መዳፎች ከመጋላቸውና ከመላላጣቸው በቀር ያገኘሁት ውጤት አልነበረም፡፡ ትዕግሥቴ ተሟጦ፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እሳት መፍጠር መቻሉንም ተጠራጥሬ ከንቱ ሙከራዬን ለማቆም ዳር ዳር ስል በድንገት የቦረቦርኩት ጉድጓድ የእሳት ላንቃ ተፉና ጭራሮዎቹ ላይ መደነስ ጀመረ፡፡

ነገሩ ድንገተኛ ከመሆኑ የተነሳ ደንግጬ ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ፡፡ ጭራሮዎቹ መያያዝ ሲጀምሩ ሁለመናዬ በደስታ ተንቀጠቀጠ፡፡ ጮክ ብዬ ልስቅ ሁሉ ፈልጌ ነበር፡፡ ካህኑን ዞር ብዬ አየሁት፡፡ እንቀላፍቷል፡፡ ልፋቴንም ውጤቴንም ሳያይ እንቀላፍቷል፡፡ ልቀሰቅሰው ፈለግኩ፡፡ ፊቱ ላይ ያየሁት ሰላም ግን ፍፁም ሊያናውጡት የሚደፍሩት ዓይነት አልነበረምና እጄን ሰበሰብኩ፡፡ ዳሩ፣ እኔን የደነቀኝ ነገር እሱን መች ይደንቀውና ነው እንቅልፍ የምነሳው?

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

## - 4 -

*"በአቋራጭ መንገድ የተገኘ ጥበብ ዕድሜው አጭር ነው::"*

በነጋታው ጉዟችንን በማለዳ ጀመርን:: ጠዋት አንድ መንደርን አልፈን ልንሄድ ስንል አንድ ሀሳብ ልቤ ውስጥ ገባ:: 'ምናልባት ዛሬም እንደ ትናንቱ ጫካ ውስጥ የምናድር ከሆነ፤ አጄ እስኪላጥ ድረስ እንጨት ከእንጨት ከማፋትግ እዚሁ አካባቢ አንድ የሸቀጥ ሱቅ ፈልጌ ክብሪት ገዝቼ መያዝ አለብኝ::' አልኩኝና በዓይኔ አማትር ገባሁ:: ከወዲያ አንዲት ትንሽ ሱቅ ታየችኝና ፈገግ አልኩ:: ካህኑ ግን ሱቋ ጋር ከመድረሳችን በፊት የገጠመንን የመንደር ቅያስ መረጠና አቅጣጫውን ለወጠ:: ቆም አልኩኝና "እዚያች ሱቅ ዕቃ ልገዛ ነበር::" አልኩት በጣቴ አቅጣጫውን እየጠቆምኩት::

"በአቋራጭ መንገድ የተገኘ ጥበብ ዕድሜው አጭር ነው::" አለኝ መራመዱን ሳያቋርጥ:: ንግግሩ አስደንግጦኝ እንዴ ወደሱ ቀጥሎም ወደ ሱቋ ተመለከትኩና ፈጠን፣ ፈጠን ብዬ ተከተልኩት::

ወደ ሱቋ ለመሄድ የፈለግኩበትን ምክንያት አውቆብኛል:: 'መቼም ሰነፍ ብሎ እንደሚታዘበኝ ነው::' እያልኩ ጎን ጎኑ መራመድ ቀጠልኩኝ::

"ጥበብ ስር ሊኖረው ይገባል:: አንድ ሰው ችግኝ መትከልን ጥበብ ሲያደርግ ያ ችግኝ ዛፍ ሆኖ እስኪያድግ ድረስ እንከብካቤ የማድረግንም



እውቀት እየተማረ ይሄዳል:: ያ ዛፍ ሲያድግም ለአካባቢው ነፋሻማ አየር እንደሚያመጣ፣ አፈሩን ከመሸርሸር እንደሚታደግ፣ ለዓይኖቹም ውበት እንደሚሆን፣ አዕዋፋትም ጎጇቸውን ሰርተውበት ጥዑመ ዝማሬያቸውን ያለስስት እንደሚለግሱት፣ ጭራሮውም እሳት ሆኖ ሙቀትና ብርሃንን እንደሚሰጠው፣ ይሄን ሁሉ እውቀት የችግኙ ጌታ ይረዳል::

ጥበብን በተገቢው ወይም ደግሞ በሚጠይቀው መንገድ ሄደህ ስትማረው፣ ለዚያ ጥበቡን ለፈለግከበት ዓላማ ብቻ ሳይሆን፤ በወቅቱ ለሚገጥሙህ ብዙ ችግሮች መፍትሔ እንድትፈልግ አብስሎ ያዘጋጅሃል:: ይሄንን የምነግርህ... እሳት፥ ክብሪት ሆኖ ከቦታ ቦታ በየኪሳችን መዘዋወር እስከጀመረበት ጊዜ ድረስ ስንት ጥበብ እንደፈሰሰበት እንድትረዳው ነው:: ለዘለዓለሙ ሳያሰልስ ከሚፈሰው የጥበብ ወንዝ ላይ የድርሻህን መጨለፍ ካልፈለግህ ግን በእርግጥም እጅህ ከሚላላጥና ውሃ ከሚቋጥር ይልቅ የምትፈልገውን እሳት ክብሪቱ ይሰጥሃል::" ብሎ ንግግሩን ደመደመ::

እኔም የስንፍናውን መንገድ በመምረጤ ራሴን እየታዘብኩ ያለምንም ንግግር መጓዜን ቀጠልኩ:: ከደቂቃዎች በኋላ ግርግር የማይታይበትን መንገድ ይዘን ስንሄድ ወደኔ ዞር አለና "እናንተ ወጣቶች የዚህ የቁሳዊው ሥልጣኔ ፍሬዎች ናችሁ::" ብሎ ጨዋታውን ቀጠለ::

"...እኛ ሽማግሌዎቹ ደግሞ የመንፈሳዊው ዓለም ፍሬዎች ነን:: ሥልጣኔያችንም መንፈሳዊ ነው:: እናንተ ይሄንን እስተውሎት ያነሰውንና ሆሆታና ጭብጨባ የበዛበትን፣ ልጓም የማያውቅ የእሽቅድምድም ዘመን ትወከላላችሁ:: እኛ ደግሞ የረጋውን ጥንታዊውን ዘመን እንወከላለን:: በእናንተ ውስጥ እርጋታና ሰላም ጠፍቷል:: ብዙ ትሮጣላችሁ እንጂ የእርካታን ደጃፍ አትረግጡም:: ቤት ለመስራት አሊያም ለቤት ኪራይ የሚያስፈልጋችሁን ገንዘብ ለመሰብሰብ ዕድሜ ልካችሁን ስትቅበዘበዙ ትኖራላችሁ:: ይሄንን ገንዘብ ለማግኘት የሕይወታችሁን አብላጫ ጊዜ

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

የምታሳልፉት ግን ከቤት ውጪ በየአደባባዩና በየስርቻው ስር ስትጉላሉ ነው::

"የኑሮ ጭንቀታችሁ የምትይዙ የምትጨብጡትን አሳጥቷችኋል:: ደስታና እርካታን የምትፈልጉበት መንገዳችሁ፣ ሁሌም ሌላ ጥያቄ ይጭርባችኋል እንጂ መልስ ሰጥቷችሁ አያውቅም:: እንዲህ እንደሆናችሁም ታልፉላችሁ::

"ለመሆኑ ሥልጣኔ ምንድን ነው?... የሰው ልጅ፣ አስቀድሞ በነፍሱ ካልሰለጠነ፣ በሰውነቱ ካልሰለጠነ፣ በማንነቱ ካልሰለጠነ ምኑን ነው ሰለጠነ የምንለው?... መገልገያ ቁሱን ነው?... በእርግጥም የሰው ልጅ ቁሶች ከሰራቸው ከሰው ልጅ በላይ ሰልጥነዋል:: ተራቀውማል:: እነዚህ ቁሶች እንደ ሰው ልጅ ነፍስ ቢኖራቸው ኖሮ ከሰው ልጅ በላይ አስተዋዮች በሆኑ ነበር::

"እስቲ ይሄን ሥልጣኔ ያላችሁትን ነገር በጥሞና ተመልከቱት:: የዘመንኛው ቁሳዊ ሥልጣኔ ግኝቶችን ልብ በሏቸው:: ዓለም ላለባት ችግር መፍትሔ ከመሻት ይልቅ፣ ግኝቶቹ ራሳቸው ከምንም የከፉ ችግር እየሆኑ እንዲያውም የቀደሙትን ችግሮች እስከማስረሳት ደርሰዋል:: ግኝቶቹ ከሚያስከትሉት ጠንቅ ይልቅ በግኝቶቹ የሚገኘው ኃይል ገንዘብና ዝና ይበልጥ ትኩረት ተሰጥቶታል::

"በዚህ ሠለጠነ ባላችሁት ዘመን ሰላምን በምድር ላይ ለማራቀቅ የተደረገ ጥረት ሳይኖር፤ የጦር መሳሪያዎችን ይበልጥ አጥፊ አድርጎ ለማራቀቅ በየደቂቃው ብዙ ሚሊዮን ገንዘብ ይወጣል:: በዚህም ሳቢያ በአንደኛው የዓለም ጦርነት በሦስት ዓመት ተኩል ዕድሜ ብቻ ሃያ ሚሊዮን ያህል ወታደሮችና ብዙ ሚሊዮን ሰላማዊ ሰዎች ተጨፍጭፈዋል:: ለሃያ ሁለት ዓመታት ያህል ይበልጥ ሲራቀቅ ቆየና ደግሞ፤ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የአምስት ዓመት እድሜ ውስጥ ከ50 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን



አጨደ:: ከዚያም ዘመን በኋላ የዓለም ጦርነት ተብሎ አይጠራ እንጂ በየሀገራቱ የተደረጉ ጦርነቶች ከ20 ሚሊዮን በላይ ሰዎችን አጭደዋል::

"ታዲያ ሰው ያልሰለጠነበት ሥልጣኔ ምንድን ነው?.... ሥልጣኔ መጀመር ያለበት ከነፍስ ነው:: በመንፈስ ስትሰለጥን በማንነትህ ላይ ሥልጣኔ ይኖርሃል:: ስራህም መልካም፣ ፍሬህም ፍቅርና ሰላም ይሆናል:: በዚህ የዘመናዊው ሥልጣኔ ዘመን የረሃብና የችነፈር ክንድ ይበልጥ በርትቷል:: ለምን ቢባል ለአንድ የተፈጥሮ በሽታ መድኃኒት ለመፈለግ ከሚወጣው ገንዘብ ይልቅ ሌላ አዲስ በሽታ ለመፍጠር ይሄ ነው የማይባል ገንዘብ ይወጣልና ነው:: ብዙ ሚሊዮን የዓለም ረሃብተኞች የረሃብን ስሙን እንኳን እንዳይሰሙ ለማድረግ፤ ከጦር መሳሪያው ስልጣኔ ካዝና ላይ ጥቂት ገንዘብ መዛገኑ ብቻ በቂ ነበር::

"ለዚህም ነው የሰው ልጅ በመንፈስ ካልሰለጠነ በቀር ፍቅርና ሰላምን አያገኝም የምልህ:: ለዚህም ነው፣ ከእርካታ እልፍኝ ተጋብዛችሁ ሳለ ታዳሚዋ መሆን ሳትችሉ እንደተራባችሁ የምታልፉት:: ኑሯችሁ ሊበጠስ አንድ ሀሙስ የቀረውን ያህል ከሯል:: በዚህ የኑሮ ግብግብ ውስጥ ላለመውደቅ ሳያሰልሱ መሮጥ ነውና፤ ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ ህብረተሰብ፣ ሀገር፣ መላው የሰው ዘር ሳይሉ በግለኝነት መገስገስ የዓለሙ ሁሉ ታሪክ ሆኗል:: ታዲያ እርካታን የቱ ጋር ቆማችሁ ትረኩባት? ደስታን ከማን ጋር ሆናችሁ ታጣጥሟት?

"የዘመናዊው ሥልጣኔ ግብ ኃይልና ገንዘብ ነው:: ኃይልንና ገንዘብን ቅድሚያ ባደረገ ግስጋሴ ውስጥ ከፍቅር ይልቅ ጥላቻ ይነግሳል:: ከመከባበር ይልቅ መናናቅ ይንሰራፋል:: ከወዳጅነት ይልቅ ጠላትነት ይበረታል:: መንፈሳዊው ሥልጣኔ የተመሰረተው ፍቅር ላይ ነው:: ፍቅር ደግሞ የሰብአዊነት ቁልፍ ነው::

Scanned with CamScanner

ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ራሱን ለፍቅር ያስገዛል፡፡ በዘመናዊው
ወይም በቁሳዊው ሥልጣኔ ውስጥ ያላችሁ ተዋናይነት ያልገዛላችሁ እርካታ
እና ሰላም በመንፈስ ብትሰለጥኑ ኖሮ ሁሌም ከደጃፋችሁ ይኖራል፡፡ ወደ
ውስጣችሁ! ወደ መሰረታችሁ በመመለስ ላይ ትጉ፡፡ ትናንት በገነነው
ላይ ዛሬ ሌላው ገንኖ! የትናንቱን ገናና በሚያስረሳው ዓለም አትወናበዱ፡፡
ዛሬ ተጨብጭቦበለት ነገ በሌላው ጭብጨባ በሚዋጠው ወረተኛ ዓለም
አትታለሉ፡፡

"ይቺ ዓለም ምንም ውብና የምታጓጓ መስላ ብትታያችሁ፤ ጥንት
የነገሥታትና የባለፀጎች መናኸሪያ የነበረችው ውቧ ባቢሎንም ከእነጌጧና
ሥልጣኔዋ ጠፍታለች፡፡" እስና ዞር ብሎ ተመለከተኝ፡፡ ከዚያም፡-

"ዛሬ ምስኪንና ተመፅዋች የሆነችው ኢትዮጵያ ለዚህ ሁሉ ችግር
መድኃኒትና የመፍትሔም ምሳሌ ትሆን ዘንድ ነበር ጥንት የተፈጠረችው፡፡
ለዚህ በቶዳ ቀለም! በዘርና በሃይማኖት ለምትጫረስ ዓለም አንድ የመሆን
ምሣሌና መፍትሔ ነበር መሰረቷ፡፡ ዛሬ ግን ያን መሆን አልቻለችም፡፡
እናንተ ልጆቿ በነፍሳችሁና በማንነታችሁ ላይ በርትታችሁ ስትሰለጥኑ
እሷንም ወደ መሰረቷ ትመልሷታላችሁ፡፡ ያኔ ዓለም ለኢትዮጵያ
ከምትሰጠው በላይ ኢትዮጵያ ለዓለም የምታበረክተው ይበዛል፡፡" አለኝና
ወደ ዝምታው ወረደ፡፡ እኔም ወደ ዝምታ መንደሬ ተመልሼ ገባሁ፡፡

የዛሬውም አዳራችን ከዱር ውስጥ እንደሆነ ተረጋገጠ፡፡ እኔም
ማረፊያችን እስከንደርስ ድረስ እግረ መንገዴን ጭራሮ እየለቀምኩ
ሄድኩኝ፡፡

"ዛሬ ሌሊቱን እዚህ ነው የምናሳልፈው፡፡" ብሎ አንድ ዛፍ አመለከተኝ፡፡
ሰብስቤ የታቀፍኩትን ጭራሮ ከፊቴ ስዘረግፈው፤ ከዛፉ ጎን ተሰብስቦ
የተከመረ ጭራሮ ተመለከትኩኝና በሁኔታው ፈገግ አልኩኝ፡፡ የአህያችንን
ሸክም አራግፈን ከዛፍ ስር አረፍ እንዳልን ካህኑ በፈገግታ፡-



"ዛሬ የጨለማው ጭራሮ ለቀማ ቀርቶልሃል ማለት ነው፡፡ ለመሆኑ
ለምን ነበር ጫካ ውስጥ ከገባን ጀምሮ ጭራሮ እየለቀምክ የመጣኸው?"
ብሎ ጠየቀኝ፡፡

"ጨለማው ሳይበረታ በፊትም መልቀምን ልሞክር ብዬ እንጂ፣
እንደትናንትናው ጨለማውንና የጫካውን መሃል ፈርቼ አይደለም፡፡"
ብዬ መለስኩለት፡፡

"እዚህ ስንደርስና ቀድሞን የተከማቸውን ጭራሮ ስታይ መንገዳችንን
ሁሉ ጭራሮ ስትለቅምና ስትሸከም በመምጣትህ ተገረምክ?"

"መገረሙንስ ተገርሜያለሁ፡፡ ግን ልፋቴን እንደ ከንቱ አላየሁትም፡፡
እዚህ ጭራሮ ተከማችቶ እንደሚጠብቀኝ እንዴት ማወቅ እችል ነበር?"
አልኩት በልበ ሙሉነት፡፡

"አሁን ግን አውቀሃል፡፡ ካወቅክ በኋላ ያገኘኸውን እውቀት በኋላ
ትነግረ ኛለህ፡፡ ዛሬ የምትማረው ሌላ እውቀት አለ፡፡ አሁን ጭራሮውን
እሳት አድርገውና እንሙቀው፡፡ ከዚያም ራታችንን እየተመገብን
እንጫወታለን፡፡" አለኝ፡፡

የዛሬው እንጨትን ከእንጨት በማፋተግ እሳት የመፍጠር ሙከራዬ
ግን እጅግ አድካሚ ሆነብኝ፡፡ ከትናንትናው ልፋቴ እጥፍ በላይ ለፋሁ፡፡
ከትናንትናው በላይ እጄ ተላላጠ፡፡ ትንሽ የእሳት ፍንጣቂ በተጫረልኝ
ቁጥር ማፋተጌን ሳላቋርጥ አጎንብሼ 'ሁፍ… ሁፍ' እያልኩ እንደጉም
የሚንከባለል የጭስ ክምር ዓይኔን ብዙ ካስለቀሰውና ከፉኛ ካሳለኝ በኋላ
ጭራሮዎቹን ማቀጣጠል ቻልኩኝ፡፡

ከዛሬ ይልቅ ትናንት በመጀመሪያ ሙከራዬ በቀላሉ እሳት ማቀጣጠሌን
ስረዳ 'ከብሪት ለመግዛት በማሰቤ ይሆን ዛሬ እንዲህ የፀናብኝ?' ብዬ
አሰብኩ፡፡

ካህኑ ከጨርቅ ኮሮጆው ውስጥ አምባሻ አውጥቶ ቆርሶ ሰጠኝና

በዝምታ ተመገብን፡፡ ውሃችንንም ጠጣን፡፡ ከዚያም በጀርባው ተኝቶ ከዋከብቱን መቃኘት ሲጀምር፣

"ዛሬ የምትማረው ሌላ እውቀት አለ ብለኸኝ ነበር፡፡ ምንድን ነው?" ብዬ ጠየቅኩት፡፡

"እሱንማ አደረግከው እኮ፡፡" አለኝ፡፡

ግራ ተጋብቼ "እዚህ ከደረስን በኋላ ያደረግኩት ነገር ቢኖር እሳት ማቀጣጠል ነው፡፡ ሌላ ምንም አላደረግኩም፡፡" አልኩት፡፡

"ታዲያ እሱ ነዋ የዛሬው አዲስ እውቀትህ፡፡" አለኝ ፈገግ ብሎ፡፡

"እሱንማ ትናንትም አድርጌዋለሁ፡፡ አዲስ እውቀትነቱ የቱ ጋር ነው?" ብዬ ሞገትኩት፡፡

"ትናንትእሳትአላቀጣጠልክም፡፡እሳትማቀጣጠልየቻልከውዛሬነው፡፡ ትናንት የዛሬውን ግማሽ ያህል ለፍተህ ተስፋ ልትቆርጥ ስትል ጭራሮው ተያያዘልህ፡፡ ዛሬ ግን ትናንት ተስፋ ልትቆርጥ ከነበረበት ልፋትህ እጥፍ በላይ ለፍተሃል፡፡ በእጥፍም ሕመም ተሰምቶሃል፡፡ ለምን ይመስልሃል?"

"ምናልባት በትናንቱና በዛሬው ጭራሮ መሃል ልዩነት ይኖር ይሆናላ!" ብዬ መለስኩለት፡፡

"በትናንቱና በዛሬው ጭራሮ መካከል ያለው ልዩነት ለመቀጣጠል በወሰዱት የጊዜ ልዩነት ሊገለፅ ይችላል፡፡ ትናንት 'አይሆንልኝም፣ አቅሙም የለኝም' ብለህ ተስፋ ልትቆርጥ በነበረበት የልፋትህ መጠንና በዛሬው እጥፍ ልፋትህ መካከል ያለው ልዩነት ግን፣ በትናንትናው አንተነትህ እና በዛሬው አንተነትህ መካከል ያለውን ልዩነት ይገልፃል፡፡ ትናንት 'አይሆንልኝም' ብለህ እጅህን ልትሰበስብ ስትል አንተ ሳታስተውለኝ ጭራሮህ ላይ ይሄን ዱቄት በትኘለሁ፡፡ ይሄ ነው የተፈጠረውን ሙቀት ነበልባል ያደረጋት፡፡" አለኝ ዱቄት የያዘች ትንሽ ብልቃጥ እያሳየኝ በፈገግታ፡፡ የትናንቱ ቡረቃዬ ታውሶኝ በራሴ ላይ በኃይል ሳቅኩኝ፡፡ እርሱም አብሮኝ ሳቀ፡፡



"አየህ?.... ትናንት የለፋኸው እሳት መፍጠር እስከምትችልበት አቅምህ ድረስ አልነበረም፡፡ ግን ደግሞ ሞክረሃልና ያችን ትንሽ ምስጢራዊ ሽልማት ብታገኝ ለዛሬ ትበረታለህ ብዬ አሰብኩኝ፡፡ ይኸው ዛሬ አልቀጣጠልም ብሎ ቢያስቸግርህም 'ትናንት አድርጌዋለሁ፤ ዛሬም የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም' ብለህ ከትናንትናው በላይና እሳት መፍጠር እስከምትችልበት ልከኛው አቅም ድረስ ተስፋ ሳትቆርጥ ተጋህ፡፡ ያለምንም እርዳታም እሳትን ፈጠርክ፡፡

"ብዙ ሰዎች፤ አንተ ትናንትና ተስፋ ቆርጠህ እጅህን ልትሰበስብበት የነበረው ቦታ ላይ ደርሰው እጅ ይሰጣሉ፡፡ ለስኬት ከዚያ በላይ መልፋት እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ ከዚያም በላይ የሆነ አቅም እንዳላቸውም አያውቁም፡፡ ስለዚህ... 'አይሆንልንም፣ አልቻልንም' ብለው ወደ ነበሩበት ይመለሳሉ፡፡

"ዛሬ እሳት መፍጠር የቻልከበት አቅምህ ትናንትም አብሮህ ነበር፡፡ አብሮህ እንዳለ ያላመንከው አንተ ነህ፡፡ ስለዚህ ነጋሪ አስፈለገህ፡፡ የትናንቱ ነበልባል 'ትችላለህ አይዞህ' እያለ በአዕምሮህ ጓዳ ሲንተገተግ፤ አንተም በእርግጠኝነት 'እችላለሁ' እያልክ እጥፍ ተጋህና ለውጤት በቃህ፡፡

"ይሄንን ቁም ነገር መቼም ቢሆን እንዳትረሳው፡፡ ሰዎችን ጥገኛ የማያደርግ ምስጢራዊ እገዛ መልካም ነው፡፡ ትናንት እንደረዳሁህ አውቀህ ቢሆን ኖሮ ዛሬም ከትናንትናው የላቀ አቅምህን አውጥተህ አትጠቀምበትም ነበር፡፡ የትናንቱን ያህል ትሞክርና 'ኤጭ!... ትናንትም እሱ ስለረዳኝ እንጂ ለውጤት መብቃት አልችልም ነበር፡፡' ብለህ ትሰበሰባለህ፡፡ ለማንኛውም...አንተም ይሄንን ለሌሎች አድርግ፡፡" አለኝ፡፡፡ በሆነው ነገርና በሰጠኝ እውቀት በጣም ተደነቅኩ፡፡

"አንተ ከመንገድ ሰብስበህ ስላመጣኸውና እዚሁ ተከማችቶ

ስለጠበቀህ ጭራሮስ ምን አሰብክ?" ብሎ ጠየቀኝ ከዋክብቱ ላይ ዓይኑን እያንከራተተ:: ጥቂት አሰላሰልኩና፡-

"የራሴን ጭራሮ ይገፍ በመምጣቴ፣ ሌላው ሰው የሰበሰበውን ጭራሮ አላጎደልኩትም:: ባለማጉደሌም፣ ምናልባት ነገ ጭራሮ ለመልቀም የማይችል ሰው እዚህ ቢደርስ ለእርሱ ያገለግለዋል:: ከእኔም ጭራሮ የተረፈውን አከዬበት እሄዳለሁ::" ብዬ ስመልስለት...

"ማን እንደሆነ የማታውቀውና ነገ እዚህ ደርሶ ይሄንን ጭራሮ የሚያገኘው ሰውም ተከምሮ ለጠበቀው ሲሳይ እግዚአብሔርን ያመሰግናል:: የምስጋናው በረከትም ቀድሞውኑ ጭራሮውን ሰብስቦ ላዘጋጀው ሰውና አግኝቶም ላላጎደለው ሰው ይሆናል::" ብሎ አከለበት:: ጥቂት ተጨዋውተንም ወደ እንቅልፍ ዓለም አመራን::



## - 5 -

"የሰው ልጅ ሁለት ዓይኖች እውነትን ሳይሆን ነፀብራቃዊ ምስሉን ይመለከታሉ:: አስተዋይ ልቦና ግን በንስር ዓይን ይመሰላል:: ከሰማይ አናት ላይ ሆኖ ውቅያኖስ ውስጥ ያለን እውነት መመልከት ይችላልና::"

.....

'አንተ ዓይኔ፣ ስለምን ነው ይሄን ወጣት ደጋግመህ የምታሳየኝ?....' መልስ የለም::

'ያሳየኸኝ አንተ ብትሆን ኖሮ ትመልስልኝ ነበር:: ... አንተ ልቤ ስለምን ነው ይሄንን ወጣት ደጋግመህ የምታሳየኝ?' አልኩት ጥያቄዬን ወደ ልቤ አዞሬው::

የሦስተኛ ቀን ጉዟችን አብላጫውን ከውስጣችን ጋር በመነጋገር አልፎ ይኸው አሁን በዘመመ የጭራሮ አጥር በተከለለች አንዲት ደሳሳ ጎጆ ውስጥ አድርሶናል:: የጎጆዋ ባለቤት ሃጂ ናቸው:: ከበሩ ፊት ለፊት በቀኝ በኩል ባለው ማዕዘን ቁርበት ላይ ተቀምጠው ጫት ይቅማሉ:: በስተቀኛቸው ይሄ መልከ መልካም ወጣት እግሮቹን አቆላልፎ ተቀምጦ በተመስጦ ጫት ይቅማል:: ዓይነ ስውር ወጣት ነው:: ከሃጂ በስተግራ ካህኑ፣ ከእርሱ ጎን ደግሞ እኔ ተቀምጫለሁ:: ከእኛ ፊት ለፊት አንዲት አሮጊት ቡና ያፈላሉ:: ከደቂቃዎች በፊት እኚሁ እናት ቤት ያፈራውን ራት ለእኛ ለእንግዶቹ መግበውናል::

Scanned with CamScanner

"እዚህ መንደር ስንደርስ፣ አንዱ ቤት በእንግድነት እንዲያሳርፉን እንጠይቃለን" ያለኝ ካህኑ ነበር፡፡ ቀኑም መሽቷል፤ እኔም ርሃብና መንገድ አድክሞኛልና ሃሳቡ አስደሰተኝ፡፡

ከሃጂ ጎጆ ጎን ያለው ግቢ በጥሩ ሁኔታ የቆመ የእንጨት አጥርና የቆርቆሮ መዝጊያ ያለው በመሆኑ፣ የቤቱ ጌታ እኛን ለማስተናገድ አቅም እንዳለው አሰቤ፣ ያንን ግቢ አንኳኩተን ማደሪያና ምግብ እንዲሰጡን እንድንጠይቅ ሃሳብ አቀረብኩለት፡፡ ካህኑ ያቺን ጥልቅ መልዕክት ያዘለች ፈገግታውን መገበኘና፡-

"አንተ ያየኸው የግቢውን አጥር እንጂ የቤቱን ጌታ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ለሺህ እንግዳ የሚተርፍ ማደሪያ ቢኖረውና ጎተራውም ሙሉ ቢሆንም የሰውየው ትንሽ ልብ ግን ጎዶሎ ናት፡፡ ባለው ላይ መጨመርን እንጂ ካለው ላይ መስጠትን አይወድም፡፡ እስቲ ከጎኑ ያለውንና በዘመመ የጭራሮ አጥር የተከበበውን ደሳሳ ጎጆ ተመልከት፡፡ በዚህ ምሽት የአጥሩ መዝጊያ ከፍት መሆኑ አይታይህም? ከዚሁ ከቆምከበት በዓይኖችህ አጥሩን ተሻግረህ ተመልከት እስቲ፡፡_ የጎጆዋስ በር ገርበብ ብሎ ተከፍቶ፣ ውስጧ ያለው ብርሃን ለዓይንህ አልደረሰም?...

"አንተ የመረጥከው ቤት የአጥሩም ሆነ የጎጆው በር ጥርቅም ተደርጎ በብዙ ቁልፎች ተከርችሟል፡፡ ከውስጡ ወደ ውጭ የሚያበራ ብርሃንም አይታይበትም፡፡ ይሄ የዘመመ ጎጆ ግን ከፍት ነው፡፡ ከፍት መሆኑ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ እኛን እንግዶቹን ለመቀበል እየጠበቀ ያለ አይመስልህም?... እና ስለምን ከፍት ሆኖ እየጠበቀህ ያለ በር ከጎንህ እያለ የተከረቸመ በር ከፍቱልኝ እያልክ ስታንኳኳ ትገኛለህ?" አለኝ፡፡

ይሄ ለእኔ ትልቅ ቁም ነገር ያለው ትምህርት ነው፡፡ መጪውን ለመረዳት አስቀድመው የሚመጡ ምልዕክቶችን ማስተዋል ማለት ይሄ አይደል እንዴ? ቤቶች በተዘጉበት እና ሰዎች ባንቀላፉበት ሰዓት ከፍት



ሆኖ የጠበቀን ቤት ጌቶቹ "እንኳን ደህና መጣችሁ" ብለው ሊቀበሉን መፍቀዳቸው አይደለምን?

ቃል ሳልተነፍስ ምን ያህል እንደተረዳሁት አንገቴን በመነቅነቅ ብቻ ገለፅኩለትና እርምጃዬን ወደተከፈተው የአጥር በር አደረኩ፡፡ እኔና ካህኑ ከፊት፣ አህያው እኛን ተከትሎ ግቢው ውስጥ ገባን፡፡ አህያው ገና ግቢው ውስጥ ከመግባቱ መሬቱ ያበቀለውን ሰርዶ መሸርሸም ጀመረ፡፡

ገርበብ ያለውን በር አንኳኳሁና "ቤቶች፣ አባካችሁ የመሸብን መንገደኞች ነን አሳድሩን፡፡" አልኩ፡፡ ከውስጥ "ግቡ... ግቡ" የሚል የእዛውንት ድምፅ ሰማን፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው እንግዲህ እዚህ የታደምነውና 'ለምን ይሄ ወጣት አትኩሮቴን ሳበ?' እያልኩ ልቤን የምጠይቀው፡፡

"ይሄ እንግዳ ወጣት ይሄን አካባቢ ያለመምሰሉ ብቻ 'ማን ይሆን? እዚህስ ምን አመጣው እያሰኝም?.... ደጋግመህ እንድታየው ያደረገህ እሱም እንዳንተ ይሄን አካባቢ ያለመምሰሉና የመጣውም ከመጣህበት ሥፍራ መሆኑ ነው፡፡ ምናልባትም ወደምትሄድበት የሚሄድም ሊሆን ይችላል፡፡' ብሎ መለሰልኝ ልቤ፡፡

"ልጆቼ ብርሃን ልብ ነው፡፡ ልብ ይስጣችሁ፡፡ ፍቅር የጀነት መንገድ ነው፡፡ እላህ፣ የምታፈቅሩበት ልብ ይስጣችሁ፡፡ በኒ አደም ስለ መፈቀር እጅጉን ይጨነቃል፤ በእጁ ያለውና ሊያገዘበት የሚችለው ኃይል ግን ማፍቀር መቻሉ ነው፡፡ ሰዎች ሊያፈቅሯችሁ ካልቻሉ ውስጣቸው ያለው የማፍቀር ኃይል ጨልምባቸው ነውና እዘኑላቸው፡፡ እናንተ ግን እነሱን ከመሆን እላህ ይሰውራችሁ፡፡" አሉን ሃጂ፡፡

ወጣቱ እጆቹን ዘርግቶ "አሜን" ሲል እኔም ተቀብዬ "አሜን" አልኩ፡፡ ይሄ ጨዋታ እኛ ከመምጣታችን በፊት የተጀመረ ይሁን ለእኛም ጭምር የተከፈተ አልገባኝም፡፡ ቁምነገሩ ግን እኔንም እንደሚመለከተኝ አላጣሁትም፡፡

Scanned with CamScanner

ሃጂ ለእኔም ለካህኑም ጫት አቀበሉን:: እኔ ጫት ቃሚ ነኝ:: የካህኑ ጫት መቀበል ግን ደነቀኝ:: ይሄ የሚደንቅ ሰው 'ካህን ነኝ' ያለኝ እኔ በማውቀው የካህንነት ትርጉም አይደለም ማለት ነው?... ስለዚህ ሰው ብዙ ማወቅ ይጠበቅብኛል:: በምን ምክንያት እንደሆነ እንጃ እንጂ ስራ ነገሩ ስለደነቀኝ አስቀድሜ 'ኮብላይ ካህን' ብዬ ሰይሜዋለሁ:: እውነትም ኮብላይ ካህን ነው::

ከእጣን ማጨሻው የሚወጣው ወፍራም የእጣን ጭስ ወደላይ ተንፏሎ እየከሳና እየሳሳ በጎጆዋ ዙሪያ ይንሳፈፍና እልም ይላል:: 'ለመሆኑ ይሄ ወፍራም ጭስ ከስቶና ሳስቶ እልም የሚለው ወደምንነት ተቀይሮ ይሆን?' ስል አሰብኩኝ::

"ሁሉም ነገር በለውጥ ውስጥ የሚያልፈው እኮ በፍቅር ሳቢያ ነው::" ብለው ሃጂ አባነኑኝ:: የባነንኩት በታላቅ ድንጋጤ ነው:: አሁን ስለ ጭሱ ያወራሁት በልቤ ነው ወይንስ ድምጼን አውጥቼ ነበር? የትኛው እውነት እንደሆነ ግራ ገባኝ::

"አንዱ ከሌላው ጋር ያለው መዋደድና መዋሃድ ለአፍታም ባለመቆሙ፤ ሁሉም ነገር በዘለዓለማዊ እንቅስቃሴና ለውጥ ውስጥ ይኖራል::" ብለው ሲቀጥሉማ 'የት ነው የመጣሁት?' ብዬ እስካስብ ድረስ ድንቅ አለኝ::

በአንድ የገጠር ጎጆ ውስጥ ሳይሆን በትልቅ የፊዚክስ መጽሐፍ ውስጥ ተረት ሆኜ የገባሁ ሁሉ መሰለኝ::

'ኃይል አይፈጠርም፣ አይሞትም:: ከአንድ ቅርፅ ወደሌላ ቅርፅ እየተለዋወጠ ይኖራል እንጂ' የሚለውን የፊዚክስ ንድፈ-ሀሳብ ነው ከሃጂ አንደበት የሰማሁት:: ግን ደግሞ እሳቸውስ ይሄን ንድፈ-ሀሳብ ተምረውት ቢሆንስ?... እንደዚያ ከሆነ መገረሜ ራሱ ያስገርማል:: የዚህ እውቀታቸው ምንጭ ምን እንደሆነ ማረጋገጥ ይጠበቅብኛል::

"ፍቅር የሁሉም ነገር መነሻና መድረሻ ነው:: አንድን ቤት ስንሰራ



ሁሉም ነገር ካልተዋደደና በአንድ ካልተዋሃደ እኮ ቤቱ ይወድቃል እንጂ አይቆምም:: ይቺ መሬታችንንም ብንወስድ ቁጥር ሥፍር የሌላቸው ብናኞች በፍቅር የመሠረቷት ህብር ናት:: እያንዳንዱ ግዙፍ ነገር ሁሉ ፍቅር የገለፀው የረቂቅ ብናኞች ህብር ነው::... እንግዲህ አላህ ማለት ይሄ ጥልቅ ፍቅር፣ ይሄ ረቂቅ ፍቅር ነው:: ታዲያ ፍቅርን ካልተረዳን እንደምን አላህን ልንረዳው እንችላለን?" አሉና በዓይናቸው ሁላችንንም ማተሩን::

"አባቴ፣ አሁን የተናገሩት ነገር እውነት ነው:: ትልቅ ቁም ነገርም ነው:: ግን.... ይቅርታ ያድርጉልኝና አንድ ጥያቄ ልጠይቆት?" አልኳቸው::

"ደግ!" አሉኝ ደግ በሆነ ድምፅ::

"እንደው ዓለማዊ ትምህርት ተምረዋል?... ማለቴ ፊዚክስ አጥንተዋል?"

"ዓለማዊ ትምህርት አልከኝ?!... በእርግጥ ትምህርት ቤት ሄዶ መማሩ መልካም ነው:: ግን የልብን እውቀት ሽሮ በተጣመመ መንገድ መሄድ ነው ትልቁ አደጋ:: እናንተ የዘመኑ ወጣቶች ደግሞ ልባችሁ ከሚነግራችሁ ይልቅ መጽሐፍ የነገራችሁን ብቻ አምናችሁ፣ ግራ በተጋባ እውቀት ውስጥ ትዋኛላችሁ::... እኔ ግን አላህ የሰጠኝን እውቀት ነው የማምን:: ትምህርት ቤትም ገብቼ አላውቅ:: አንተም የተፈጥሮን ምስጢር ራስህ መርምረውና የአላህን ቋንቋ ትረዳዋለህ:: አላህ ስራውን የሚሰራው በብዙ ምስጢራዊ ጥበቦች ውስጥ ነው:: የአላህን ቋንቋ ስትረዳ እውነተኛውን ጥበብ ታገኘዋለህ::" ብለው መለሱልኝ::

በመስማማት አንገቴን ነቀነቅኩኝ:: ካህኑም ዓይነ ስውሩም ወጣት በሃጂ ንግግር በመስማማት አንገታቸውን ነቀነቁ::

"ይሄ ወጣት እንዳንተው ፊደል የቆጠረ የከተማ ልጅ ነው:: እዚህ እኔ ጋር ከመጣ ሳምንት ያልፈዋል:: የሚያስገርም ታሪክ ያለው ወጣት ነው:: መቼም አንዳችን ከሌላችን የምንማረው ብዙ ቁም ነገር ይኖራል:: እስቲ

Scanned with CamScanner

መጀመሪያ ስላንተ አጫውተንና ከዚያ ደግሞ እሱ ታሪኩን ያጫውተናል::" አሉኝ ሃጂ::

ከየት እንደምጀምር ትንሽ ካሰላሰልኩ በኋላ እዚህ ጎጆ እስከደርስ ድረስ ያለውን ታሪኬን በአጭሩ አጫወትኳቸው::

ከእኔ ታሪክ በኋላ የተደመጠው የዚያ ዓይነ ስውር ታሪክ ግን የሚያስደነግጥ ከመሆኑ አልፎ 'በእኔ ቢደርስ ኖሮ ምን እሆን ነበር?' አሰኘኝ::

'ወይ ዕድላዊት! ለካ ምንም ያደረግሽኝ ነገር የለም:: ይቺን አደረግሽኝ ብዬ ይሄን ያህል ስሰቃይ፣ ለካስ ከምንም የገዘፈ በደል ደርሶበት ይቅርታ በማድረግ ስቃዩን የገደለ ሰውም አለ::' አልኩኝ በልቤ::

"ፍቅረኛዬ እጅጉን ውብ ነበረች::" ብሎ ጀመረ ወጣቱ:: "ዓይኖቿ ከተፈጠረችበት ዕለት ጀምሮ ማየት አይችሉም ነበር:: ዓይነ ስውር በመሆኗ ሳቢያ ብቻ ራሷን ጨምሮ፣ ሁሉንም ሰው ትጠላ ነበር:: ለእሷ የነበረኝን ፍቅር መግለፅ ይከብደኛል:: እሷም ብትሆን በማንኛውም ሁኔታ ሁሌም ከጎኗ የማልለየው እኔ ብቻ ነበርኩና ትወደኝ ነበር::

'ዓለምንበዓይኖቼማየትብችልአገባህነበር'ትለኛለችደጋግማ::አንድቀን ጥንድ ዓይኖች ተለገሷት:: እኔን ጨምሮ የጓጓችለትን ብርሃን ማየት ቻለች:: 'የኔ ውድ፣ አሁን ዓለምን ማየት ችለሻል:: እንደቃልሽ እንጋባ::' ብዬ ጠየቅኋት:: ያኔ ግን በድንጋጤ ተንቀጠቀጠች:: እኔ ፍቅረኛዋም ዓይነ ስውር መሆኔን ስታይ ከፉኛ ተንቀጠቀጠች:: እንኳን ልታገባኝ አብራኝ መሆን እንኳ እንደማትፈልግ አረዳችኝ::

"ፍፁም ያልጠበቅኩት ነገር ነበርና የምገባበት እስካጣ ድረስ ደነገጥኩኝ:: ግን ምን ማድረግ እችል ነበር? በዕንባዬ እየታጠብኩ ሄድኩ፣ ራቅኳት:: ከቀናት በኋላ ጥቂት ቃላት የያዘ ደብዳቤ ላኩላት:: 'ውዴ፣ ዓይኖቼን



አደራ ተንከባከቢልኝ::' የሚል ደብዳቤ:: የዚያኑ እለት ያን እምነት የጣልኩበትን ዓለም ትቼ ሩቅ ለመሄድ ተነሳሁ::

"እንግዲህ ሁኔታዎች ሲለወጡ የሰው ልጅ አዕምሮም እንዲህ አብሮ ይለወጣል:: አየህ የሰው ልጆች ስንባል እንዲህ ነን:: ጥቂት የታደሉ ሰዎች ብቻ ናቸው በእነዚያ እጅጉን በከፉ የጨለማና የስቃይ ዘመናት ውስጥ ሁሌም ከጎናቸው ያልተለዩ ሰዎችን የማይረሱ::" ብሎ የፍቅር ገጠመኙን በአጭሩ አጫወተን:: ምን ዓይነት ጥንካሬ ቢኖረው ነው ይሄን ታሪክ ዛሬ እንደተረት ለማውጋት የበቃው?... አስደናቂው ወጣት ንግግሩን ቀጠለ::

"እናባንተላይየሆነውበእኔላይከደረሰውጋርሲነፃፀርምንምነው::እኔግን ያቺን ምስኪን ልጅ ሙሉ ለሙሉ ይቅርታ አድርጌላታለሁ:: ላዝንላት እንጂ ላዝንባት እንደማይገባኝ አሁን ተረድቻለሁ:: ከሁሉም ከሁሉም የሚፀፅተኝ አንድ ነገር ብቻ አለ:: የተረገምኩ ጨካኝ ነኝና እግዚአብሔር ይቅር ይለኝ ዘንድ ይኸው በየቀኑ እፀልያለሁ:: ቀሪ ዕድሜዬን ዓይነ ስውር ሆኜ እንድኖር የወሰነው አፍቃሪ ልቤ እንዴት ጨካኝ መሆን ቻለበት?... የሆነው ሁሉ ከሆነ በኋላ ስለምን የእኔን ዓይኖች እንደለገስኳት ነገርኳት? እንዴት አፈቅራት የነበረችን ምስኪን ልጅ ቀሪ ዕድሜዋን በፀፀትና በስቃይ እንድትኖር ፈረድኩባት? ዓይኖቿ የእኔ ዓይኖች መሆናቸውን ስለነገርኳት ስቃይን ፈረድኩባት እንጂ ምን ተጠቀምኩ? ምንም::

"ዛሬ፣ እሷ የተወችኝ ዕለት ከደረሰብኝ ስቃይ በላይ በዚህ ጭካኔዬ እየተሰቃየሁ አለሁ:: እናንተም እግዚአብሔር ይቅር ይለኝ ዘንድ ዱዓ አድርጉልኝ::" አለና አቀረቀረ:: የእንባ ዘለላዎች ከመነፅሩ በታች ሲወርዱ ተመለከትኩኝ::

'ይሄ ወጣት ምን ዓይነት ተዓምር ነው የሚያወራው?... ለዚያች ሴት ይቅርታ ማድረጉ ሲደንቀኝ፣ ዛሬ ዓለምን ያየችባቸው ዓይኖች የርሱ

Scanned with CamScanner

መሆናቸውን ስለነገራት ብቻ ራሱን እንደ አረመኔ ቆጥሮ የሚሰቃይ ሰው ምን ዓይነት ተፈጥሮ ነው?' ብዬ እጅጉን ተደነቅኩኝ::

ለራሴ የሰጠሁት ቦታ በእነዚህ ሦስት ቀናት እያሽቆለቆለ ወርዶ አሁንማ በአፍጢሙ ተደፋ:: ይሄ ወጣት ይሄን ያህል መስዋዕትነት ከፍሎም ላገኘው ምላሽ ይሄን ማድረግ ከቻለ፤ እኔስ ማን የሚሉኝ ነኝ?... ከንቱ ነበርኩ ማለት ነው:: የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ከንቱ ከመሆኔም ብሶ፣ ከንቱ መሆኔን እንኳ እስከዛሬ ያለማወቄ ነው:: አሁን ግን ቢያንስ ከንቱ መሆኔን ተረድቻለሁ:: ቀሪው ነገር ከንቱነቴን ከነፍሴ ውስጥ አጥቤ የማፅዳት ስራ ነው:: ለዚህ ደግሞ መንገድ ላይ ነኝ ብዬ አሰብኩ::

"ልጄ ሁሉም ነገር የሚሆነው በምክንያት ነው:: ለልጅቱ ይቅርታ ማድግህ መልካም ነው::" አለና ካህኑ መምህሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፁን አሰማ::

"... ግን ደግሞ ለራስህም ይቅርታን አትንፈግ:: ዓይኖችህን እንደሰጠሃት መንገርህ እኮ አንተ እንዳሰብከው ያን ያህልም ጉዳት አይኖረው ይሆናል። ምናልባትም ይሄን ሳትነግራት ቀርተህ ቢሆን ኖሮ ለሰራችው በደል ንስሃ ሳትገባ ታልፍ ይሆናል ልጄ:: አሁን ቢያንስ ለንስሃ ጊዜ ሰጥተሃታል። ከዚህ በኋላ ያለው ነገር የእርሷ ፈንታ ነው:: አየህ... ዓይኖቿ ማየት ስላልቻሉ ብቻ ራሷን ጨምሮ ዓለምን ሁሉ ስትጠላ የኖረች ሴት በመሆኗ፣ የልቧን ብርሃን ጋርዳዋለች::

"አንተ ዛሬ የተፀፀትከበትና ያኔ የላከላት ደብዳቤ ይሄንን የልቧን ብርሃን የጋረደውን ጨለማ ገፎ፤ ነገሮችን እስከዛሬ ባላየችበት መንገድ እንድታይ ረድቷት ቢሆንስ ምን ታውቃለህ?... ሁሉም ነገር የሆነውና የሚሆነው በምክንያት መሆኑን አታምንም?"

ልጁ ልክ በዓይኖቹ እንደሚመለከት ሁሉ ነው ካህኑን የሚመለከተው።

"ልክ ተናግረዋል አባቴ:: በፍፁም በዚህ መንገድ አላሰብኩትም ነበር።"



እስከአሁን ያልታየ ጥልቅ ሰላም የሰፈነበት ፈገግታ ፊቱ ላይ ታየ:: በብርሃን የተጥለቀለቀ ፈገግታ::

"እንግዲያውስ ለራስህ ይቅርታን አድርግ:: አይሁዶችና ሮማውያን ክርስቶስን መስቀል ላይ ሰቅለው ሲያሰቃዩት ወደ ሰማይ አንጋጦ የተናገረውን ሰምተሃል መቼም:: 'አባቴ ሆይ፣ የሚሰሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው::' ነው ያለው:: ይቅር ባይነትን ጥግ አድርሶ ሲያስተምር መሆኑን ልብ በል:: ከዚያስ ምን ተፈጠረ?... ልክ ነፍስና ስጋው ሲላቀቁ መሬት ራደች፣ ቀኑን ፅልመት ዋጠው፣ የቤተ መቅደስ መጋረጃዎች ተሰነጠቁ:: ይሄስ ለምን የሆነ ይመስልሃል?....መስቀል ላይ ሰቅለው ያሰቃዩት 'እውነትን' እንደሆነ ሰዎቹ እንዲያውቁት ነው:: አየህ፣ እየሱስን ሀሰተኛ አድርገው አሰቃይተው የሰቀሉት ሁሉ፣ እሱ እውነት እንደሆነ እንዲረዱት ብሎ እግዚአብሔር ያንን ተዓምር አሳያቸው:: የተዓምሩ መልዕክት ምን ማለት እንደሆነ ገብቶሃል?... ያንን ሀጢያት የሰሩ ሰዎች ሁሉ እርሱ እውነት እንደሆነ አውቀው ንስሃ እንዲገቡ ብሎ ነው እንጂ ቀሪ ዕድሜያቸውን በሰሩት ሀጢያት በፀፀት እየተሰቃዩ እንዲኖሩ ብሎ አይደለም::

"አንተም በመጨረሻው መልዕክትህ ለልጅቱ የንስሃ ጊዜ ሰጥተሃታል እኮ:: ንስሃውን የመጠቀም አሊያም ያለመጠቀሙ ጉዳይ በልጅቱ ብቻ ተወስኖ ነው የሚቀር:: አንተ ያደረግከው ግን ትክክለኛውን ነገር ነው::" በማለት ካህኑ ንግግሩን ቋጨ:: ወጣቱም አንገቱን በገባኝ እየነቀነቀ በተመስጦ አደመጠው:: ፊቱ ላይ ያነበብኩት ሰላም አስቀናኝ::

እነዚህ ሰዎች ሰውን ከውስጥ ስቃዩ የመፈወስ ትልቅ ኃይል አላቸው:: ሃጂም ሆኑ ካህኑ በታላቅ ጥበብ ተጠምቀው ሳሉ፤ እነርሱ ግን እኛ መናኛ ብለን የምናስበውን ዓይነት ኑሮ ይኖራሉ:: እኛ ደግሞ በጥቂት

Scanned with CamScanner

እንንገማለሳለን:: ድንቅ እውቀታችን ሰማይ ነከተን፣ አዩን፣ አዩን ኢያልን ነገር፣ ድንቅ ተዓምር::

ስቃይ በምን ይሆን የሚለካው?... በቆይታ ጊዜው?... በሚያደርሰው የጉዳት መጠን?... በምንም ይሁን በምን ብቻ የእኔ ስቃይ መጠኑ ቀንሷል:: በእርግጥ ጨርሶ አልጠፋም:: መዘናጋቴን አይቶ ብቅ ይልና በደረቱ እየተሳበ ሙሉ ለሙሉ ሊቆጣጠረኝ ሲሞከር ድንገት አባንንና እናቱን በኩርኩም ብዬ ኩም አደርገዋለሁ::

'የምናባቱ ስቃይ ነው!... ይሄን ስቃይ የሚሉትን ሰይጣን በይቅርታ ፀበል እያጠመቅኩ ሁለተኛ ባለፍኩበት እንዳያልፍ ከገነቴ ላባርረው እየጣርኩኝ ነው:: በቅርቡም ይሳካልኝና ከሕመሙ እፈወሳለሁ::' እለዋለሁ ራሴን:: አሁን የገባኝ አንድ ነገር አለ:: ከስቃይ መንፈስ ሙሉ ለሙሉ ካልተፈወስክ፤ ብዙ ቁጭቶች፣ ብዙ ቂሞች... ብቻ ይቅርታህን የሚሹ ብዙ፣ ብዙ የስቃይ ጅረቶች ከልብህ ስር ቤታቸውን መስርተዋል ማለት ነው::

እነዚህ የስቃይ ጅረቶች ከልብህ ስር ይነሱና በደም ቧንቧህ አድርገው እየፈሰሱ በየደም-ስሮችህ ይሰራጫሉ:: ከዚያም መላ ሰውነትህን ያዳርሳሉ:: እያሰቃዩህ፣ ሰላምና እርጋታህን እየነጠቁህ የአዕምሮህን ስራ ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥረው ያሳብዱሃል:: በቃ ውጤቱ ይሄ ነው::

ቂምና ቁጭትን የመሳሰሉ የስቃይ ጅረቶችን ለሌሎችም ሆነ ለራስህ ይቅርታ በማድረግ አድርቃቸው:: በልብህ ፍቅር እና ይቅር ባይነት አይጥፉ:: የደስታና የሰላም መንገዱ በዚያ ነውና::

እናም፥ እኔም ውስጥ የቀረው ስቃይ የነገረኝ ይቅርታዬን የሚሹ ብዙ ቂሞችና ቁጭቶች በልቤ ውስጥ እንዳሉ ነው:: ለምሣሌ ካህኑን ከማግኘቴ ከጥቂት ቀናት በፊት በጣም ተከፍቼ ነበር:: ዕድላዊት ስልክ እያወራች እኔ ወዳለሁበት ክፍል ገባች::



"አሁንስ አይሰማህም?" አለችው በወዲያኛው መስመር ያለውን ሰው:: ፍቅርና ስስት በተላበሰ ድምፅ:: ወዲያኛው ክፍል ስልኩ እየተቆራረጠ አላሰማማ ብሎ መሰል እኔ ወዳለሁበት ክፍል የመጣችው::

"እና ለምንድነው የጠፋህብኝ? ናፍቄሃለሁ እኮ..." አለችው:: ድምጿ ውስጥ ሐዘንና መማፀን ሰማሁበት:: የዚያ ሰው ልብ በደስታ ዕልልታዋን ታቀልጠው ይሆናል:: የእኔ ልብ ግን ስለራሷ አነባች::

'እኔ ወዳጇ ነኝ ጠላቷ?... ሌላው ቢቀር እየተሰቃየሁ መሆኔ ለምን አይገባትም?... ያሻትን ታድርግ፤ ግን ስለምን ፊት ለፊት ታሰቃየኛለች? ምናለ ዞር ብላ እንኳ ብታናግር?' እያልኩ እሰቃያለሁ::

እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ላለፉት ሁለት ዓመታት ተደጋግመው ተከስተዋል፤ ቅርፅና ዓይነታቸውን እየለዋወጡ::

ይሄ በሆነ በሁለተኛው ቀን ከዚያ ሰው ጋር ተያይዛ ሄደች:: የት እንደሄደችእንጃ::ብቻካህኑንእስካገኘሁበትቀንድረስአልተመለሰችም:: አሁንም አልተመለሰች ይሆናል::

"ታዲያ ከዚህ ምን ትረዳለህ?... ምስኪኗ ዕድላዊት ፍቅር ላይ መሆኗ አልታየህም?" አለኝ ልቤ::

"በእርግጥ ዛሬ ብቻ ሳይሆን ከዓመት በፊትም ይሄው ሰው ናፍቋት ለሳምንት ያህል ተኮራምታ ታለቅስ ነበር::" አልኩት ልቤን::

"ታዲያ ፍቅር ላይ መሆኗን ካወቅክ እንደምን ትፈርድባታህ?... አንድ ሰው ፍቅር ላይ ከሆነ እኮ ሌላው ነገር ሁሉ ለእርሱ ገለባ ነው:: ሀሳቡም ፍላጎቱም ያ ያፈቀረው ሰው ብቻ ነው:: ምነው... አንተስ በእርሷ ፍቅር ሳቢያ ብቻ ብዙ ነገሮችን እንደማይረቡህ ሁሉ አሽቀንጥረህ አልጣልክም እንዴ?" አለኝ::

"ልክ ነህ:: ከእኔ ይበልጥ ያፈቀረችው ሰው ስላለ ነው እኔን የዘነጋችኝ:: ወዳ አይደለም:: ለእኔ ያላትን ነገር ሁሉ የወሰደባት የዚያ ሰው ፍቅር

Scanned with CamScanner

ነው፡፡ እኔ የራሴን እየሁ እንጂ፤ እሷም እኮ ደስተኛ የምትሆነው ከስንት አንዴ ነው፡፡ አንድ ቀን ስለዚሁ ሰው በእኔ ፊት ለእንዷት ጓደኛዋ ስታወራ በደስታ ተሞልታ እንደነበር አስተውያለሁ፡፡ ታዲያ ብዙ ሐዘን ያለባትን ሴት ትንሽ ደስታን ለምን አጣጣመች ማለት ራሱስ ግፍ አይሆንም?... ይሄስ ራስ ወዳድነት አይደለም?... ለእኔ ፍቅር ከሌላት፣ ሌላን ሰው አፍቅራ ብትደሰት ምን አለበት?... እኔስ ብሆን ከሌላ ሰው ፍቅር እንደያዛት እያወቅኩ ስሯ ምን ጎለተኝ?... አብሬያት ባልሆን ኖሮ እኮ ፊት ለፊቴ ፍቅሯን ስትናዘዝ ባልሰማኋት ነበር፡፡ አዎ!... የሞተን ፍቅር ከዛሬ ነገ ይሽር ይሆናል እያልኩ እዚያው ቁጭ ብዬ ባልጠብቅ ኖሮ ብዙ ነገሮች ይቀየሩ ነበር፡፡"

"ያ ሁሉ ነበር ነው፡፡ አሁንስ?" ልቤ በጥያቄ አጣደፈኝ፡፡

"አሁንማ ያ ፍቅር ሞቷል፡፡ አርም አውጥቼ ልቀብረው ግድ ይላል፡፡ በጀመርኩት ጉዞ እገፋለሁ፡፡ ዕድላዊትንም የያዛት ፍቅር ስቃዬን እንዳታይ አውሯታልና፤ሳቃስትእንዳትሰማምጀሮዋንደፍኗታልናአልፈርድባትም፡፡ ለዚህም ይቅርታ አድርጌላታለሁ፡፡ የቀሩኝን ቂምና ቅሬታዎቼን ሁሉ ከውስጤ እያደንኩና እያወጣሁ ይቅርታ አደርግላታለሁ፡፡" ብዬ መለስኩለት፡፡

"በል በዚሁ በርታ፡፡ ግን ልብ አድርግ፡፡ በእርሷ ሳቢያ ትንሽም ቢሆን የስቃይ ስሜት ከተሰማህ ይቅርታ ያላደረግከበት ርዝራዥ ቂምና፣ ቁጭት በደምህ ውስጥ ቀርቷል ማለት ነው፡፡ ቂምና ቁጭት ከውስጥህ እስኪጠፋ ድረስ ይቅርታ ማድረግን እንደ ጠመንጃ ታጠቀው፡፡ ለወደፊቱም ጠመንጃውን አታውልቀው፡፡ እነዚህ ሁለት የስቃይ ጅረቶች ልብህ ውስጥ ቤት ከመመስረታቸው በፊት ትመልስበታለህ፡፡" አለኝና ልቤ ተራውን ለኮብላዩ ካህንና ለሃጂ ለቆ አደፈጠ፡፡



"ልጆቼ፣ ለሰዎች መልካምን ስታደርጉ ከነበረ፣ አሁንም መልካምን በማድረግ ትጉ፡፡ መልካም ያደረገ በመልካም ይመለስለታል፡፡ 'ላደረግነው መልካም ነገር ያገኘነው መልስ ክፋትን ነው፡፡' ብላችሁ ካሰባችሁ ተሳስታችኋል፡፡ ማንም ቢሆን የዘራውን ያጭዳል፡፡ ስህተቱ፣ ላደረጋችሁት መልካም ነገር ሁሉ ምላሹን የጠበቃችሁት ከዚያ መልካምን ካደረጋችሁለት ሰው መሆኑ ነው፡፡ የመልካም ስራ ዋጋው የሚገኘው ምንም ከማይሳነው አላህ ዘንድ ነው፡፡

"ግን አደራ ልጆቼ!... መልካምን በማድረግና መስዋዕት በመሆን መካከል ያለውን ግዙፍ ልዩነት አስተውሉ፡፡ በሙሉ ልቡ ካለው ላይ የሰጠ እሱ፣ በመስጠቱ ደስተኛ ነው፡፡ በመስጠቱ ብቻ የሁሉም ሩጫ ውጤት የሆነውን እርካታን ያገኛልና፡፡

"መስዋዕት መሆን ግን ፀፀትን ያመጣል፡፡ የትናንት ፀፀት ደግሞ የዛሬን ኑሮና ደስታን ይነጥቃል፡፡ የነገንም ኑሮ ይመርዛል፡፡ ልጆቼ በፀፀት ሳቢያ ደስታቸውን ሲያጡ ማየትን አይወድምና ራሳችሁን መስዋዕት ታደርጉ ዘንድ አላህ አይፈቅድም፡፡ አላህ ከልባችሁ የጠየቃችሁትን መልካም ነገር ሁሉ ይሰጣል፡፡ እስቲ ለሆነላችሁ ሁሉ አመስግኑና ማግኘት ወይም መሆን የምትፈልጉትን ነገር ከቀልብ ሆናችሁ ፀልዩና ጠይቁት፡፡ እንደሚያደርግላችሁ በሙሉ ልብ እመኑና የሆነላችሁ ያህል ይሰማችሁ፡፡ አመስግኑትም፡፡ ምንም የማይሳነው አላህ የሚያሳጣችሁ ምንም ነገር አይኖርም:

"አንድ ጊዜ ምን ሆነ መሰላችሁ፤ ሀገራችን ላይ ዝናብ ጠፋና የድርቅ ወሬ እዚህም እዚያም ሆነ፡፡ ሙስሊሙም በመስጅዱ፣ ክርስቲያኑም በመቅደሱ ወደ ፈጣሪ ሊጮህ በነቂስ ወጣ፡፡ አንድ አባወራ ሕፃን ልጁን "ና ወደ መስጅድ እንውጣ ፡፡ ሙስሊም ክርስቲያኑ ሁሉ ተሰብስበን ዝናብ እንዲሰጠን ወደ

Scanned with CamScanner

አላህ ልንፀልይ ነው::" ይልና የሕፃኑን እጅ ይዞ ከቤት ይወጣል:: ገና ደፉን እንደተራመዱ ሕፃኑ ልጅ "ቆይ፣ ቆይ አባዬ መጣሁ" ይልና እየሮጠ ወደ ቤት ይመለሳል:: ወደ መስጅድ ለመሄድ የተቻኮለው አባት "ምን ፈልጎ ነው?" እያለ በር በሩን ያያል:: ሕፃኑ አፍታም ሳይቆይ እየሮጠ ይመለስና "ዣንጥላ ረስተን ልንሄድ ነበር::" አለው በእጁ የያዘውን ዣንጥላ እያመለከተው:: የዚያ ሕፃን ልጅ ቀልብ ከሁሉም የተሻለ መሆኑን ተመልከቱ እንግዲህ:: አላህን ተሰባስበን ዝናብ ከጠየቅነውማ ዝናቡ በእርግጥም ይዘንባል ብሎ የሚጠለሉበትን ዣንጥላ ይዞ ወጣ:: የዚህን ሕፃን ቀልብ ከያዛችሁ የጠየቃችሁትን ታገኛላችሁ ልላችሁ ፈልጌ ነው::" አሉን ሃጂ።

በእውነትም የሕፃኑ ልጅ ልብ ይደንቃል:: ትልቅ ምስጢር ያዘለ አጭር መልዕክት ነው ከሃጂ የተላለፈልን:: በከተማ ወሬ አፍ አስከፉቶቹ እኛማ ጆሮ ብቻ ሆነናል:: መሆንም ይጠበቅብናል እንጂ::

"መቼም ጨዋታን ጨዋታ ያነሳዋል::" አሉና ከማርም የሚጣፍጥ ጨዋታቸውን ለመቀጠል አፋቸውን አበስ አደረጉ፣ ሃጂ::

"ወሎ ውስጥ የሆነ ታሪከን ነው የምነግራችሁ:: መቼም ወሎ የታላላቅ ሼኮች ሀገር ናት:: እና ምን ሆነ መሰላችሁ:: አንድ ባለጠጋ ሰው ዱዓ ማስደረግ ይፈልግና ከሸኮቹ አንዱን ቤቱ ይጋብዛል:: አድራው ሞቆ፣ ጫት እየተቃመ ዱዓ ሲደረግ፣ ሲመረቅና አሜን ሲባል ይመሻል:: ዱዓው አብቅቶ ሸኹም ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ:: መቼም እንዲህ ካለ በላኽ አላህ ይሰውረንና ሌሊት ሁሉም ባንቀላፋበት ሰዓት የባለጠጋው ቤት በእሳት ተያይዞ ከሞላ ንብረቱ ጋር አመድ ሆኖ ይወድማል:: ባለጠጋውና ቤተሰቡ ግን አንዲትም ጭረት ሳይነካቸው ከእሳቱ ይተርፋሉ:: ባለጠጋውም 'ቀኑን ሙሉ እንደዚያ ዱዓ ስናደርግ ቆይተን፣ ለዓመታት የገነባሁት



ንብረቴ እንዴት እንደዚህ የእሳት ራት ይሆናል?' እያለ ተብሰለሰለና ይሄንኑ ጥያቄ አስይዞ ወደ ሸኹ በማለዳ መልዕክተኛ ይልካል:: ሸኹም መልዕክቱን ካደመጡ በኋላ በመገረም "አንተዬ፣ ባንቅምበት ምን ሊመጣ ነበር?" ብለው መልስ ላኩለት:: 'ዱዓ ባናደርግበት ኖሮ ምን ሊመጣ ነበር?' የአስተዋይ ሰው ግሩም መልስ ነው:: እውነት እኮ ልጆቼ፣ የባለጠጋውና የቤተሰቦቹ ከዚያ ንብረቱን ዶግ አመድ ካደረገ እሳት መትረፍ ራሱ ተዓምር ነው:: ያቀን የዋሉበት ዱዓ የሱንና የቤተሰቡን ሕይወት እንዳተረፈ አልገባውም ነበር:: እናም የሰው ልጅ ሁሌም የሚያየው የላይ የላዩን፣ የግልቡን እንጂ ውስጡን አይመረምርም::" አሉና ሌላ ድንቅ ታሪከ አከሉልን::

## - 6 -

በነጋታው እስተዋዩን ሃጂን፣ አስገራሚ የሆነውን ወጣት እና ደጓን እናት ተሰናብተን ጉዟችንን ተያያዝን::

ስለ ኩብላዩ ካህን ብዙ ለማወቅ ብዙ የምጠይቀው ጥያቄ ነበረኝ:: ግን ካህኑ ማውራት ካልፈለገና ዝምታን ከመረጠ፣ ፊቱን በማየት ብቻ ዝምታውን መስበር ይከብድ ነበርና እኔም ወደ ውስጤ መመለስን መረጥኩኝ:: እናም በልቤ ማህደር ውስጥ 'ዕድላዊት' በሚል የዶሴ ስም ተመዝግበው የተቀመጡትን ቀሪ ቂሞችና ቅሬታዎች እያወጣሁ በይቅርታ እየገደልኳቸው ራሴን የማንፃቱ ስራ ላይ ተጠመድኩ::

ቀኑን ሙሉ ስንጓዝ ከካህኑ ጋር አንድ ሁለቴ ብቻ ጥቂት ቃላት ረፋድ ተለዋውጠናል::
አካባቢ አንድ የገበያ ቦታ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ከመቆማችን በቀር ጉዟችን ሰው አልፎ አልፎ በሚታይበት ሜዳና ጫካ ውስጥ ነበር:: ገበያ ውስጥ በቆምንበት ጊዜ ካህኑ ሁለት ሰዎች ቆመው ሲያወሩ በእንክሮ ሲያስተውላቸው ሳይ 'እነዚህ ሰዎች ማን ይሆኑ?' ብዬ እኔም የሚያወሩትን በትኩረት ማድመጥ ያዝኩ::

"እና ዛሬ እዚሁ ቀዬ ነዋ የምናሳልፍ?" አለ አንደኛው ገበሬ::

"ታዲያ እዚህ መጥቼ ያቺን ወዳጄን ሳልጎበኝ የምመለስ ይመስልሃል፣ ሞኞ?!... ባለቤቴ እንደሁ የልጅ ነገር እምቢ ብሏታል:: እንደው ተስፋ አልቆርጥ ብላ ለየቤተክስያኑ በመሳል ዕድሜዋን ገፋችው እንጂ ምንም እርባና የላት:: ይቺን ወዳጄን አጥብቄ ልያዝና መጠሪያዬን ላብጅ እንጂ… እኔኮ ግራ የሚገባኝ የዘራህበት መሬት እንዴት አላፈራ ይላል?! ተወኝማ ወዳጄ!.. ሸከማችንን ቶሎ፣ ቶሎ ሸቅጠን ከኮማሪቷ ዳሌ ጋር እንላፋ እንጂ ሌላ መላም የለው::" አለ ሁለተኛው ገበሬ በጨፈገገ ፊት::

ካህኑ እነርሱን ትቶ መንቀሳቀስ ሲቀጥል እኔም ተከትዬው ወደ መንገዳችን ገባን:: ጀምበር ልትጠልቅ ስታኮበኩብ አንድ የገጠር መንደር ደረስንና ካህኑ እየመራኝ አንድ ጎጆ በራፍ ላይ ቆምን:: ካህኑ በሩን ሲያንኳኳ "ማነው?" እያለች አንዲት ሴት ብቅ አለች::

"እሜቴ፣ የሩቅ ሀገር ሰዎች ነን:: ይሄን መንደር አልፈን ብንሄድ በድቅድቅ ጨለማ የሚገጥመን ጫካው ብቻ ነው:: ማረፊያ ትሰጭን እንደሁ ብለን ነው ደጅሽ የቆምነው::" አላት:: ሴትዮዋ ካህኑንም እኔንም በዓይኗ ገመገመችና፤

"ቤት የእግዚሀር ነው ግቡ::" አለችን:: የአህያችንን ጭነት አራግፈን እዚያው ደጇ ላይ ተውነውና ገባን:: ለእንግዳ የሚደረገው መስተንግዶ ቀረበልን:: እጃችንን አስታጥባን በጠላ የታጀበ ራት አቀረበችልን:: እርሷም ከእኛ ጋር ማዕድ ቀረበች:: የምግቡ መጣፈጥና የጠላው ጣዕም ድንቅ ባለሙያ ወይዘሮ መሆኗን ይመሰክራል::

ጎጆዋ በጣም ጠባብ ናት:: በዚያ ላይ ኩሽናውም እዚያው ነው:: ከርሷ መደብስርቁርበትጎዘጎዘችልንናአንድየነተበብርድልብስጣልአደረገችበት:: ሴትዮዋ ወግ አዋቂ ናት:: እዚህ በእርሷ ቀዬ የደረሱ አስቂኝ ገጠመኞችን እያነሳሳች አዝናናችን::

በመሃል ካህኑ ድንገት ብድግ አለና "እስቲ ዞር ዞር እያልኩ የዚህን ምሽት ውበት ልቃኝ:: ብቆይም ምንም ስጋት አይግባችሁ:: ይሄ ወጣት ጫካውን ይፈራል እንጂ እኔ ያደግኩት ጫካ ውስጥ ነው:: ምንም አይተናኮለኝም:" ብሎን ወጣ::



Scanned with CamScanner

መቼም ስራ ብዙ ነው:: የት እንደሚሄድና ምን እንደሚሰራ አይታወቅም:: ምሽቱ ጠንክሮ ሊደገፉት የማይችሉት ጨለማ እስኪመስል ድረስ በጠላችንና በወጋችን ዘና እያልን ቆየን:: ካህኑ ግን አልተመለሰም:: 'ምን ገጥሞት ይሆን?' ብዬ አሰብኩና 'ብዙ አዋቂ የሆነውን ካህን ችግር እንደሚገጥመው ቢያስብ ኖሮ ቀድሞውንም አይወጣም ነበር' ብዬ ራሴን አረጋጋሁት::

"በል እንግዲህ እንቅልፍ መጥቶህም ከሆነ ጋደም በል:: እኚህ ጓደኛህ የገጠር ሰው ይመስላሉ:: ሁኔታውን ሁሉ ያውቃሉና ብዙ አትስጋ::" አለችኝ ሀሳቤ ገብቷት::

"እንቅልፌ እንኳ አልመጣም:: ባይሆን አንቺም እኛን ብለሽ እንቅልፍ አጣሽ:: ግዴለም አንቺ ተኚ፣ እኔም እስኪመለስ ጋደም ብዬ እጠብቀዋለሁ::" አልኩኝና የተዘጋጀልን ቦታ ላይ ገብቼ ብርድ ልብሱን ለበስኩት::

"እንግዲያውስ እስከታንቀላፋ ጠላህን ጠጣ::" የእኔንም የሷንም ኩባያ ጠላ ሞልታ አቀረበችና መደቧ ላይ ወጥታ ጨዋታችንን ቀጠልን::

ቁርበቱ ላይ ተቀምጬ የማወራት የከተማ ወሬ እሷን እያንከተከተና እያንሳፈፋት፣ እሷም የምታወጋኝ የገጠር ወግ እኔን እየደነቀኝና እያዝናናኝ ብዙ ቆየን::

"አንተዬ፣ እኚህ ሰው ከመጡም ያንኳኳሉ:: ድንገት እንቅልፍ ቢጥለን መዝጊያውን ሳልሸነቁር እንዳልቀር::" አለችና ተራምዳ አልፋኝ ወደ በሩ አዘገመች:: ከለበሰችው ልብስ ስር የሚንሳፈፈውን ዳሌዋን በኩራዙ ብርሃን አስተዋልኩት::

'ምን መሆኔ ነው? ጠላው መሆን አለበት ይሄን ያሳየኝ::' ብዬ ራሴን ታዘብኩት:: ራሴን ታዝቤ ሳላባራ ብልቴ ሲወጣጠር ታወቀኝ::



ራሴን ሰደብኩት:: በሩን ሸንቁራው ስትመለስም ዓይኔ ከዳሌዋ ላይ አልተነቀለም::

ሴትዮዋ ወደ መደቧ አልወጣችም:: ድንገት ጎኔ ቁጭ አለችና ዓይኔን ማየት እየሸሸች ተለጠፈችብኝ:: 'ጉድ ፈላ!' አልኩኝ በልቤ:: የእንግዳነት አዚያ ጋር አበቃ:: በምን ፍጥነት እንዳደረግነው አላውቅም ተጣብቀን መናጥ ጀምረናል::

የሰራነውን ሰርተን እንዳበቃን እሷም ቀና ብላ ልታየኝ ድፍረቱን እንዳጣች፣ እኔም ቀና ብዬ ላያት አፍሬ፣ ተነስታ መደቧ ላይ ወጣችና ፊቷን ወደ ግድግዳው አዙራ ጥቅልል ብላ ተኛች:: እኔም ብርድ ልብሴን እስከ አናቴ ተከናንቤ ተጋደምኩና ማሰብ ያዝኩኝ::

'ምን እያሰበች ይሆን?... ይሄ ካህን እንዴት እንዲህ ልቆይ ቻለ?...' ብዬ ስጠይቅና ስተነትን ከአንድ ሰዓት ያላነሰ ጊዜ ቆየሁ:: ከዚያም የሴትዮዋ አተነፋፈስ ሲለወጥ ሰማሁና እንቅልፍ እንደወሰዳት ተረዳሁ:: 'እፎይ!' አልኩ:: 'እፎይ!'... እሷም በዚህ ሰዓት ስላደረግነው ነገር እያሰበች ቢሆን ኖሮ ሌሊቱም የዘለዓለምን ያህል የረዘመ የጭንቅ ሌሊት ይሆን ነበር:: ደግነቱ የርሷ ማንቀላፋት ከጭንቅ ገላገለኝ::

ይሄን እያሰብኩ ሳለ ከውጪ እየቀረበ የመጣ የእርምጃ ኮቴ ሰማሁ:: ካህኑ መሆኑን ምንም አልተጠራጠርኩም:: ብቻ እንኳኩቶ እንዳይቀሰቅሳት ብዬ ቶሎ ተነሳሁና መዝጊያውን ከፈትኩት:: ካህኑ ራሱ ነው:: በኩራዙ ጭላንጭል ብርሃን ፊቱን ተመለከትኩት:: ያው ሰላም የሰፈነበት ገፁን እንደያዘ ነው:: በዝምታ ወደ መኝታችን ገባንና ኩራዙን አጥፍተን ተኛን::

ሌሊት ወፎች ሳይንጫጩ ካህኑ ከንዴን ወዝውዞ ከትኩስ እንቅልፌ ቀሰቀሰኝና ተነሳ:: ቀና ብዬ ላየው ብሞክር ምርግ ጨለማ እንጂ ምንም ማየት አልቻልኩም::

ብቻ ወደበሩ ሲራመድ ታወቀኝ:: ዞር ብዬ ወደ መደቡ ተመለከትኩኝ:: በዚህም ጨለማ ነው:: ካህኑ በሩን ከፍቶ ወጣ:: መንገዳችን ልንቀጥል መሆኑ ቢገባኝም የካህኑ ሁኔታ ግን ገርሞኛል:: 'እንዴት በእንግድነት ካደረበት ቤት ባለቤቷ ሳታውቅ ሹልክ ብሎ ይወጣል?' በእንግድነት የተቀበለችውን ሴት ሳያመሰግንና ሳይሰናበት ሹልክ ብሎ መውጣቱ አንድ ነገር ሹክ አለኝ::

'እሱም እንደኔ ሴትዮዋ ነቅታ በማታው ነገር እንዳትሳቀቅ ፈልጎ ይሆን?' ብዬ አሰብኩኝ:: እንደዚያ ከሆነ፣ ያደረግነውን አውቋል ማለት ነው?... ለማንኛውም፣ እኔም እሷም እንድንሳቀቅ ምርጫዬ አይደለም:: ስለዚህ ካህኑ አልተሳሳተም:: በዚህ መልኩ ነው ከዚህ ቤት መውጣት ያለብን:: ለዋለችልን ውለታ ምስጋናችንን ማቅረብ ባንችልም ለመልካምነቷ ብዬ ኪሴ ውስጥ ካሉት ሁለት የሃምሳ ብር ኖቶች መሃል አንደኛውን በቀስታ የመደቡ ራስጌ ላይ አኑሬላት፣ ኮቴዬን አጥፍቼ ወጣሁና በሩን በቀስታ ዘጋሁት::

በዚህ ፍጥነት ካህኑ ሸክሙን አህያው ላይ ጭኖ ጠበቀኝና ያለምንም ንግግር ጉዟችንን ቀጠልን::

'ምን እያሰበ ይሆን?... እንዴት ይታዘበኝ ይሆን?' እያልኩ እየተሳቀቅኩ የማለዳዋ ፀሐይ ጮራዋን ከአድማስ ወዲያ ማዶ ሆና እስክትፈነጥቅ ድረስ ተጓዝን::

ከዚያ በላይ ይሄንን የከበደ ዝምታ መታገስ አቃተኝ:: እየተሳቀቅኩ ውስጤን ከማሰቃይ ያበጠው ይፈንዳ አልኩና:-

"መቼም ካንተ የተሰወረ ነገር እንደሌለ አውቃለሁ:: ማታ ተነስተህ የወጣኸውና እስከ እኩለ ለሊት ድረስ ቆይተህ የተመለስከው፣ በእርግጥም የምትሰራው ስራ ኖሮህ ነው? ወይንስ የሆነው ሁሉ እንዲሆን ነው?... ያስተናገደህን ሰው ሳታመሰግን በሌሊት ሹልክ ብለህ መውጣት



አንተ የምታደርገው ዓይነት ነገር አይደለምና ምክንያት ይኖርህ ይሆናል ብዬ አስቤ ነው::" አልኩት:: ዞር ብሎ በዚያ በለመድኩት ፈገግታው ዳሰሰኝና::

"በእርግጥም እዚያ ጎጆ ውስጥ ስለተፈጠረው ጉዳይ ምስጢሩን ብገልፅልህ አልጠላም" አለኝ:: ጉድ ፈላ!... እኔና ሴትዮዋ የፈፀምነው እኮ ዓይን ያወጣ ማመንዘር ነው:: ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱን እንዳፈረስን እያወቀ ይገስፀኛል ብዬ ሳስብ፣ ጭራሽ በጉዳዩ ውስጥ እጁ ያለበትን ያህል ምስጢሩን ልግልፅልህ ይለኛል?... እሱ ራሱ ያቀነባበረው ነገር እንደሆነ እኮ ነው ሳይገረም እየጠቆመኝ ያለው:: ይሄ ሰው ካህን አይደለም በቃ:: 'ካህን ነኝ' ብሎ ይዋሸኛል ብዬ ባላስብም እኔና እሱ 'በካህን' ትርጉም አልተግባባንም ማለት ነው::

"ምሥጢሩን ስትሰማ ይሄን ያህልም አትገረምም:: እየህ ይቺ ሴት ንፁህ ናት:: ለጨዋነቷ ምንም ጥርጥር አይግባህ:: አንተ ከምታውቃቸው ጨዋ ሴቶች ሁሉ የላቀች ጨዋ ናት:: ትናንት የሆነው ነገር ምክንያት ነበረውና የሴትዮዋን ጨዋነት አያጎድለውም:: ትናንት ረፋዱ ላይ ገበያው መሃል ያየናቸውን ሁለት ገበሬዎች አስታውስ:: 'የዘራህበት መሬት እንዴት አላፈራ ይላል?' ሲል የሰማኸው ገበሬ የሴትዮዋ ባል ነው::" አለኝና ዞር ብሎ ተመለከተኝ::

'ወይ ጉድ!... ሊያውም ባለትዳር ከሆነች ሴት ጋር ነው የተኛሁት? ወደዚህ ጎጆ እንደምንመጣ አውቆ እነዚያን ሁለት ገበሬዎች እንዳስተውል አድርጎኛል ማለት እኮ ነው::' ብዬ እያሰላሰልኩ በአግራሞት ተመለከትኩት::

"እነዚህን ሰዎች ታውቃቸዋለህ ማለት ነው?.. የዚህ አካባቢ ነዋሪ ነህ እንዴ?" ብዬ ጠየቅኩት::

"አውቃቸዋለሁ:: ግን በዚህ መልኩ እዚህ አካባቢ መጥቼ አላውቅም::" አለኝ።

"በዚህ መልኩ ስትል?"

"እሱ ምንም አይረባህ:: ጉዳዩን ብቻ ልግለፅልህ:: ያ ገበሬ ሚስቱ ልጅ ስላልወለደችለትእዚያመንደር ወሽሟል::...እንግዲህ ይቺ ጨዋ፣ ደመግቡ እና ባለሙያ ወይዘሮ የሚጎድላት ነገር ኖሮ ሳይሆን ልጅ ስላልወለደችለት ነው ውጪ፣ ውጪ የሚለው:: ሴትዮዋ ግን በየታቦታቱ እየዞረች ልጅ እንዲሰጧት ከመፀለይና ስለት ከመሳል አልቦዘነችም:: ይሄ ደግሞ ልጅ ወልዳ ለመሳም እና የእናትነት ፍቅርን ለመስጠት ከመጓጓቷ የተነሳ ብቻ ሳይሆን፤ የአስራ ሁለት ዓመት ትዳሯ በቋፍ ላይ መሆኑንም ስለተረዳች ነው:: ባሏ ደጅ፣ ደጅ ማለት ከጀመረ መከራረሙን ታውቃለች:: ግን ሁለቱም የማያውቁት ነገር ቢኖር ዘር ማፍራት የማይችሉት ማንኛቸው እንደሆኑ ነው:: ሰውየው የእሷ ችግር እንደሆነ ደምድሟል፤ እርሷም ይሄንን አምና ተቀብላለች:: እነርሱ የማያውቁት ምስጢር ግን ዘር ማፍራት የማይችለው አባ ወራው መሆኑን ነው:: ገበያው መሃል ሲናገር የሰማኸው ነገር የጎበዝ ገበሬ ንግግር አይደለም:: ስለዚህ ሰውየው ሰነፍ ገበሬ ነው ማለት ነው:: 'የዘራህበት መሬት እንዴት አላፈራ ይላል?' ሲል ችግሩ የመሬቱ መሆኑን መግለፁ ነው:: መሬቱ ደግሞ እርሷ ናት::

"ጎበዝ ገበሬ ቢሆን ኖሮ፣ የዘራው ዘር ፍሬ አልሰጥ ሲለው ችግሩ ከመሬቱ አሊያም ከዘራው ዘር ሊሆን እንደሚችል ያስብ ነበር:: ያቺ መልካም ሴት ትናንት በራሷ ፈቃድ መጥታ የተኛችህ ጨዋነቷ እየተናነቃት፣ ከህሊናዋ ጋር ብዙ ታግላ ነው:: 'ልጅ ያለመውለዴ ችግር ድንገት የባሌ ቢሆንስ?' የሚል ድንገተኛ አዲስ ሀሳብ ልቧ ውስጥ ሸው ሲል ነው አንተን ለመተኛት ከራሷ ጋር ትግል የገጠመችው:: ራሷን ማሸነፏ ደግሞ ለፀሎቷ ሁሉ ምላሽ ሰጥቷታል:: ልጅ ትወልድና



ትስማለች፤ በቋፍ ያለው ትዳሯም ይፀናል::" ያለኝ ጊዜ ደነገጥኩኝ::

"እየነገርከኝ ያለኸው ይቺ ሴት ከእኔ እንደምትወልድ ነው እኮ::"

"አዎ:: በሁለታችሁ ዘር ልጅ ይኖራታል::" አለኝ የስሜት ለውጥ ሳይነበብበት::

"ቆይ፣ ቆይ... ሁሉም ነገር የተወሳሰበ ሆነብኝ:: ሲጀመር እኔን እዚህ ጉዳይ ውስጥ ምን የሚያገባኝ ነገር ኖሮ ተሳታፊ ሆንኩኝ? ሁለተኛው ደግሞ፣ እግዚአብሔር ለፀሎቷ ምላሽ ሌላ መንገድ አጥቶ ነው በሀጢያት መንገድ ልጅ የሚሰጣት?... እኛ በፈፀምነው የሀጢያት ድርጊት ውስጥ እግዚአብሔርን ተሳታፊ ማድረግ አይሆንብህም?" አልኩት ሁሉም ነገር ግራ ገብቶኝና ተወሳስቦብኝ::

"የሰው ልጅ በየቀኑ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ተዓምራትን እያስተናገደ ሳለ ባለማስተዋል ብቻ ተዓምራት ከሰማይ እንዲወርዱለት እየጠበቀ ለሺህ ዘመናት አንቀላፍቷል:: እጅህ ላይ ያሉትን ተዓምራት ሳትጠቀምባቸው ሌላ ተዓምር ከሰማይ ለምን መጠበቅ ያስፈልግሃል? 'ለምን እዚህ ጉዳይ ውስጥ ተሳታፊ ሆንኩኝ' ብለሃል:: ተሳታፊ መሆንህ ምን የሚገርም ነገር አለው?.. ይሄ ለምን እንደሆነ እኔ ባልገልፅልህም ኖሮ'ኮ በሁኔታው ላይ ተገኝተህ የሆነውን ሁሉ በራስህ ፈቃድ አድርገኸዋል:: አይደል እንዴ?...

"ደግሞ ለማመንዘሩም ከሆነ ከዚህ በፊት ሺህ ጊዜ አመንዝረሃል:: ዕድላዊትን አላገባሃትም፤ ግን ደግሞ ተኝተሃታል:: ስለዚህ የትናንቱ ማመንዘርህ አዲስ ክስተት ሳይሆን አስቀድሞም በልብህ ውስጥ ያለ ባህሪህ ነው:: እንድታስተውለው የሚገባው ትልቅ ነገር ግን፤ የሌሊቱ ድርጊት ለሴትዮዋ ትልቅና መልካም ውጤት አምጥቷል:: በዚያ መንገድ እየውና ለዚያች መልካም ሴት ወልዶ መሳምና በቋፍ ያለ ትዳሯ መፅናት ላይ አስተዋጽኦ ያደረከ ተዓምር መሆንህን ተቀበል::

" 'ለምን የሴትዮዋ ተዓምር እኔ ሆንኩኝ?' የምትል ከሆነ ደግሞ፤ አንተ

Scanned with CamScanner

ሲቃይህንም ልታከመው
ከዕድላዊት ጋር ባለህ ግንኙነት የምትሲቃየውና ሲቃይህንም ልታከመው
ያልቻልከበት ምክንያት ሌላ ሴት ያለማወቅህ እንጂ ሌላ አለመሆኑን
ለልብህ ስትነግረው ነበር:: በዚህም ሳቢያ ትናንት መንገዱን ጀምረኸዋል::
ስለዚህ መነሻው ያንተ የልብህ ፈቃድ ነው:: ከዚህ በፊት አድርገኸው
የማታውቀውን ነገር ለማድረግ ከልብህ ጋር ስትማከር ነበር::... በዚህ
ፍላጎትህ ሳቢያ ከአዲስ እውቀት ጋር ተዋውቀሃል:: እንግዲህ የአንተ
ተሳታፊነት የመነጨው ነፍስህ አዲስ እውቀትን በመሻቷ ሳቢያ ነው::
"በሴትዮዋ ድንገተኛ ደራሽ ሀሳብና ባንተ ሌላ ገላን የመሻት ፈቃድ
ሳቢያ የሆነው ሆኗል፤ የሚሆነውም ይሆናል:: እግዚአብሔርንም በነፍስህ
ፍላጎት ውስጥ ተጠያቂ አታድርገው:: እሷ መጥታ ጎንህ ከመተኛቷ በፊት
ነፍስህ በምኞት ቀድማ አመንዝራለች:: ነገር ግን ለዚህች ሴት ፀሎት
ምላሽ ለመስጠት ዕድሉን አግኝተሃል:: በሁለተኛ ደረጃ፤ 'እግዚአብሔር
ለፀሎቷ ምላሽ ሌላ መንገድ አጥቶ ነው ወይ በሀጢያት መንገድ ልጅ
የሚሰጣት?' ብለህ ጠይቀኸኛል:: እግዚአብሔር ስራውን የሚሰራበት
ጥልቅ ምስጢራዊ መንገድ አለው:: የሰው ልጅ ፈፅሞ ሊደርስበት
የማይችለው ምስጢራዊ ጥበብ:: ያንተ ጥያቄም ያንን ጥበብ ካለመገንዘብ
የመነጨ ነው:: ሁሉንም ነገር የምታወሳስበው እኮ አንተ ለራስህ በገባህ
መንገድ ብቻ ነገሮችን እየተረጎምክ ስለምትዳኝ ነው:: እስቲ አንድ
ትዕይንት እንፍጠርና ጉዳዩን በቀላሉ ለማስቀመጥ እንሞክር::
"በአንድየጨለማመንገድእየተጓዝክነውእንበል::መንገዱጭርብሏል::
በድንገት ከየት መጡ ሳትል ቀማኞች ጉብ ይሉብህና ደህና አድርገው
ይቀጠቅጡሃል:: ያለህንም ዘርፈው ይሄዳሉ:: አንተ ግን ራቁትህን
እዚያው ጋር ወድቀህ ራስህን እንደሳትክ ሌቱ ይነጋና ሰዎች አግኝተውህ
ህክምና እንድታገኝ ይረዱሃል:: ለመሆኑ ይሄንን ነገር እንዴት ተርጉመህ
ታየዋለህ?.. እንደተረገመ አጋጣሚ? እንደተረገመ ዕለት?... ቀማኞቹንስ



እንደተረገሙ ሰዎች ታያቸዋለህ? ለመሆኑ እነዚያ ቀማኞች እዚያ ሥፍራ
ሳይገጥሙህ መንገድህን ቀጥለህ ቢሆንና ትንሽ እንደተጓዝክ ገድሎ ያለህን
የሚገፍ ቀማኛ እየጠበቀህ ቢሆንስ ኖሮ?... ከፊትህ ምን ሊገጥምህ ይችል
እንደነበር የምታውቀው ነገር አስከሌለ ድረስ ቀማኞቹ ባደረሱብህ ነገር
ማማረርና እንደ መጥፎ ዕድል መቁጠር እንደሌለብህ አሁን ተረዳህ?..."
"እግዚአብሔር ስራውን የሚሰራበት መንገድ እጅጉን ምስጢራዊና
ለመረዳትም ከባድ ነው:: ለዚህም እኮ ነው መጽሐፉ 'ነገር ሁሉ ለበጎ
ነው' እያለ የሚያስተምረው:: ምክንያቱም የደረሰብህ አደጋ እጅጉን
ከከፋው አደጋ ሊጠብቅህ የሆነ እንደሆነ ልታስብ ይገባል ይህን በልብህ
ያዘው::

"ወደተነሳንበት ጉዳይ ስንመለስ ሴትዮዋ ልጅ መውለድ እንድትችል
እግዚአብሔር ሌላ መንገድ አጥቶ አይደለም:: ምክንያታዊ በሆነ መንገድ
የሆነው ሆኗል፤ የሚሆነውም ይሆናል:: እስቲ እንደው ማገኛውም
ሰው ቢሆን የሚለውን ሌላ ተዓምራዊ አማራጭ አንስተን እንይ:: አንተ
ራስህ እንዳሰብከው፣ የሰውየው ዘር ፍሬ እንዲያፈራ ያድርገው እንበል::
በውጤቱ ልክ እንደ አሁኑ ሴትዮዋ ትፀንሳለች፤ ልጅም ትወልዳለች::
እንግዲህ የሁለቱም አማራጮች ውጤት አንድ ሆነ ማለት ነው:: ግን ያንን
ገበሬ አስተውለው:: አስተዋይነት እንደሚያንሰው ቀድም ተነጋግረናል::
ታዲያ በየትኛው ጉብዝናው ነው ይሄን ሽልማት የሚያገኘው? ሚስቱ
ብትወልድለትስ ሌላ ሴት ጋር መሄዱን ያቆማል ብለህ ታስባለህ?... ከሌላ
ሴትም ልጅ ይወልድና ይቺን ፀሎተኛና ጨዋ ሴት ያስለቅሳት ይቀጥላል::
አሁን ግን ይቺ ሚስቱ ልጅ ሰጥታዋለች:: እሱ መሃን ስለሆነ ግን ከሌላ
መውለድ አይችልም:: ስለዚህ ይቺ ልጅ የሰጠችው ሴት ከሌሎች ሴቶች
ሁሉ ትበልጥበታለች:: የኋላ ኋላ ይቺን የልጁን እናት አጥብቆ መንከባከብ
ይቀጥላል:: እሷም በደስታ እግዚአብሔርን እያመሰገነች ትኖራለች::

Scanned with CamScanner

አሁንስ ተረድተኸኛል?"

"ይሄ በሚገባ ገብቶኛል። ግን ያልተረዳኝ አንድ ነገር አለ። የሰራነው ሀጢአትስ? ይሄ ነገር የሆነው እኮ ትዕዛዝ በማፍረስ ነው። ይሄንንስ ምን ትለዋለህ?" ግራ መጋባቴ እንደቀጠለ ነው።

"ታዲያ... እንኳን አውቀህ ለሰራኸው ሀጢአት ቀርቶ ሳታውቅ ለፈፀምከውም እኮ ንስሐ መግባት ይኖርብሃል። ንስሃ ግባ። ይሄን ያህል የተጨነቅከበትን ሰዓት ንስሃ ገብተህ ቢሆን ኖሮ እኮ ይሄን ያህልም አትሳቀቅ ነበር።" አለኝና እያየኝ ሳቅ አለ። ይሄ ሳቁ ነገሩን እንዳድበሰበሰብኝ አስረዳኝ።

"ያቺ ሴት ካንተ የተሻለ ቀልብ አላት። አንተን ከመተኛቷ በፊት 'ፈጣሪዬ ይቅር በለኝ' ስትለው ነበር። አንተን እየተኛች ሳለም ደጋግማ 'እኔ ሀጢያተኛ ነኝ፤ አንተ ግን መሃሪ ነህና ይቅር በለኝ።' ስትል ነበር። ወደ መደቧም ስትወጣ እንቅልፍ እስኪወስዳት ድረስ 'ትዕዛዝህን ጥሻለሁ። አንተ ይቅር ባይ ነህና ይቅር በለኝ።' ስትል ነበር። ዛሬም በማለዳ ከቤተክርስቲያን ደጅ ተደፍታ እያለቀሰች ይቅር በለኝ ማለቷ የማያጠራጥር ነው። አንተም ራስህን አድን። ንስሃ ግባ።" አለኝና ፈገግ አለ። 'እውነቱን ነው። ከማይረባ የቃላት ጋጋታና ምክንያት ድርደራ ይልቅ የሁለት ሰከንድ 'ይቅር በለኝ' ትልቅ ውጤት አለው።' ብዬ አሰብኩና "እውነትህን ነው። ያቺ ሴት ከእኔ የተሻለ ቀልብ አላት። ለሰራ ሁት ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ።" አልኩኝ። መለስ አልኩናም፤

"ግን ይሄን ነገር እንድንወያይበት የፈቀድከው የእግዚአብሔርን ጥበብ እንድረዳ ፈልገህ ነውና ከፈቀድክልኝ አይቀር በአጭሩ የቀጨኸውን ጉዳይ በሚገባ ግለፅልኝ።" አልኩት ያድበሰበሰብኝን ጉዳይ በጥልቀት ለመረዳት ፈልጌ።



"ይበልጥ መረዳት የፈለግከው 'የኃጢአት መንገድ ነው' ስላልከው ጉዳይ ነው አይደል?... እኔ ግን ጉዳዩን አንተው ራስህ እንድትመረምረው ነው የምመክርህ። እኔ ከምነግርህ ነገር ይልቅ አንተው የምትደርስበት ምስጢር ትልቅ እውቀት አለው። መነሻ ነጥብ ግን ልስጥህ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ አብርሃም፣ ሣራና አጋር የተፃፈውን ታሪክ አስታውስ። ሳራ ለአብርሃም ልጅ ስላልወለደችለት ከአገልጋይዋ ከአጋር ጋር እንዲተኛ አድርጋዋለች። የንጉሥ ዳዊትን፣ የልጁን የንጉሥ ሰለሞንና የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት ማከዳ ታሪክንም አስተውለው። የእግዚአብሔር ህግ ደግሞ ለየትኛውም ሰው፣ ለየትኛውም ወገንና ባህል አያዳላም። ያንን ታሪክ ተንትነውና ማግኘት የሚገባህን እውቀት አንተው ድረስበት።" ብሎኝ ውይይቱን ቋጨው።

እንግዲህ ቀሪው እውቀት የእኔ የቤት ስራ ሆኗል። ተግቼ አብሰለስለዋለሁ። እውነትም ግን እግዚአብሔር ስራውን የሚሰራው ምሥጢራዊ በሆነና እኛ ልንረዳው በማንችለው መንገድ ነው።

እንግዲህ እኔም ለመጀመሪያ ጊዜ የዕድላዊት ያልሆነን ገላ አቀፍኩ፤ ያቺ ሴትም ፀነሰች። ያ ገበሬም እግሩን ሊሰበስብ ሆነ። ማን ያውቃል? ማታ በተፈጠረው ነገር ሰበብ ብቻ ሌሎች የማልረዳቸው እልፍ አዕላፍ ነገሮች ተፈጥረው ሊሆን ይችላል። አሊያም ነገ ከነገ በስቲያ ብዙ የማልረዳቸው ነገሮችም ሊፈጠሩ ይችሉ ይሆናል። የሚወለደውም ልጅ ንጉሥ ወይም ካህን፣ ወታደር አሊያም ባቅኔ ይሆን ይሆናል።

እኛ አንረዳውም እንጂ ዓለም ሁሉ እንዲህ የተጠላለፈች ናት ማለት እኮ ነው። እኛ የምናየው የፊት ለፊታችንን ብቻ ነው። ዛሬ መንገድ ላይ አይተን፣ አሊያም ሳናስተውለው በትከሻ ገጭተን ያለፍነው ሰው ነ በሕይወታችን ውስጥ ትልቁን ቦታ ይዞ ሊገኝ ይችል ይሆናል። ምናልባት

Scanned with CamScanner

ዛሬ አንድ ካፍቴሪያ ውስጥ ቁጭ ብዬ ማኪያቶ የጠጣሁበትን ብርጭቆ ከደቂቃዎች በፊት የነገ ፍቅረኛዬ የምትሆነው ቆንጆ ማኪያቶ ጠጥታበት ይሆናል:: ምናልባትም... ብዙ ሚሊዮን ምናልባታዊ ትዕይንቶች ይኖራሉ:: ማን ያውቃል?...

ምናልባትም ዕድላዊት ወደ እኔ ሕይወት የገባችው፣ ዛሬ ለማደርገው ጉዞ እንድዘጋጅ ልታደርገኝ ይሆናል:: እያንዳንዱ ያደረገችኝ ነገር ሁሉ እኔን በዚህ እውቀት ለማብሰል የተማገደ ማገዶ ይሆን ይሆናል::... እንዲያውም በትኩረት ስመረምረው 'ይሆን ይሆናል' ከማለት ይልቅ 'ነው' ማለቱ ይቀለኛል::

'የማፈቅርሽ ዕድላዊት ሆይ!.. ይቅርታ ከማድረግም አልፌ አንቺን የማመሰግንበት ቀን ደረሰ መሰለኝ::... እንኳንም አቀረብሽኝ፣ እንኳንም ገፋሽኝ፣ እንኳንም የገለባን ያህል አቀለልሽኝ፣ እንኳንም በሌላ ለወጥሽኝ፣ እንኳንም ተሰቃየሁ፣ እንኳንም... እንኳንም...' ለብዙ ሺህ እንኳንሞች ምስጋና የማቀርብበት ዕለት ደረሰ መሰለኝ:: ይሄን ካህን ያገኘሁትና ከእነዚህ ምስጢራዊ ጥበባት ጋር ፊት ለፊት የተጋፈጥኩት በእነርሱ ምክንያት ነውና- እግዚአብሔር ይመስገን::



## - 6 -

"የሰው ልጅ እምነት እርግጠኝነት ይጎድለዋል::"

ያደርኩት አዳር አዳር አይበለው:: በጭንቅ የተሞላ ሌሊት:: በእንግድነት ተቀብለው ያሳደሩን በበሽታ ከፉኛ የምትሰቃይ እናት እና በስቃይዋ የሚሰቃዩ ሦስት ልጆቿ ናቸው:: ከበራፋቸው ደርሰን "የመሸብን እንግዶች ነን አሳድሩን::" ስንላቸው ትልቁ ልጁ "ቤት የእግዚአብሔር ነውና በእንግድነት ብንቀበላችሁ ደስተኞች ነን፤ ነገር ግን በበሽታ ከፉኛ የምትሰቃይ እናት አለችን:: በዚሁ ሳቢያ እሷም እኛም እንቅልፍ አጥተን እናድራለን:: በዚህ ሁኔታ ማደር ከፈቀዳችሁ ግቡ::" አለን::

እኛም "የታመመን እግዜር ይማር::" ብለን ገባን:: የተቀባያችን ሁለት ታናናሽ እህቶችም እናታቸውን ከበው ተቀምጠዋል::

ከእናትየው ራስጌ ግድግዳ ላይ የማርያምና የመላዕክት ምስሎች ተንጠልጥለዋል:: በየሐኪሙና በየፀበሉ እናታቸውን ይዘው ቢንከራተቱም በሽታዋ ከመዳን ይልቅ እየበረታ መሄዱን ልጆቿ እየተቀባበሉ አስረዱን:: እናትየው አልፎ፣ አልፎ ጥቂት ቃላት ከመስንዘር ውጪ ድምጿ የሚሰማው ስታቃስት ብቻ ነው:: እንደምንም ነጋና በማለዳ ከቤት ወጥተን አንድ ጋራ ላይ ቁጭ አልንና ተፈጥሮን መቃኘት ጀመርን:: በመሃል "ለዚህች ምስኪን ሴት ምንም ማድረግ አትችልም?" ብዬ ጠየቅኩት::

ዞሮ ተመለከተኝና "የሆነ ነገር ማድረግ ይቻላል ብለህ እንዴት አሰብክ?" ብሎ ጠየቀኝ::.

"ላንተ የሚሳንህ ነገር የለም ብዬ ማሰብ ከጀመርኩ ቆይቻለሁ::"

"ላንተ የሚሳንህ ነገር የለም ብዬ ማሰብ ከጀመርኩ ቆይቻለሁ::"

"ለእኔ የሚሳነኝ ነገር እንደሌለ በእርግጠኝነት ካመንክ፤ እንግዲያውስ ላንተም የሚሳንህ ነገር የለም:: ታዲያ ለምን አንተ የሆነ ነገር አታደርግላትም?"

ይሄ ሰው እስካሁን ሲቀልድ አላየሁትም:: አሁን ግን የማያስቅ ቀልድ ቀልዷል:: ዓይኔን ከዓይኑ ሳልነቅል በትኩረት ተመለከትኩት:: የእሱም ዓይኖች እኔው ላይ እንደተተከሉ ቀሩ:: ፊቱ ላይ ምር እንጂ ቀልድ አይነበብም::

"እኔ እንኳን ይሄንን፣ ተራ የተባለውንም ነገር ማድረግ እንደማልችል ሁለታችንም እናውቃለን::"

"ሁለታችንም እናውቃለን?... እኔ በበኩሌ አላውቅም:: አንተ 'ምንም ማድረግ አልችልም' ብለህ ካመንክ ግን፤ እኔም ማድረግ እንደምችል ጥርጣሬው አለህ ማለት ነው::"

"ባንተ ላይ ቅንጣት ጥርጣሬ የለኝም::" አልኩት ቃላቱን ረገጥ አድርጌ::

"እንግዲያውስ የጎደለህን ነገር በመንገር ልርዳህ:: በማታውቀኝ በእኔ ላይ የጣልከውን የተረጋገጠ እምነት በራስህ ላይ መጣል ብቻ ነው የሚያስፈልግህ:: እኔን ያለ ቅንጣት ጥርጣሬ ያመነው ልብህ ያለው አንተ ጋር ነው:: የዚህን ያህል ባንተ እንዲያምን አድርገውና እርዳት::"

"ይሄን ማድረግ አልችልም:: እያንዳንዱ ድርጊትህ እኔን አንድ ነገር ለማስተማር ካልሆነ በቀር ለዋዛ፣ ፈዛዛ እንዳልሆነ አውቃለሁ። ግን... እዚያ ቤት ውስጥ ምስኪኗ ሴትና ልጆቿ እንዲያ እየተሰቃዩ የእነርሱን የስቃይ ዕድሜ በማራዘም እውቀት ከምሸምት ይልቅ ወደ ነበርኩበት ሕይወት መመለሱን እመርጣለሁ::"



አልኩት ጠበቅ አድርጌ:: ለእኔ የቁጣ ንግግር ያገኘሁት የእርሱን ፈገግታ ብቻ ነው::

"... አባክህን አሁኑኑ ወደ ቤት እንመለስና አንድ ነገር አድርግላት::" እንባ እያነቀኝ ተማፀንኩት::

"አንድ የማትለውጠውን ነገር ልንገርህ:: የእናትየው የስቃይ ዕድሜ መርዘም ወይም ማጠሩ በአንተ እጅ ላይ ወድቋል:: ይሄንን የምትሞግተኝ ከሆነ የምታተርፈው የስቃዩዋን ዕድሜ ማርዘም ብቻ ይሆናል::"

"ግን እኮ ይቺ ሴት በፈጣሪዋ ላይ ትልቅ እምነት አላት:: ለዓመታት በየፀበሉ ስትንከራተት ኖራ ምንም መፍትሔ አላገኘችም:: እንዴት ይሄንን ምንም በማላውቀው በእኔ ላይ ትጥለዋለህ?"

"በፈጣሪዋ ላይ ያላት እምነት ትልቅ መሆኑን ነግረኸኛል:: እኔም ተሳስተሃል አልልህም:: ግን... ስለ ሰው ልጅ እምነት አንድ ነገር ልንገርህ:: የሰው ልጅ እምነት እርግጠኝነት ይጎድለዋል::

"የፀሎትህን ምላሽ ከማታይባቸው ምክንያቶች ዋነኛው መሆን በመቻሉ ላይ ጥርጣሬ ስላለህ ነው:: ፍፁም የሆነ ኃይል እለ ካልክና በእሱም ካመንክ፤ ፍፁም ከሆነው አምላክ ዘንድ የሚመነጨው ደግሞ ፍፁም የሆነ ነገር ብቻ ነው:: ሕይወት፣ ፍቅር፣ ጤና፣ ብርሃን፣ እውነት፣ ውበት እና ሌሎችም መልካም የሆኑ የፍፅምና መገለጫዎች ናቸው ከእርሱ የሚፈልቁት:: እግዚአብሔር ደግሞ እነህን ሁሉ ለሰው ልጅ ሰጥቷል::

" 'እውነት እላችኋለሁ፣ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም::' ብሎ እየሱስ ያስተማረን ወዳልጎደለው ፍፅምና፣ በዓለማዊ ህግጋትና ልማዶች ወዳልተበረዘው ፍፅምና እንድንመለስ ሲያሳስበን ነው:: ያ ፍፅምና ደግሞ ስንወለድ ለእያንዳንዳችን ተሰጥቶናል:: ከውልደታችን ጀምሮ በህፃንነት ዘመናችን ነፍሳችን ከመልካምነት ውጪ ሌላ እውቀት የላትም ነበር:: ፍፅምና

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

የውልደት መብታችን ሆኖ ተሰጥቶን ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ባለው ዘመናችን ከዓለም የሰበሰብነው ከፋት የነፍሳችንን መልካምነት እያጎደለው ተዳበለን፡፡ በዕድሜ በላቅንም ቁጥር ፍፅምናችን አሻራውን እንኳ ሳይተው ከነፍሳችን ውስጥ ደብዛው ጠፋ፡፡ ለዚህም ነው ተመልሳችሁ እንደ ህፃናት ሁኑ ያለን፡፡ ወደ ነፍሳችን ጠልቀን፣ ቁልቁል ነፍስን፣ ወዳልጎደለው መልካምነት፣ ወደ ስረ-መሰረታችን እንድንመለስ የነገረን፡፡

“እንዲህ ሆኖ እንጂ እኛ አዋቂዎች ታይተን ‘እግዚአብሔር የሰው ልጅን በአምሳሉ አድርጎ ፈጠረው፡፡’ ቢባል ምኑ ይታመናል? እኛ ነን በዕድሜ ስንጎላ ከተፈጠርንበት አምሳል ፍፁም ርቀን፣ አንዲትም ተዓምር መስራት የማንችል ደካማ ፍጡራን የሆንነው፡፡ አየህ?.. .እኒያ፣ ፍፁም ከሆነው አምላክ የሚመነጩት መልካም ስጦታዎች ጎድለው፣ ተቃራኒዎቻቸው ሞት፣ ጥላቻ፣ በሽታ፣ ጨለማ፣ ሀሰት እና ሌሎቹም የሚከሰቱት፣ እኛ ከዚያ ፍፅምና ስንጎድል ወይንም ያንን ፍፅምና ስናጎድል ነው፡፡

“እነዚያ የፈጣሪ ስጦታዎች ሁሉ ግን አሁንም ቢሆንም በሰው ልጅ ነፍስ ጥልቀት ውስጥ ታስረው ተቀምጠዋል፡፡ በተቃራኒዎቻቸው ተጋርደው ይገኛሉ፡፡ እንደ ህፃናት በመሆን ነፃ ልናወጣቸው፣ የጋረዳቸውን ገፈን ልንገልጣቸው ይገባል፡፡ እምነታችን እንደ ህፃን ልጅ እምነት ይሁንና ይሄ ብቻውን የሚሰራውን ተዓምር እያየን እንደነቅ፣ እንፈወስ፡፡ እየሱስ ስለፈወሳቸው ሁለቱ ዓይነ ስውራንና ስለ ሌላኛዋ ሴት አንብበህ የለ?.... ዓይነ ስውራኑ ‘የዳዊት ልጅ ሆይ ማረን’ ብለው ተከተሉት፡፡ እየሱስም ‘ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን?’ አላቸው፡፡’አዎን ጌታ ሆይ’ አሉት፡፡ በዚያን ጊዜ ‘እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ’ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ፡፡ ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ፡፡

ሴቷም እንዲሁ፡፡ ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት ከኋላው ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፡፡ በልቧ ‘ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ



እንደሆነ፣ እድናለሁ’ ትል ነበርና፡፡ እየሱስም ዘወር ብሎ አያትና “ልጄ ሆይ አይዞሽ እምነትሽ አድኖሻል” አላት፡፡ ሴቲቱም ከዚያች ሰዓት ጀምራ ዳነች፡፡

እነዚህ ሁለት ተዓምራት የሰው ልጅ ሊመረምረውና ሊረዳው የሚገባን ጥልቅ ምሥጢር ይዘዋል፡፡ እየሱስ ያላቸው ‘እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ፡፡’ እና ‘እምነትሽ አድኖሻል፡፡’ ነው፡፡ ያዳናቸው ከጥልቁ ልቦናቸው የመነጨው እምነታቸው መሆኑን ልብ አድርግ፡፡ ይሄንን ተዓምር ያደረገውና ተዓምሩንም በእነዚህ ቃላት ያተመው፣ ከእርሱም ዘመን በኋላ የሚኖረው የአዳም ልጅ ሁሉ የዚህ ተዓምር አንባቢ ብቻ ሳይሆን ተቋዳሽም እንዲሆን ጭምር ብሎ ነው፡፡ ፈውሱ ያለው በእያንዳንዳችን ጥልቅ እምነት ውስጥ ነው፡፡ ይሄ ነው ምስጢሩ፡፡

ለነገሩ ‘የሰናፍጭን ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ይሄን ተራራ ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል’ ብሎስ አስተምሮ የለ፡፡ አየህ!... የሰው ልጅ ራሱ የእግዚአብሔር ትልቅ ተዓምር ነው፡፡ ምን አድርጎ እንደፈጠረው ተመልከት፡፡ በቅንጣት ታህል እምነቱ ተራራን ወደ ባህር እንዲወረውር፤ በቅንጣት እምነቱ ዓይነ ሥውሩ እንዲበራ፤ በቅንጣት ታህል እምነቱ ከዓመታት ደዌው እንዲፈወስ፤ በቅንጣት እምነቱ ብዙ ተዓምራትን እንዲሰራ አድርጎ ፈጠረው፡፡

“የሰው ልጅ ግን ሁል ጊዜ ‘አምጣ ፣ አምጣ ፣ አምጣ ’ እያለ ወደ ሰማይ ይመለከታል፡፡ ሰማይ ተከፍቶ ተዓምር እንዲዘንብ ይጠብቃል፡፡ እግዚአብሔር እኮ ሁሉንም ነገር አስቀድሞ ሰጥቶናል፤ ተዓምር ልንሰራ የምንችልበትን ረቂቁን ልቦናችንን ጨምሮ፡፡ የዚህ ሁሉ ቁም ነገር ማሰሪያው ግን ‘እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ’ እና ‘እምነትሽ አድኖሻል’ የሚለው መልዕክት ነው፡፡ ይሄን በሚገባ በልብህ ፃፈው፡፡ የዛሬው መሣሪያህም ይሄው ነው፡፡ ይቺ እኔ አንድ ነገር እንድፈጥርላት

Scanned with CamScanner

የተማፀንኩኝ ሴትም የቱንም ያህል ሃይማኖተኛ እና ለህግ ተገዢ ትሁን እንጂ፤ እምነቷ ከልማድ ቁርኝት አልፎ ከነፍሷ አልተዋሃደም፤ በጥልቁ ልቦናዋ ላይ አልነገሰም::

"ይቺን ሴት እግዚአብሔር ላይ እምነት እንዳላትና በፌዋሽነቱም ታምን እንደሆን ብትጠይቃት፣ ያለምንም ማመንታት 'አዎ' ትልሃለች:: 'እርግጠኛ ነሽ ወይ?' ብትላትም እርግጠኛ በሆነ ድምፅ ታረጋግጥልሃለች:: አንተም በእሷ ቦታ ላይ ብትሆን እርግጠኝነቷ ይሰማሃል:: መፈተሽ ያለበት ይሄ እርግጠኝነት ነው:: ለባለቤቱ የተረጋገጠ እርግጠኝነት ይምሰለው እንጂ ከአዕምሮውና አልፎ ከጥልቅ ልቦናው አሊያም ከነፍሱ አልሰረፀ ይሆናል::

"ከልጅነት እስከ አውቀት በቀሰምነው የሃይማኖት ትምህርት፣ በአስተዳደግ፣ በባህልና በሌሎችም ምክንያቶች ህግ አክባሪ የሃይማኖት ሰዎች ልንሆን እንችላለን:: አዕምሯችንንም ለዚሁ እናስገዛለን:: የእምነት እርግጠኝነታችንም የመነጨው ከዚሁ ከቅርቡ ሕሊናችን ነው:: ከእሱ የራቀውን ሥፍራ ግን አናውቀውም:: ስለማናቀውም የፍፅምና መስኮት የሆነውን እውነተኛ ምስክር ለጥያቄ አናቀርበውም:: ስለዚህ የአዕምሯችንን 'እርግጠኛ ነኝ' የሚል መልስ ይዘን እንቆማለን:: ታዲያ የዚህን ያህል የተረጋገጠ ፅኑ እምነት ካለን እንደምን 'የሰናፍጭ ቅንጣት' ታህል እምነት ያለው ሰው ይሰራዋል የተባለውን ተዓምር ያህል እንኳ መስራት አቃተን?... ከዚህ ተነስተህ ስታስበው ይሄ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት' የተባለው፣ አዕምሯችን ከነገረን 'እርግጠኛ ግዙፍ እምነት' የላቀ እና የራቀ ሆኖ አይታይህም?...

"ይሄ፣ በሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ተራራን ነቅሎ ወደ ባህር የሚወረውር ኃይል የሚመነጨው ከእዘቦቱ ሕሊናችን በላይ ከሆነው ከጥልቁና ረቂቁ ልቦናችን መሆኑስ ተገለፀልህ? ስለዚህ የሰው ልጅ



በየዕለቱ እልፍ አዕላፍ ተዓምራትን ይሰራ ዘንድ እምነቱ ነፍሱ ውስጥ ጠልቆ መግባት አለበት:: የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እንኳ ባታህልለት አለኝና ረጅም ማብራሪያውን ደምድሞ ሩቅ መመልከት ጀመረ:: በዝምታ ያለኝን ሳውጠነጥን ቆየሁና፤

"ፈፅሞ ያላስተዋልኩትና ያልጠየቅኩት ነገር ነው:: ግን… የሴትዮዋ ጉዳይስ?"

"እሱንማ ጨረስን እኮ:: ላንተ ትቼዋለሁ:: ያላትን ታውቃለህ፤ የጎደላትን ደግሞ አሁን አውቀሃል:: የጎደላትን ከሞላህላት ባላት ላይ ተጨምሮ ተዓምር እናያለን:: ይሄም ተዓምር በአጥቢያው ሁሉ ይነገራል:: የብዙ ሰዎችንም እምነት ይበልጥ ያጠነክራል:: በል እንግዲህ ዛሬን እዚሁ ቤት ውለን እናድራለን:: ነገ ግን ጉዟችንን እንቀጥላለን:: ይሄም ልናጥፈው የማንችለው ነው:: ስለዚህ ይህቺን ሴት ከበሽታዋ የሚፈውስ ተዓምር ይዘህ ወደ ቤት እንድትመለስ:: አሁን ለብቻህ ትቼህ መሄዴ ነው::" ብሎኝ ብድግ አለ::

በድንጋጤ አብሬው ተነሳሁ:: ዓይኖቹ ውስጥ ያየሁት እንደ ብረት የጠነከረ አስተያየት ግን ለሌላ ድንጋጤ ጋበዘኝና ተመልሼ ቁጭ አልኩኝ:: ያየሁት ቁጣ አይደለም:: ታዲያ ምንድነው?... እኔ እንጃ! እፌ ተሳሰረብኝ:: እብዶ ካልሆነ በቀር እንዴት እንዲህ ያደርጋል?... ፈገግ እየተመለከትኩት ትቶኝ ሄደ:: አዞረኝ:: ዙሪያዬ በሙሉ በደብዛዛው ነው የሚታየኝ:: ከጋራው ላይ ተንከባልዬ እንዳልወድቅ ፈራሁና በእጆቼ መዳፎች መሬት የነከሱ ድንጋዮችን ግጥም አድርጌ ያዝኩ::

በዚህ ሁኔታ ለምን ያህል ደቂቃዎች አሊያም ለምን ያህል ሰዓት እንደተቀመጥኩ አላውቅም:: ብቻ ብዙ ቆይቻለሁ:: ራሴን መግዛት ስጀምር በረጅሙ እየተነፈስኩ ለመረጋጋት ሞከርኩ::

Scanned with CamScanner

በመጀመሪያ አንድ ሀቅ መቀበል ነበረብኝ:: ካህኑ አይቀልድም ፈፅሞ:: አንድ መንገድ ከሌለ በቀር 'ደመና ዝገን' ብሎ አያዘኝም:: ይሄን ደጋግሜ ለራሴ በመንገር ተቀበልኩት:: ከዚያም ጨዋታችንን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው በተደጋጋሚ ከለስኩት:: ጆምበር ማዘቅዘቅ እስክትጀምር ድረስ አብላላሁት::

ጆምበር ከአድማሱ ወዲያ ማዘቅዘቅ ስትጀምር፤ በነፍሴ አድማስ ላይ ግን ብርሃኗን ወለደች:: ደነገጥኩ:: እያሰብኩ ያለሁት ነገር ከሀሳብ ልቆ፣ ምስል ሆኖ ሁሉ ይታየኝ ጀመር:: የልቤ ምት ጋራውን የሚንድ መስሎ ተሰማኝ::

"አገኘሁት፤ ምስጢሩን አገኘሁት" ብዬ ሳይታወቀኝ በጣም ጮህኩኝ::

ከመቅፀበት ተነሳሁና እየተንደረደርኩ ጋራውን ወረድኩት:: ብቻ... ሮጬ ይሁን ከንፍ አውጥቼ አላውቅም ከጎጆዋ ደረስኩ:: በሩን በርግጄ እየተንደረደርኩ ሴትየዋ የተጋደመችበት ስር ተንበረከኩ:: ፊቴ በደስታ እንዳበራ ትንፋሼ እየተቆራረጠ፤

"ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን::" አልኩ ጮክ ብዬ:: በሽተኛዋ እናት ፊቷን ወደኔ መለሰች:: ቀኝ እጇን በሁለት እጆቼ ያዝኩና "ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይሁን:: ተፈውሰሻል፣ ተፈውሰሻል:: አሁን... እዚያ ጋራው ላይ ቁጭ ብዬ ጆምበር ስታዘቀዝቅ እመለከት ነበር:: ድንገት ፊት ለፊቴ ትልቅ ብርሃን ተፈጠረና አንዲት በብርሃን የተሞላች ሴት አየር ላይ እየተንሳፈፈች ወደኔ ቀረበች:: የማየውን ባለማመን በድንጋጤ ደርቄ ቀረሁ:: ሴትዮዋ ወደኔ ቀርባ 'አይዞህ አትፍራ:: የመጣሁት በእንግድነት ወዳሳደረችህ ልጄ ልልከህ ነው:: ፀሎትሽ ተሰምቷል:: ከበሽታሽ ተፈውሰሻል:: ዝከሬን ከአልጋ ወርደሽ ታወጫለሽ:: እኔም ዛሬ ሌሊት በህልም እናግርሻለሁ:: ሁሌም ከጎንሽ አለሁ ብለህ ንገራት':: አለችኝና ተመልሳ ወደ ሰማይ አረገች:: ያኔ..



እኔም ባነንኩኝ:: በሁኔታው ተደንቄ ይሄንን ተዓምር ላበስርሽ ስከንፍ መጣሁ:: እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን:: ተፈውሰሻል::" አልኩ በመደነቅ ተሞልቼ እየጮህኩ::

የሴትዮዋ ፊት እየበራ እየፈካ ሄዶ ፀሐይ መሰለ:: እናም በድንገት ከህልሙ እንደባነነ ሰው ሆነችና "እልልልልል..." እያለች ከወገቧ ቀና ብላ ቁጭ አለች:: ሦስቱ ልጆቿም በዕልልታ ዘለሉ:: መጥተውም ተጠመጠሙባት:: ዕልልታው ተደጋገመ:: ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ ሄጄ ቆምኩኝ::

"የታለህ?... የታለህ አንተ የማርያም መልዕክተኛ?" ከልጆቿ እቅፍ ስር እየወጣች እጆቿን ዘርግታ ወደእኔ ተወረወረች:: አቀፈችኝ:: አቅፋኝ ተንሰቅስቃ አለቀሰች:: ቆማ መራመዷ ተዓምር የሆነባቸው ልጆቿ ከእልልታቸው አላባሩም::

ሴትዮዋ ከእቅፌ ወጣችና "እልልልልል..." እያለች ወደ ቤቱ ማዕዘን ሄደች:: በዓይኔ ተከተልኳት:: ተንበርከካ የካህኑን ጉልበት ሳመች::

በስሜት ከመዋጤ የተነሳ የካህኑን ቤት ውስጥ መኖር አላስተዋልኩትም ነበር:: በሁለት እጆቹ ከንዷን ይዞ ብድግ አደረጋት:: ተያየን:: ፈገግታው ከእግር እስከ ፀጉሬ ድረስ ደስታን አለበሰኝ:: የሴትዮዋ ጎረቤቶች በሰሙት ጩኸት ተደናግጠው ግር ብለው ገቡ:: በደስታ ሰክራ ቤቱን የምትዞረውን ሴት ሲያዩ ሁሉም ተደነቁ:: "ዕልል" አሉ::

ከቤቱ ቀስ ብዬ ወጣሁና ከነፋሻማው አየር ተነፈስኩ:: በትልቁ ከመፈገግ ውጭ ደስታዬን የምገልፅበት ሌላ መንገድ አጣሁ:: የሆነውን ሁሉ ቆሜ አወጣሁ አወረድኩ:: እዚህ መደምደሚያ ላይ ያደረሱኝን ነገሮች በህሊናዬ ከለስኳቸው::

ዙሪያዋን የከበቧት የማርያምና የመላዕክት ምስሎች፣ እንዲሁም

Scanned with CamScanner

ሴትዮዋ ከስቃይዋ መሃል ደጋግማ 'ቅድስት ድንግል ማርያም ምነው እንዲህ ተውሽኝ?' እያለች በደከመ ድምፅ የምታሰማው አቤቱታ ውስጧ የተዳፈነውን ኃይል የምቆሰቁስበትን ጥበብ ጅራቱን ያስጨበጡኝ ከስተቶች ነበሩ፡፡ በዚህም ላይ ልጆቿ ሲያጫውቱን፣ በየወሩ የማርያም ዕለት ዝከሯን ሳታስተጓጉል የምታደርግ ሴት ናት፡፡ እንዲህ የአልጋ ቁራኛ ሆና ሳለ እንኳ ለነገው የማርያም ዕለት ዝክር ተጨንቃ ልጆቿን ስታስጠነቅቅ ነበር፡፡ በዚህ ድህነቷ ተበድራም ቢሆን በወሩ ማርያምን መዘከሯ፣ በማርያም ላይ ያላትን የእምነት ፅናት ያሳያልና ይሄን ፅናቷን ይበልጥ ላበረታላት እንደሚገባ ወሰንኩ፡፡

ካህኑ ኮቴውን ሳያሰማ ቆሜ ሰማይ ሰማይ ከማይበት ሥፍራ ደረሰና ጎኔ ቆመ፡፡

"ዛሬ ህልም ባታይስ?" አለኝ ፈገግ ብሎ፡፡

"ህልም እንደምታይ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ እምነቷ እስካዳናት ድረስ እምነቷ ህልም እንደሚያሳያት አልጠራጠርም፡፡ የነገርኳትን እሷም እንድታይና ምስሉ ዕድሜ ልኳን ከአዕምሮዋ ታትሞ እንዲቀር ብዬ ነው፡፡" ብዬ መለስኩለት፡፡



# ክፍል ሁለት
## የዕጣ ፈለግ

### - 8 -

አሁን ፀሐይ ትኩስ ብርሃኗን ወልዳለች፡፡ ከተማዋም ነቅታለች፡፡ ትናንት ግን እዚሁ ቦታ ሆኜ ጀምበሯን አዘቅዝቃ ሳያት ነበር፡፡ በማላውቀው ከተማ ውስጥ አሁን የተደገፍኩትን የድንጋይ ግድግዳ ተደግፌ ቆሜ ወደ ቤቱም፣ ወደ ምሽት ጉዳዩም የሚተራመሰውን ህዝብ ስማትር ነበር፡፡ ካህኑ እንደሁ ተሰናብቶኝ ወደማላውቀው ሥፍራና ጉዳዩ ሄዷል፡፡

የጀምበሯ ማዘቅዘቅ ስለ ማደሪያዬ እንዳስብ አደረገኝ፡፡ እንደ ገጠር፣ መዝጊያ አንኳኩቼ 'የመሸብኝ እንግዳ ነኝ አሳድሩኝ' ብዬ እንዳልጠይቅ ያለሁት ከተማ ውስጥ ነው፡፡ የሆቴል አልጋ ይገኝ እንዳልተኛ ኪሴ ባዶ ነው፡፡ ለማንኛውም የት እንደማድር ያለማወቄ ያን ያህል ሊያሳስበኝ አይገባም ብዬም ሳስብ ነበር፣ ትናትና ማታ፡፡

ስለ ማደሪያዬ ማሰብ ሳቆም ደግሞ ሆዴ 'ተርቤያለሁ' እያለ ይወተውተኝ ገባ፡፡ ረፋዱ ላይ ካህኑ ከያዘው ኮሮጆ ውስጥ የቀረንን ቁራሽ ደረቅ እምባሻ ከውሃ ጋር ተቋድሰናል፡፡ እና 'ምግብ አምጣ' እያለ ሆዴ መጮህ ጀምሯል፡፡ ምግብ ልሰጠው ካልቻልኩ ሆዴን ልረሳው ይገባል፡፡ ከረሳሁት እሱም ረሃቡን እንደሚረሳ እርግጠኛ ነበርኩኝና ስለሌላ ነገር ለማሰብ ወደ ነፍሴ ታዛ ቁልቁል ጋለብኩኝ፡፡

'ለመሆኑ ወዴት እየሄድክ እንደሆነ ታውቃለህ? የት ለመድረስና ምን

ለማግኘት ነው እየተጓዝክ ያለኸው?... የምትሄድበትን ሳታውቅ እንዴት ያለህበትንትለቃለህ?'እነዚህጥያቄዎችከእኔምሆነከሁሉምየአዳምልጆች መልስየሚሹናቸው፡፡እኔወዴትእየሄድኩእንደሆነአውቃለሁ፡፡ይሄንስል የቦታን ስም ወይም አቅጣጫን መጠቆሜ አይደለም፡፡ ወደ የትኛውም ሥፍራ፣ ወደየትኛውም አቅጣጫ ተጉዤ ቢሆን ኖሮ የማገኘው አሁን ያገኘሁትን ነውና እየሄድኩ ያለሁት ወደ ጥበብ፣ ወደ ፍቅር፣ ወደ ሰላም ሀገር ነው ብዬ ነው የምመልሰው፡፡

ስቃይ ተሸንፎ ደስታና ፍቅር ወደነገበት የጥበብ ሀገር ነው እየሄድኩ ያለሁት፡፡ በመጓዜ የማገኘውም ጥበብን፣ ፍቅርንና ሰላምን ነው፡፡ እነዚህ ሦስት የነፍስ ጌጦች ደግሞ ከነፍሳችን ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘን፣ በይቅርታ ጎዳና ላይ በየትኛውም አቅጣጫ አድርገን ወደ የትኛውም ሥፍራ ብንጓዝ የምናገኛቸው ሽልማቶቻችን ናቸው፡፡ እናም የምሄድበትን ስላወቅኩ ስንቄን፣ ማቄን ሳልል እንኳንም የነበርኩበትን ለቅቄ ጠፋሁ፡፡

ትናንት ረፋድ ላይ ከካህኑ ጋር እየተጓዝን ሳለን "ለመሆኑ ይሄ አህያ የጫነው ሸክም ምንድነው?" ብዬ ጠየቅኩት፡፡

"ወርቅ ነው፡፡" ብሎ መለሰልኝ- እንደዘበት፡፡ ደነገጥኩኝ፡፡ በአህያ የተጫነ ጆንያ ሙሉ ወርቅ እንዴት አያስደነግጥ?

"መቼም አንተ ይሄን ያህል ሀብት አያስፈልግህም፡፡ የማን ንብረት ቢሆን ነው?" ለአምስት ቀናት ያህል ይሄን ስፍር ቁጥር የሌለው ሀብት በአህያ ጭነን እየተጓዝን ነው ብዬ ላስብ ቀርቶ፣ ሌባ ቢያገኘው ንቆ የሚተወው ተራ ጓዝ የያዝን ነበር የመሰለኝ፡፡

"ከእኔ ሀብት ጋር ሲወዳደርማ ይሄ ብናኝ ነው፡፡ ከምትገምተው በላይ የገዘፈ ሀብት አለኝ፡፡ይሄ ንብረት ግን የአንድ መልካም ሰው የአደራ ንብረት ነው፡፡ ያ ሰውም ይሄን ለማግኘት መንገድ ላይ ይገኛል፡፡ ይሄን ከማግኘቱ በፊት ግን ፈታኝ ጉዞዎች ከፊቱ ይጠብቁታል፡፡



በመጀመሪያ ወርቁ የሌላ ሰው ነበር፡፡ አሁን ግን የዚህ ሰው ሊሆን ነው ጉዞውን በድል ካጠናቀቀ፡፡

የመጀመሪያው ባለዕድል ግን መልስ የሚሻ እንቆቅልሽ አለው፡፡ በወርቁ ፈንታየሚፈልገውሌላነገርአለ፡፡...ለማንኛውምይሄሸክምከእኔእጅወጥቶ በሌሎችሰዎችዕጣፈንታውስጥተሳትፎውንየሚጀምርበትጊዜደርሷል፡፡" አለኝና፤

"የሚጠብቁህ ሰዎች አሉ፡፡ በል ጉዞህን ቀጥል!" ብሎ አህያውን አዘዘው፡፡አህያው ሲሄድ የነበረበትን አቅጣጫ ለውጦ ከእኛ በስተቀኝ ያለውን አቅጣጫ ይዞ ተጓዘ፡፡ ካህኑ ዞር ብሎም አህያውን ሳያይ በጀመርነው አቅጣጫ መንገዱን ቀጠለ፡፡ እኔ ግን ለአፍታ ቆሜ አህያው የጫነውን ሲሳይ ተመለከትኩና ፈጠን፣ ፈጠን ብዬ ተራምጄ ካህኑ ላይ ደረስኩበት፡፡

ከሰዓታት ጉዞ በኋላ አሁን ያለሁበት ከተማ ገባንና ለቀናት ከረሳሁት ግርግርና ረብሻ ጋር ተገናኘን፡፡ የመጀመሪያው የተጨበጠ ትዕይንቴ አንዲት መንገድ ዳር ድንጋይ ላይ ተቀምጣ የምታለቅስ ሴት ነበረች፡፡ የተቀደደ ነጠላ ለብሳ፣ አንገቷን ጉልበቷ ላይ ደፍታ ስቅስቅ ብላ ታለቅሳለች፡፡

ድምጿ አንጀት ይበላል፡፡ ካህኑ አላስተዋላትም ማለት ባልችልም ምንም ሳይመስለው አልፏት ሄደ፡፡ እኔ ግን ፍፁም ላልፋት አልቻልኩም፡፡ ቀረብኳትና እጄን ትከሻዋ ላይ አድርጌ "ምን ሆነሽ ነው የምታለቅሺው?" ብዬ ጠየቅኳት፡፡ ካቀረቀረችበት ቀና ብላ ተመለከተችኝና "እዩ! ስንቱን ተናግሬ ልጨርስ?" አለችኝ በሚያሳዝን የእንጉርጉሮ ዜማ፡፡

"ምንድነው የገጠመሽ?"

"ልጄ ታማ ነው፡፡ ሕፃን ልጄ፣ የድህነት ልጄ፡፡ ጤና ጣቢያ ወስጄት

ነበር:: ያዘዙላትን ኪኒን ግን በምን አቅሜ ልግዛው?" ዕምባዋ ማቆሚያ አልነበረውም::

"... አርባ ሁለት ብር ነው አሉኝ:: ልጄ! አሁንስ እግዜሩም ዓይን አጣ መሰለኝ::

አለችና በድጋሚ በነጠላዋ ተናፈጠች::

"በቃሽ ይሄን ያህልም አትማረሪ:: ይሄን ያገርና ለልጅሽ መድሃኒቱን ግገርላት:: ታዲያ ስለአወሳሰዱ በሚገባ እንዲያስረዱሽ ጠይቂ::" ብዬ የቀረኝን ድፍን ሃምሣ ብር ልሰጣት እጄን ዘረጋሁ::

ሴትዮዋ ባለማመንና በገረሜታ ቀና ብላ ተመለከተችኝና ዓይኗን ከዓይኔ ሳትነቅል እጇን ዘርግታ ብሩን ተቀበለችኝ:: እጇ በጣም ይንቀጠቀጥ ነበር::

"አይዞሽ እግዜር አለ:: ልጅሽ ቶሎ ይሻላታል:: በይ ተነሽ!" ብዬ ከንዷን ይዤ አስነሳኋት:: እጄን ግጥም አድርጋ ይዛ ደጋግማ በምስጋና ሳመችው:: ትኩስ እንባዋ እጄን አራሰው::

"ልጄ፣ እግዚአብሔር ፈጥኖ ይድረስልህ:: ያላሰብከው እንጀራ ይግጠምህ:: ወይ አምላኬ! ለካ ቅርብ ነው ያለኸው?" አለችና ወደ ሰማይ ተመለከተች::

"አይዞሽ በቃ:: አሁን ሂጂና መድኃኒቱን ግገር::"

"እሺ፣ እሺ የኔ ጌታ:: እግዚአብሔር የልብህን ሁሉ ይሙላልህ:: ዕድሜህን ያርዝምልህ:: ደህና ሁን:: ደህና ሁን፣ የኔ ልጅ::" መርቃኝ የምትጠግብ አልመሰላትም:: በእኔ ገፋፊነት እየሮጠች ሄደች::

በሐዘኔታ አንገቴን እየነቀነቅኩ ቆሜ አስተዋልኳትና መንገዴን ቀጠልኩ:: ካህኑ ጎን እንደደረስኩ:-

"እንግዲህ ለጥቂት ጊዜ ልለይህ ነው:: እንዴትና የት ላገኝህ እንደምችል



አውቃለሁና ያጣኛል ብለህ አትጨነቅ::" ብሎ አረዳኝ:: ያላሰብኩት ነገር ነበርና ከው አልኩኝ:: ለመረጋጋት ግን ጊዜ አልፈጀብኝም:: ፊቱን አጤንኩት፤ የተረጋጋ ገፅታው እንዳለ ነው::

"ወዴት ለመሄድ አስበህ ነው?" አልኩት::

በፈገግታ ተመለከተኝና "ስለ እኔ ይህን ልጨምርልህ:: ወደ ብዙ ስፍራዎች ስጓዝም፤ ከነበርኩበትም አለሁ:: የዘመናትን ምእራፍ ብገልጥም ልጅነቴ ግንባሬ ላይ ነው:: መሮጤና መዳኼም አብሮ ተበጅቷል:: ሽምግልናዬ ከጉርምስናዬ ጋር አብሮ ተገምዷል:: ትናንትናዬ ውስጥ ነገዩ አለ:: መሄዴ ውስጥም አለመሄዴም አለና 'እዚያ ነኝ' አልልህም:: የትም ሁን፣ መቼም ይሁን ላገኝህ ስፈልግ አገኝሃለሁ:: ስትፈልገኝም ታገኘኛለህ:: በነፍስህ ውስጥ የጀመርከውን መንገድ ቀጥል:: እስካሁን የደረስከበትን ቁም ነገር ይበልጥ የምታፀናበት ጊዜ አሁን ነው:: በል ደህና ከረም፣ ወዳጄ::" አለኝ::

ፍርሃት፣ ፍርሃት ሲለኝ ታወቀኝ:: "ሂድ! የምን ፍርሃት ነው?!" ብዬ የፍርሃቴን እናት በኩርኩም ነደልኩት::

"እሺ ደህና ከረም::" ስለው ሳይጨብጠኝም፣ ፊቱንም ሳይመልስ መንገዱንቀጥሏል:: የማላውቀው ሀገር ላይ ፀሐይዋ ልትጠልቅ ስታዘቀዝቅ ተሰነባብተን ተለያየን:: ደግሞም እኮ፣ ልክ የመጨረሻ ገንዘቤን ለሴትዮዋ ሰጥቼ ያለሽራፊ ሳንቲም ስቀር ጠብቆ ነው መሄዱ ነው ያለኝ::

በጥቂት ቀናት ቆይታችን ውስጥ ያፈራሁትን ሲፈትሽ እንደሆን አላጣሁትም:: እናም ወደ ከተማው መሃል ይበልጥ ሰርጌ ገባሁና ሀሳቤን ለማሰባሰብ የግንቡን ግድግዳ ተደግፌ ቆምኩኝ:: መቆሙም ታከተኝና መሬት ላይ ቁጭ አልኩኝ::

በተቀመጥኩበት አሻግሬ አካባቢው ላይ የሚገኙትን የንግድ ሱቆችና

Scanned with CamScanner

ቡና ቤቶች ማስተዋል ቀጠልኩ:: አንዳንዶቹ ሱቆች የምሽቱን መምጣት ምክንያት በማድረግ እየዘጉ ነው:: በሁለት ቡና ቤቶች የበር መስታወት ብልጭ ድርግም የሚል ህብር የቀለማት ብርሃን እስከስታ ሲወርድ ይታያል:: ለእነዚያ ቡና ቤቶች ቀኑ ገና መወለዱ ነው:: ለእኔ ግን መሽቷል:: እንቅልፌም ከመጣ እዚሁ ጋር ጥቅልል ብዬ እተኛለሁ:: እስካመንኩበት ድረስ የትም ልሁን የት መጪው ሌሊት እኩል ያልፋል:: መጪውንም ንጋት እኩል እቀበለዋለሁ:: ታዲያ ከባዱ ነገር የቱ ጋር ነው? ብዬም ነበር:: እውነትም ይኸው ሌሊቱ ለሁላችንም እኩል ነጋና ያንን የምሽት ግርግር በማለዳ ብርሃንም ለማየት በቃሁኝ::

'ይሄንን የህዝብና የከንውን እንቅስቃሴ ቁጭ ብዬ ለመታዘብ ሳይሆን፣ የዚህ እንቅስቃሴ አንድ አካል ለመሆን ነው እዚህ የደረስኩት:: እናም ተነስቼ ከዚህ የከንውን ጅረት ጋር በአንድ መፍሰስ አለብኝ::' ብዬ አሰብኩና ከተቀመጥኩበት ተነስቼ የከተማው እምብርት ነው ብዬ ወዳሰብኩት አቅጣጫ መንገድ ቀጠልኩኝ::

የተጓዝኩት የንግድ ቤቶች ይበልጥ ወደሚበዙበት መንገድ ነበር:: ሆዴ የተርቢያለሁ መልዕክቱን ትናንት ማምሻውን ካቆመበት ቀጠለ:: እንግዲህ የሆድን ረሃብ ለማስታገስ ያለው አማራጭ ሁለት ነው:: ቢቻል ማንኛውንም ፈጣን ስራ ሰርቶ ለጥሪው በፍጥነት መድረስ፤ ይሄ ካልሆነም እርቦኛል ብሎ ከአንዱ ምግብ ቤት ትርፍራፊ መለመን ነው መፍትሔው:: በተረፈ መጨነቅ እርባና የለውም::

ድንገት ዓይኖቼ አንድ አጭር ራሰ በረሃ ሰው ላይ አረፉ:: ከአንድ ሱቅ በር ላይ ቆሟል:: እግሩ ስር በማዳበሪያ ቀረጢት የተቋጠረ ሸክም ተጋድሟል:: በዓይኖቹ ግራና ቀኙን ሲቃኝ የሚሸከምለት ሰው ፈልጎ እንደሆነ አሰብኩኝና ተጠጋሁት::

"ጋሽዬ፣ የሚሸከም ፈልገው ነው?" አልኩት በትህትና:: ከአነጋገሬ ነው



መሰል ሸቅብ ተመለከተኝና፤

"እዎ፣ ትሸከማለህ?" ብሎ ጠየቀኝ:: ከዚህ በፊት ክብደት ያለው ነገር ተሸከሜ ባላውቅም፣ ሸክሙ እንደማይከብደኝ ራሴን አሳመንኩትና፤

"እዎ::" አልኩት::

"በል፣ እዚያ መኪና ላይ ወስደህ ጫንልኝ::" ብሎ ጎዳናውን ተሻግሮ የቆመ መኪና አሳየኝ:: ሸክሙን ብቻዬን ለማንሳት ስንደፋደፍ በትኩረት አየኝና ከአንድ በኩል እግዛ አሸከመኝ:: "የአምላክ ያለህ!" አልኩኝ ለራሴ ብቻ በሚሰማ ድምፅ:: 'ይሄማ ዝሆን ነው፤ ግን ደግሞ መድረሻው ቅርብ ነው::' ብዬ ተፅናናሁ::

ሸክሙ እያንደረደረ ጎዳናውን አሻገረኝና መኪናው ጋር ደረስኩ:: የሚከብደውን ሸክም የዕቃ መጫኛው ላይ ለማስቀመጥ ግራ ትከሻዬን ሳዘነብል 'ዝሆኑ' ከላዬ ላይ ተወርውሮ መኪናው ላይ ከፉኛ ዘጭ አለ::

"አንተ!... ምናባቱ ይሄ!... የአባትህ ንብረት መሰለህ የምታሸቀነጥረው?" አለኝና ተንጠራርቶ በጥፊ አጮለኝ:: የወገቤ ህመም ላይ የጥፊው ህመም ሲጨመርበት ባለማመንና በድንጋጤ ዓይኖቼ ፈጠጡ:: የሰውየው ዓይኖች ግን በንዴት ይበልጥ ፈጠዋል::

በዕድሜዬ ሙሉ በጥፊ የተመታሁበትን ቀን አላስታውስም:: የውርደት ስሜት በመላ ሰውነቴ ሲሰራጭ ተሰማኝ:: ከንፈሬ ተንቀጠቀጠ፣ ጉልበቴ ተብረከረከ:: ፊቱን ሳይሆን ሙልጭልጭ መላጣውን ቁልቁል አጉኜው በቆመበት ልቀብረው አማረኝ:: ድንጋጤዬ ግን ባለሁበት የጨው አምድ አርጎ አስቀርቶኝ ነበር:: ሰውየው ፊቱን እንዳጨማደደው ወደ ሹፌር በር እየሄደ፣ ኪሱ ገብቶ ሳንቲም አወጣና ፊቴ ላይ ወረወረብኝ:: ሳንቲሟ ግንባሬን ቀውራ መሬት ላይ 'ቂው' ብላ ወደቀች::

የሳንቲሟ ዱላ ከደነዘዝኩበት አነቃኝና ልጣላው አሰቤ አንድ እርምጃ ብቻ እንደተንቀሳቀስኩ መልሼ ቆምኩኝ:: በትኩረት እያየሁት መኪናው

Scanned with CamScanner

ውስጥ ጉብቶ ሞተሩን አስነሳ። አንባ አነቀኝ፡፡ አንባ ስላነቀኝ ደግሞ በራሴ ተናደድኩ፡፡

'ለመሆኑ የትኛው ከብሬ ተነካ ብዬ ነው እንዲህ የበገንኩት?' ብዬ ራሴን ጠየቅኩ፡፡ እሱ መኪናውን አስነስቶ ሄደ፤ እኔ ግን ባለሁበት አለሁ፡፡

'ልስራ ባልኩ ጥፊ መቅመሴ እንዴት ውርደት ይሆናል?... ማፈር ያለበት እሱ ነው፡፡ የውርደት ስሜት ሊሰማው የሚገባው እርሱ ነው፡፡ ሰዎች ያገለገሉበትን የጉልበት ዋጋ በቅጡ እንኳ የማይሰጥ ውርደታም እሱ ነው፡፡' እያልኩ ስብሰለሰል የሆዴ ረሃብ በቁንጥጫ መዘለገኝና ሳንቲሟ ታወሰችኝ፡፡ ሀሳቤን ትቼ ወደ ሳንቲሟ ስዞር አንድ ድሪቶ የለበሱ ለማኝ የሚመስሉ ሰውዬ አንስተዋት በፈገግታ ተሞልተው መንገዳቸውን ሲቀጥሉ ተመለከትኩ፡፡

እንዴት ብዬ የእኔ ገንዘብ ነው ልበላቸው? ያገኟት መሬት ወድቃ፤ በዚያ ላይ ሽማግሌ ለማኝ፡፡ ሳንቲሜን ማንሳት ትቼ ከብር፣ ውርደት፣ ምናምን ስል ያጠፋሁት እኔ፡፡ ተስፋ ቆርጬ መንገድ ስቀጥል አንድ ሰው በትኩረት ሲመለከተኝ አየሁ፡፡

"ና እስቲ፡፡" ብሎ ጠራኝ፡፡ በእርግጠኝነት የሆነውን ሁሉ አይቷል፡፡ ተጠጋሁት፡፡

"ና እርዳኝ፡፡" አለና አጠገቡ ያለ ሱቅ ገባ፡፡ ተከተልኩት፡፡ በካርቶን የታሸጉ ዕቃዎች ተደርድረዋል፡፡ አንዱን አንስቶ አቀበለኝና ሌላ አንድ ለራሱ ይዞ ቀድሞኝ ወጣ፡፡ ተከተልኩት፡፡ ከውጭ የቆመች መኪና ላይ ጭነን ተመለሰን፡፡ ሁለታችንም ከሃያ የማያንሱ የካርቶን እሽጎችን መኪና ላይ ጭነን ስናበቃ፤

"ና አብረኸኝ ሂድ፡፡ እዚያ ስንደርስ ደግሞ በማውረድ ትረዳኛለህ፡፡" ብሎ የመኪናውን ቁልፍ ከኪሱ አወጣ፡፡

"ደስ ይለኝ ነበር፡፡ አሁን ግን እርቦኛል፡፡" አልኩት፡፡ የቅድሟ ሳንቲም



ትምህርት ሰጥታኛለች፡፡ የመጀመሪያ ቁም ነገሬ ማድረግ የነበረብኝ እሷን ነበር፡፡ ምክንያቱም ከከብሬ ይልቅ ለረሃቤ እሷ ትደርስልኝ ነበርና፡፡ አሁን የሰራሁበት ገንዘብም ለአሁኑ ረሃቤ ሊደርስልኝ ሲችል፣ ሸቀጡን ካራገፍን በኋላ አንድ ላይ ይከፍለኛል ብዬ ስለምን የረሃቤን ዕድሜ ላራዝም?

ሰውየው ለአፍታ አጤነኝና "ና ቁርስ ልጋብዝህ፡፡" ብሎ ቅርብ ወደሚገኝ ካፍቴሪያ አስከትሎኝ ገባ፡፡

በሕይወቴ እንዲህ የሚጣፍጥ ምግብ በልቼ የማውቅ አይመስለኝም፡፡ ከካፍቴሪያው በጥጋብና በፈገግታ ወጣሁና ከሰውየው ጎን ተቀምጬ ወደ ማራገፊያው አቀናን፡፡

በደቂቃዎች ጉዞ የሰውየው ሱቅ ደረስንና ሸቀጡን አራግፈን አበቃን፡፡ የሰውየው ሱቅ በተለያዩ ሸቀጦች የተሞላና የሚያምር ነው፡፡ የሱቁን ዙሪያ በዓይኖቼ ሰማትር ተመልከቶ፤

"ይቅርታ ትቸኩላለህ እንዴ?" አለኝ፡፡

"አይ፣ የሚያስቸኩል ምንም ጉዳይ የለኝም፡፡" ብዬ መለስኩለት፡፡ አሥር ብር አውጥቶ ሰጠኝና "ቅድም ትዕግሥትህን በጣም አድንቄልሃለሁ፡፡ ለምንድነው በጥፊ የመታህ?" አለኝ፡፡ "የተሸከምኩት ዕቃ ከባድ ስለነበር መኪናው ላይ ስጭነው ከቁጥጥሬ ውጪ በኃይል ወደቀብኝ፡፡ በዚያ ተናዶ ነው፡፡" ብዬ መለስኩለት በፈገግታ፡፡

"ባለጌ ነው፡፡ ታግሰህ ባታልፈውና ተናደህ ብትመታው ኖሮ የሚዋረደው እሱ ነበር፡፡ ለማንኛውም እንኳን ታግሰህ አሳለፍከው፡፡ የልብ ድካሙ ተነስቶበት ሰበብ ይሆንብህ ነበር፡፡"

"ታውቀዋለህ?"

"እዚህ ሀገር እሱን የማያውቅ ማንም የለም፡፡ ስግብግብ ሀብታም ነጋዴ ነው፡፡ አንተ የዚህ ሀገር ሰው አይደለህም ማለት ነው?"

"እኔ እንኳ እዚህ ሀገር የመጣሁት ትናንት ማምሻው አካባቢ ነው::" ብዬ ዝም አልኩ:: ሰውየው ግን እንድቀጥለት እየጠበቀ ነው::

"ሀገሩንም ሰውንም አላውቅም:: ከነበርኩበት ስነሳም እዚህ እንደምደርስ አላውቅም ነበር:: እግር የጣለኝ የሀገራችሁ እንግዳ ነኝ እንግዲህ::" አልኩት በፈገግታ::

"ሽከም ስራህ ያለመሆኑን ቅድምም ጠርጥሬያለሁ:: ከየት ነው የመጣኸው?"

"ከአዲስ አበባ::"

"ለምን ጉዳይ ብለህ?"

"አዲስ አበባን ለጥቂት ጊዜ መልቀቅ ስለፈለግኩ ነው:: በዙሪያዬ ካሉት ነገሮች ሁሉ አፈንግጬ፣ ከራሴ ጋር ብቻ በመሆን፣ አዲስ ልምድ ለማካበትና የሚጎድለኝን ነገር ለመሙላት መጓዝ ነበረብኝ:: ይኸው ጉዞዬ እዚህ አድርሶኛል::"

"ገንዘብም ጓዝም ሳትይዝ ነው ለጉዞ የተነሳኸው?!" የሰውየው ጥያቄዎች ከማዘን እንጂ ከመጥፎ ስሜት የተሰነዘሩ ስላልነበሩ ነው በአጭሩ ልመልስለት የሞከርኩት:: ግን ምን ብዬ እያንዳንዱን ነገር ልነግረው እችላለሁ?

"የተነሳሁት ሳላስበው በአጋጣሚ ነው:: ይሄንኑ ልብስ እንደለበስኩና ኪሴ ውስጥ መቶ ብር ይዤ:: አንድ ቦታ ላይ በድንገት ከአንድ ካህን ጋር ተገናኘን:: ትናንት ሊመሻሽ ሲል እዚህ ደረስን:: ካህኑ ሌላ የሚሄድበት ሥፍራ ነበረው:: እሱም ሄደ፤ እኔም እዚሁ ቀረሁ:: የነበረኝን መቶ ብር ደግሞ መንገድ ላይ እያለሁ ጨርሼዋለሁ:: ትናንትም ያደርኩት አንዱ ግምብ ጥግ ነው:: ካንተም ጋር ያገናኘኝ የሆዴ ረሃብ ነው:: ይሄው ነው እንግዲህ ታሪኩ በአጭሩ::"



"እና አሁን ወደ አዲስ አበባ መመለስ ትፈልጋለህ?" ከድምፁ ለሰዎች እርዳታ በማድረግ የሚረካ ሰው መሆኑን ተረዳሁ::

"ለጊዜው የመመለስ ሀሳብ የለኝም:: እንደዚህ ዓይነቱን እንግዳ ኑሮ ተጋፍጬ የጎደለኝን እውቀት ለመሙላት ነው ሀሳቤ::" ብዬ መለስኩለት::

"በጣም ትገርማለህ::" አለኝና ፈገገ:: "እና አሁን ምን ለማድረግ አስበሃል?"

"እንጃ!... ዕቅድ ማውጣት የሚያስፈልገኝ አይመስለኝም:: ሁሉንም ነገር እንደ አመጣጡ ለመቀበል ነው ያሰብኩት::"

Scanned with CamScanner

## - 9 -

"የአንድ ዕቃ ወይም ጉዳይ ዋጋ የሚለካው፣ በዕቃው ወይም በጉዳዩ ዓይነት ሳይሆን፣ ዕቃው ወይም ጉዳዩ ባረፈበት ሰው ማንነት ነው"

'እሺ! ... ዛሬ ምን ላይ ደረስክ?... ትናንት ላይመለስ አልፏል ወይንስ ጊዜ የሚባል ነገር ከእነአካቴው የለም?... መምሸትና መንጋት ይፈራረቁ እንጂ ያው ቀን ይሆን እየደጋገመ የሚመጣው?'... በእርግጥ የትናንቱን ዓይነት ሕይወት ዛሬም ከደገምነው፣ ነገም ከሰለስነው፤ በትናንት፣ በዛሬና በነገ መካከል ምንም ልዩነት የለም ማለት እንችላለን:: ትናንት የኖርነውን ሕይወት፣ ዛሬ ከለወጥነውና፤ የዛሬውንም ነገ ካልደገምነው እያንዳንዱ ዕለት ውስጡ በቋጠረው የክንውን ዓይነት የተለያየ መልክ ይኖረዋልና ልዩነት አላቸው ማለት የምንችል ይመስለኛል::

ትናንት ላይመለስ ይለፍም እየደጋገመ ይምጣም፣ መቅበር ወይም መለወጥ ያለብን ቀኑን ሳይሆን ውስጡ ያጨቅነውን አሰልቺና ተደጋጋሚ ኑሮ ነው:: ዕድላዊትና ድርጊቶቿ ደግሞ የዚያ ኑሮ ራሶች ናቸውና መቀበርም መለወጥም አለባቸው::

ማንኛውም ሰው ወደ ስኬቱ ወይም ወደ ደስታና እርካታው ለመጓዝ ሦስት እርምጃዎች በቂ ናቸው እላለሁ:: የመጀመሪያው እርምጃ 'ለራስ ታማኝ መሆን' ነው:: 'ዛሬ ባለኝ ሕይወት ደስተኛ ነኝ ወይ?'.... መጀመሪያ መመለስ ያለበት ይሄ ጥያቄ ነው:: ራስን ሳያታልሉ ይሄንን ጥያቄ መመለስ



ያስፈልጋል:: መልሱ 'ደስተኛ አይደለሁም' የሚል ከሆነ ሁለተኛውን እርምጃ መራመድ ነው::

ሁለተኛው እርምጃ፣ ደስተኛ ያልሆንባቸውን የሕይወታችን ክፍሎችን ነቅሎ ማውጣት ነው:: ችግሮቻችንን ለይተን ማወቅ:: አሁን እንግዲህ በሕይወታችን ውስጥ ለስቃይና ለሐዘን የዳረጉንን ጉዳዮች ለይተን አስቀምጠናቸዋል:: ወደ ደስታችን ለመንደርደር እነዚህን የደስታችን ቀበኛ የሆኑ ጉዳዮችን መለወጥ እንዳለብን ማመን ይገባናል::

ሦስተኛው ደረጃ፣ ተግባራዊነት ነው:: ያለፉት ሁለት ርምጃዎች ቀላል ሲሆኑ የተግባራዊነት ርምጃ ግን ከባድና ውሳኔ ሰጪነትን መጎናፀፍ የሚሻ ነው:: ብዙዎቻችን እዚህ ደረጃ ላይ ስንደርስ ነው ሁሉን ነገር እርግፍ አድርገን የምንተወው:: ምክንያት ቢባል፣ ፍራቻ:: የነበረውን ለመተውና አዲስ ነገርን ለመጋፈጥ ድፍረት ማጣት:: ፍራቻው የተፀነሰው በእኛው ውስጥ እስከሆነ ድረስ፣ እኛ ደግሞ ፈሪዎች ተብለን መጠራት ይገባናል:: ይሄንን ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ እስከፈራን ድረስ ፈሪ እንጂ ጀግና፣ ደፋር ወይም ልበ ሙሉ መባል አይገባንም:: ይሄን ዓይነት ፍርሃቱን መግደል ያልቻለ ሰው እንደምን ልበ ሙሉ ነኝ ሊል ይችላል?

እንግዲህ 'ዛሬ ምን ላይ ደረስክ?' ለሚለው ጥያቄ ያለኝ መልስ፣ ሁለቱን ርምጃዎቼን ጨርሼ ሦስተኛው የተግባራዊነት ርምጃ ላይ ደርሻለሁ::

በስቃይና በሐዘን ውስጥ እየኖርኩ እንደሆነ አኛለሁ:: የስቃይና የሐዘኔን መንስኤም አውቄ ለውጥ እንደሚያስፈልገኝ ተረድቻለሁ፤ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ግን ጀምሬያለሁ እንጂ ተዘፍቄበታለሁ ማለትን አልደፍርም:: ወደ ተነሳሁበት ሥፍራ ተመልሼ ጉዳዮቼን በተገቢው መልኩ ሳደራጅ ነው እውነተኛ የተግባር ሰው መሆኔን የምመሰክር::

ምናልባትም ግን ወደ ተነሳሁበት ሥፍራ ከእነአካቴውም መመለስ ላያሻኝም ይሆናል:: እዚህ እሊያም ሌላ ቦታ ኑሮዬን ከመሰረትኩና

Scanned with CamScanner

ስቃዬን ገድዬ ደስታዬን ከወለድኩት፣ ይሄም እኮ የገዘፈ ርምጃና ትልቅ ውሳኔ ነው:: ስለዚህ ለተግባራዊ ርምጃ ሥፍራ መምረጥ የለብኝም- ዛሬ ላይ በቆምኩበት ሥፍራ ሆኜ ሁሉንም ነገር መወሰንና ርምጃ መውሰድ እችላለሁና::

እናም በመጀመሪያ ደረጃ እዚህ በመቆየት አዲሱን ሕይወት በመጋፈጥና ሕይወትን በመመርመር እተጋለሁ:: ዕድላዊትም ደህና ሁኚ- በሰላም ላሰናብትሽ ይገባልና:: ከዚህ በኋላ እንደ ከዚህ በፊቱ አንቺን ወደ ሕይወቴ ለመመለስ በመጣር ሳይሆን፤ ለድርጊቶችሽ ሁሉ ይቅርታ በማድረግ ላይ እተጋለሁ:: እስከማመሰግንሽ ድረስ ይሄን በማድረግ እተጋለሁ:: እዚሁ ባለሁበት ሆኜ ያዳፈንኩትን የነፍሴን ጥሪ ለመተግበር ቀን ከሌት እተጋለሁ:: የነፍሴን ዜማ ከነፍሴ ቅኔ ጋር እያዋሃድኩ የነፍሴን ጥበብ ለአጥናፍ አደርሰዋለሁ:: የራሴን ውብ የነፍስ ከተማ በመገንባት ላይ እተጋለሁ::

ደስታ በሳቅ መንፈስ ውስጥ ሆኖ ያለ ከንፍ የሚከንፍበትን፣ እርካታ እንደታላቅ ማዕበል አካልን የሚያናውጥበትን፣ ውብ የነፍስ ከተማዬን ራሴው ለራሴው በመገንባት ላይ እበረታለሁ::

ይቺ የነፍስ ከተማ ምን መምሰል እንደሚገባት በአዕምሮዬ ውስጥ ሳልኳት፣ በልቤ ውስጥ ቀረፅኳት፤ ከውስጧ የሚመነጨው ሙቀት እስኪያግለኝ ድረስ፣ መዓዛዋ በእርካታ እስኪያሰክረኝም ድረስ በደም ስሮቼ አመላለስኳት:: ደጋግሜ ሳያትና ሳሰማምራት ልክ ገንብቼ እንደጨረስኳት ሁሉ በእርካታ አጥለቀለቀችኝ:: ከየት እንደመጣ የማላውቀው የእርግጠኝነት እምቅ ስሜት በቅርቡ እውን እንደማደርጋት ደጋግሞ ሹክ አለኝ:: አመንኩት:: ያሰብኩበት እደርሳለሁ:: ያለምኩትን እኖራለሁ፣ የኔ የሆነውን ሁሉ እወርሳለሁ:: በቅርቡ በመንበሬ ላይ



እቀመጣለሁ፣ እነግሳለሁ:: በቅርቡ ራሴን፣ በራሴ ሙሉ ቁጥጥር ስር አውዬ አሳድረዋለሁ::

'በቅርቡ' የሚለው አገላለፅ ያልተወሰነ ጊዜን የሚገልፅ ነው:: 'በቅርቡ' ማለቴ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ የማደርገው ተግባራዊ የለውጥ እንቅስቃሴ የሚያመጣው ውጤት ተደማምሮ፤ የሚታይና የሚጨበጥ ግዙፍ ውጤት ላይ የሚደርስበትን ጊዜ ለመጠቆም ነው::

እያንዳንዱ ከንውን የራሱን ውጤት ፈጥሮ፣ እያንዳንዱ ውጤት ተደራርቦና ተንሰላስሎ የሚታይና የሚዳሰስ ግዙፍ ውጤት እንዲሆን አሁን ያለን መነሳሳትና በራስ መተማመን የመጀመሪያው ወሳኝ መሣሪያ ነው::

እናም ሁሉንም ነገር እንደ አመጣጡ ለመቀበል መወሰን ብቻ ሳይሆን በመቀበሉም ገፋሁበት:: ከዚህ ጥበበኛ ኮብላይ ካህን ጋር በአንገናኛለን ከተሰነባበትን ድፍን አንድ ወር ሆኖናል:: ጠዋት ከእንቅልፌ ስነቃ ራሴን እንደማገኘው ሁሉ እሱም ይደቀንብኛል:: ቀኑን ሙሉም ከልቤ እየመነጨ በደሜ ላይ እየተንሳፈፈ፣ በየደም ስሮቼ ሲመላለስ ይውላል፣ ያድራል:: ሁሌም ከእኔ ጋር እንደሆነ ነው የሚሰማኝ:: ይሄ ደግሞ እጅጉን አበርትቶኛል:: በዓላማዬ እንድፀና ረድቶኛል::

እዚህ ከተማ ስገባ የመጀመሪያውን ቁርስ ያበላኝ ነጋዴ አማን ይባላል:: እንደ ስሙ ሰላም የሆነ ሰው ነው:: ሊዲያ የምትባል ውብና ፀመለ ሸጋ ሚስት አለችው:: አማን ሱቁ ውስጥ እንድሰራ ቀጥሮኛል:: በሂሳብና በሽያጭ እየረዳሁት እገኛለሁ:: ቀኑን ሙሉ ከእርሱ ጋር ስሰራ ውዬ አዳሬም በእርሱ ቤት ነው:: አማንና ሊዲያ ከዋናው መኖሪያ ቤታቸው ጀርባ የሚገኝ አንድ የሰርቪስ ክፍል ሰጥተውኛል:: እናም በነፃነትና ምንም ረብሻ ሳይገጥመኝ ለመፃፍ ስለሚመቸኝ አንድ ረጅም ልብ ወለድ ታሪክ መፃፍ ጀምሬያለሁ::

Scanned with CamScanner

ቁርስ፣ ምሣና ራቴን የሚያበሱኝም እነርሱ ናቸው:: ለሚያስፈልጉኝ ሌሎች ነገሮችም ከጎኔ ናቸው:: በዚህም ላይ በወር ሦስት መቶ ብር ደሞዝ አለኝ::

ባልና ሚስቱ ስለኔ የሚያውቁት እውቀትን የመፈለግ፣ ጥበብን የመመርመርና የመፃፍ አባዜ እንዳለብኝ እንጂ ሌላው ሌላው ታሪኬን አልነገርኳቸውምና አያውቁም::

ዕለቱ እሁድ ነው:: ሊዲያ ከእናቷ ጋር የሩቅ ዘመድ ለቅሶ ለመድረስ ስለሄደች ቤት የለችም:: እኔና አማን በአንድ ገበታ ተቀምጠን ምሳችንን እየበላን ነው::"ይገርምሃል፣ አንድ ትልቅ ውለታ የዋልኩለት ሰው ትናንት ደውሎ፣ 'እንዴት ያለ ቆንጆ ስጦታ እምጥቼልሃለሁ መሰለህ' አለኝ:: ከሩቅ ሀገር ትናንት ገና መመለሱ ነበር:: እናም፣ ዛሬ ቤት ድረስ ይዞልኝ እንደሚመጣ ነግሮኝ ተለያየን:: ያመጣልኝ ስጦታ ምን እንደሆነ ባይነግረኝም፣ ድምፁ ውስጥ የሰማሁት እርካታ፣ ልክ የሰውን ውለታ ስትመልስ የሚሰማህ ዓይነት እርካታ ነው:: እናም፣ ዛሬ ጠዋት በመኪናው ጭኖ አመጣልኝ:: ምን ቢሆን ጥሩ ነው?..." ቀና ብሎ ተመለከተኝና፤

"አንድ ጆንያ ከሰል! አይደንቅም?" ብሎኝ ፈገገ::

አማን ከእኔ የመደነቅ መልስ ጠብቆ የነበረ ቢሆንም፣ ንግግሩ አንድ የዘነጋሁትን ነገር እንዳስታውስ ስላደረገኝ ሀሳቤን ወደዚያ ጉዳይ ሰደድኩት:: የነገሩ መገጣጠም አጅጉን ደንቆኝ ራሴን በገረሜታ ነቀነቅኩት::

"እኔ ከሰል አልቸገረኝም:: ምን ይሆን ያመጣልኝ እያልኩ ስብሰለሰል ቆይቼ፣ መደምደሚያው ከሰል ሆኖ ሲገኝ በራሴ ጉጉት ላይ ሳቅኩበት::" አለና ጨዋታውን አሳረገ::

"ያመጣልህ ስጦታ ምንም ዋጋ የማይኖረው እኮ፣ አንተ ከሰል ሞልቶ



ስለተረፈህና ያለህንም ያን ያህል ስለማትፈልገው ነው:: ከሰሉን ለአንዲት ምስኪን አሮጊት ብትሰጣቸው፣ ከልባቸው ሲመርቁህ የሚከርሙበት ትልቅ ዋጋ ያለው ውለታ ይሆንልህ ነበር:: ምናልባትም ለዋልከለት ውለታ ሰውየው ከመረቀህና ካመሰገነህም በላይ በምስኪኗ አሮጊት የሚያስመሰግንህና የሚያስመርቅህ ውለታ ይሆናል::

"የአንድ ዕቃ ወይም ጉዳይ ዋጋ የሚለካው፣ በዕቃው ወይም በጉዳዩ ዓይነት ሳይሆን፣ ዕቃው ወይም ጉዳዩ ባረፈበት ሰው ማንነት ነው:: ይሄ ከሰል ላንተ ዋጋ የለውም፤ ነገር ግን ይሄው ከሰል ለምስኪኗ አሮጊት እጅግ ዋጋ ያለውና ጠቃሚም ነው:: ይሄን ሁሉ ለምን እንደምዘላብድልህ ታውቃለህ?" አልኩት እየፈገግኩ:: 'አላውቅም' ሲል እናቱን በመነቅነቅ መለሰልኝ:: መገረሙ ፊቱ ላይ ይነበባል::

"አንተ፣ 'አንድ ጆንያ ከሰል ይዞልኝ መጣ' ብለህ ስትነግረኝ ልዘነጋው የነበረን አንድ ነገር አስታወሰከኝ:: ደሞዜን ስትከፍለኝ ለአንድ ምስኪን አሮጊት ከሰል ገዝቼ ልሰጣቸው አስቤ ነበር:: አልፎ፣ አልፎ ሱቅ እየመጡ ሸቀጥ ሲገዙን የምታውቃቸው ይመስለኛል::

"ያለፈው ሳምንት እሁድ ትንሽ ልንሸራሸር ብዬ ወጥቼ ሳለ መንገድ ላይ አገኙኝና ቤት ካልገባህ ብለው ያዙኝ:: ቤታቸው የእኛ ሱቅ አቅራቢያ ነው:: እሺ ብያቸው ገባሁኝ:: ልክ እንደሳቸው ያረጀና አቅመ ቢስ ቤት ነው:: ቡና ካላፈላሁልህ ብለው የግድ አፍልተው አጠጡኝ:: ታሪኩን ለማሳጠር... ብርዱ እያንዘፈዘፋቸው እንደሆነና ያለፈውም ክረምት እንዴት እንዳሰቃየቸው አንጀት በሚበላ ድምፃቸው አጫወቱን:: ለቡና ግብዣው አመስግኛቸው ስወጣ፣ ደሞዜን ስቀበል አንድ ኩንታል ከሰል ገዝቼ ጀባ ልላቸው ለራሴ ቃል ገባሁኝ:: የደሞዝ ቀኔ ደግሞ ነገ ነው:: እኔ በነገው ዕለት ልገዛው ያቀድኩት ከሰል ዛሬ በሌላ በር ገብቶ ጎኔ ቁጭ

እንዳለ አሁን አንተ ነገርከኝ:: እኔ ደግሞ እንዲህ ያሉ ግጥምጥሞሾችን እንደተራ አጋጣሚ የምመለከት ሰው አይደለሁም::

“ባንተ በኩል ዋጋ ያጣው ከሰል ለእኒያ አሮጊት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው አሁን ተረዳህ?... ዛሬውኑ ወስደን ጀባ እንላቸዋለን:: ምን ትላለህ?” አልኩት እየተፍነከነኩ::

“ንግግርህም ሆነ ስራ ነገርህ እየደነቀኝ፣ ሳምንት እንኳ ሳይመስለኝ ወር ሆነን:: የተናገርከው ነገር ምንም የሚጣል የሌለው ሀቅ ነው:: ምሳችንን እንደጨረስን ጭነን እንወስድላቸዋለን:: እንደውም ዛሬ እሳቸው ጋር ነው ቁጭ ብለን ዱዓ የምናደርገው::” ብሎ ይበልጥ አስደሰተኝ::

ከምሣ በኋላ ከሰሉን በአማን መኪና ጭነን፣ ጫታችንን፣ ሁለት ኪሎ ቡናና ሁለት ኪሎ ስኳር ጭምር ገዝተን፣ መልካም መልካሙን እያወጋን ወደ አሮጊቷ ቤት ሄድን:: የአሮጊቷም ቤት ከፍት ሆኖ ጠበቀን:: መኪናችንን ከበራቸው ትይዩ አቆምንና ከሰሉን ተጋግዘን አውርደን ደጃፋቸው ላይ አደረስነው::

“ቤቶች” ብዬ አንኳኳሁ::

“ማነው? ይግቡ::” እያሉ ብቅ አሉ:: አዩኝ፣ አማንንም አዩት::

“ውይ ልጆቼ! እናንተው ናችሁ እንዴ? ግቡ” አሉን በፈገግታ::

“ይሄንን የት እናድርግልዎት እማማ?” አልኳቸው::

“ምንድነው እሱ፣ ልጄ?” አሉኝ ዓይናቸውን ወደ ሸከሙ ልከው::

“ከሰል ነው:: ለብርዱ እንዲሆንዎት ብለን ነው::” አልኳቸው በፈገግታ:: ሳግ ያነቀው ደስታቸውን ዓይናቸው ውስጥ አየሁት::

“አይ ልጆቼ! የተባረካችሁ ልጆች ናችሁ:: የተባረከው ነገር ሁሉ ለእናንተ ይሁን:: ያላሰብኩትን ሲሳይ ስላሳያችሁኝ ያልታሰበ ሲሳይ ይስጣችሁ::.... አይ እማምላክ! ጭንቄን አይተሽ እነኚህን ፀሐይ ልጆሽን



ላከሽልኝ?” አሉ እጆቻቸውን ዘርግተው፣ አንገታቸውን እዘምመው ዓይኖቻቸውን ሰማይ ላይ ተከለው::

“በሉ ግቡ፣ ግቡ ልጆቼ:: ደጅ ላይ ገተርኳችሁ:: እዚህች ጋር አድርጉትና ቁጭ በሉ እስቲ::” ድምፃቸው የመቶ እንስፍስፍ እናቶችን ያህል ጉልበት አለው:: ከሰሉን ከመዝጊያው ጀርባ አቆምነውና ወደ እርሳቸው ዞር አልን::

ያኔ ነበር ቤቱ ውስጥ ሌላም ሰው መኖሩን ያስተዋልኩት:: ጠይም ቆንጆ ወጣት ቆማ ታየናለች:: ዓይኔን በፍጥነት ከርሷ ላይ ነቀልኩና፤

“እማማ፣ ሰንበትን ከእርስዎ ጋር ዱዓ እያደረግን ለማሳለፍ አቅደን ነው የመጣነው:: እንግዳ ይቀበላሉ?” አልኳቸው በፈገግታ::

“እግኝቻችሁ ነው ልጆቼ!” አሉኝ ሆዳቸውን በሁለት እጆቻቸው ይዘውና ከወገባቸው እጥፍ ብለው::

አማን ጫቱን፣ ቡናውንና ስኳሩን ለማምጣት ቀድሞ ወጥቶ ነበርና በፍጥነት ተመለሰ::

“ይኸው ቡናም ስኳርም መጥቶልዎታል::” አለና ረከቦቱ ጎን አስቀመጠ ላቸው:: እማማ የሁለታችንንም እጆች በየተራ ሳሟቸው::

“ዓለማችሁን እዩ፤ ፀሐዮቼ ናችሁና እንደ ፀሐይ ግነኑ፤ እንደ ጨረቃ ተዋቡ፤ ግርማችሁ እንደ ጨለማ የሚያስደነግጥ ይሁን፤ ቃላችሁ የሚታመን፣ ትዕዛ ዛችሁ የሚከበር ይሁን::” እሳቸውም አብዝተው መረቁን፤ እኛም እጆቻችንን ዘርግተን አብዝተን ‘አሜን፣ አሜን’ አልን::

ሁለታችንን በአንድነት የት እንደሚያስቀምጡን ግራ ሲገባቸው ጊዜ፣ ጠይሟ ልጅ ልታግዛቸው ተንቀሳቀሰች::

“ቆይ እማማ፣ እርስዎ ይቀመጡ:: እኔ አነጥፍላቸዋለሁ::” ብላ አንዱ ጥግ ላይ ምንጣፍ አነጠፈችልን::

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

"እሰይ ልጄ! ተባረኪ:: በየሄድሽበት የሚያስተናግድሽ ይብዛ::" ብለው መረቋት::

ልጅቷ ያዘጋጀችልን ሥፍራ ላይ ተሰየምን:: ቡናውም ተቆላ:: በድጋሚ ብዙ ተመረቅን፤ ብዙም አሜን አልን:: ጫታችንም በአማን ዱዓ ተፈታ:: እማማና ልጅቷ አይቅሙምና እኔና አማን ተያያዝነው:: በመሃል እማማ ያጫወቱን ታሪክ ያመጣነውን የከሰል ዋጋ አናረው:: የጆንያው ከሰል ለእማማ ያለው ትርጉም እኛ ካሰብነውም በላይ የገዘፈ ነውና የሚሰጠውም ዋጋ ሰማይ ነካ::

"ልጆቼ ይገርማችኋል፣ ባለቤቴ ከሞተ አሥራ አምስት ዓመት ሆኖታል:: በሕይወት ሳለ እንዴት ያለ ጠንካራ የስራ ሰው ነበር መሰላችሁ? የጭነት መኪና ላይ ረዳት ሆኖ ነበር የሚሰራው:: ታዲያ፣ ሁሌም ወጣ ብሎ በተመለሰ ቁጥር አንድ ነገር ሳይጭን አይመለስም ነበር:: ጤፍ ነው፣ ከሰሉ ነው፣ ሰንዴው ነው..." አሉና በረጅሙ ተነፈሱ::

"ይኸው ድፍን አሥራ አምስት ዓመት፣ ባለቤቴ ከሞተ በኋላ የጆንያ ከሰል ቤቴ ገብቶ አያውቅም:: ዛሬ ግን ባሌ ከሞት የተነሳ ያህል ነው የተሰማኝ:: ዕድሜያችሁን ያርዝምላችሁ ልጆቼ:: የተመኛችሁትን አግኙ፣ የወደዳችሁትን እፈሱ::" ብለው መረቁን::

አማን፣ 'እንኳን ዛሬን እዚህ መጣን፤ እንኳንም ያደረግነውን አደረግን' የሚለውን መልዕክቱን ጀርባዬን ቸብ፣ ቸብ በማድረግ ገለፀልኝ:: እኔም መደሰቴን በፊት ሙሉ ፈገግታ ገለፅኩለት::

ልጅቱ ከአሳት ማቀጣጠሉ ጀምሮ እስከ ቡና መውቀጡና ውሃ ማቀበሉ ድረስ ተፍ ፣ ተፍ ስትል አጤንኳት:: የለበሰችው ጂንስ ሱሪ በጣም የሚያምርና ውድ ዋጋ የወጣበትም ይመስላል:: ከንግግሯም ከአረማመዷም ቆጠብ ያለች ናት:: የተቀመጠችው ከእኔ ጎን ያለ አሮጌ ሳጥን ላይ ነው:: ለእማማ ውሃ ልታቀብል ብድግ ስትል ፣



ዓይኔ ሳጥኑ ላይ ያስቀመጠችው ዳጎስ ያለ መጽሐፍ ላይ አረፈ:: አገስቼተመለከትኩትናርዕሱንእንዳየሁበገረሜታቀናብዬተመለከትኳት:: ሳታየኝ ተቻኩዬ ዓይኔን ወደ መጽሐፉ መለስኩት:: 'ዘ ፋውንቴን ሄድ' የሚለው የአየን ራንድ መጽሐፍ ነው:: በጣም ከማደንቃቸውና ከማከብራቸው መጻሕፍት አንዱ ነው:: ተመልሳ ከቦታዋ ስትቀመጥ "ይሄን መጽሐፍ እያነበብሽው ነው?" አልኳት::

"አዎ::" አጭር መልስ፣ ለነገሩ ቢረዝምስ ምን ይረባል?

"በጣም ቆንጆ መጽሐፍ ነው:: ደራሲዋም ጎበዝ ናት:: ሌሎቹን መጽሐፎቿን አላገኘኋቸውም እንጂ ሁሉንም ባነባቸው ደስ ይለኝ ነበር::"

"አዎ፤ ጎበዝ ናት::" አለችኝ:: መጽሐፉን አስረከብኳትና ወደ አማን ዞሬ ማውጋታችን ቀጠልን::

ይህ በሆነ በሁለተኛው ቀን፣ ማክሰኞ ዕለት ይቺው ጠይም ወጣት ሱቅ መጣች:: እኔም፣ አብራኝ የምትሰራውም ልጅ ደንበኞቻችንን በማስተናገድ ፋታ አጥተን ነበር:: ቀና ብዬ ሳያት ፈገግታ በሌለው ፊት እጇን አውለብልባ ሰላም አለችኝና በእጇ የያዘችውን መጽሐፍ በርቀት እያሳየችኝ ከደንበኞች ጋር በሚለየን ረጅም የሱቅ ጠረጴዛ ላይ አስቀምጣልኝ ወጣች::

ሁኔታዋ እየገረመኝ ማስተናገዴን ለመጨረስ ተጣደፍኩኝ:: በመጨረሻም ወዳስቀመጠችልኝ መጽሐፍ ሄጄ አነሳሁት:: የአየን ራንድ ሌላው መጽሐፍ 'አት ላስት ሽሩግድ' ነው:: ይገርማል! እሁድ ዕለት 'የደራሲዋን ሌሎች መጻሕፍቶች ባገኝቸውና ባነባቸው ደስ ይለኝ ነበር' ስላት አለኝም፣ የለኝምም አላለችኝም:: ዛሬ ግን ምንም ሳትናገር ያለሁበት ድረስ መጥታ ቁጭ አድርጋልኝ ሄደች:: በአርሷ ሁኔታ ብገረምም መጽሐፉን በማግኘቴ በጣም ተደስትኩኝ::

በቀጣዩ እሁድ ከቁርስ በኋላ በአግሬ እየተንሸራሸርኩ ቅርብ ወዳለ

Scanned with CamScanner

ካፍቴሪያ አቀናሁ:: ያቺ ስሟን የማላውቀው ጠይም ወጣት ብቻዋን ተቀምጣ አየኋት:: ላዋሰችኝ መጽሐፍ ምስጋና ለማቅረብ ጥሩ አጋጣሚ ስላገኘሁ ደስ እያለኝ ወደ እርሷ ተራመድኩ::

"ሃይ!" አልኳት፡ መጽሔት እያነበበች ነበር:: ቀና ብላ ተመለከተችኝና ያለምንም ፈገግታ "ሃይ!" አለችኝ::

"ጠረጴዛሽን መጋራት ይፈቀዳል?"

"ይቻላል::" ስትለኝ ተቀመጥኩ::

"በነገራችን ላይ ላዋሰሽኝ መጽሐፍ ምስጋናዬን እንኳ ለማቅረብ ዕድሉን ሳትሰጪኝ ነው ፈጥነሽ የሄድሽው:: በጣም አመሰግናለሁ::"

"ምንም አይደል::" አለችና መጽሔቷን ማንበብ ቀጠለች::

የእርሷን ማኪያቶ ያመጣላትን አስተናጋጅ ቡና አዝዤው ዙሪያዬን ቃኘሁ:: ዓይኖቼ ሌላ ማረፊያ ስላጡ ተመልሰው እሷ ላይ ተተከሉ:: በሕይወት ዘመኔ የዚህችን ልጅ ያህል ቁጥብ ተናጋሪ አጋጥሞኝ አያውቅም:: ድንገት ቀና ብላ ስታየኝ ዓይን ለዓይን ተገጣጠምን:: ግን ሲሰርቅ እንደተያዘ ሌባ ዓይኖቼን መስበር አልፈለግኩም:: የእርሷም ዓይኖች አቅጣጫ አልለወጡም:: ተፋጠጥን::

"ስምሽ ማነው?" አልኳት::

"ዕንቁጣጣሽ" ብላ መለሰችልኝ::

"ዕንቁጣጣሽ... በጣም ደስ የሚል ስም ነው:: የመጀመሪያ ሴት ልጄን ዕንቁጣጣሽ ብዬ እጠራታለሁ::" ያዘዝኩት ቡና ደርሶ ዓይኖቻችንን ተተክለው ከቀሩበት ቦታ ነቀላቸው::

"የዚህ ከተማ ነዋሪ ነሽ ወይንስ የአዲስ አበባ ልጅ?" ብዬ ጠየቅኳት፤ ቡናዬን ፉት አልኩና::

"እዚሁ ነኝ:: አንተስ?"



"እኔ ውልደቴም ዕድገቴም አዲስ አበባ ነው:: እዚህ ከመጣሁ አንድ ወር ከሳምንት ሆኖኛል::" ጭንቅላቷን በገባኝ ነቀነቀችና ወደ ንባቧ ተመለሰች:: መጫወቱን አልጠላም ነበር፤ ግን ጨዋታ የምትወድ ዓይነት አልሆነችብኝም:: ዝም ልላት ወሰንኩ:: እናም በተቻለ መጠን ዓይኖቼን ወደሷ ሳልመልስ ዙሪያዬ ያሉትን ሰዎችና ቁሶች ማጤን ጀመርኩኝ:: ሁሉንም አይቼ ጠገብኩ:: ሌላ የሚታይ ሲጠፋ፤ በዚህ ዝምታ ውስጥ ላለመቆየት ቡናዬን ቶሎ ቶሎ ፉት ፉት አልኩኝና ጨረስኩት::

ያስተናገደንን ልጅ በምልክት ጠርቼ አስር ብር ሰጠሁትና የሁለታችንንም ሂሳብ እንዲቆርጥ ነገርኩት:: ካቀረቀረችበት ቀና ብላ አየችኝና እጇን ወደ ኪሷ ላከች::

"ተቀድመሻል:: ሌላ ቀን እንደዛሬው ድንገት ከተገናኘን ተረኛ አንቺ ነሽ::" አልኳት:: እጇን ከኪሷ መለሰችና "አመሰግናለሁ::" ብላኝ ወደ ንባቧ ተከተተች:: አስተናጋጁ መልስ እንዳመጣልኝ "በይ ደህና ዋይ" አልኳትና ተነሳሁ::

"ወዴት ነው የምትሄደው?" ብላ ጠየቀችኝ:: ይሄንን እንደ መጀመሪያ ንግግሯ መዘገብኩላት::

"እንዲሁ ዘወር፤ ዘወር ማለት አስቤ ነው::"

"ቆይ!... እኔም ዎክ ለማድረግ እያሰብኩ ነበር::" አለችና ብድግ አለች:: በአንድነት እየተራመድን ከካፌው ወጣን:: መንገድ እንደጀመርን፤

"ዘ ፋውንቴን ሄድን ጨረሰሽው?" አልኳት::

"ከሁለት ቀን በፊት ጨረስኩት::"

"እንዴት አገኘሽው?"

"በጣም ግሩም መጽሐፍ ነው:: ካራክተሮቹም በደንብ ተስለዋል"

"ሮርከንና ዶሚኒከን በጣም ቀንቼባቸዋለሁ::" ስላት ዞር ብላ ተመለከተችኝና ፈገግ አለች:: ይሄም የመጀመሪያ ፈገግታዋ ነው::

Scanned with CamScanner

"በደንብ አንብበኸዋል ማለት ነው::" ከዚህ ንግግሯ የተረዳሁት ነገር ቢኖር አስቀድሞ ለእኔ የነበራት ግምት አነስተኛ እንደነበር ነው::

"አዎ:: በደንብ ስላነበብኩት ነው የምወደው:: በራሴ ሕይወት ውስጥም ተፅዕኖ መፍጠር የቻለ መጽሐፍ ነው::"

"በምን መልኩ?" ይሄን ጥያቄ ለመመለስ አመነታሁ:: መልሱ በሁለት መልኩ ስላለፈው ሕይወቴ ፍንጭ የሚሰጥ ሊሆን ነው:: ስላለፈው ሕይወቴ አንኳር ጉዳዮች ጓደኛዬና አሳዳሪዬ ለሆነው ለአማንም ምንም አልነገርኩትም:: ስዘገይባት ጊዜ፤

"ምነው?.... መመለስ ካልፈለግክ ግድ የለብህም እኮ::" አለችኝ::

"ኖኖ!... ብዙም ጠልቄ ሳልገባ ልነግርሽ እችላለሁ:: የዘገየሁት እንዴት በአጭሩ ላስረዳሽ እንደምችል እያሰብኩ ስለነበር ነው:: አንድ ወቅት የእኔ የሆነን አንድ ስራ አንድ የማውቀው ሰው ያለፈቃዴ ወስዶ ራሱ እንዳዘጋጀው አድርጎ ተጠቀመበት:: ይሄንን ያደረገው ስራውን ስለፈገውና ከእኔ ጋር ደግሞ ልንስማማ ስላልቻልን ነበር:: በዚህ ስራ በገንዘብ ካለመጠቀሜ የበለጠ ለስራው ባለቤትነት ሌላ ሰው በመመዝገቡ በጣም ተበሳጨሁ- ልነግርሽ ከምችለው በላይ:: ለወራት ያህል መስራት የሚባል ነገር ከነአካቴው አቆምኩ::

"አንድ ቀን አንድ ጓደኛዬ ስለዚሁ ጉዳይ አንስቼ ስብሰከሰክ አስተዋለኝ:: ከዚህ በፊትም ስለዚህ ጉዳይ በተደጋጋሚ ተጫውተን ነበር:: የዚያን ዕለት ግን አየኝ፣ አየኝና በትልቁ ፈገገ::

"ምነው?" አልኩት

"ሮርክን ባንተ ቦታ አስቀምጬ አየሁትና ሰፊው ልዩነታችሁ አስደንቆኝ ነው::" አለኝ እንደፈገገ:: ሊለኝ የፈለገው ከመቅፅበት ነበርና የገባኝ ራሴን ታዘብኩት::

"ስለሮርክና ስለ ፋውንቴን ሄድ ለዚህ ጓደኛዬ ብዙ የደሰኮርኩለትና



መጽሐፉን ተውሼ ያስነበብኩትም እኔው ነበርኩ:: እኔ ለአፍታም ያላስተዋልኩትን ነጥብ እሱ መዝዞ አወጣውና ለወራት ከተሰቃየሁበት በሽታዬ በአንድ ዐረፍተ ነገር ፈወሰኝ::

"እሱ ሰርቶ የሰጠውን የሕንፃ ንድፍ፣ ጓደኛው ልክ ራሱ እንደነደፈው አድርጎ አውጥቶ ብዙ ገንዘብና ዝና ሲያገኝበት፣ ሮርክ 'ይሄ ስራ የእኔ ነውና ዝናውና ገንዘቡ የሚገባው ለእኔ ነው' ብሎ አልተብሰለሰለም:: ጓደኛው በዚያ ንድፍ የዓመቱ ምርጥ አርኪቴክት ተብሎ ሲሸለምና ዝናው ባህር ሲሻገርም እሱ ቅርም አላለው::

"የዓለም ህዝብ ሁሉ የዚያ ንድፍ ባለጥበብ ያ ጓደኛው እንደሆነ ቢያስብም፣ ያ ለእርሱ ግድ አልሰጠውም:: ግድ የሰጠው ሁለት ነገር ብቻ ነው:: የመጀመሪያው ያ እሱ የተጠበበበት የሕንፃ ንድፍ ድንቅና የዓመቱ ምርጥ ንድፍ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የዚያ ንድፍ ባለጥበብ እሱ ራሱ መሆኑን እሱና ተሸላሚ ጓደኛው ያውቃሉ:: ይሄ ለእርሱ በቂው ነበር:: ሌላው ሰው አደነቀው፣ አላደነቀው፣ የእርሱ ስራ መሆኑን አወቁለት፣ አላወቁለት ግድም አልሰጠው:: በቃ ስራው የርሱ ነዋ::

ጓደኛዬም ሊጠቁመኝ የፈለገው ይሄንን ነበር:: 'ቆንጆ ስራ ስለሰራሁ ነው:: ማንም ይሄ ስራ የእከሌ ነው ይበል፣ እኔና ነጣቂው ግን የእኔ እንደሆነ ያለምንም ጥርጥር እናውቃለን:: ይሄንን ስራ ያፈራው አዕምሮዬ አሁንም አብሮኝ አለ:: ስለዚህ ከዚህም በላይ ምርጥ ነገር መስራት እችላለሁ::' ብዬ ለራሴ ነገርኩትና ሳልዘገይ ተመልሼ ስራዬን ቀጠልኩ:: ብዙም ሳልቆይ ይበልጥ ውጤታማ ያደረጉኝን ስራዎች ሰራሁ::"

"ሀሳብህን በተወሰነ መልኩ እጋራዋለሁ:: ግን ደግሞ ሮርክ ያደረገውን ነገር የግድ አንተ እንድታደርግ አይጠበቅብህም:: ምክንያቱም ሮርክ ያደረገው ነገር ከጅማሬው ጀምሮ በባህሪው ውስጥ ስናየው የነበረውን ነገር ነው:: ለምሳሌ በዩንቨርስቲው ውስጥ ቁጥር አንድ የአርኪቴክቸር

Scanned with CamScanner

ተማሪ ነው:: በዚያ ውጤቱ ከተመረቀ ደግሞ በሀገሪቱ አለ የሚባል የኮንስትራክሽን ካምፓኒ በትልቅ ደሞዝ እንደሚቀተረውም ያውቃል:: ግን የመመረቂያ ንድፉን በታዘዘው መሰረት ካልሰራ ተቀባይነት እንደማያገኝና ጨርሶውንም ሊመረቅ እንደማይችል ቢነገረውም፣ የመመረቂያ ስራውን ማቅረብ የሚፈልገው ራሱ በመረጠውና ቀድሞውንም ባቀረበበት መንገድ ብቻ እንደሆነና ሌላ እንደማይሰራ ነው ደግሞ ያሳወቃቸው:: የዩኒቨርስቲው ምሁራን በዚህ ሰበብ ብቻ ሳይመረቅ እንዳይቀር ለማድረግ ብዙ ቢወተውቱትም በሀሳቡ ፀናና ሳይመረቅ ቀረ:: ከፊቱ የነበረው የስራ ዕድልም ከእሱ በታች ውጤት ለነበረው ጓደኛው ተሰጠው:: እንግዲህ ያመነበትን ብቻ ለመስራት ስለፈለገ ያንን ታላቅ ዕድል አሳልፎ ሰጥቶ፣ መሬት ቆፋሪና ድንጋይ ጠራቢ ሆኖ ስርቷል::

"ቅድም አንተ ስለሮርክ የነገርከኝን ዓይነት ሰው ለመሆን፣ አሁን እኔ ስለሮርክ የነገርኩሀን ዓይነት ሰው መሆን ይኖርብሃል:: አለዚያ ግን በጣም ከባድ ነው:: ያመንከበትን ብቻ ለመኖር የቆረጥክ ዓይነት ሰው ከሆንክ ግን ሮርክ ምርጥ ሞዴል ነው:: ተንዛዛሁ መሰል?"

"አልተንዛዛሽም:: ግን... በእርግጠኝነት ለመናገር ይሄ የዓመቱ ረጅም ንግግርሽ ነው::" አልኳት በፈገግታ::

ዞር ብላ በገረሜታ ተመለከተችኝና "በደንብ ታዝበኸኛላ!?" ብላ በመጠኑ ፈገገች::

"አዲስ አበባ እያለሀ ምን ነበር የምትሰራው?"

"ቅድም ዳር ዳሩን የሄድኩልሽ እሱን ላለመናገር መስሎኝ::" አልኳት ፈገግ ብዬ::

"እንዲያ ከሆነ ተወው::"

"አንቺስ ተማሪ ነሽ ወይስ...?"

"ተማሪም ሰራተኛም አይደለሁም::"



"የሙሉ ሰዓት አንባቢ ነሻ?"

"የሙሉ ሰዓት አንባቢ ከመሆን ይልቅ እየተማርኩ ወይም እየሰራሁ ብኖብ የተሻለ ነበር::"

"ታዲያ ምን አገደሽ?"

ለአፍታ ፀጥ አለችና "ምንም::" አለችኝ::

"ምንም ካላገደሽማ ታደርጊው ነበር:: ጥያቄዬን መመለስ አልፈለግሽም መሰል?" ዞር ብላ አይታኝ 'ገብቶሃል' በሚል ስሜት ፈገገችና፣

"ለማንኛውም እዚህ ጋ ቻዎ ልበልህ::" ብላ ቆመች:: በገረሜታ አየኋት:: ጨዋታዋን ወድጄዋለሁ:: ብንቀጥልበት ደስተኛ ነኝ፣ ግን ደግሞ መሄድ ፈልጋለች:: 'ስለዚህ ትሂድ' ብዬ አሰብኩ::

የተጫወትነው ለጥቂት ደቂቃዎች ቢሆንም በደንብ ተደሰቼባቸዋለሁና አመሰግናለሁ:: "ደህና ዋይ::" ብዬ እጄን ዘረጋሁላት::

"ቻዎ! ደህና ሁን::" ጨበጠችኝና ወደ መረጠችው አቅጣጫ አቀናች:: እኔም የጀመርኩትን አቅጣጫ ይዤ የረፋዱን ለስላሳ ሙቀት እያጣጣምኩ ተጓዝኩ::

ብቻዬን እየተራመድኩ ሳለ ዓይኔ ምስሏን፣ ጆሮዬም ድምጿን ሲደግሙብኝ ጊዜ የፍርሃት ስሜት ተሰማኝ:: ስለ እሷም ሆነ ስለሌላ ሰው ደጋግሜ ማሰብ አልፈልግም:: ማሰብ የምፈልገው እኔው ራሴ ስለዚያ ነገር ማሰብ ፈቅጄ እና በሀሳቤ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ለማድረግ ነቅቼ ስጠባበቅ ብቻ ነው:: አንድ ሀሳብ ሳልፈቅድለት አዕምሮዬ ውስጥ ከገባና ካብሰለሰለኝ ቶሎ ነቅቼ ላቆመው አሊያም ልቆጣጠረው ይገባል::

ሀሳባችንን እኛ ልንቆጣጠረው ካልቻልን፣ እሱ እንዳሻው እንዲነዳን ፈቅደንለታል ማለት ነው:: እንዲያ ከሆነ ደግሞ፣ እንደ ባህር አሸዋ የበዙ እልፍ አዕላፍ አረሞችን በአዕምሯችንና በልባችን እየዘራ የሚኖር ታታሪ ወፍ አብሮን እንዲኖር ፈቅደንለታል ማለት ነው:: እነዚያ አረሞች

ማሳችንን አጥለቅልቀው፣ እሸታችንን አቀጭጨው፣ ፍሬያችንን አምክነው ያሰብንበት ሳይሆን ያላሰምነው ገሃነም ውስጥ ሲጥሉን ተግተው ይበቅላሉ:: ለዚህም ነው ሀሳባችንን ልንቆጣጠረው ይገባል የምለው::

እንዲያውም አንድ የማውቀው አባባል አለ:: "You are master of your mind and driver of your thoughts" 'የአዕምሮህም ጌታ ፣ የሀሳቦችህም ሹፌር አንተ ነህ' ይላል::

የሀሳቤ ሹፌር የመሆን ኃላፊነቴን አሳልፌ ሰጥቼው ሀሳቤ እንዳሻው እንዲሾፍረኝና ካገኘው ጋር እንዲያላትመኝ አልፈቅድለትም:: እኔው ራሴ ሲያሻኝ አስፈረጥጠዋለሁ፤ አይሆኑ ቦታ ሲገባ ሲል ደግሞ በልጓም አቆመዋለሁ፣ መንገድ ሊስት ሲል እመራዋለሁ::

እናም አዕምሮዬ ዕንቁጣጣሽን ያለ ፈቃዴ ሲያስባት ደረስኩበትና ዶሴዋን አዘግቼው ወደ ሌላ ስራ መራሁት:: በእርግጥም ስለእሷ ማሰብ ለምን ያስፈልገኛል? ማለት የቀረኝ ነገር ካለ ፊቷ ልለው ነው የሚገባው:: ከዚህ በፊት ፊት ለፊት ልናገራቸው የሚገቡኝን ብ...ዙ! ነገሮች በተለያየ ምክንያት ከእንደበቴ ለማውጣት በመቆጠቤ ብቻዬን ስሰቃይባቸውና ስንገላታባቸው ኖሬያለሁ:: ያ ጊዜ ከአሁን በኋላ አይደገምም:: መናገር የሚገባኝን በአግባቡ እናገራለሁ፤ መጠየቅ የሚገባኝንም በአግባቡና በወቅቱ እጠይቃለሁ፤ እንጂ ሀሳብ ሆኖ በአዕምሮዬ ውስጥ እንዳሻው እንዲፈነጭ አልፈቅድለትም::

ሀሳባችን በራሱ የሕይወት ጉዟችንን የሚቀርፅ ረቂቅ ኃይል ነው:: ወደምናልመው ግብ ለመድረስ፣ ሃሳባችንን እዚያ ሊያደርሰን በሚችል ሁኔታ ልንቀርፀው፣ ልንሾፍረው፣ ከጎዳናው ወጥቶ በተጣመመ መንገድ እንዳይሄድም መሪውን በጥንቃቄ ይዘን ትኩረታችንን ጎዳናው ላይ ብቻ ማድረግ ይጠበቅብናል::

መጽሐፉም 'እሹ፣ ይሰጣችሁማል' ይላል:: የሀገራችን ብሂልም 'የፈሩት



ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል::' ይላል:: ሁለቱም አባባሎች የሀሳብን ረቂቅ ኃይልነት የሚገልፅ ታላቅ ምስጢር የያዙ ቁም ነገሮች ናቸው::

እንዳይደርስ ደጋግመን የምናስበውና የፈራነው ነገር የሚደርሰው፣ እኛ ደጋግመን ስለእርሱ ስላሰብንና ሀልውናውን ስላወጅንለት ነው:: ሀልውናውን ካወጅንለት ደግሞ እንዲኖር ወይም እንዲሆን ፈቅደንለታል ማለት ነው::በፈቃድ ቃል 'ይድረስም' ብለን አስብን፣ በከልካይ ቃል 'አይድረስም' ብለን አሰብን በሁለቱም ሀሳቦቻችን ውስጥ የዚያን ነገር ሀልውና ፈቅደናል:: ስለዚህ ከጅምሩ እንዳይሆን ለምንሻው ጉዳይ ሀልውና መስጠት አያሻንም:: ውስጣችን ሞቶ መቀበር ይገባዋል::

እንዳይደርስ የምንፈራውን ነገር እንዳይደርስ ከምናስብ ይልቅ፤ ሀሳባችንን በምትኩ እንዲሆንልን በምንመኘው ተቃራኒ ሀሳብ ላይ ማድረግ ወደምንፈልገው ውጤት ያደርሰናል::

"ጦርነት ሊነሳ ነው ይባላል:: ኧረ ባልተነሳ!" ብለን ስለጦርነት ያለመነሳት ከማሰብ ይልቅ፤ "ሀገራችን ሰላም ትሁን" ብለን ብናስብ፣ ሀሳብን በምንፈልገውና በተመኘነው የሰላም ጎዳና ላይ እየሾፈርነው ነው ማለት ነው::

'እሹ ይሰጣችሁማል' ሲልም ልክ ከላይ እንዳነሳነው ነው:: የፈለግነው ሰላምን ከሆነ መጠየቅ የሚገባንም ሰላምን ነው::

"ፍቅረኛዬ እንዳትለየኝ" ብሎ እብዝቶ ከማሰብና ከመጨነቅ ይልቅ "ከፍቅረኛዬ ጋር አንድ ሆነን ለቁም ነገር እንበቃለን::" ብሎ በማሰብ፣ የሀሳብን አቅጣጫ እንዲሆንልን በምንፈልገው ጉዳይ ላይ ብቻ አድርገን ልንሾፍረው ይገባል::ሀሳብን በምንሻው ጉዳይ ላይ እንጂ በማንሻው ጉዳይ ላይ ማድረግ ውጤቱ ውድቀት ነው:: የሚሰጠንም የምንሻውን እንጂ የማንሻውን አይደለም::የማንሾፍረው አሊያም የማንቆጣጠረው ሀሳብ በአዕምሯችን ገብቶ ያላቀድነውን እንዳያቅድብንና እንዳሻው እንዳይፈነጭብን ስሜታችንን የማዳመጥና የመከታተል ልምድን ማዳበር ይገባናል::

Scanned with CamScanner

## - 10 -

### "የማይነጋ ሌሊት ቀድሞውንም አይጨልምም::"

ፀሐይ በመንበሯ ሳለች ምድርን ጨለማ ይውጣታል:: የፀሐይን መንበር መንጠቅ የማይቻለው፤ ግን ደግሞ በየዕለቱ ቢያንስ ለቀን እኩሌታ ያህል የፀሐይን ግዙፍ ስልጣን የሚጋርደው፣ ይህ ጨለማ ማን ነው?... ስልጣኑና አቅሙንስ ከየት አገኘው?... ለመሆኑ ይሄ ጨለማ የተባለው የብርሃን ባላጋራ ህልውና አለው? ካለውስ ምን ይመስላል? ምንጩስ ከየት ነው?... ፀሐይስ ጨለማ ለሚባለው ባለጋራዋ እጅ ሰጥታ ታውቃለች? ወይንስ የ'አለሁ' እና የአልሸነፍም ትግሏን ለሰከንድ ፍንክትካች እንኳ ሳታቋርጥ ጦር ትሰብቃለች?...

አዎ፤ ፀሐይ ሁሌም አለች:: ብርሃኗም ለሰከንድ እንኳ ሳይነጥፍ ይንቦገቦጋል:: "ፀሐይ የት አለች? ከእኛ ጋር የምትግባባት ቋንቋዋ ብርሃንስ ስለምን አልታይ፣ አልሰማ አለ?" ብለን ብንጠይቅ መልሱ፤ የእኛዋ ምድር ደረቷን ለፀሐይ ሰጥታ፣ ጀርባዋን ደግሞ ከፀሐይ ስለምትሸሽግ፣ በተራችን በምድር ደረት ላይ ሆነን እስከንንጎማለል ድረስ ስለማናያት ብቻ ነው እንጂ፤ እሷስ በታላቁ መንበሯ ላይ እንደተንቦገቦገች አለች፤ ለዘላለምም ትኖራለች::

ስለዚህ ጨለማም፣ መሬት ጀርባዋን ከፀሐይ በመሸሸጓ ሳቢያ የሚፈጠር ውጤት (ጥላ) እንጂ የራሱ ህልውናም ሆነ ምንጭ የለውም:: ህልውናም ሆነ ምንጭ ከሌለው ደግሞ የለም ማለት ነው:: እኛ በጀርባዋ በአንቀልባ



እዝላን ከብርሃን በሸሸገችን ምድር ስር ተጋድመን ሰማይ፣ ሰማይ የምናይ ሰዎች ጨለማውን 'አለህ' ብለን እውቅና ሰጠነው እንጂ በዙሪያዋ ካሉት ሀያዋን ድምር ሁሉ እጅግ የምትገዝፈው ፀሐይ ጨለማን አታውቀውም:: ደግሞም ጀርባ ሰጡኝ ብላ አላኮረፈችንም:: በጨረቃ በኩል 'አለሁ' ብላ በብርሃን ቋንቋዋ እያወራችን ነውና::

እናማ... ጨለማ የሚባል ነገር የለም፤ አልተፈጠረም:: ያለው ዘለዓለማዊ ብርሃንና ምድር የአሽከርከሪትና የአኩኩሉ ጨዋታዋን እስካላቆመች ድረስ ያለማሰለስ የሚከሰት የብርሃን ግርዶሽ (ጥላ) ነው፤ ሊያውም በሙሉ ኃይል ብርሃንን መጋረድ የማይችል ግርዶሽ::

ሁሌም ብርሃን ነው:: ሁሌም ሰላም ነው:: ሁሌም ፍቅር ነው:: ሁሌም ደስታ ነው:: ሁሌም እርካታ ነው:: ሁሌም መልካም ነው:: ሁሌም...:: እነዚህን መልካም ነገሮች የምናጣቸው ከጀርባቸው ተሸሽገን፣ በግርዶሹ በመዋጣችን ብቻ ነው:: በግርዶሹ ስር ሆነንም ባገኙት ቀዳዳ እየሾለኩ በብርሃናቸው ይዳስሱናል፣ ይጠቃቅሱናል፣ ያሳስቁናል::

እርካታ በማይሰጥህና ሕሊናህን በሚቆረቁርህ ስሜት ውስጥ ራስህን ካገኘህ፣ ያለኸው በግርዶሹ ውስጥ ነውና አምልጥ :: ታዲያ ሀሳብህን ከግርዶሹ በማምለጥ ላይ አታድርገው የግርዶሹ ጎዳና እያስፈራ መንገዱን ያረዝምብሃልና:: ሀሳብህን ከፊትህ ባለውና መልካም በሆነው ብርሃን ላይ ብቻ አድርገው መልካሙን የማየት ጉጉትህ ኃይል፣ መልካሙን የማየት ተስፋህም ትዕግሥት በመሆን ያግዙህና ካለምከብት በቶሎ ትደርሳለህ::

በብርሃናማው መልካም ጎዳና ላይ ከሆንክም ከጎዳናው ስላለመውጣት ወይም ደግሞ ወደ ግርዶሹ ስላለመግባት አታስብ ስጋትህ ትኩረትህን ይነጥቅሃልና:: ትኩረት ማጣትህ ደግሞ ለእንቅፋት ይዳርግሃል:: ሀሳብህን በመልካሙ ጎዳና ላይ በመመላለስ ላይ ብቻ አድርገው

Scanned with CamScanner

ትኩረትህ በጎዳናው ላይ ብቻ በመሆኑ ቆጥረህ የማትጨርሳቸው ገፀ-በረከቶችን ትሰበስባለህና:: በገፀ-በረከቶቹም እርካታን ትጎናፀፋለህ፣ ሁሌም ምስጋናን ታደርጋለህ::

ምስጋናን የሚያውቁ የመስጠት ክብር የገባቸው ናቸውና በፈንታቸውም ይሰጣሉ:: በመስጠታቸውም ይረካሉ:: የእርካታ ምንጫቸውንም ያበዛሉ::

ምስጋናን የሚያውቁ የመስጠት ክብር የገባቸው ናቸውና በፈንታቸውም ይሰጣሉ:: በመስጠታቸውም ይመሰገናሉ:: ምስጋና ደግሞ ይበልጥ የሚያነ ቃቃ፣ ለተሻለ ስኬት ጥረትን የሚጋብዝ ሽልማት ነውና ይበልጥ ስኬታማ ለመሆን ሃይል ይሰጣቸዋል::

እናንተ በጨለማው ውስጥ ነን ያላችሁ፣ በግርዶሹ ስር ሆናችሁ እንጂ ያ ብርሃን ለዘለዓለም በመንበሩ ላይ እንዳለ እመኑ:: 'የሕይወት እሽከርከሪት ውስጥ የማይነጋ ሌሊት ቀድሞውንም አይጨልምም::' ብላችሁ እመኑ:: ወደ ብርሃን በመሮጥ ጀግኑ- ግርዶሹ የፈጠረው ጨለማ መች እንደሞተ ካማወቃችሁ በፊት መቃብር ይወርዳል::

በብርሃን አደባባይ ላይ ታዩ፣ አጊጡ፣ ተሞሸሩ:: እርካታችሁን በሳቃችሁ ውስጥ አብስሩ:: አዲስ ነገርን ለመጋፈጥ ድፈሩ የእርካታ ምንጫችሁን ታበዙት ዘንድ:: እዚህ እውነት ነው የተባለ ነገር እዚያ ሀሰት ሆኖ ታገኙታላችሁ:: እዚህ መጥፎ የተባለውንም እዚያ መልካም ሆኖ ሲያስወድስ ታገኙታላችሁና ረጅም ጉዞ ማድረግን ልምድ አድርጉት በምድር ላይ ፍፁም የሆነ እውነት ያለመኖሩን ጥበብ በጉዟችሁ ውስጥ በሚገባ ትረዱታላችሁና:: አብሮን የተፈጠረውን፣ አብሮን ውሎ የሚያድረውን ልቦናችንን የሚያህል የእውነት ሚዛን መቼም እንደማይኖር በጉዞ ውስጥ በቀላሉ ትማራላችሁና ተጓዙ:: የማይደረስበት ባይኖርም እስከምትደርሱበት ተጓዙ::



ቀድመን ያወቅነውን እውቀት አስቀምጠን ሌላ ጥበብ ለመፈልፈል ወደ ሌላ ሥፍራ ብንጓዝ ምን የምናጣው ነገር ይኖራል? የቀድሞውን ጥበብ እንዲሁ መቼም አንስተን ልንጠቀምበት ብንሻ እጃችን ላይ አለ:: አዲስ እውቀት ለመፈለግ፣ አዲስ ጥበብ ለመማር ግን ጊዜው አሁን ነውና እንነሳ:: መወሰንን ለልባችን እናልምደው- መወሰን የቻለ ልብ ለድርጊት ይፈጥናልና::

ይሄንን እየፃፍኩ ያለሁት፣ ጨረቃና ከዋክብት ዳንኪራ የሚረግጡበትን ሰማይ አንጋጦ ከሚመለከተው የቤቴ ጣሪያ ስር፣ የትልቅ ሜዳን ያህል ተንሰራፍቶ በተዘረጋውና እንደ ከዋክብቱ ሁሉ ዳንኪራ ስረግጥበት ከነበርኩበት አልጋዬ ላይ ተቀምጬ ነው:: ዓይኖቼም ከጎኔ ሆና የሰላምና የእርካታ እንቅልፍ የወሰዳትን ጠይም ቆንጆ ወጣት እልፍ እዕላፍ ጊዜ በፍቅር እየተመለከቱ ነው::

የተኛችው ሙሉ ለሙሉ እርቃኗን ቢሆንም ከፊል ገላዋን አልጋ ልብሱ ሸፍኖታል:: አስተካክዬ አልብሻት ወደ ፅሁፌ እመለስና አፍታም ሳልቆይ ዞሬ ሳያት ከእናቷ እስከ ወገቧ ድረስ ያለው ገላዋ ተራቁቶ ሽቅብ ሲያፈጥብኝ አገኘዋለሁ:: ስንቴ እንዳለበስኳትና ስንቴ እንዳራቆተችው እንጃ:: እንዲህ በእንቅልፍ ዓለም ውስጥ እያለች ስንቴ ዓይኖቿን፣ ከናፍሯን፣ አንገቷንና ጡቶቿን እንደሳምኳቸውም እንጃ::

እንደ ታላቅ ወንዝ ያለማቋረጥ በሚፈሰው እርካታዬ ውስጥ እንደ ደራሽ ውሃ እረፋ እየደፈቀ የሚወረወረውን ስሜቴን ሲገልጡት በሚሳናቸው አቅመ ቢስ ቃላት ወረቀት ላይ ላሰፍረው በመጓጓቴ እንጂ፣ በእጆቼም በእግሮቼም እቅፍቅፍ አድርጌያት አንድ እስከንሆን ድረስ ገላችንን ገምጄው ብጋደም አልጠላም ነበር:: ግን.. ፅሁፉን በይደር ባቆየው ቃላቶቼ ከዚህም በላይ አቅም አልባ ይሆኑብኛልና አሁን መፃፉን

Scanned with CamScanner

መርጫለሁ:: በዚህ ውብ ገላ አቅፍ ውስጥ በድጋሚ ውሃ ሆኜ ለመፍሰስ ጥቂት ትዕግሥት አለኝ::

ዕንቁጣጣሽ ከበዓላት ሁሉ እጅጉን የምወደው ብቸኛው ዓመት በዓሌ ነው:: እሷንም አየኋት:: ዓመት በዓሉን መስላ ታየችኝ:: 'ስምን መልዓክ ያወጣዋል::' ማለት ይሄ ነው ብዬ አሰብኩ::

ከዕንቁጣጣሽ ጋር ያለፉትን አሥራ አምስት ቀናት በየዕለቱ ባይባልም በተደጋጋሚ ተገናኝተን ስንጫዋወት ከርመናል:: ትመጣለች፤ ትቆያለች ብዬ ሳስብ ፈጥና ትሄዳለች:: በሌላ ቀን ደግሞ ትመጣለች፤ ቸኩላለች ብዬ ሳስብ አብራኝ ታመሻለች:: ሁሉ ነገሯ ግን ሲለምዱት ይጣፍጣል:: ካላመነችበት ለሰው ቁብ የማይሰጣት ጅንን ነች፤ እንደ ንግግሯና እንደ አረማመዷ::

ዛሬ ቀኑ ቅዳሜ ነው:: ሱቅ ልንዘጋ በተቃረብንበት ሰዓት ላይ ተከሰተች:: ጥቂት ተጨዋውተን ሱቁን ዘጋንና ከእኔ ጋር ቤት ለማምሸት አብራኝ መጣች:: ከአማንና ከሊዲያ ጋር ሆነን ራት በላንና ወደኔ ክፍል ተዘዋወርን::

በጀመርኩት ፅሁፍ ላይ ለመግፋት በሙሉ ጉጉትና ኃይል ነበርኩኝ:: እሷም ይሄንን ተረድታ ነበርና "አንተ መኖሬን ሁሉ እርሳና ፅሁፍህ ላይ ብቻ አተኩር:: እኔ ደግሞ እንዳለፈው ሳምንት ቡና እያፈላሁልህ በዚህ ሳምንት የፃፍከውን በዝምታ አነባለሁ::" አለችኝና ከሊዲያ ማጀት የቡና ቁሳቁሶች አምጥታ ተፍ፣ ተፍ ማለት ጀመረች:: ይሄን ሳይ ደስ አለኝ::

እነ አማን ብቻችንን እንድንሆን ፈልገው ይመስለኛል ሰበብ ሰጥተው ብቅ አላሉም:: ቡናዬን እየጠጣሁ ፅሁፌን እንደወራጅ ውሃ አፈሰው ቀጠልኩኝ:: በመሃል አንድ ሦስት ጊዜ መፃፌን አቋርጬ አጫውቻታለሁ:: በአራተኛው ሰዓቴን ተመለከትኩኝ:: ለአራት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ሆኗል::

"ሰዓቱ ለካ በሯል:: ለማደር የመጣሽ መሰለኝ እኮ::" አልኳት::



"ማደር ይከለከላል እንዴ?"

"ሊያውም አንቺ ብለሽኝ!.. በደስታ ነው እንጂ"

"አድራለሁ::" ብላ በትኩረት አየችኝ:: ፊቴ በደስታ በራ::

"ታድያለኋ! ይሄንን ውበትና የረጋ መንፈስሽን እያየሁ ምን ያህል ገፅ እንደፃፍኩ አታይም?" አልኳት፣ የፃፍኩባቸውን ወረቀቶች እፍሺ እያሳየኋት::

ጥቂት ተጨዋውተን ወደ ፅሁፌ ተመለስኩና እስከ እኩለ ሌሊት ድረስ ፃፍኩኝ:: ያኔ እኔም ደካከምኩኝ፣ ሀሳቦቼም ፍሰታቸው ቀንሶ መቆራረጥና አልገለፅ ማለት ጀመሩ:: እናም 'ለዛሬ በቃኝ' ብዬ ወሰንኩኝ::

"እንግዲህ የዛሬው ፅሁፍ እዚህ ጋር ያብቃና ወደ መኝታችን እንግባ:: አንቺ ተነጥፎ በጠበቀሽ አልጋ ላይ ተኚ:: እኔ ደግሞ እዚሁ ፍራሽ ላይ አንጥፌ እተኛለሁ:: የታጠበ ቱታ እሱ ቁም ሳጥኑ ውስጥ አለ:: ቆይ እንደውም ላውጣልሽ::" ብዬ ብድግ አልኩኝ:: ከቁም ሳጥኑ ውስጥ ቱታዬን አውጥቼላት ዞር ስል ጃኬትና ቲሸርቷን አውልቃ ሱሪዋን እየፈታች አየኋት:: ዓይኖቼ ተወርውረው አብጠው በቆሙ የጡቶቿ ጫፎች ላይ ተተክለው ቀሩ:: ሱሪዋን አውልቃ በፓንት ብቻ እንደሆነች ወደ እኔ መጣች::

ደንግጬ በቆምኩበት ደርሳ እጆቿን በአንገቴ ዙሪያ ጠመጠመችና ከንፈሬን ግጥም አድርጋ ሳመችኝ:: ከዚያም ከናፍሮቿን ከከናፍሬ አላቅቃ ፊቷን ወደ ኋላ መለሰችና ዓይን ዓይኔን አየችኝ:: አየኋት::

"የቤቴን አልጋ ትቼ የመጣሁት ብቻዬን ለመተኛት አይደለም:: ሳመኝ!" ብላ አዘዘችኝ:: በእርጋታ አቀፍኳትና ትንፋሽ እስኪያጥረኝ ድረስ ሳምኳት፤ ሳመችኝ:: እየተሳሳምን ልብሴን ማወላለቅ ቀጠለች:: በፓንት ብቻ ስቀር ወደ ቦርሳዋ ተራምዳ የኮንዶም ፓኬት አወጣችና አልጋው ላይ ካኖረች በኋላ፤ በጀርባዋ ተጋደመችና ሸቅብ አየችኝ:: እንዴ

Scanned with CamScanner

የኮንዶሙን ፓኬት፣ አንዴ እሷን እየሁና በፈገግታ አልጋው ላይ ወጣሁ::
"ታጥቀሽና ተደራጅተሽ ነዋ የመጣሽልኝ::" አልኳት ገላዬን ከገላዋ ጋር
እየቃኘሁት::
"አዎ:: ለሁለት ዓመት ያህል የዘጋሁትን በር ለመክፈት ታጥቄና
ተደራጅቼ ነው የመጣሁት::" ብላ ጭምቅ አርጋ አቀፈችኝ::
በምናውቀው ቅኝት ሁሉ ብዙ የፍቅር ዜማዎችን አዜምን:: መቼም
የማንረሳውን ዳንኪራ የእሳት ጅረት ሆነን እስከንፈስ ድረስም ረገጥን::
ለንግግር የሚሆን የድምፅ ጉልበት አጥተን በምልክት እስከናወራ ድረስ
የምንሆነውን አጥተን ተወለጋገድን:: የሆንነውን በምን ቋንቋ መግለፅ
እችላለሁ? በቃ ልለፈው:: ሁሉም ከሆነ በኋላ እሷ በሰላምና በእርካታ
ተሞልታ እንቀላፋች:: እኔ ግን ቀስ በቀስ ኃይሌን እሰባስቤ የሆነውንና
የተፈጠረብኝን ስሜት ወረቀት ላይ ማስፈር ያዝኩኝ፤ ያሰብኩትን ያህል
ባይሳካልኝም::

ይቺን ውብ ወጣት በድጋሚ እቅፌ ከማንቀላፋቴ በፊት ግን ለራሴ
የማቀርበውና መመለስም የሚገባኝ ጥቂት ጥያቄዎች አዕምሮዬ ውስጥ
ተከስተዋል::

'ጥሩ አፍቃሪ ነኝ ወይ?... ይሄን፣ እያሳሳቀ መጥቶ ጭልጥ አርጎ ይዞ
ሊወስደኝ የሚንደረደረውን ፍቅር ለመሸፈር ብቃቱና ዝግጁነቱ አለኝ
ወይ? .... ከዕድላዊት ጋር የነበረኝ የፍቅር ግንኙነት ትክክለኛ እንከኑ ምን
ነበር?... ለዕድላዊትስ በእርግጥም ጥሩ ፍቅረኛ ነበርኩኝ ወይ? ... እንዲህ
አደረገችኝ፤ ይሄን በደለችኝ ከማለትስ ውጪ መንሰዔው እኔስ ብሆን ብዬ
ራሴን መርምሬ አውቃለሁ?'

በዚህ ጉዳይ ውስጥ ራሴን ካልመረመርኩ ለአዲስ ፍቅር ዝግጁ
መሆን አለመሆኔን በምን አውቃለሁ? አዲስ ጎህ ከመቅደዱ በፊት ራሴን
መመርመር መቻል አለብኝ፤ አሮጌ ካባዬን አውልቄ በአዲስ ካባ እተካው
ዘንድ::



ብዙ ጊዜ 'ሰዎች ከፋትን አድርገውብኛል' ብለው ተቀይመው ያውቁ
እንደሆነ መጠየቅ አያሻኝም:: እኔ ራሴ ብዙ ጊዜ ሰዎችን በአድራጎታቸው
ተቀይሜ አውቃለሁ:: በተለይም ለዛሬው ጉዞ ያበቃችኝን ዕድላዊትን::
እስቲ ከፋኛ የተቀየምናቸውንና አሰቃይተውናል፣ ለሐዘን ዳርገውናል
ያልናቸውን ሰዎች እና የበደሉንን በደል መለስ ብለን እናጢናቸው::
በተለይም ራሳችንን በእነዚያ ሰዎች እግር ተከተን ጉዳዩን እንመርምር::
ዕድላዊት የፍቅር ሕይወቴን ብቻ ሳይሆን መላው ሕይወቴን ገሃነም
እንዳደረገችው አምን ነበር:: እስቲ ዛሬ ላይ ሆኜ፣ ራሴን በእርሷ ቦታ
አድርጌ ልመልከተው:: ለመሆኑ እኔ ሴት ብሆን ኖሮ ምን ዓይነት ፍቅረኛ
እንዲኖረኝ ነው የምመኘው?

የሚያፈቅረኝ፣ የሚያስብልኝ፣ በትንሹም በትልቁም የሚጨነቅልኝ ፣
የሚንከባከበኝ፣ ጉዳዮቼን እንደራሱ ጉዳይ የሚያይ፣ በሚያስደስቱ
መዝናኛ ቦታዎች ላይ ዘና እያደረገ ጭንቀቴንና ሐዘኔን የሚያስረሳኝ፣
በጨዋታው ዘና የሚያደርገኝ፣ ስራዬን የሚወድልኝና ለምናፍቀው ስኬት
የራሱን ሚና በሚገባ የሚጫወት፣ የሚያደንቀኝ፣ ጭቅጭቅ የማይወድ...
እኔ ሴት ብሆን ኖሮ የምመኘው እንዲህ ያለ ፍቅረኛ እንዲኖረኝ ነው::
እነዚህ ነጥቦች በበቂ ሁኔታ ራሴን በዕድላዊት ቦታ አድርጌ ለማየት
ይረዱኛል:: 'እንግዲህ ዕድላዊትስ እንዲህ ያለ ፍቅረኛ እንዲኖራት
የምትመኝ ከሆነ፤ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ሆኜላታለሁ ወይ?' የሚለው
ጥያቄ ወሳኝ ነው:: እስቲ እያንዳንዱን ነጥብ ሚዛናዊ ሆኜ ለመመለስ
ልሞክር::

አፈቅራታለሁ:: ለዚህ ምንም ጥርጥር የለውም:: በጣም አስብላታለሁ::
አጨነቅላታለሁ፤ ግን አብዛኛው ጭንቀቷ የሚመጣው፤ በተደጋጋሚ
እንዲህ አናድርግ ብዬ መከሬያት በእምቢተኝነት ሌላ መንገድ ተከትላ
በመሄዷና ለስህተት በመዳረጓ ሳቢያ ነው:: ይሄ እንደሚመጣ አስቀድሜ

Scanned with CamScanner

እነግራት ስለነበር በተደጋጋሚ እወቅሳታለሁ:: ወቀሳዬም ጭንቀቷን ላያቀል ነገር ያብስባታል::

እንከባከባታለሁ፣ ግን ሙሉ ለሙሉ ተንከባከቤያታለሁ ብዬ አላስብም:: አንድ ወንድ ፍቅረኛውን መንከባከብ ያለበትን ያህል እንዳልተንከባከብኳት አምናለሁ::

ጉዳዮቿ ጉዳዮቼ ነበሩ::

በሚያስደስቱ መዝናኛ ቦታዎች ላይ ዘና እያደረግኩ ጭንቀቷንና ሐዘኗን ለማስረሳት የማደርገው ጥረት እንኳ እምብዛም ነው ከማለትም ያንሳልና የለም ማለቱ ይቀለኛል::

በጨዋታም ብዙ ዘና ላደርጋት አልቻልኩም:: ሰዎችን በጨዋታ ዘና የማድረግ ተሰጥዖ ቢኖረኝም እሷ ላይ ግን አልሰራም:: ምናልባትም ጠነን ያሉ ብዙ ጉዳዮች በተደጋጋሚ ስለሚገጥሙን፣ እኔና እሷ አብረን ስንሆን ዘና የሚያደርግ ስሜት አይኖረን ይሆናል::

ስራዋን እወድላታለሁ፤ በስራዋም በጣም እግዛታለሁ:: ለስኬት እንድትበቃም የራሴን ሚና በሚገባ ተወጥቻለሁ:: ስኬቱንም አይተን ለማጣጣም በቅተናል:: እደንቃታለሁ፤ ለዚህ ምንም ጥርጥር የለውም:: ጭቅጭቅ አልወድም:: ሰላማዊና የተረጋጋ ሕይወትን መኖር ነው የምፈልገው:: ከዕድላዊት ጋር ግን ይሄንን ሰላማዊና የተረጋጋ ሕይወት ለመኖር አልታደልኩም:: ብዙ ጊዜ እንጨቃጨቃለን፣ እንኳረፋለን:: መንስኤው ደግሞ ብዙ ነው:: የሀሳቦቿ ብዛት እና የምትወስዳቸው አማራጮች ያናቁሩናል:: 'የእኔ ልፋት ምንም አይታያትም' እላለሁ:: የመጨረሻውን ዓመትማ ከእነአካቴው በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም ሳልናገራት ሁሉንም በዝምታ ማለፍ ጀመርኩ:: የትም ትሂድ፣ ከማንም ጋር ትሂድ፣ ምንም ታድርግ በዝምታ መቀበል:: በዝምታ እቅፎ መተኛት:: ጭልጥ ባለ እንቅልፍ ውስጥ ሆና ስታንኮራፋ እየሰማሁ በሀሳብ መብሰልሰል ብቻ ሆነ



ስራዬ:: ቀን ቀን ደግሞ ሕልሞቿን ዕውን ለማድረግ እየተፍጨረጨርኩ፣ 'ምናልባትም አንድ ቀን ሁሉንም ትታ ልቧን ወደ እኔ ትመልስ ይሆናል:: ' ብዬ የተሰፋ ካባዬን እደርታለሁ::

እስቲ እንግዲህ ምን ያህል አዎንታዊና ምን ያህል አሉታዊ ምላሽ ሰጥቻለሁ? ምን ያህል 'ግን' የሚል አፍራሽና ማብራሪያ የሚያስከትል ቃል ተጠቅሜያለሁ? በ'ግን' የታጀቡ ማብራሪያዎች 'አዎንታዊ' ወይም 'አሉታዊ' ምላሾችን የሚያጣምሙ የስሜት አሊያም የምክንያት ድሪቶዎች ናቸው::

ከአስር መስፈርቶች ውስጥ አምስቱን አሟልቻለሁ:: ሁለት ሙሉ ለሙሉ ያላሟላኋቸው መስፈርቶች አግኝቻለሁ:: ማድረጌን ገልጬ 'ግን' የሚል አፍራሽ ቃል የተጠቀምኩባቸው መስፈርቶች ደግሞ ሦስት ሆነዋል፤ በማድረግና ባለማድረግ መካከል ያንሳፈፉኝ::

እንግዲህ ከሁለቱ አሉታዊ መልሶቼ ጋር እነዚህ ሦስት የ'ግን' ጋጋታዎች ተጨምረው ፍቅራችንን መቃብር አውርደውታል:: በዕድላዊት ዓይን ስታይ ግማሽ ለግማሽ መስፈርቷን የማላሟላ ሆኜም ይሆናል:: ስለዚህ በግማሽ ፍላጎቷ ሳቢያ ሳታጠብቅ ይዛኝ ለቀረው ግማሽ ፍላጎቷ ማሟያ ደግሞ ዙሪያዋ ከተኮለኮሉት ውስጥ ያሻትን ያህል እንድትለቅም አድርጓታል:: ምክንያት ቢባል እኔ ሙሉ ልሆንላት ስላልቻልኩ::

እናም ዛሬ እነዚህን ግማሽ ጉድለቶቼን አርሜ አዲሱን ፍቅር ለመንከባከብ ከአሁኗ ደቂቃ ጀምሮ እተጋለሁ:: ራስን በሌላው ሰው ቦታ ላይ አድርጎ ማየት ጉድለትን ማረሚያ ሚዛን ነውና::

Scanned with CamScanner

## - 11 -

ዛሬ በዕንቁጣጣሽ ጋባዥነት የሰንበትን ቅዳሴ አስቀድሰን፣ ትንሽም መንፈሳዊ ትምህርት ወስደን ወጣን፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለቀብር ካልሆነ በቀር እንደዛሬው ለፀሎት ወይም ለሃይማኖታዊ ትምህርት ከገባሁ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ስወጣ ትልቅ ሰላምና ንቃት ይገኔ ነው የወጣሁት፡፡ ያ ሰላምና ንቃት እስከ አሁንም ውስጤ አለ፡፡ በቅዳሴ ስነ-ስርዓቱ ላይ እንድገኝ ስለጋበዘችኝ ዕንቁጣጣሽን አመሰገንኳት፡፡

ያገኘሁትን ሰላም እንደወረደ ተቀበልኩት፡፡ ያገኘሁት ንቃት ግን ብዙ ጥያቄዎችን አዝሎ መልስ አምጣ እያለ አፋጠጠኝ፡፡ ከቅዳሴ በኋላ አንድ ካህን ትምህርት ሲሰጡ ተከታተልን፡፡ ትምህርቱ ስለ አብርሃምና ስለካህኑ መልከ ዴዴቅ ነበር፡፡ ይሄ ትምህርት ለእኔ አዲሴ አይደለም፡፡ ሺህ ጊዜ ደጋግሜ መፅሐፍ ቅዱስ ላይ ያነበብኩት ነው፡፡

ቄሱ ታሪኩን ሲያተምሩ ግን በጆሮዬ ብቻ አይደለም ያደመጥኳቸው፡፡ አራት ሺህ ዘመናት ወደ ኋላ ተጉዤ ቦታው ላይ ያለሁ ያህል ታሪኩና ሰዎቹ በዓይነ ሕሊናዬ እየታዩኝ ጭምር ነው፡፡ እንዲህ ያለ ነገር ከዚህ በፊት ገጥሞኝ ያለማወቁ ሁኔታውን አስገራሚ ቢያደርግብኝም ይበልጥ ያስገረመኝ ግን በብዙ አጃቢዎች ታጅቦ መጥቶ የእስራኤሎች አባት የሆነውን አብርሃምን የሚባርከው ካህኑ መልከ ጼዴቅ የከህነት ልብስ ከመልበሱ በቀር ያን የእኔን መምህር ዮቶርን መምሰሉ ነው፡፡



ነገሩ መች በዚህ አበቃ? የቁም ህልሜ ሌላ ዘመን ላይ ወስዶ ሙሴንና ፊት ለፊቱ ቆሞ መስዋዕት የሚያቃጥለውን፣ ኢትዮጵያዊውን ካህን ዮቶርን አስጎበኘኝ፡፡ ይሄኛውም የእኔን ኮብላይ ካህን ይመስላል፡፡ የሁለቱ ዮቶሮች የሦስት ሺህ ዘመንን የልዩነት ግንብ ያፈረሰ አንድነት አስደነቀኝ፡፡

ከሄድኩበት ሰመመን ስነቃ ሁሉም ነገር ተደናበረብኝ፡፡ ያለሁበትን ለማወቅ ዙሪያዬን ማተርኩኝ፡፡ ከደቂቃዎች በፊት የነበርኩበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነኝ፡፡

'ምንድነው የሆንኩት?.. በቁሜ እየቃዠሁ ነው ወይንስ?...'

የእኔ ኮብላይ ካህን ሁሌም አብሮኝ እንዳለ ነው የማስበው፡፡ አንዳንዴም በሕልሜ እየዋለሁ፡፡ ዛሬ ግን ህልም ይሁን ሌላ በማላውቀው ነገር ውስጥና በማልጠብቀው ታሪክ ውስጥ ቆሞ አየሁት፡፡

መልከ ጼዴቅን፣ የሙሴ አማች ካህኑ ዮቶርንና የእኔን ኮብላይ ካህን ያቆራኛቸው ምንድን ነው?... ምናልባት ካህንነታቸው ኮብላዩን ካህን አስታውሶኝ ይሆናል ብዬ አሰብኩ፡፡ ግን ደግሞ ዛሬ ብዙ ካህናት አይቻለሁ፡፡ ይሄንን ትምህርት የሰጡን አባም ካህን ናቸው፡፡ በየትኛውም ካህን እግር ኮብላዩን ካህን አልሳልኩም፡፡ ምናልባት ከሁለት ወር በፊት ስለማመንዘር ስናወራ 'የአብርሃምን፣ የሣራንና የአጋርን ታሪክ መርምር' ስላለኝ ይሆን ከአብርሃም ጋር በቆመው በካህኑ መልከ ጼዴቅ ውስጥ እሱን ማየቴ?

ምንም ይሁን ምን ግን ኮብላዩ ካህን አንድ አዲስ ነገር ነግሮኛል፡፡ ምን እንደነገረኝ? ያላደመጥኩት እኔ ነኝ፤ መልዕክቱን ፈልፍዬ መረዳት ያለብኝም እኔው ነኝ፡፡ ዛሬ ያገኘሁት ንቃት ይሄ ነው፡፡ ይሄ መነቃቃት ውስጤ ጥያቄዎችን ጭሮብኛል፡፡ ጥያቄዎቹም የት እንደሚያደርሱኝ አላውቅም፡፡ የማውቀው መመለስ እንዳለባቸውና መልስ ለማግኘት መመርመር ያለብኝን ሁሉ ለመመርመር ፍላጎቱ እንዳለኝ ነው፡፡

Scanned with CamScanner

ከዕንቁጣጣሽ ጋር ቁርስ እየበላን ሳለ “የሆነ ነገር እያሰብክ ነው ያለኸው:: ምንድነው?” ብላ ጠየቀችኝ::

“አዎ፣ አንድ ነገር እያሰብኩ ነው:: ቅድም ቤተክርስቲያን ውስጥ እያለን አንድ ሀሳብ መጥቶልኝ ነው:: ሌላ ጊዜ በሰፊው እነግርሻለሁ::” አልኳት::

“ስላንተ ካልነገርከኝ ብዙ ነገሮች ጋር እሱም ከተጨመረበት ምስጢር ያደረግክብኝ ታሪክህ ሊበዛ ነው:: ቢያንስ ጥቂቱን እኔ ልግለፅልህና የምሥጢርህን መጠን ልቀንሰው::” አለችኝ እየፈገገች:: ማለት የፈለገችው ስላልገባኝ በትኩረት ተመለከትኳት::

ፈገግታዋ ውስጥ የተደበቀ ተንኮል ያየሁ መሰለኝ::

“ግራ የተጋባህ ትመስላለህ”

“አንቺ ደግሞ የሆነ ተንኮል ያሰብሽ ትመስያለሽ::” እንቆቅልሿን ለመፍታት አዕምሮዬ በስራ ተጠመደ::

“ተንኮል አስቤ ሳይሆን ካለፈው ሕይወትህ ጥቂት ምስጢሮችን ተሸከሜ ነው የመጣሁት:: ትናንትና አንድ ጓደኛዬ ካንተ ጋር አይታኝ ነበር:: መጽሔት ትባላለች:: ካንተ ከተለያየን በኋላ አገኘችኝና ስላንተ ብዙ ነገር አወራችኝ:: መጽሔት ለምትነግረኝ ታሪክ እንግዳ መሆኔን ስትረዳ በጣም ነበር የተገረመችው:: ስልህ... እንግዳ የሆንኩት ለታሪኩ አይደለም:: ያ ታሪክ ያንተ መሆኑን ነው አላውቅ የነበረው:: ፍቅረኛዬ ዝነኛ መሆኑን ከሀገሩ ሁሉ ዘግይቼ ፣ እሷ ከነገረችኝ በኋላ ነው የተረዳሁት::” አለችኝ ፈገግታዋ ሳይጠፋና ይሄን ሳልነግራት በመቅረቴ መገረሟ እየታየባት::

“ያ እንኳ የዛሬውን እኔን ብዙም አይገልፅም:: ግን... ለዛሬ ያቀበለኝ ትናንት ነውና መሰረቴ ነው ማለት ይቻላል:: ዛሬ ማን እንደሆንኩ ታውቂያለሽ፤ ከትናንትናዬም ጥቂት ዘግነሻል::... ነው ወይንስ ይበልጥ ማፈስ ትፈልጊያለሽ?” አልኳት በፈገግታ::



“አንተ እንዳውቅ ከፈለግክ ብቻ አዎ”

“ሁሉንም ነገር አንድ ቀን መናዘዜ አይቀርም ነበር:: በአጋጣሚ ቀደምሽኝ:: ስለዚህ ያ አንድ ቀን ዛሬ እንዲሆን ተፈቅዷል ማለት ነው::”

ታሪኬን በአጭሩም በረጅሙም ሳይባል ተረኩላት:: ያደመጠችኝ በመደነቅ ነበር::

“ይገርማል!...ሳንተዋወቅምበፊትበጥቂቱአውቅህነበርማለትእኮነው:: እንዴት ያለ አጋጣሚ ነው::... እና ከኮብላዩ ካህን ጋር በድጋሚ ሳትገናኙ ቀራችሁ?”

“ለእኔ የሚሰማኝ ሁሌም አብሮኝ እንዳለ ነው:: በእርግጥ በአካል አላገኘሁትም:: ግን በሁሉም ነገሮች ውስጥ አየዋለሁ፤ እሰማዋለሁ:: ብቻ የእሱ የሆኑ አሻራዎቹን በተለያየ አጋጣሚ አገኛለሁ:: የዛሬው ግን የተለየ ሆነብኝ::”

“ዛሬ ማለት?...” ስለ ኮብላዩ ካህን ብዙ ለማወቅ መጓጓቷ ገባኝ::

“ለካ አልነገርኩሽም:: ቅድም ‘የሆነ ነገር እያሰብክ ነው’ ያልሽኝ ጊዜ ስለዛሬው ገጠመኜ እያሰብኩ ነበር::” አልኩና የቤተ ክርስቲያኑን ገጠመኜን በሙሉ አወራኋት::

“እና ምን ብለህ ደመደምክ?” አለችኝ ተደንቃ:: እንዲህ ስትደነቅ አይቻት አላውቅም::

“ይሄን ኮብላይ ካህን የሳሌም ንጉሥ የሆነውን ካህኑ መልከ ጼዴቅን እና የምድያሙን ዮቶርን የሚያስተሳስራቸው አንድ ነገር እንዳለ ተገንዝቤያለሁ:: ያ ነገር ምን እንደሆነ ለመመርመር ነው የወሰንኩት:: ስንሰነባበት ‘ላገኝህ ስፈልግ የትና እንዴት እንደማገኝህ አውቃለሁና ያጣኛል ብለህ አትጨነቅ’ ነበር ያለኝ:: ሳስበው፣ ዛሬ በመረጠው ቦታና ሁኔታ አግኝቶኛል:: በመጀመሪያ ወደኔ ሲመጣም የልቤን ብርሃን ለመግለጥ እንጂ ሌላ ዓለማ አልነበረውም:: ዛሬም ሆነ ነገ ወደ እኔ

የሚመጣው የብርሃን መንገድን ሊመራኝ እንጂ እንደ ስጋ ዘመድ 'እንዴት ነህ?'... ምናምን እያለ ሊጠይቀኝ አይደለም:: ዓላማው የነፍሴን ጥሪ እንድከተል የብርሃን መንገድ በመሆን ሊመራኝ እስከሆነ ድረስ የማየውም ሆነ የማደምጠው በነፍሴ ውስጥ ሊሆን ይችላል:: የትና እንዴት እንደሚያገኘኝ እሱ ያውቃል:: በጠቆመኝ መንገድ እየተከተልኩ ላገኘው ይገባል:: ይሄ ነው እንግዲህ መደምደሚያዬ::"

"በጣም የሚደንቅ ታሪክ ነው:: መጨረሻውን ለማወቅ ጓጉቻለሁ:: ምነው አንተን ባረገኝ!" እጁን ልካ እጄን ያዘችው::

"እኔንምኮ ሆነሻል:: እኔም አንቺን ሆኛለሁ:: ፍቅር ነፍስን ከነፍስ የማቆራኘት ኃይልና ስልጣን እንዳለው አታውቂም? የእኔና ያንቺ ነፍስም በፍቅር ተቆራኝቷል:: ስለዚህ ቀድሞውንም እኔን ሆነሻልና 'ምነው አንተን ባረገኝ' ማለት አይገባሽም::"

"ጥሩ ገለፃ ነው:: ስለዚህ... ነፍሳችንን በአንድ ያቆራኘው ፍቅር አካላችንንም አንድ ያደርግ ዘንድ ፈጥነን ወደቤታችን እንሂድ::" አለችና ሳቀች::

"በይ ተነሽ::" ሂሳባችንን ከፍለን ወደ እኔ ቤት በረርን::



# - 12 -

ሊዲያን ያየ ሰው የቱንም ያህል ትሁት ነኝ ብሎ ቢያስብ እንኳ ደጋግሞ ራሱን ይታዘባል:: ምክንያት ቢባል፣ እሷ ትሁት ሳይሆን ራሱን ትህትናን ናትና::ከአማን ጋር ከተዋወቁ ዓመት ከመንፈቅ፣ ከተጋቡ ደግሞ ዘጠኝ ወራት አካባቢ ሆኗቸዋል:: ሊዲያን ፀሐይ ናት ማለት እችላለሁ. ሙቀትንና ብርሃንን መፍጠር ትችልበታለችና:: ከእሷም አልፎ ሌሎችን ታሞቃለች፤ ታበራለች:: ብዙዎቻችን ደስታን ከውጫዊው አካባቢያችን እንጠብቃለን፤ እርሷ ግን ደስታን ራሷ መፍጠር ታውቅበታለች::

ሊዲያም ሆነች አማን የወንድምነትንና የጓደኝነትን ቦታ ሰጥተውኛልና ብዙ ጉዳያቸውን ያወሩኛል:: የተገናኙት በጓደኞቻቸው ኒካህ ላይ ነበር:: አማን ገና እንዳያት ነበር የደነገጠውና የተመኛት:: የዚያኑ እለት፣ በበነጋው ተገናኝተው ለመነጋገር ቀጠሮ ያዙ:: በቀጠሯቸው ዕለት ግን የማያገናኝ እንከን ተፈጠረ::

እንደ ትናንት ድንገት አይቷት ልቡን የሰረቀችውን ቆንጆ አግኝቶ እጁ ሊከታት በጓጓበት በቀጠሯቸው ዕለት ድንገተኛ የቤተሰብ ጉዳይ ገጠመውና ወዲህ ወዲያ ሲዋከብ ቆየ:: በመጨረሻ ሰዓቱን ተመለከተ:: ለቀጠሮው የቀረው አሥራ አምስት ደቂቃ መሆኑን ሲገነዘብ በድንጋጤ ከእናቱ ቤት እየተጣደፈ ወጣ:: ግዙፍ ጥላ የተከናነበ ከፉ ሰማይ፣ የሚያስቀይም እልቃሻ ቀን ተቀበለው:: ሊዲያ ሐምሌን የምታስረሳ ውብ ናት:: ሐምሌን እቋርጣ የምታልፍ ተወርዋሪ ኮከብ፣ የመስቀል አበባንም

Scanned with CamScanner

ትመስላለችና ፊቷ ለመቆም ጊዜውን ቀድሞ መስከረምን መስሏል:: ገንጥ ያለች ፀደይ ሆኗል ሽከ ብሎ:: ጥድፊያውም እንደ ፀደይ ቀናት ነው::

በጥድፊያ የመኪናውን በር ከፍቶ ገባና ሞተሩን ቀሰቀሰ::... ገዞም!

"ምን?!" አለ ደንግጦ:: በድጋሚ ሞከራት:: የሞተር ድምፅ የለም::

"የአምላክ ያለህ!" ብሎ የኮፈኑን ቁልፍ ሳበና ተጣድፎ ወርዶ ኮፈኑን ከፈተ:: የአውቀቱን ያህል ነካካት:: ተመልሶ ገባና በድጋሚ ሞከራት:: የሞትን ያህል የሚከብድ ዝምታ::

"ኧረ እባክሽ!".. ሰዓቱን አየ:: ለቀጠሮው ስምንት ደቂቃ ጉዳይ:: በፍጥነት ከመኪናው ወረደና በሩጫ ጎዳናው ላይ ደረሰ::

አንድ ትንሽ ታክሲ መጣች:: ጋቢናዋ ባዶ ነው::

"አልሃምዱሊላኽ!" ብሎ አጉተመተመና እንድትቆምለት እጁን አውለበለበ:: ታክሲዋ አለፍ ብላ ቆመችለት:: ተንደረደረ:: ከምድር ይውጣ፣ ከሰማይ ይውረድ ያላየው ሰው የጋቢናዋን በር ከፍቶ ተደረገመባት:: ሹፌሩ አገዞናለሁ የሚል የእጅ ምልከት አሳየውና ታክሲዋን ይዟት ከነፈ:: እማን ተናደደ:: ሰዓቱን ተመለከተ::

ሌላ ታክሲ መጣ፤ በመማፀን እጁን አርገበገበ:: ትቶት መንገዱን ቀጠለ:: በሁለቱም አቅጣጫ ዓይኑን እንከራቶ ማተረ:: አንድ ባዶ ታክሲ መጣች::

"አልሃምዱሊላኽ!"አለበድጋሚ::ታክሲዋአሁንምአለፍብላውቆመች:: ወደ ታክሲዋ ሩጫውን እንደጀመረ በፍጥነት የምትሽከረከር የቤት መኪና መንገዱ ያቆረውን ቆሻሻ ውሃ ከላይ እስከታች አከናንባው ከነፈች በድንጋጤ ቀጥ ብሎ ቆመና አቀርቅሮ ራሱን ተመለከተ:: ከዚያም በረጅሙ ተንፍሶ "ሐምሌን አስመሰለችኝ::" ብሎ ቅስሙ በተሰበረ ድምፅ አጉተመተመ::



"ኧረ እንዲያውም ሐምሌ ያምራል!" ቀና ብሎ ታክሲውን ተመለከተ፤ መልሶ ልብሱን አየ::

የታክሲውን ሹፌር እንዲሄድ በምልክት ነገረውና የፊቱን ቆሻሻ በልብሱ ጠረገ:: ከዚያም ወደ ኋላው ዞሮ ወደ እናቱ ቤት አንገቱን ደፍቶ መንገድ ቀጠለ::

"ምን ዓይነት የተረገመ ቅዱስ ቀን ነው?" እያለ::

ዱዳ መኪናውን ተደግፎ ተንቀሳቃሽ ስልኩን ከኪሱ አወጣና ላሸበረቀላት፣ ለተጣደፈላት ውብ ደወለ:: አነሳችው::

"ሊዲ የእኔ ቆንጆ፤ እንዴት ነሽልኝ?" አላት ቅስም በማያውቀው ድምፅ::

"ምነው?" አለችው::

"ቀጠሮዬን በአካል ባላከብርም በድምፅ በሰዓቱ ልገኝ ብዬ ደወልኩልሽ::"

"ምነው?... ቀረህ እንዴ?"

"የተረገመ ቅዱስ ቀን ሆነብኝ::"

"የተረገመ ቅዱስ ቀን?! ለምን አልክ?" የእሷም ድምፅ አነከሰ::

"ምን እንደገጠመኝ ብነግርሽ ትገረሚያለሽ::" የገጠመውን ሁሉ ዘርዝሮ ነገራት:: "አይገርምም?... ፊቴን ተይውና ለቀጠሯችን ሙሽራ ያስመሰለኝ ልብስ የጋራዥ ቱታ መስሎ፤ ሙት መኪናዬን በሐዘን ተደግፌ ነው እያወራሁሽ ያለሁት::"

"የሚገርም አጋጣሚ ነው::" አለችው ሊዲያ::

"በጣም!.. አንቺን በድጋሚ የማይባት ቀን በመሆኑ ቅዱስ ቀን ብዬው ነበር:: ግን የተረገመ ቅዱስ ቀን ሆነብኝ:: ይቅርታ ይደረግልኛል አይደል?"

"ባትጠይቅም ይቅርታ ተደርጎልሃል::" አለችው በረጋ እንደበቷ::

"ላይሽ በጣም ጓጉቼ ነበር:: ዛሬን እንዳልምሽ እንጂ እንዳይሽ አልቻልኩም ማለት ነው:: አላሳዝንም?"

"አትዘን፡፡ የዛሬ ቀጠሯችንን አላህ አልፈቀደው ሆኖ ነው፡፡" አለችው በሚያፅናና እና በሚያነቃ ድምፅ፡፡

"ነገ መገናኘት እንችላለን ሊዲ?"

"ኢንሻ አላህ"

"በቃ ነገ በምሣ ሰዓት ተገናኝተን ምሳ አብረን እንብላ፡፡"

"ኢንሻ አላህ፡፡ ነገ ደውልልኝና ሰዓትና ቦታ እንቀጣጠራለን፡፡ ለአሁን፣ ልብስህ የጋራዥ ቱታ መምሰሉ ካልቀረ መኪናህን ፈታትሸና ወደ ቤት ግባ፡፡" ሳቅ አለች፡፡ እሱም ሳቅ አለ፡፡

በዚህ መልኩ ነበር የአማንና የሊዲያ የፍቅር ሕይወት የተጀመረው፡፡ ሊጋቡ ከወሰኑም በኋላ ከሊዲያ ቤተሰቦች ተስፋ አስቆራጭ ተቃውሞ ገጥሟቸዋል፡፡ ሊዲያን የተከበረና ባለፀጋ ነው ላሉት ሰው ሊድሯት ተስማምተው ስለነበር፤ የአማንን የጋብቻ ጥያቄ 'የማይደረግ!' ብለው መለሱት፡፡ ሊዲያ ግን ግልፅ አቋም ወሰደች፡፡ ወላጆቿን በቤተ ዘመድ ደጋግማ ካስጠየቀች በኋላ፣ ሊሰሟት ስላልፈቀዱ በራሷ ውሳኔ ከአማን ጋር ኒካህ አሰሩና አብረው መኖር ጀመሩ፡፡ ይሄ በሆነ በወሩ ግን ወላጆቿ የግዳቸውን ጋብቻቸውን ተቀበሉና ሰርግ ለመደገስ በቁ፡፡

የእኔ ሕይወት አሁን በእርጋታ መፍሰስ ጀምሯል፡፡ ፍቅር፣ ሰላምና ደስታ አለኝ፡፡ በእያንዳንዱ አርምጃዬ እርካታን እያጣጣምኳት ነው፡፡ የረጋ በሚመስለው የአማንና የሊዲያ ሕይወት ውስጥ ግን ሰሞኑን መጠነኛ መናወጥ እየተመለከትኩ ነው፡፡ ምክንያቱን ይበልጥ ለመረዳት ወደ ውስጥ በዘለቅኩ ቁጥር ከሚያስገርምና ለፍርድ ከቸገረኝ ጉዳይ ጋር ፊት ለፊት ተላተምኩ፡፡ አጀማመሩ እንዲህ ነበር....



# - 13 -

"እጣው አንድ ከሆነ፡- አንዱ ያጣውን ነው ሌላው የሚያገኘው፤ ካልተጋሩት በቀር፡፡"

አንድ ነፋሻማ የጥር አመሻሽ ላይ ነው... በጫካው የወፎች ዜማ ታጅቦ፣ በጅረቱ የማያቋርጥ ፍሰት ላይ እየተንሳፈፈ እና በጫካው ነፍሳት ፉጨት እያጌጠ የምታዜመው ዜማ ይፈስሳል፡፡ የምትገርፈው የጊታር ክር ንዝረት ልብ ጋር ይደርሳል፡፡ ሲጳራ ተመስጣ ታንጎራጉራለች፡፡ እሱ አፉን ከፍቶ ያዳምጣታል፡፡

ዘፈኗን ከጨረሰች በኋላም ከሰሰመኗ አልተመለሰችም፡፡ እሱም ዝምታዋን እያዳመጠ ይመስል አፉን ከፍቶ መመልከቱን አላቋረጠም፡፡ ሲጳራ በረጅሙ ተነፈሰችና ፊቷን ወደ አማን መለሰች፡፡

"እንዴት ነኝ?" አለችው በሙዚቃ ድምፅ፡፡

"አ!... በጣም ትመስጫለሽ! ሙዚቀኛ ያለመሆንሽ ግን ገርሞኛል፡፡"

"ሙዚቃን ለራሴ ስጫወተው ነው የሚመስጠኝ፤ ስራዬ ላደርገው ፍላጎት የለኝም፡፡" ብላ የተጫወተችበትን ጊታር ከጎኗ አኖረችው፡፡

"እርግጠኛ ነኝ... ሕይወትን በሙዚቃ ኃይል እያስዋብሽና እያጣፈጥሽት ትኖሪያታለሽ፡፡" አላት በአድናቆት ተሞልቶ፡፡

ሲጳራ ዝም አለች፡፡ የውስጧ ታላቅ ኡኡታ ተቀስቅሶ ድብልቅልቋን አወጣው፡፡ ጆሮዋን እንኳን ደፍና የማትሸሸው ጩኸት፣ ተደብቃ የማታመልጠው እሪታ ተረከባት፡፡

"ምነው በሀሳብ ነጎድሽ?" አለና ከጩኸቱ ገላገላት::
"እ... አዎ:: አንዳንዴ ሳላስበው ርቄ እሄዳለሁ::... 'ሕይወትን በሙዚቃ
ኃይል እያጣፈጥሻት ትኖሪያታለሽ' ነበር ያልከኝ፣ አይደል?"
"አዎ:: ልክ አይደለሁም እንዴ?"
"ቢሆንማ ምንኛ በታደልኩ ነበር:: ሙዚቃ ኃይል አለው:: ልክ ነህ፤
ግን ሁሉንም አያሸንፍም:: ብዙም የተዋበ፣ ብዙም የሚጣፍጥ ነገር
ቢገጥምህም እንዳያምርህና እንዳይጣፍጥህ የሚያደርግ ሌላ ኃይል
ውስጥህ ካለ፤ መዓዛው ለአፍንጫህ፣ ቃናውም ለጆሮህ አይደርስም::
ዘበዘብኩ መሰለኝ?" አለችና ፈገገች::
"በፍፁም:: በጥምና እያዳመጥኩሽ ነው:: ግን.. ከአንደበትሽ የሰማሁት
ነገርና ካወቅኩሽ ጀምሮ አንቺ ላይ የማየው ነገር አልገጣጠም አለኝ::"
"ልክ ነህ:: ላዩን እንጂ ውስጤን እንዴት ልታየው ትችላለህ?..
ለማንኛውም አሁን ሌላ ጨዋታ እንጫወት:: አይሻልም?"
"የሚሻል አይመስለኝም:: እያወራሽ ያለሽው ነገር 'ሰርፕራይዝ'
አድርጎኛል:: በእርግጥ የግል ምሥጢርሽን ንገሪኝ የማለት መብት
እንደሌለኝ አውቃለሁ:: ግን.. የላይ የላዩን ለመጫወት ብዙ አጋጣሚዎች
አሉን:: በበኩሌ ደስተኛ ነሽ ብዬ አስብ ነበር፤ መሳሳቴን ነገርሽኝ::
ፈቃደኛ ከሆንሽ ስለዚህ ብናወራ እመርጣለሁ::"
ሲጳራ በጥምና አስተዋለችው:: የሁለቱም ዓይኖች ለአፍታ ተፋጠጡ::
እሱ ቀድሞ ዓይኖቹን አሸሸ::
"ከብዙ ጊዜ በኋላ በጣም የቀረብኩት ሰው አንተን ብቻ ነው::
ብዙ ነገርህ ከረጅም ዘመን ጀምሮ የማውቅህ ያህል እንዲሰማኝ
ያደርገኛል:: ይሄ ሳምንት ከሌሎች ብዙ ሳምንቶች ይልቅ ለእኔ ልዩ
እንደሆነ ነግሬሃለሁ?... ከረጅም ጊዜ በኋላ ደስ የሚልና የሚያዝናና
ስሜት የተሰማኝ በዚህ ሳምንት ነው:: ምክንያቱ ደግሞ አንተ ነህ::



ካንተ ጋር ስጫወት ብዙ ነገሮችን እረሳለሁ፤ ቅልል ይለኛል:: ምን ነበር
ከዓመታት በፊት ተገናኝተን በነበር!" ዓይኖቿን ሩቅ ልካ ዝም አለች::
በዝምታ ጠበቃት::
"ከአንድ ከምትወደውና እምነትህን ከጣልከበት ሥፍራ የምትገለልበት
ጊዜ አጭር እንደሆነ ቢነገርህ ምን የምትሆን ይመስልሃል?"
"በጣም እንደማዝን አልጠራጠርም::" ብሎ መለሰላት::
"ከምትገምተው በላይ ታዝናለህ:: ከዚያም በላይ የከፉ እንግዳ
ስሜቶችን ታስተናግዳለህ:: ወደ ሀገሬ ለመምጣት ያበቃኝ ዋንኛው
ምክንያት ካንሰር እንዳለብኝ መስማቴ ነው::"
"ካንሰር?!" ከው አለ::
"ያስደነግጣል አይደል?... እንግዲህ ይሄ መርዶ ሲነገረኝ እንዴት
እንደደነገጥኩ ገምት:: ይበልጥ ያስደነገጠኝ ግን እዚህች ምድር ላይ
ለመኖር የቀረኝ ከሁለት ዓመት ያነሰ ጊዜ መሆኑን ሲነግሩኝ ነው::...
ሕይወቴን ውብና ጣፋጭ ላደርጋት ለምን እንደማልችል አሁን ገባህ?"
እንባ ከዓይኖቿ እየተንከባለለ ወረደ:: ድንጋጤና ሐዘን የተደባለቀበት
ስሜት አንደበቱን ለጉሞ ጭጭ አደረገው::
"በጣም አዝናለሁ ሲጳራ::" ሌላ ምንም ማለት አልቻለም::
ድምጿን ሳታወጣ እያነባች አቀረቀረች:: አቀፈና ደረቱ ላይ ለጠፋት::
"አዝናለሁ::" አለ በደከመ ድምፅ:: "ይሄን ከሰማሽ ምን ያህል ጊዜ
ሆነሽ?"
ሲጳራ ዕምባዋን ጠራርጋ፣ ስሜቷን ለመቆጣጠር ሞከረችና "ዘጠኝ
ወር አካባቢ ሆኖኛል:: ምናልባትም ከዚህች ዓለም ጋር ያለኝ ኮንትራት
የዓመት ዕድሜ ቢቀረው ነው:: ይሄን የሰማሁ ዕለት ምነው ሞት መጥቶ
አሁኑ በወሰደኝ ብዬ ተመኝቼ ነበር:: የምትሞትበትን ቀን እያሰብክ
መኖር እንኳን ለሁለት ዓመት ለአንድ ቀን እንኳ እንዴት እንደሚከብድ

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

እስቲ አስበው፡፡ ከሆስፒታሉ እንደወጣሁ የሚያፅናናኝ ሰው አስፈለገኝ፤ ሰው ናፈቀኝ፡፡ ከፍቅረኛዬ ከቤን ሌላ ማንም ጎኔ አልነበረም፡፡ ግን ምን ዋጋ አለው? ይሄ በሆነ በወሩ በጣም ሐዘን ተሰማኝና ብቻዬን መሆን ሲያስፈራኝ ጊዜ ለቤን ደወልኩለት፡፡ ፍራቻዬን እቅፉ ስር ልደበቀው ነበር የፈለግኩት፡፡ ስልኩ ዝግ ሆነብኝ፡፡ ሌላም ሰው የለኝና ወደ ቤቱ ሄድኩኝ፡፡ ባይኖር እንኳ እዚያው ትካዜዬን እያስታመምኩ እጠብቀዋለሁ ብዬ ከፍቼ ገባሁ፡፡ መኝታ ቤቱ ውስጥ ፍቅረኛዬ ቤን ከሌላ ሴት ጋር ተኝቶ አገኘሁት፡፡ ምድርና ሰማዩ ተገለባብጦብኝ ሮጬ ወጣሁ፡፡ ከአራት ወር በኋላም ጓደኞቼንና በቅርብ የማውቃቸውን በጎ አድራጊዎች አስተባብሬ አሁን እየሰራሁ ያለሁበትን የሕፃናት በጎ አድራጎት ድርጅት ለመመስረትና የቀረኝን አጭር ዕድሜም ሀገሬ ላይ ለማሳለፍ ወስኜ ወዲህ መጣሁ፡፡ ... እንግዲህ አንተ የማታውቃት ሲጻራ ይህቺን ትመስላለች፡፡" አለችና የግዷን እየፈገገች ከእቅፉ ወጣች፡፡

አማን በመገረም አንገቱን ነቀነቀና "በጣም ጠንካራ ሰው ነሽ፡፡ የምሬን ነው፡፡" አላት፡፡

"አንዳንዴ እኔም እንደዚህ እላለሁ፡፡... ይሄን ቦታ አረጀንበት እኮ፤ አንሄድም?"

"የት እንድንሄድ ፈለግሽ?"

"መጀመሪያ ወደ ቤት እንመለስና ከዚያ እንወስናለን፡፡" እየተጫወቱ ቤቷ ደረሱ፡፡

"ዛሬ የማከብረው በዓል አለብኝ፡፡ እንዲያውም የሐዘን ወሬ አውርቼ ስላሳዘንኩህ የበዓሌ ተካፋይ አድርጌ ልካስህ፡፡" አለችው ቀድሞ በሚያውቀው ፈገግታ ሆና፡፡

"የምን በዓል ነው?"



"ና ግባና እነግርሃለሁ፡፡" ከፍታ ገባች፤ ተከተላት፡፡ ጠረጴዛዋ መሃል ያልተለኮሰ ሻማ ተቀምጧል፡፡

"የዛሬዋ ቀን ደግሞ ከሞት አደጋ የተረፍኩባት ናት፡፡ የካንሰሩን መርዶ ከሰማሁ በኋላ ምን ነበር በዚያው በወሰደኝ ብዬ ስለተመኘሁ ከአደጋው መትረፌን እጠላው ጀምሬ ነበር፡፡ በዚህ የበጎ አድራጎት ስራ ላይ መንቀሳቀስ ከጀመርኩ ወዲህ ግን ቢያንስ ይቺን ለማድረግ እንኳንም በሕይወት ቆየሁ ብዬ በየወሩ ሻማ ለኩሼ አስበዋለሁ፡፡ እናም ዛሬ፣ በሻማ ብቻ ሳይሆን በግብዣም ጭምር ካንተ ጋር ባከብረውስ ብዬ አሰብኩ፡፡ ምን ይመስልሃል?"

"ደስ ይለኛል፡፡ ግን ስለአደጋው አልነገርሽኝም እኮ፡፡"

"የዛሬ አሥር ወር ኒውዮርክ ውስጥ የመኪና አደጋ ገጥሞኝ ነበር፡፡ የመኪናውን ፍጥነትና የእኔን አወዳደቅ ያየ ሁሉ የምተርፍ አልመሰለውም ነበር፡፡ በተዓምር ተርፌ ለዛሬው ቀን ደርሻለሁ፡፡ ይኸው ነው፡፡"

"ይገርማል!"

"ምኑ?"

"የዛሬ አሥር ወር አካባቢ እኔም ከመኪና አደጋ በተዓምር ተርፌያለሁ" አላት፡፡ ቀና ብላ ተመለከተችው፡፡ ቀጠለላት፡፡ "ሊዲ ከመንገዱ ማዶ ቆማ እየጠበቀችኝ ነበር፡፡ እሷ ጋር ለመድረስ ተቻኩዬ በሩጫ ጎዳናውን ሳቋርጥ መሃል አስፓልት ላይ የምትበር መኪና መጣችብኝ፡፡ በድንጋጤ ባለሁበት ደርቄ ቀረሁ፡፡ ሹፌሩ በዚያ ፍጥነት ያደርገዋል ተብሎ በማይታሰብ ፍጥነት የመኪናዋን አቅጣጫ ለወጠ፡፡ እኔና መኪናዋ ተነካክተናል ብልሽ ምንም ግነት የለውም፡፡ እኔም ወደ ኋላዬ ወደቅኩኝ፡፡ የሊዲና የሌሎች ሰዎችን ጩኸት መቼም አይረሳኝም፡፡ ከዚያ አደጋ ከተረፍኩ ከአንድ ወር በኋላ ነው ከሊዲ ጋር የተጋባነው፡፡ እሷም፣ በተዓምር የተረፍክበት ቀን ነው ብላ በየወሩ ሻማ ታበራለች፡፡ አሥረኛ ወሩ ትናንት ነበር፡፡" አላት፡፡

Scanned with CamScanner

"የሚደንቅ ተመሳሳይ አጋጣሚ ነው:: ልዩነቱ እኔ በአደጋው ተጎድቼ ሆስፒታል የተኛሁ ሲሆን፣ አንተ ለጥቂት መትረፍህ ነው:: ለማንኛውም ወደ በዓላችን እንመለስ::"

"ትክክል:: እንዴት ነው ታዲያ የበዓል አከባበራችን?"

"እንዲህ ብናደርግስ? እዚሁ ኮሪደራችን ላይ ልዩ ራት አዘጋጅተን፣ ሻማችንን ለኩሰን፣ ወይናችንን እየጠጣን ብናከብረውስ?"

"ቆንጆ ሀሳብ ነው:: ታዲያ ዝግጅት ይጀመራ?"

የምሽቱን ውበት ተቀላቅለው በዓሏን ያከብሩ ገቡ:: ራት ተመግበው ጨረሱ::

"ደስ የሚል ምሽት ነው አይደል?" ብላ ጠየቀችው፣ ደስታዋ ፊቷ ላይ እየተነበበ::

"በጣም!"

"ምን አለ ሁሌም እንዲህ ደስ የሚል ቢሆን?" ቆዘመች::

"ለምን አይሆንም? አሁንም እኮ እኛ ነን ደስ የሚል እንዲሆን ያደረግነው:: አይደል እንዴ?" አላት የሰፈነባትን ሐዘን በሚያፅናና አንደበት::

"እሱስ ልክ ነህ:: ብቻ.. እንዲህ ያለ አጋጣሚ በብዛት አይገኝም:: እንኳን በዓመት በዕድሜ ልክም ቢሆን እንደልብ የማታገኘው ውድ ምሽት ነው ልልህ ፈልጌ ነው::"

"እንደዚህ አታስቢ:: እያንዳንዷን ቀን ልታደርጊው በምትወጂውና በሚያስደስትሽ ነገር ላይ ልታውያት ይገባል:: የሕይወትን ትርጉም የምትረጂው እንዲህ ባለ ሁኔታ ላይ ስትሆኚ ነው:: በገፍ ታፍሶ የተሰጠሽን ፍሬ ሳስተሽና አጣጥመሽ ስለማትጠቀሚበት የምታባክኚው ይበዛል:: ተቆጥቦና ተቆጥሮ የተሰጠሽ ፍሬ ግን ውድ ነው:: እያንዳንዷን ፍሬ ውበቷን እያደነቅሽና መዓዛዋን እያሸተትሽ፣ ወደ አፍሽም ስትሰጃት



በከንፈርሽ ዳብሰሻት፣ በእርጋታ አጣጥመሽ እያኘከሻት... በልዩ እርካታ ነው የአካልሽ ክፍል የምታደርጊያት::

"ያንን ፍሬ እንጠባጥበው የሚያባክኑት ታፍሶ የተሰጣቸው ናቸው:: ላንቺ ተቆጥሮ ተሰጥቶሻልና ያ ፍሬ ተንጠባጥቦ ሊባክን የማይገባ ውድ ስጦታ ነው:: ከምገምተው በላይ ጠንካራ መሆንሽን አውቃለሁ:: ግን... ጊዜን በወራት መቁጠርሽን አቁሚና በቀናት ለኪው:: ብትችይም በደቂቃ ተንትነሽ ተጠቀሚበት:: ፈፅሞ 'አንድም ወር እንዲባክንብኝ አልፈልግም' አትበይ:: 'አንድም ቀን ያለ ደስታ እንዲባክንብኝ አልፈልግም' እያልሽ አስቢ:: ያኔ ብዙ ውብና ጣፋጭ ደቂቃዎችን ትኖሪያለሽ:: ማንም ያን ያህል የበዛ ውብና ጣፋጭ ደቂቃዎችን ያልኖረውን ያህል አንቺ ትኖሪያለሽ:: የባከነው ቢቆጠር እኮ ከዚህ በፊት ባለፈው ዕድሜሽ የዓመትን ያህልም በሚገባ አልኖርሽ ይሆናል:: ተረድተሽኛል?"

በእያንዳንዱ ቃል ልክ ፊቷ ይበልጥ ሲያበራ እየተመለከታት ነው::

"እንዲህ የሚጣፍጥ ንግግር በሕይወቴ ሰምቼ አላውቅም::" ብላ በደስታ ልትስመው ተንጠራራች:: በድንገት ፊቱን ወደሷ ሲመልስ ከንፈሮቻቸው ተገጣጠሙ:: ጊዜ ጉዞውን ያቆመ ያህል ሁሉም ነገር ለአፍታ ረጭ አለ:: ከናፍሮቻቸው በዝግታ ተላቀቁ:: ያለምንም ንግግር ወደተለያየ አቅጣጫ ዓይኖቻቸውን ወረወሩ:: ከአፍታ ዝምታ በኋላ፤

"እንዲህ የሚጣፍጥ ነገርም ለከንፈሬ ጋብዤው አላውቅም::" ስትለው ሁለቱም ሳቁ::

"ግን ይቅርታ:: ሳላስበው ነው::" አለችው::

"አትጨነቂ እርሺው::" አላት:: ዞር ብላ አየችው፤ አያት::

"ለሁሉም ነገር በጣም አመሰግንሃለሁ:: ቅድም፣ 'ምን ነበር ከዓመታት በፊት ባወቅኩህ ኖሮ' ያልኩህ የምሬን ነው:: ሕይወት የሆነ ቦታ ላይ ደባ

Scanned with CamScanner

ሰርታብን ይሆናል እንጂ ድሮ ልንተዋወቅ ይገባን ነበር፡፡ በዕጣ-ፈንታ ታምናለህ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ግን የማምን ይመስለኛል፡፡ ለምን ጠየቅሽኝ?"

"እኔ በጣም አምናለሁ፡፡ ለምን እንደጠየቅኩህ ግን አልነግርህም፡፡" ሳቀች፡፡

"እሺ፤ ለምን እንደማትነግሪኝ ንገሪኝ፡፡"

"ለምን እንደማልነግርህ የማልነግርህማ..." ወይኗን ተጎነጨችና "እሱ ውስጥ ለምን እንደጠየቅኩህ መልሱን ታገኘዋለህ ብዬ ነው፡፡"

"እንግዲያው ይነጋታል እንጂ እስከትነግሪኝ ድረስ ከዚህ ቦታ መንቀሳቀስ የለም፡፡" አላት እየሳቀ፡፡

"ታድዬ!... አግኝቼ ነው?"

"አሃ! እንዲያ ከሆነማ ተቃራኒውን ሀሳብ ነው መያዝ ያለብኝ፡፡ ካልነገርሽኝ ወደ ቤቴ መሄዴ ነው፡"

"እኔ ደግሞ ትተኸኝ ከሄድክ ጭራሹንም ቤት አልገባም፡፡ እዚሁ ቁጭ ብዬ ብርድ ሲደበድበኝ አድራለሁ፡፡ ይሄን ለማየት ጭካኔው ስለሌለህ ትተኸኝ እንደማትሄድ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ስለዚህ አልነግርህም፡፡ አሁንስ ምን ይዋጥህ?"

"አሁን እንኳ እጅ ሰጥቻለሁ፡፡"

ካፊያ ጀመረ፡፡ ሳይዋከቡ ወደ ሳሎን ተዘዋወሩና ጨዋታቸውን ቀጠሉ፡፡ ከቆይታ በኋላ "ነገ ጠዋት ባለስራዎች ነን፡፡ አንቺም ወደ መኝታሽ፣ እኔም ወደ ቤቴ የምሄድበት ሰዓት የደረሰ አይመስልሽም?" አላት፡፡ ቅር ተሰኘች፡፡

"ሌቱ እንዳይነጋ የምናደርግበት አንድ መላ እንፍጠር እንጂ በእኔ በኩል ለእንቅልፍ ዝግጁ አይደለሁም፡፡" አለችው በደብዛዛ ፈገግታ፡፡

"አንድ ደብተራ አያት አሉኝ፡፡ ዝናብንም ጊዜንም ያቆማሉ፡፡ እሳቸው



ጋር እንሂድና እንሞክር እንጂ እኛ በምን አቅማችን?" ብሎ ዘና ሊያደርጋት ሞከረ፡፡

"ደብተራነት በዘር አይወራረስም?" ስትለው ሁለቱም ሳቁ፡፡ ሳቃቸው ሲያበቃ ዝምታቸው ተረኛ ሆነ፡፡

ሲጸራ እያመነታች "እንቅልፍ ካልወሰደኝ ግን ደውዬ እንደምቀሰቅስህ እወቅ፡፡" አለችው፡፡ አማን እየፈገገ "ቤት እንደገባሁ የማደርገውን አውቅ የለ፡፡ ለማንኛውም ደህና እደሪ፡፡" ብሏት ተነስቶ ቆመ፤ ተነስታ ቆመች፡፡ ቅሬታዋ አሁንም ይታያል፡፡ አልተሰናበተችውም፡፡ እንዲሁ በዝምታ ዓይን ዓይኑን ተመለከተችው፡፡ እጃቸው እንደተቆላለፈ ነው፡፡ በደመ ነፍስ ፊቷን ወደ ፊቱ አስጠጋችው፡፡ ከንፈሯ የዝግታ ጉዞውን አጠናቆ ከንፈሩ ላይ ተለጠፈ፡፡ ለስለስ አድርጋ ሳመችው፡፡ ለስለስ አድርጎ ሳማት፡፡ ጎረሰችው፣ ጎረሳት፡፡ እጆቿን አንገቱ ዙሪያ ጠምጥማ ትንፋሽ እስኪያጥራት ሳመችው፡፡ ወገቧን አቅፎ ከሰውነቱ አጣበቃት፡፡ በመሃከላቸው ክፍተት እንዳይፈጠር እየሳሳች ልብሱን ማውለቅ ያዘች፡፡ እሱም እንደዚያው፡፡ መራመዳቸውን እንኳ ሳያውቁ መኝታ ቤት አልጋው ጎን ደርሰዋል፡፡

ራቁታቸውን ቀሩ፡፡ ተቃቅፈውና ተጎራርሰው አልጋው ላይ ተጋደሙ፡፡ ለደቂቃዎች ማን እንደሆኑና የት እንዳሉ ረስተው በነኑ፡፡ ግብግቡ ሰማይ ነክቶ ከመቅፅበት ተፈጠፈጠ፡፡ ቁና ቁና እየተነፈሰች ደረቱ ላይ ተጋደመች፡፡ እንዲያ እንደሆኑ ጥቂት ቆዩ፡፡ ቀና ብላ ተመለከተችው፤ እያየት ነው፡፡ ውስጡን እያነበበች እስከትመስል ድረስ በጥሞና ተመለከተችው፡፡

"ምን እያሰብሽ ነው?" አላትና እጁን ሰዶ ፀጉሯን አሻሻት፡፡

"ካንተ ጋር እንኳን ይሄን ሕይወት ገሃነምን እንኳ ቶሎ አለምደዋለሁ፤ ብዬ እያሰብኩ ነው፡፡" አንገቱን ሳመችውና ውሸቅ አለችበት፡፡

"... ዛሬን ብቻዬን አትተወኝ፡፡ እንዲህ አንገትህ ስር ተወሽቄ እንቅልፍ

ይዞኝ ይሂድ፡፡ በሕይወቴ ካገኘኋቸው ገፀ በረከቶች ድምር ሁሉ ይሄ ይበልጥብኛል፡፡"

እንባዋ እንገቱን ማራስ ሲጀምር "እያለቀስሽ ነው እንዴ?" አለና ፊቷን ቀና አድርጐ ተመለከታት፡፡

"አዝኜ እኮ አይደለም፡፡ ደስ ስላለኝ ነው፡፡ አንተን ባላገኝ ኖሮ ምናልባትም አንድም የደስታ ቀን ሳላይ ቀሪ ዕድሜዬን እጨርሰው ነበር፡፡" እንባዋን ጠራረገችና " ... ቅድም ስለ ዕጣ ፈንታ አንስቼልህ ለምን እንደጠየቅኩህ አልነገርህም ብዬህ ነበር፡፡ አሁን መስማት ትፈልጋለህ?"

"የማታለቅሽበት ከሆነ ብቻ ንገሪኝ፡፡ ስታለቅሽ ማየት አልፈልግም፡፡"

ፈገገችና "አላለቅስም፤ አይዞህ፡፡ ምን መሰለህ?" ብላ ለማውራት ተመቻቸች፡፡

"ለፍቅር ከደረስኩበት ዕድሜ ጀምሮ እንዲህ ዓይነት ፍቅረኛ ቢኖረኝ እያልኩ በልቤ የምስለው ሰው ነበር፡፡ ይሄን የውስጤን ሰው 'ፊል' አደርገዋለሁ እንጂ የሆነ የተጨበጠ መልክ ኖሮት አላየውም፡፡ የሚገርምህ ከሆነ ወንድ ጋር የፍቅር ግንኙነት ስጀምር ፍቅር የያዘኝ ይመስለኛል እንጂ ውሎ ሲያድር ፍቅር አለመሆኑን እረዳዋለሁ፡፡ በቃ የነፍሴን ከር እንደ ጊታር መትቶ ድምፅ የሚፈጥርባት፣ የሚያቃትታት፣ እንድታዜም የሚያደርጋት፣ ለእኔ የተፃፈው ያ ውስጤ የተፈጠረው ሰው ነው እላለሁ፡፡ ግን የት ላግኘው? መልክና አድራሻ የለው እል ነበር፡፡ ምን ዋጋ አለው?! ያ በነፍሴ ውስጥ የተቀረፀውንና ነፍሴን ሊያነዝራት የሚችለውን ሰው በጣም ከረፈደ በኋላ ዛሬ አገኘሁት፡፡

"ሕይወት ለኔ 'ፌር' የሆነችልኝ አይመስለኝም፡፡ ሕይወት ከዕጣ-ፈንታ ጋር የምትገናኝባት አሊያም የምትተላለፍባት መድረክ ናት፡፡ ምናልባትም እኮ ሳላስበው በዙሪያህ ሺህ ጊዜ ተመላልሼ ይሆናል፡፡ እንዲሁ ስንተላለፍ ኖረን ይሆናል እንዲህ ከረፈደ የተገጣጠምነው፡፡ እየህ አሽናፊና ተሸናፊ



የሚለዩት በዚህ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ያልተፈቀደልንን ፈቅደን፣ ያልተፃፈልንን ፅፈን፣ ይሄ ካልሆነ ብለን ከዕጣ-ፈንታችን ጋር እንታገላለን፡፡ ተፈጥሮ ደግሞ የራሷ ቋንቋ አላት፡፡ ይሄንን ታሪክ መዝገባችሁ ላይ አላውቀውም ብላ ስትነግረን ሺህ እንከን ትደረድርብናለች፡፡ ቋንቋዋን ካወቅን እንረዳታለን፤ ካላወቅን ደግሞ በትግላችን እንፀናለን፡፡ ምናልባትም አሸንፈን በዕጣ ፈንታ መዝገባችን ላይ ያልተፃፈውን ፅፈን በአንፃራዊ ስኬት ልንኖርም እንችላለን፡፡ ለምን መሰለህ በአንፃራዊ ስኬት ያልኩት?... ስኬቱ ደስታና ፍቅርን አግኝተህ መኖር በመቻልህ ነው፡፡ አንፃራዊነቱ ደግሞ ምናልባት ታግለህ ያፀናኸው ሳይሆን በትክክል ላንተ የተፃፈው ዕጣ-ፈንታህ አንድ ቀን ቢከሰት፣ ያ ከዚህ በፊት ታግለህ ያፀናኸው እውነት፣ ውሸት ይሆንብሃል፡፡ ያ የመጀመሪያው ፍቅር፣ ደስታና ውበት ባዶ ይሆንብሃል፡፡ ወደ አዲሱ ስታዘነብል የመጀመሪያውን ትንደዋለህ፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ደስታና ፍቅር በሁለተኛው ይሸነፋል ማለት ነው፡፡... ዛሬ ግን ምን ሆኛለሁ? ማነው ለመሆኑ ፈላስፋ እንድሆን የፈቀደልኝ? ደግሞ ያንተ ነው የሚገርመኝ፡፡"

አማን ሳቀና " እኔ ደግሞ ምን አደረግኩ?" አላት፡፡

"ስቀባጥር ዝም ብለህ ትሰማኛለህ?"

"ታዲያ ይሄን የመሰለ ፍልስፍና ዝም ብሎ ከመስማት ውጪ አብሬሽ ባወራ ያለ እውቀቴ መቀባጠር አይሆንብኝም?... ለማንኛውም ፅንሰ ሀሳብሽን ብወደውም ከእኔ ወይም ከአንቺ ጋር የሚያያይዘው ጭብጥ ግን አልተገለፀልኝም፡፡"

"ያልተገለፀልህ ከእኔ የማስረዳት አቅም ማነስ ችግር ነው፡፡ ስለዚህ መንዛዛቴን ትቼዋለሁ፡፡ ይልቁንስ ልሳምህ፡፡" ሳመችው፤ ተሳመላት፡፡

"እስቲ ደግሞ ስላንተ አውራኝ፡፡"

"ስለኔ ምን ላውራሽ?"

Scanned with CamScanner

"ከሊዲያ ጋር መቼና እንዴት እንደተገናኛችሁ፣... በቃ ሁሉንም ታሪክ አጫውተኝ::"

በዝርዝር አወጋት፤ በጥሞና አዳመጠችው:: በመጨረሻም "እና ከተዋወቃችሁ ዓመት ከስድስት ወር ከተጋባችሁም ዘጠኝ ወር ሆናችሁ ማለት ነው?"

"እንደዛ መሆኑ ነው እንግዲህ::"

"ከሁሉም ያስገረመኝ የመጀመሪያ ቀጠሯችሁ ዕለት የተፈጠረው ነገር ነው::" አለች በፈገግታ::

" እኔም ባሰብኩት ቁጥር ይገርመኛል:: የሚገርመው እኮ እዚያው አካባቢ መኪናዬን ሰርቪስ የሚያደርግልኝ መካኒክ አለ:: ደውዬ ጠራሁትና ቁልፉን ተቀብሎ ተረክ ሲያደርጋት ሞተሯ አይነሳ መሰለሽ? ተገርሞ 'መኪናህ ምንም እንከን የለባትም::' አለኝ::"

"በእንዲህ ያለ ሁኔታ የጀመራችሁት ፍቅር ለዚህ መብቃቱ ድንቅ ነው:: ብዙ ጊዜ እንዲህ ያለ የተደራረበ እንከን ሲገጥመን ይሄን ነገር ለእኔ ባይለው ነው እንላለን:: አንተ ግን እንደዚህ ያልክ አይመስለኝም:: ምንም ቢገጥምህ እጅህ አስገባሃት::"

"የዚያን ዕለት ገጠመኜን ለሊዲ በስልክ ስነግራት 'አላህ ዛሬ እንድንገናኝ ባይፈቅድ ነው:: ኢንሻ አላህ ሌላ ጊዜ እንገናኛለን' ነበር ያለችኝ::"

"አስተዋይ ናት:: ሳስበው በአንተ ብርታት ሳይሆን በእሷ ፅናት ለዚህ የበቃችሁ ይመስለኛል::"

"ቆይ፣ቆይ! ወዴት፣ወዴት ነው ነገሩ? አንተ አስተዋይ አይደለህም እያልሽኝ ነው?" የቀልዱን ተኮሳተረ::

"አንተማ ከማውቃቸው አስተዋይ ሰዎች መካከል ቁጥር አንድ ነህ:: ያንተ አስተዋይነት እንዳለ ሆኖ እሷ አስተዋይ መሆን አትችልም?"

"እንደዛ ከሆነ ተቀብያለሁ::... ለነገሩ ልክ ነሽ እኔና እሷ ብዙ ፈተና



አይተናል:: ብዙዎቹን ችግሮች እንድንወጣ ያስቻለን የእሷ ፅናት ነው:: ግን እንዴት እንዲህ ደመደምሽ?"

"አልደመደምኩም እኮ፤ ይመስለኛል ነው ያልኩት:: ሆነም ቀረም... ሁለታችሁም በጣም ዕድለኞች ናችሁ:: እሷ አንተን የመሰለ ባል በማግኘቷ እግዚአብሔርን እያመሰገነች የምትኖር ይመስለኛል:: በእምነቷና በፅናቷ ብርታት የራሷን 'ዴስቲኒ' ፅፋ ማፅናት የቻለች ጠንካራ ሴት ናት:: አንተም እሷን የመሰለች ሚስት አግኝተህ በደስታ መኖር በመቻልህ ዕድለኛ ነህ::"

"አንዳንዴ ንግግርሽ ውስጥ ግራ የሚያጋቡ ነገሮችን አገኛለሁ:: የገባኝ መስሎኝ አልፈውና መልሼ ሳስበው እንዳልገባኝ እረዳለሁ::"

"ለምሣሌ..." አለችው በፈገግታ ሆና በጣቶቿ ፊቱን እየደባበሰች::

"ለምሣሌ... አሁን ስለ ሊዲ ዕድለኝነት ስትነግሪኝ የራሷን 'ዴስቲኒ' ፅፋ ማፅናት የቻለች ናት ብለሽኛል:: ምን ማለት እንደሆነ አብራሪልኝ እስቲ::"

"እያወራሁህ ያለሁት የተፈጥሮን ምስጢር እኔ በተረዳሁበት ቋንቋ ነው:: ምናልባት በትርጉሙ አትስማማ ይሆናል:: ግን ያመንኩበትን ልንገርህ:: የመጀመሪያ ዕለት እንዳትገናኙ በተደጋጋሚ የደረሰብህ እንከን የተፈጥሮ ቋንቋ ነው:: ተፈጥሮ ያንተ ካልሆነ ነገር ልትመልስህ የዘረጋችው ወጥመድ ነው:: ሊዲያ ይሄ ስለገባት ነው::' አላህ ዛሬ እንድንገናኝ ባይፈቅድ ነው' ያለችህ:: ከዚያም በኋላ ቤተሰቦቿ ለሌላ ሰው ሊድሯት ስለፈለጉ ብዙ ሳንካ ገጥሟችኋል:: እሷ ግን ካንተ ጋር አብሮ የመኖር ህልሟን ለማሳካት የተጠየቀችውን መስዋዕትነት ሁሉ ከፍላ፣ሁሉንም እንከኖች ደረማምሳ በመጣል ለስኬት በቅታለች:: ስለዚህ ምናልባት ዕጣ-ፈንታዋ ካንተ ጋር እንዲሆን አስቀድሞ ባይፃፍ እንኳ በፅናትና በመስዋዕትነት ራሷ ፅፋ አፅንታዋለች ማለቴ ነው:: አንተም እንደዚያው:: አሁንስ፣ በሚገባ ማስረዳት ችዬበታለሁ?"

አማን እየሳቀ "ስለ ዕጣ ፈንታ ያለሽ እውቀት ጥልቅ ነው:: በዚህ ጉዳይ

Scanned with CamScanner

ላይ አንድ መፅሐፍ መፃፍ አለብሽ:: አሪፍ ሃሳብ አይመስልሽም?" አላት::

"ይሄንን እንኳ አንተ ተማሪዬን በደንብ ሌክቸር ካረግኩህ በኋላ የመመረቂያ ፅሁፍህ አርገህ ብታቀርበው የሚሻል ይመስለኛል:: ምክንያት ቢባል... እኔ ከዕጣ-ፈንታዬ ጋር ብዙ ጊዜ ስተላለፍ ሊያም ሳልገጣጠም የኖርኩ ሰው ነኝ:: ወይም ደግሞ ዕጣ-ፈንታዬን ራሴው ልፅፈው ብሞክርም በደስታና በአርካታ ላይ ላፀናው አልቻልኩም:: አንተ ግን ወይ ሁለቱም ላይ አሊያም አንደኛው ላይ ያለህ ነህ:: በዚህም ላይ መምከር የሚያምርበት በሕይወት ቁማር ውስጥ አሸናፊ የሆነ ሰው ነው::"

"ታዲያ እኔን አሸናፊ፣ አንቺን ደግሞ ተሸናፊ የሚያደርግ ምን ነገር ተገኘ?"

"ይሄ እውነት እንደሆነ በቀላል ምሣሌ ልግለፅልህ:: የዛሬ ዓመት ከመንፈቅ አንተና ሊዲያ የፍቅር ግንኙነት ጀመራችሁ:: አጀማመራችሁም በቀላሉ ሳይሆን በፈተና ነው::

"እኔም በዚያው ወቅት አካባቢ ከቤን ጋር የፍቅር ግንኙነት ጀመርኩ:: የእኔ አጀማመር ደግሞ ልዝብ ነበር:: እናንተ በመሃል ብዙ ፈተና ገጠማችሁና አለፋችሁት:: እኔ ደግሞ ፍቅር ነፍሴን ኮርኩሮ አይጋልባት እንጂ የፍቅር ሕይወቴ ላይ ይሄ ነው የምለው ችግር አልገጠመኝም:: ከዚያ የዛሬ አሥር ወር አንተ ከመኪና አደጋ ለጥቂት አመለጥክ፤ እኔ በተመሳሳይ ወቅት ከፍተኛ የመኪና አደጋ ደረሰብኝ፤ ተጐዳሁ:: ሁለት በል...

"ሦስተኛ፣አንተ የዛሬ ዘጠኝ ወር ከምታፈቅራት ሴት ጋር ተጋብተህ በመኖር አዲስ ሕይወት ጀመርክ:: እኔ ደግሞ በተመሳሳይ ወቅት የቀረኝ ዕድሜ አጭር እንደሆነ ተገለፀልኝና ከጨለመ አዲስ ሕይወት ጋር ተዛመድኩ:: ይሄን መርዶ በሰማሁ በአንድ ወሩ ደግሞ የጨለማው



ሕይወቴ ብቸኛው ሻማን ከሌላ ሴት ጋር አገኘሁትና እሱም ጨለመ:: አንተና ሊዲያ ደግሞ በዚያው ወቅት ቤተሰቦቿን ድል ነስታችሁ በአደባባይ ተሞሸራችሁ::

ይሄ ሁሉ ካለፈ በኋላ ይኸው ዛሬ ተገናኝተን ታሪካችንን እንተነትናለን:: ቅድም ስላንተ ታሪክ ስታጫውተኝ ይሄን ሁሉ እየገጣጠምኩ በማሰብ ስገረም ነበር:: ብቻ..." በረጅሙ ተነፈሰችና "ሕይወት ትገርማለች:: በ'ዴስቲኒ'ህ ላይ የቱ ጋር ስህተት እንደፈፀምክ እንኳ ሳታውቀው እንዲሁ ፊትህ ያገኘኸውን ብቻ ዝም ብለህ ትኖራለህ:: ይሄን ምስጢር የተረዳሁት በጣም ዘግይቼ መሆኑ ያበግናል:: ለማንኛውም የዛሬው ዲስኩር እዚህ ጋር ያብቃ:: ቅድም በመከርከኝ መሰረት ብዙ ደቂቃዎች ያለሳቅ አለፉን:: ቀጣዮቹን ብዙ ደቂቃዎች በአጥፍ ልንስቅባቸው ይገባል::" ብላ ላዩ ላይ ተንቆራጠጠች::

"ሁሉ ነገርሽ ይደንቃል:: ልክ እንዳንቺ የሚያስደንቁ ነገሮችን የሚያወራኝ አንድ ጓደኛ አለኝ:: የዕጣ-ፈንታ ምስጢር፣ ተፈጥሮ ከእኛ ጋር የምታወራበት ቋንቋ ምናምን ይለኛል:: ልክ በአንድ ምላስ የምታወሩ ነው የምትመስሉት:: እንደውም ፅንሰ-ሀሳቦቹ በእኔም አስተሳሰብ ላይ ተፅዕኖ ከማሳደራቸው የተነሳ አንዳንዴ በንግግሮቼ መካከል አገኛቸዋለሁ::"

"እንደኔው በሕይወት ጉዞው ግራ የተጋባ አሊያም ዕጣ-ፈንታውን እያሳደደ የሚኮመኩም ጀግና ቢሆን ነዋ!"

"ቆይ እንደውም አስተዋውቅሻለሁ::"

"ትወደዋለህ መሰል..."

"አዎ:: አንዳንዴ ግራ ቢያጋባኝም ሕይወትን አቅልዬ እንድኖራት ያደርገኛል::"

ከዚያም ጊዜ በኋላ ከሲጳራ ጋር ለጥቂት ቀናት ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ተጉዘዋል:: ሲጳራ ሐመሮችን ለማየትና ከነርሱ ጋር ጥቂት የደስታ

Scanned with CamScanner

ቀናትን ለማሳለፍ ባመጣችው ሀሳብ መሰረት ነው የተጓዙት፡፡ አማን የጉዞውን ምክንያትና የት እንደሚሄድ አልገለፀልኝም ነበርና ሁሉንም ነገር የተረዳሁት ዘግይቼ ነው፡፡ ይሄ ሁሉ ታሪክ የሆነው ታዲያ ሊዲያ ወደ አዲስ አበባ ሄዳ በከረመችበት ወቅት ነው፡፡ እኔ እንደተረዳሁት ከሆነ የአማን አድራጐት ከራስ ወዳድነት ወይም ሌላን ገላ ከመመኘት የመነጨ አይደለም፡፡ ለሲጳራ በጣም አዝኖላታል፡፡ በሕይወት መቆየት የምትችለው ግፋ ቢል ለአንድ ዓመት ያህል መሆኑን ማወቁና እሷም ማንም ባላየላት ጥልቅ ሐዘን ውስጥ መገኘቷን መረዳቱ ይመስለኛል ለዚህ ያበቃው፡፡

አንድ ቀን " የቀራትን ውስን ጊዜ ተደስታ ልታልፈው ይገባል፡፡ የተመኘችውንደስታየምታገኘውበእኔውስጥከሆነምንማድረግእችላለሁ? እስቲ ንገረኝ፡፡" ሲል አፋጥጦኛል፡፡ ምን ልነግረው እችላለሁ? ... እኔ ማን ነኝና ነው ዳኝነት የምቀመጠው? አማን ለሲጳራ የቀሪ ዕድሜ ደስታ ሲል የሊዲያን ፍቅርና ትዳሩን መስዋዕት እያደረገ መሆኑን ነጋሪ ሳያስፈልገው ተረድቶታል፡፡ ታዲያ ይሄን ዓይነቱን መስዋዕትነት ምን ልበለው? ሰብዓአዊነት ወይንስ ሞኝነት? ወይንስ ሌላ?፡፡

አንድ ዕለት፣ አማን ከሲጳራ ጋር አስተዋወቀንና ምሣ አብረን በላን፡፡ ከምሳ በኋላ ሻይ ቡና እያልን ሳለ፣ የአማን አብሮ አደግ ጓደኛ ልውል ሰገድ ወደ ጠረጴዛችን መጣ፡፡ ከአማን ጋር ሞቅ ያለ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ሲጳራ ላይ አፍጥጦ ቀረና በመገረም "ልዕልት ሲጳራ ነኝ እንዳትይኝ ብቻ!" አላት፡፡

እሷም እየሳቀች፤ "ልውል ነኝ እንዳትል ብቻ!" ብላ ተነሳች፡፡

"የአምላክ ያለህ!" ብሎ ተጠመጠመባት፡፡ ተቃቀፉ፡፡

"አንቺ በሕይወት አለሽ?"



"ሊያውም አምሮብኝ ነዋ!" አለችው እየሳቀች፡፡

"በጣም ይገርማል!" እያለ እኔንም ጨበጠኝና ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡

"አስተዋዋቂ ለመሆን የተዘጋጀሁትን ሰው እኮ ጦጣ አደረጋችሁኝ፡፡ ለመሆኑ ይሄ ሁሉ መተቃቀፍና ፈንጠዝያ የመቼ ትውውቅ መሆኑ ነው?" አለ አማን በፈገግታ፡፡

"ምን ነካህ? 'ሃይ ስኩል' ነዋ!... ዘጠኝና አስርን አንድ ላይ ከተማርን በኋላ እኮ ነው የት እንደገባች ሳይታወቅ ጠፍታ የቀረችው፡፡ አይገርምም?... ግን የዓመታቱን ብዛት ያህል ብዙ አልተለወጥሽም፡፡" አላት ልውልሰገድ እያደነቀ፡፡

"ቆይ፣ቆይ... እኔና አንተ ሃይስኩል አንድ ክፍል የተማርን መስሎኝ፤ ነው ወይንስ ከሌላ ትምህርት ቤት ተባረህ ነው እኛ ጋር የተቀላቀልከው?" ብሎ ጠየቀ አማን፡፡

"አንተ የምታውቃት ትምህርት ቤት አይደለም ማለት ነው?" አለው ልውል ተደንቆ፡፡

"'ኖኖ'!...እኛ የተዋወቅነው በቅርቡ ነው፡፡"አለና ሲጳራን ተመለከታት፡፡ እሷም ፊት ላይ ግርምት የፈጠረው ስሜት አፍጥጧል፡፡

"ምን ነካችሁ?... ማን ነበረች እኛ ክፍል የነበረችው ጓደኛሽ?... አዎ ላምሮት፣ ላምሮትን ብላ እኛ ክፍል ትመጣ ነበር እኮ፡፡ እንዴት አላስታወስካትም?... ወይ ሲጳራ! እኔማ ወደ አስራ አንድ ተዘዋውረን ትምህርት ሲጀመር የእኔና ያንቺ ነገር ይለይለታል ብዬ ፎክሬ ነበር የተገኘሁት፡፡ በዚያው የውሃ ሽታ ሆነሽ ቀረሽ እንጂ፡፡"

አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ተምረው እንደነበር መስማታቸውና ከዓመታት በፊት ሊያውም ለሁለት ዓመታት ያህል የመተያየት ዕድል ገጥሟቸው እንደነበር ማወቃቸው ሁለቱንም እጅግ አስገርሟቸዋል፡፡

ሲጳራ፣ በቁጭትና በግርምት አናቷን እየነቀነቀች አማንን

ትመለከተዋለች:: እሱም ያያታል:: "ሕይወት ቁማር ናት:: የካርታ ጨዋታ:: የተሰጠህን ካርድ አስተውለህ ካልተመለከትከና አጨዋወትህን ካላሳመርክ ትሸነፋለህ::"ብላ ፈገገች::

"እኔ እንኳን የተሰጠኝን ካርድ አስተውዬ ነበር:: አጨዋወቴን ግን ያሳመርኩ አይመስለኝም:: ለዚያ ነው ያመለጥሽኝ::" ብሎ ሳቀ ልዑል ሰገድ::

የሲጻራ ንግግር መልዕክቱ የገባን እኔና አማን ነን:: 'ምን ነበር ከዓመታት በፊት ተገናኝተን በነበር?' እንዳለችው አማን የነገረኝ ትዝ ብሎኝ እኔም ተደንቄያለሁ::

ልዑል ሰገድ ለጥቂት ደቂቃዎች ያህል ሲያጫውተን ቆይቶ ተሰናብቶን ሄደ::

"እንደዚህ የሚያስደንቅ ነገር በሕይወቴ ገጥሞኝ አያውቅም::" አለችው::

"እኔም በጣም ገርሞኛል::" አላት::

"እንዴት ያኔ ሳላስተውልህ ቀረሁ?" ቁጭት የተሸከመ ጥያቄ አቀረበች:: አማን ምን አውቄ ሲል ትከሻውን ሰበቀ::

"ሕይወት የሆነ ቦታ ላይ ደባ ሰርታብኛለች ያልኩት ትልቅ ስህተት ነው:: እኔው ነኝ ለካ ከወዲያ ወዲህ ስከንፍ በራሴ 'ዴስቲኒ' ላይ ያደባሁት:: እሷማ ሮጩ የማላበቃውን ሁለት ዓመታት ያህል የገዘፈ ሰፊ ሜዳ ሰጥታኝ ነበር:: ምን አጠፋች?" ቅስሟ ምን ያህል እንደተሰበረ ከድምጿ መረዳት ቻልኩኝ::

እዚያ ቦታ ላይ ከዚህ በላይ ለመቆየት አልፈለግኩምና ተሰናብቼ ተለየኋቸው:: ሁኔታውን ግን ከአዕምሮዬ ላወጣው አልቻልኩም:: ከኮብላይ ካህን ጋር ባሳለፍኳቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ የተረዳሁት የተፈጥሮ ምስጢር በአማንና በሲጻራ ውስጥ ገዝፎ ይታየኝ ጀመር::



ግን የዚህ ሁሉ ነገር ግጥምጥሞሽ በሲጻራ አዕምሮ ውስጥ እንደተደመደመው፣ አማን በተፈጥሮ ሰፊ መዝገብ ውስጥ የተፃፈ ዕጣ-ፈንታዋ ነው ያሰኛል? ልክ የዕጣ ፈንታን መዝገብ ያነበብን ያህል እንዲህ ነው ብለን እንዴት መናገር እንችላለን?... እኛ የምንችለው መገመት እና በግጥምጥሞሹ መደነቅ እንጂ፤ እርግጡንማ ከባለመዝገቡ ከፈጣሪ አምላክ ውጪ ማን ሊያውቅ ይችላል? ግጥምጥሞሹንስ ቢሆን ማን አፅዳቂ አደረገን?... ለመሆኑ እነዚያን፣ በቦታ እጅግ ተራርቀው በጊዜ የተገናኙ ክስተቶችን ግጥምጥሞሽ ብለን ልንጠራቸውስ ይገባል?...

ሁለቱም በተመሳሳይ ወቅት ፍቅረኛ ኖራቸው፤በተመሳሳይ ወቅት የመኪና አደጋ ገጠማቸው:: እሱ ለጥቂት ዳነ፤ እሷ በአደጋው ጉዳት ደረሰባት:: አማን ትዳር ይዞ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ሲከፍት፣ በተመሳሳይ ወቅት ሲጻራ ካንሰር እንዳለባት አወቀችና ከአዲስ ሕይወት ጋር ተዋወቀች:: አማን በተሞሸረበት ወቅት እሷ ከፍቅረኛዋ ጋር ተለያየች:: ከወራት በኋላም እዚህ ተገናኙ:: እሷ ደስታን ተነጥቃ፣ የሕይወት ትርጉም አልገባሽ ብሏት ሳለ ያ ከልጅነቷ ጀምሮ ስትስለውና ስትመኘው የነበረው ሰው በድንገት ተገኝቶ ብርሃን ፈነጠቀላት:: ደስታን መልሳ እንድታጣጥም አደረጋት:: በተረፈ ዛሬ እንደሰማነው ከዓመታት በፊት አንድ ትምህርት ቤት ይማሩ ነበር፤ የጋራ ጓደኞችም አሏቸው::

ግን ደግሞ የእሷን እርግጠኝነት ምን አመጣው? "ሕይወት የሆነ ቦታ ላይ ደባ ሰርታብን እንጂ ከዓመታት በፊት ልንገናኝ ይገባን ነበር:: ዕድሜ ልኬን ስፈልገው የነበርኩት የነፍሴ ሰው አንተ ነህ::" ያለችው ለሁለት ዓመታት ያህል በዙሪያው ስትሽከረከር እንደነበር ከመረዳቷ በፊት ነው::

ይሄንን ጉዳይ ደጋግሜ ሳሰላስለው አንድ ሀሳብ ድንገት ተወርውሮ አዕምሮዬ ውስጥ ሰረፀ:: "ሁለት ሰዎች አንድ ዕጣ ካላቸው ወይ አብረው

Scanned with CamScanner

ይጋሩታል፤ አሊያም እንዳቸው ያነሱታል፡፡ አንዱ ከወሰደው ደግሞ ሌላኛው ያጣዋል፡፡" በሌላ አገላለፅ "ዕጣው አንድ ከሆነ አንዱ ያጣውን ነው ሌላው የሚያገኘው-ካልተጋሩት በቀር፡፡"

ይሄ ሀሳብ ሁሉንም ነገር በድጋሚ እንዳጤነው ጋበዘኝ፡፡ ሲጻራ እንደምታስበው የሁለቱ ዕጣ-ፈንታ አንድ ላይ እንዲሆን ወይም አማን የነፍሷ ተቋራጭ ሆኖ ተፅፎ ነበር ብዬ በማሰብ እስቲ ልነሳ፡፡ አማንና ሊዲያ በተገናኙበት ወቅት ሲጻራና ቤን ተገናኙ፡፡ እነ አማን የጠማቸውን አልፈው ለዛሬ ሲበቁ፤ የሲጻራና የቤን ፍቅር ግን በመለያየት ተደመደመ፡፡ ስለዚህ ዕጣው ለአማን ደረሰው ልበል፡፡ የመኪና አደጋውን ከፉ ዕጣ ደግሞ ሲጻራ ወሰደች፡፡

አማን ከሊዲያ ጋር ኒካህ አስሮ የሕይወትን አዲስ የደስታ ምዕራፍ ሲጀምር፣ ሲጻራ የካንሰር በሽተኛ መሆኗን አውቃ ካላለመችው አሳዛኝ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ጋር ተዋወቀች፡፡ በወሩ እነ አማን ሲሞሸሩ የእሷና የቤን እህል ውሃ አበቃ፡፡ አማን መልካሙን ዕጣ ሲመዝ ሲጻራ ደግሞ ከፋውን ዕጣ ወስዳለች እንደማለት ነው፡፡

እና ምን ይፈጠር?... ማነው እኔን እንዲህ ያለውን ምስጢር መርማሪ አድርጎ የሾመኝና የምቀባጥር?... የሀሳቤን ቁልል በአንድ ጊዜ ንጄው ወደ ሱቅ ገባሁ፡፡

ስራዬን መስራት እንደጀመርኩ ዓይኔ ተንቀዥቅዞ የሸቀጥ ካርቶኖች መሃል የተወተፈ የቀን መቁጠሪያ ላይ አረፈ፡፡ በቀጥታ ሄጄ አነሳሁትና ያለምንም ማመንታት አማን ከመኪና አደጋ ለጥቂት የተረፈበት ወርና ቀን ላይ ገለፅኩት፡፡ ቀኑን ለአራት ወራት አንድ ላይ ሻማ ለኩሰን ስላሰብነው አስታውሰዋለሁ፡፡ ያ ዕለት በአውሮፓውያን አቆጣጠር ምን ላይ እንደዋለ ከተመለከትኩ በኋላ ወዲያውኑ ለአማን ደወልኩለትና ሲጻራ በመኪና የተገጨችበትን ቀን እንዲነግረኝ ጠየቅኩት፡፡ ትክክለኛውን ቀን ከእሷው



ጠይቆ ነገረኝ፡፡ እንደገመትኩት የተጠቀመችው የአውሮፓውያኑን የቀን ቀመር ነው፡፡

"ምነው?"አለኝ፡፡

"ምንም፡፡" ብዬው ስልኩን ዘጋሁና ከራሴ ጋር ግብግብ ገጠምኩኝ፡፡ ሁለቱም የመኪና አደጋ የገጠማቸው በተመሳሳይ ዕለት ነው፡፡ በአንድ ቀን ምናልባትም በተመሳሳይ ሰዓት፡፡ በዚህኛው ወር በለኮሱት ሻማ መካከል የአንድ ቀን ልዩነት የተፈጠረው በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠርና በአውሮፓውያን የዘመን አቆጣጠር መካከል ባለው ልዩነት ሳቢያ ብቻ ነው፡፡ ሌሎቹም ቀናት እንዲህ ከተገጣጠሙ ተደንቄም አላባራ፡፡

Scanned with CamScanner

## - 14 -

የሊዲያ ደስታ ፈጣሪነት ሰሞኑን የለም:: ከሩቅ የሚሰማው ውብ ሳቋ ነጥፏል:: ንግግሯ እንኳ የዝምታን ያህል ሆኗል:: አንድ የሰማችው ነገር እንዳለ ለመረዳት አልከበደኝምና ተጨነቅኩኝ::

ለመሆኑ ስለዚህ ጉዳይ ብትጠይቀኝ ምን መልስ ይኖረኛል?... ተሳቀቅኩ:: አማንን አወራሁት:: እሱም ተረብሿል፤ ግራ ተጋብቷል:: ሊዲያን ያፈቅራታል:: በሚያደርገው ነገርም ምን ያህል ሊያሳዝናት እንደሚችል ያውቃል::

"ምን አባቴ ባደርግ እንደሚሻለኝ አላውቅም:: አማክረኝ እስቲ" አለኝ::

"ሊዲያን ከሚያስቀይምና ከሚያሳጣህ ነገር ውጭ፣ ሲጻራን ደስተኛ ሊያደርግ የሚችልን ማንኛውንም ነገር አድርግ::" ብዬ የሁልጊዜ ንግግሬን ደገምኩለት::

የሊዲያ ዝምታ ግን አንድ ምሽት አፍ አወጣ::

"አሚ፣ ሰሞኑን አንድ ነገር ካንተ እሰማለሁ ብዬ ስጠብቅ ነበር:: ዛሬም አትነግረኝም:: ምናልባትም ነገም፣ ከነገ ወዲያም ካንተ አይመጣም ይሆናል:: ሁሉንም ነገር ቀድሜ ካንተው አፍ ብሰማው ምንኛ ይሻለኝ ነበር መሰለህ:: ዝምታዬ ቀንድ እስኪያወጣ ድረስ መጠበቅ ስለሌለብኝ ነው ዛሬም ያነሳሁልህ:: ከእኔ አፍ ሲወጣ ስለሚያመኝ የማውቀውን እንድነግርህ አትጋብዘኝ:: ካንተ አፍ ግን መስማት እፈልጋለሁ::" አለችው:: አማን አናቱን በዱላ የተመታ ያህል ድንጋጤ ጭጭ አደረገው::



ይሄን ተናግራ ፊት ለፊቱ ሶፋው ላይ ተቀመጠች:: አያት፣ እያየችው ነው:: ከዓይኖቿ ሸሸ:: አንገቱን እንደደፋ፤

"ይቅርታ አድርጊልኝ ሊዲ:: አንቺ ፊት መቆም የማይገባኝ ሰው ነኝ:: በድዬሻለሁ::" አላት አንባው እየወረደ በዝምታና በትዕግሥት ጠበቀችው::

"ከሌላ ሴት ጋር ግንኙነት አለኝ::" አላት ቀና ለማለት ሳይደፍር::

"እና የሰማሁት እውነት ነዋ?"

"በጣም አዝናለሁ ሊዲ"

ቤቱ ውስጥ ከመቃብር የከበደ ዝምታ ሰፈነ:: ከአፍታ በኋላ ሊዲያ በረጅሙ ተነፈሰችና ከተቀመጠችበት ተነሳች:: በተረጋጋ አንደበቷም፤

"ለጥቂት ጊዜ ብቻዬን እንድሆን ፍቀድልኝ::" ብላው መኝታ ቤት ገብታ በሩን ዘጋች:: ኃይለኛ ራስ ምታት ጀመረው:: ሶፋው ላይ በጀርባው ተኝቶ በዝምታ ማንባቱን ቀጠለ::

ሊዲያም ራስ ምታት እናቷን ይወቅረው ገባ:: አልጋዋ ላይ በጀርባዋ ተጋድማ ኮርኒስ ኮርኒሱን እያየች ማንባቱን ተያያዘችው:: በሆዷ ተጋደመች፤ በጐን ዞረች፤ ትራሱ ስር ተወሸቀች:: ከብዙ ጣር በኋላ እንቅልፍ ይዟት ጭልጥ አለ::

ምን ያህል ሰዓት እንዳንቀላፋች ሳታውቀው ባነነች:: የከፍሉ መብራት ጠፍቷል:: አልጋ ልብስም ለብሳለች:: መብራቱን አበራችውና አማንን አልጋው ላይ ፈለገችው:: የለም:: የግድግዳውን ሰዓት ተመለከተች:: ስምንት ሰዓት ላይ ይጠቁማል:: ደነገጠች:: ከአልጋ ወርዳ ወደ ሳሎን ሄደችና መብራት አበራች:: አማን ሶፋው ላይ ከነልብሱ ተኝቷል:: ቆማ በሐዘን ተመለከተችውና ወደ መኝታ ክፍል ተመልሳ ለብሳው የነበረውን የአልጋ ልብስ ይዛ ተመለሰች:: የአልጋ ልብሱን ስታለብሰው ነቃ::

"ተነሳሽ እንዴ፣ ሊዲ?" አላት እንቅልፍ ባጐረነነው ድምፅ::

Scanned with CamScanner

"ሳላስበው እንቅልፍ ጥሎኝ እኮ ነው፡፡" አለችና ከጐኑ ተቀመጠች፡፡ ሰዓቱን ተመለከተና "ገና ስምንት ሰዓት እኮ ነው፡፡ ግቢና ተኚ፡፡"

"አሚ፣ መኝታ ቤት የገባሁት ትቼህ ለመተኛት ብዬ አልነበረም፡፡ ሳላስበው ነው እንቅልፍ የወሰደኝ፡፡ ድንገት ስነቃ ካጠገቤ የለህም፡፡ ብርድ ላይ ትቼህ ስለተኛሁ ይቅርታ፡፡ ግን... ለምን ገብተህ አልተኛህም?" አለችው ልክ እንዳጠፋ ሰው ድምጿ ለስልሶ፡፡

አማን እግሮቹን ሰብስቦ ተቀመጠና አልጋ ልብሱን አብረው ለበሱት፡፡

"ሊዲ፣ አንቺ የዋህና ትሁት ሴት ነሽ፡፡ ለበደልኩሽ በደል እዚህ ጋር መጋደም አይደለም ከቤት ብታባርሪኝም ይገባኛል፡፡ ይቅርታ ለመጠየቅ እንኳ ብቃቱ የለኝም፡፡"

"እስቲ ለምን እንዳደረግከው ንገረኝ፡፡ ቆንጆ ናት?"

ቀና ብሎ ተመለከታትና "ካንቺ በላይ ቆንጆ አይደለችም ሊዲ፡፡" አላት፡፡

"እኔ መሃን ስለሆንኩ ይሆን አሚ?"

"ሊዲ እንዲህ ያለ ሀሳብ በፍፁም አዕምሮዬ ውስጥ የለም፡፡"

"እሺ ንገረኛ!.. እኔጋ ያጣኸውና እሷ ጋር ያገኘኸው ምን ነገር ቢኖር ነው ታዲያ?"

አማን ስለ ሲጻራ በዝርዝር ነገራት፡፡ የዋህና ትሁቷ ሊዲያ ለሲጻራ አነባችላት፡፡ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ላይ ተያይዘው መኝታ ከፍላቸው ገቡና ተቃቅፈው ተኙ፡፡ እሱ ብዙም አላንቀላፋም ነበርና ወዲያውኑ እንቅልፍ ይዞት ሄደ፡፡ እሷ ግን ማንቀላፋት አልቻለችም፡፡ ስለ ሲጻራ ስታወጣና ስታወርድ ሱብሂ አዛን አለ፡፡ ከአልጋዋ ወርዳ ውዱኽ አደረገችና ወደ ፀሎት ክፍል ገባች፡፡

መደበኛ የሱብሂ ስግደቷን ብትጨርስም ከአምላኳ ጋር የምታደርገውን ንግግር ገና አልጨረሰችም፡፡ እንባዋ በጉንጮቿ ላይ እየተንከባለለ ለሲጻራ



ፀለየችላት፡፡ አላህ በመሃሪነቱ ጤናዋን እንዲመልስላትና ዕድሜዋን እንዲያረዝምላት ተማፀነችው፡፡

"አምላኬ እርዳኝ፡፡ የምወደውን ሰው ላለማጣት ስል፣ ትዳሬን ለማፅናት ስል የአጭር ዕድሜ ደስታና ፍቅሯን ነፍጌያታለሁ፡፡ የማደርገው ነገር ትክክል ይሁን ስህተት ተምታቶብኛል አምላኬ፡፡.. ቀሪ ዕድሜዋን በሐዘንና በመከራ ሆና ብታሳልፍ፣ ያደረግኩት ነገር ትክክል ነው ብዬ ምንም እንዳልበደለ ሰው ለመቆም ይቻለኛል?... ፍቅሬን አሳልፌ መስጠትስ የጽድቅ ስራ ነው?... የትኛው ነው ጽድቅ? የትኛው ነው ኩነኔ?... የቱ ነው እውነት?.. የቱስ ነው ስህተት?.. ማንኛችን ነን ትክክል?... ማንኛችንስ ነን ስህተት?... የሁሉም ነገር ትርጉም ተምታታብኝ፡፡

"የማውቀው ነገር ሁሉ እውቀት አልሆንሽ አለኝ፡፡ እባክህ አምላኬ ጽድቅና ኩነኔን የምለይበት ሕሊና ስጠኝ፡፡" ለጥቂት ደቂቃዎች እንደተንበረከከች በዝምታ ስታነባ ቆየችና ተነስታ ወደ መኝታ ቤቷ ገብታ አማን እቅፍ ስር ሽጉጥ ብላ ተኛች፡፡

Scanned with CamScanner

## - 15

ሲጳራ ትምህርቷን እስከ አሥረኛ ክፍል ድረስ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ከተከታተለች በኋላ ነው ወደ አሜሪካ ያቀናችው:: የሁለተኛ ደረጃንና የኮሌጅ ትምህርቷን በአሜሪካ አጠናቅቃ ወደ ሀገሯ እስከተመለሰችበት ጊዜ ድረስ ዩኒሴፍ ውስጥ ተቀጥራ ትሰራ ነበር:: በካንሰር መጠቃቷን ካወቀችና ከፍቅረኛዋ ቤን ጋር ከተለያየች በኋላ ጓዟን ጠቅልላ ወደ ሀገሯ በመመለስ፣ ዩኒሴፍ ውስጥ ስትሰራ ባገኘችው ተሞክሮ ወላጅ አልባ የሆኑ እና ከችግረኛ ቤተሰብ የተገኙ ሕፃናትን የሚረዳ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት መስርታ በሰብዓዊ ስራ ላይ ተሰማርታለች::

አማንና ሊዲያ በሲጳራ ጉዳይ ላይ በተነጋገሩ በነጋታው፣ አማን ለሲጳራ ደወለላትና ለምሣ ተገናኙ:: የባጥ የቆጡን እያወሩ ምሳ ከተመገቡ በኋላ ከሊዲያ ጋር የተፈጠረውን ነገር ነገራት:: ሲጳራ ሳቅ ጨዋታዋ ጠፍቶ፣ በምትሰማው ነገር ደንግጣ ፀጥ አለች:: በመጨረሻም:-

"አማንዬ፣ ራስ ወዳድ ሆኜ የራሴን ደስታ ስቆፍር አንተን ችግር ውስጥ ከተትኩህ::" ብላ ቆዘመች::

"ራስሽን አትውቀሺ:: የሁሉም ነገር መንስዔ እኔ ነኝ:: አሁንም ቢሆን ደግሞ... ሁሉንም ነገር ለማስተካከል ዕድሉ አለን:: አይመስልሽም?"

"አይደል?!" አለች እንደደነዘዘች:: "ልክ ነህ:: በእኔ የተነሳ ትዳርህን ማጣት የለብህም:: ማታ ከተፈጠረው ነገር በኋላ አሁን መገናኘታችን



ራሱ ችግሩን ማባባስ ነው:: ለነገሩ ራስ ወዳድ ሆኜ እንጂ ከቤን ጋር የተለያየሁት ከሌላ ሴት ጋር ተኝቶ ስላገኘሁት አይደል?"

"ራስሽን መውቀስሽን አቁሚ:: ጥሩ ጓደኞች መሆን እንችላለን:: እህት ትሆኚኛለሽ፣ ወንድም እሆንሻለሁ:: በማንኛውም ነገር ጎንሽ መገኘት እፈልጋለሁ:: ይሄንን ምንም አይለውጠውም:: አይደል እንዴ?" ብሎ ሊያፅናናት ሞከረ::

"እኔ እንጃ አማንዬ... ይሄን ለማድረግ ጊዜው የረፈደ ይመስለኛል:: የረፈደ ጉዞዬን ለመጠገን የሞኝ ሙከራ ሳደርግ ነበር የከረምኩት:: የማይጠገነውን ከመነካካት ይልቅ እንዳለ መተው ይሻል ነበር:: ምን ዋጋ አለው?!" ብላ አቀረቀረች::

"ቀና በይ የእኔ ቆንጆ:: እኔ እንደዚህ አላስብም:: ችግሩን ለማስተካከል አሁንም ዕድሉ አለን::"

ሲጳራ በረጅሙ ተነፈሰች:: እንባ ያነቃትም ትመስላለች:: ዓይኖቿን ከዓይኖቹ አሸሽታ ወደ ሌላ አቅጣጫ መመልከትን መረጠች:: በዝምታ አስተዋላት:: ጥቂት ቆይታ ወደሱ ዞረች::

"አማንዬ፣ አንተ በጣም ጥሩና ውድ ሰው ነህ:: ለእኔ ላለህ አክብሮትና ፍቅር ደጋጋሚ ባመሰግንህም አይወጣልኝም:: ሊዲያም በጣም ቅን ሴት ናት:: ይሄን ቅንነቷን ስለተፈታተንኩት እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ:: _ አሁን ወደ ቤት ልሂድና ሉብ ያለ ውሃ ውስጥ ተነክሬ ራሴን ላረጋጋ::" ብላ ቦርሳዋን አንስታ ታቀፈች::

"ሲጳራ ይሄንን ጉዳይ በደንብ እንድንነጋገርበት እፈልጋለሁ:: ሁሉም ነገር አንቺ እንዳሰብሽው ከባድ አይደለም:: እሺ በይኝና እንማከር::"

"ግዴለህም አማንዬ አሁን ተረብሻለሁ:: ቤት ገብቼ ትንሽ አረፍ ልበል::" አለችው የግዷን እየፈገገች::

"እሺ በኋላ ልደውልልሽ?"

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

"ባይሆን እንደሱ ይሻላል።" ብላው ተነሳች። እሱም አብሯት ተነሳና መኪናዋ ድረስ ሸኝቷት ወደ መኪናው ተመለሰ።

ከሰዓታት በኋላ ግን የሚያስደነግጥ ዜና ተሰማ። አማን ወደ ሲጳራ ስልክ ሲደውል ያነሳችው ጓደኛዋ ትዝታ ነበረች። አማንን የምታውቀው ትዝታ ፈጥኖ ወደ ሆስፒታል እንዲመጣ ጠየቀችው። ሲጳራ በድንገት ታማ ስለደወለችላት ፈጥና በመድረስ ሆስፒታል ወስዳት ኖሯል።

አማን ራሱን ሳያውቅ ነው ከሆስፒታሉ የደረሰው። ትዝታን አገኛት። ሲጳራ ግን ራሷን ስለሳተች ሕክምና እየተደረገላት ነበርና እንዲገባ አልፈቀዱለትም። አማን አለቀሰ።

ትዝታ የተፈጠረውን ነገር እያለቀሰች ነገረችው።

"ስትደውልልኝ.. ድምጿ እየተቆራረጠ ነበር። ድረሺልኝ 'ዲዚ' እያደረገኝ ነው አለችኝ። እኔ ስደርስ ራሷን አታውቅም ነበር። ወድቃ ያገኘኋት ቦታ ላይ ብዙ አስመልስሏታል። ስጮህ የሰሙ ጎረቤቶች ተሯሩጠው ደረሱልኝና በፍጥነት ወደዚህ አመጣናት። ይኸው እስካሁን አልነቃችም። ጠዋት እኮ ጤነኛ ነበረች፤ በአንድ አፍታ እንዲህ ያደርጋል እንዴ?" አለችው።

"ካንሰር እንዳለባት ለዶክተሮቹ ነገርሻቸው?" አላት እንባውን እየጠረገ።

"አዎ። ከነገርኳቸው በኋላ ወደ ቤት ተመልሼ የሕክምና ሪፖርቷንና የምትወስደውን መድኃኒት አምጥቶቼ አሳየኋቸው። ምን ሆና ነው ግን አማን?... በድንገት እንዲህ እንደሚያደርጋት እኮ ነግራኝ አታውቅም።"

አማን በረጅሙ ተነፈሰና "እኔ ነኝ ለዚህ የዳረግኳት።" ብሎ ግድግዳውን በቡጢ ነረተው። ትዝታ ምክንያቱን እንዲያወራት ዓይን ዓይኑን እያየች ጠበቀች።

"ምሳ አብረን ነው የበላነው። በአንድ ጉዳይ ላይ ተነጋግረን ነበር። በዚያ ምክንያት ተረብሻ ስለነበር ወደ ቤት ሄጄ ማረፍ አለብኝ አለችኝ።



ሁኔታዋ ስላላማረኝ ላስረዳት ሞከርኩ። ለጊዜው ማረፍ እፈልጋለሁ በኋላ ደውልልኝ ብላኝ ተለያየን።"

"እንዲህ የሚያደርግ ምን ጉዳይ ቢኖር ነው? እንዲህ ራስ የሚያስት?"

"እንዲህ የሚያደርግ ምን ጉዳይ ቢኖር ነው? እንዲህ ራስ የሚያስት?" ከቆይታ በኋላ ሲጳራ ራሷን ማወቅ ጀመረች። ነርሷ ብዙ እረፍት እንደሚያስፈልጋትና ባትረበሽ መልካም እንደሆነ ብትገልፅላቸውም በብዙ መማፀን ከማየት በቀር እንደማያዋሯት ቃል ገብተው እንዲገቡ ተፈቀደላቸው።

አማን ሲመለከታት በምሳ ሰዓት ያገኛት ሲጳራን አልመስል አለችው። ፊቷ ገርጥቷል። ግሉኮስ ተሰኩቶላታል። ዓይኖቿን ከፍታ ስታያቸው የግዷን ለመፈገግ ሞከረች። እነሱም የግዳቸውን ፈገግታ አሳዩዋት።

አማን ቀረብ ብሎ ግምባሯንና ፀጉሯን ደባበሳት። ከዚያም እጇን ይዞ ጎኗ ተቀመጠና በዝምታ እየተመለከታት አነባ። ሲጳራ በደከመ ድምፅ፤

"አማንዬ" ብላ ጠራችው።

"አይዞሽ የኔ ቆንጆ አሁን ደህና ትሆኛለሽ። ነርሷ እረፍት ያስፈልግሻል ብላለች። ለማውራት አትሞክሪ እሺ?"

"አይ!.. አሁን እኮ.. ደ... ደህና ነኝ። ትዙ... ቁጭ በይ።" ትዝታ ያለንግግር ተቀመጠች።

"ትንሽ አዙሮኝ እኮ ነው። በ.. በጣም ታመምኩ እንዴ?" አለች ወደ ግሉኮሱ ላስቲክ ተመልከታ።

"አይ ደህና ነሽ። 'ሬዚስታንስ' ስለሚያስፈልግሽ ነው ቆንጅዬ።" አለቻት ትዝታ።

አማን ከዶክተሩ ጋር ስለሁኔታዋ ተወያየ። ዶክተሩም ካለባት ችግር አንፃር ጭንቀት ማብዛት እንደሌለባትና ለጊዜው ቢያንስ እስከ ነገ ድረስ እዚያው ቆይታ ክትትል ማድረግ እንደሚገባት ገለፀለት። አማን ሆስፒታል አድሮ ሊያስታምማት ቢፈልግም ሲጳራ ወደ ቤት ሄዶ ጠዋት

ቢመለስ እንደሚሻል አጥብቃ ስለነገረችውና ትዝታም ለማስታመሙ ከሷ እንደማይሻል ስላሳመነችው፤ ለእራት የሚሆን ምግብ ከሆቴል አምጥቶላቸው አመሻሹ ላይ ወደ ቤቱ ተመለሰ::

የሊዲያን ግንባር ስሞ፣ ጃኬቱን አወለቀና በዝምታ ተቀመጠ:: ሊዲያ መረበሹን ተረድታለች:: "ምን ሆነሃል እሚ?" አለችው ጎኑ እየተቀመጠች::

ዞሮ ተመለከታትና "ሲጳራ በድንገት ታማ ሆስፒታል ገባች::" አላት ሐዘን በለበስ ገፅታና በደከመ ድምፅ::

"ምን?!..." በድንጋጤ አፏን በመዳፏ አፈነች:: "የአላህ!.." ከየት መጣ ሳይባል እንባዋ ወረደ:: "እንዴት?.. ት... ትናንት ደህና አልነበረችም?"

የአማንም እንባ ወረደ:: "ዛሬ... ምሳ ሰዓት ተገናኝተን ነበር፣ ሊዲ:: ..." በረጅሙ ተነፈሰና "ትናንት ካንቺ ጋር የተፈጠረውን ነገር ነገርኳት:: በጣም ነበር የደነገጠችው:: እህትና ወንድም መሆን እንደምንችልና... በማንኛውም ጊዜ ጎኗ መገኘት እንደምፈልግ ቃል ገባሁላት::... እሷ ግን... በተፈጠረው ነገር በጣም ተረብሻ ሄደች:: ከሰዓታት በኋላ ሰደውልላት ጓደኛዋ አንስታ ሆስፒታል እንደገባች ነገረችኝ::"

"የአላህ!... አሁን እንዴት ናት እሺ?"

"ትንሽ ሻል ብሏታል:: ዶክተሩን አናግሬው ለዚህ የዳረጋት ከፍተኛ ጭንቀት እንደሆነ ነው የነገረኝ:: እስከ ነገ ድረስ ሆስፒታል ቆይታ ክትትል እንዲደረግላት እዚያው ነው ያለችው::"

"ታዲያ እንሂድና እንደርላታ:: እዚያ ሰው አላት?" አለችው ተጨንቃ:: አማን በገረሜታ አንገቱን ነቅንቆ አቀፋትና ደረቱ ላይ ለጥፏት አናቷን ሳመው::

"ጓደኛዋ አድራላታለች ሊዲ::... እንዴት ያለሽ ጥሩ ሴት እንደሆንሽ በምን ቃል ልንገርሽ?"

"ይኸው ነገርከኝ አኮ::"



"ሲጳራ ራሷ፣ ምሳ ሰዓት ላይ በጣሙ ቅን ሴት እንደሆንሽ ስትነግረኝ ነበር::"

ሊዲያ ቀና ብላ አየችውና "ታውቀኛለች እንዴ?" ብላ ጠየቀችው::

"ስላንቺ በጣም ብዙ አጫውታት ስለነበር በዝና በደንብ ታውቅሻለች::" ብሎ ግድግዳውን መመልከት ቀጠለ:: ለአፍታ ያህል ሁለቱም በየራሳቸው ሀሳብ ነጎዱ::

"አላህ አለ፤ ምንም አትሆንም:: ዱዓ እናደርግላታለን:: ጠዋት ግን አብረን ሄደን እንጠይቃታለን:" ብላ ዝምታውን ሰበረችው::

"ጥሩ ሀሳብ ነው ብለሻል ሊዲ?... አንቺን ስታይሽ ደግሞ ይብስ ትረበሽ ይሆናል::"

"እሱስ ልክ ነህ:: ታዲያ እንዴት ይሻላል?" አልመለሰላትም::

"በቃ በጠዋት ቁርስ ላዘጋጅላትና አንተ ትወስድላታለህ:: አሁን ገብተን እንስገድ:: በዚያውም እንፀልይላታለን::" ብላ ብድግ አለች:: አማንም ዑዱኹ ለማድረግ አብሯት ተነሳ::

## - 16 -

ዛሬ ወደ ራሴ የሚመልሰኝ አስገራሚ ታሪክ ገጠመኝ፡፡ በእልፍ አዕላፍ ጥልፍልፍ መስመሮች የተሞላውን የዕጣ-ፈንታ ሰንጠረዥ የሰው ልጅ እንዴት ሊረዳው ይቻለዋል?... ጥቂቱን እንኳ መረዳት መቻል ትልቅ ስጦታ ነው፡፡ ከዚያ የላቀ መረዳት ግን ተዓምር ነው ሊባል ይገባል፡፡

ከወራት በፊት በነበረኝ ግንዛቤ "የሁሉም ነገር ዕጣ-ፈንታ በፈጣሪ መዝገብ ላይ ተከትቧል፡፡" የሚለውን ነገር በከፊል ስቀበል በከፊል ደግሞ አይዋጥልኝም ነበር፡፡ "የአንድ ሰው ነፍሰ ገዳይነት ቀድሞውንም በዕጣ ፈንታ መዝገቡ ላይ ተፅፎ ከሆነ፤ ያ ሰው ከመወለዱ በፊት የተፃፈውን ዓይነት ሰው ከመሆን ውጪ አማራጭ ላይኖረው ነው፡፡ ታዲያ በምንም ዓይነት መልኩ ነፍሰ-ገዳይነቱን ሊገታው ካልቻለና ከተፃፈው ውስጥ ጠብ የሚልም ነገር ከሌለ፤ እንደምን 'ነፍሰ-ገዳይ' ተብሎ ከገሃነም ይጣላል?" ብዬ ነው የምሟገተው፡፡

ከዚህም ሌላ አንድ ሰው ሲሞት፣ "እንዲህ ቢያደርግ ኖሮ!.. ወይም 'ይሄንን ብናደርግ ኖሮ ይተርፍ ነበር፡፡' ሲባል ሁሌም ምላሹ 'አይ!.. ምንስ ቢደረግ ፈጣሪ ቀድሞ ከቆረጠለት ቀን አንዲትም ሰከንድ መጨመር አይቻል!" የሚል ነው፡፡ ይሄ አባባል የሚገልፀው፣ የሁሉም ሰው ዕድሜ አስቀድሞ የተቆጠረና ከቀኗ ውልፊት እንደማትል ነው፡፡ ይሄም እንደማይዋጥልኝ ምክንያቴን አቅርቤ እማጓት ነበር፡፡

ምክንያቴም "እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደሃ ሀገራት የሰው አማካይ ዕድሜ



ከ40 ዓመት በታች ሲሆን፤ በሥልጣኔ በገፉ ሀገራት ደግሞ አማካዩ የሰው ዕድሜ 70 ዓመት ድረስ ይጠጋል፡፡› የሚል ነው፡፡ በደሃ ሀገራት በረሃብ ሳቢያ ሰው ያለ ዕድሜው ይረግፋል፡፡ በቀላሉ ሊድኑ የሚችሉ በሽታዎች በቂ ሕክምና ባለመኖሩ ሳቢያ ብዙ ሕዝብ ይጨርሳሉ፤ በዚህም ምክንያት የሕዝቡ አማካይ ዕድሜ አጭር ሊሆን ችሏል፡፡

በሥልጣኔ በገፉ ሀገራት ደግሞ የተሟላ የምግብ አቅርቦት በመኖሩና በቂ ሕክምና ስለሚገኝ፤ ህዝቡ በቀላሉ ሊድኑ በሚችሉ በሽታዎች ሳቢያ ለሞት አይደርስም፤ ለዚህ ነው አማካዩ ዕድሜ ከፍ ያለው፡፡ 'ታዲያ የእያንዳንችን ዕድሜ አስቀድሞ ስለተወሰነ ነው? ወይንስ ዕድሜን ከፍና ዝቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ከኢኮኖሚና ከቴክኖሎጂ ጋር ቁርኝት ያላቸው ምክንያቶች ስላሉ ነው ይሄ የሆነው?' በማለት የሰው ልጅ ዕድሜ አስቀድሞ የተወሰነ ያለመሆኑን እሞግታለሁ፡፡

እግዚአብሔር ፍፁም ዲሞክራሲያዊ በመሆኑ ለነፍሳችን ባህሪያትን ከትቧል፡፡ እንደ ሕሊና፣ አዕምሮና ስሜት ሁሉ ፈቃድ የሚባል ባህሪን በነፍሳችን አትሟል፡፡ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ 'በገነት ካሉት ዛፎች መካከል ከዚህ ዛፍ አትብላ፣ ከበላህ ሞትን ትሞታለህ' ብሎ ለአዳም ነግሮታል፡፡ እንደ እኔ አመለካከት ይሄ ተምሣሌታዊ ንግግር ነው፡፡

'ከበላችሁ ትሞታላችሁ፤ ካልበላችሁ ዘለዓለማዊ ናችሁ፡፡' የሚል ፈቃድ ላይ የተመሰረተ ትዕዛዝ ነው፡፡ ከዚያ ዛፍ ፍሬ እንደሚበሉ አስቀድሞ ፅፎ ቢሆን ኖሮ ከተፃፈው ውጪ የሚሆኑበት ምንም ተዓምር የለምና እነሱን የሚቀጣበት ምንም ምክንያት አይኖርም ነበር፡፡ ያስቀጣቸው የእነሱ ፈቃድ ወይንም ምርጫ ነው፡፡ ፈቃዳቸው መብላት ሆነና ከገነትም ተባረሩ፤ ሞትንም ሞቱ፡፡

ስለዚህ ከዛፉ ፍሬ ከመብላታቸው በፊት አስቀድሞ የተፃፈው የዕጣ-ፈንታ መዝገባቸው እኛ እንደምናውቀው የልብ ወለድ ወይም የታሪክ

Scanned with CamScanner

መጽሐፍ፣ አንድን መስመር ብቻ ተከትሎ ታሪክን የሚያሰፍር ሳይሆን፤ ከሁለት መስመሮች (አቅጣጫዎች) የላቀና እንዲያውም ብዙ ጥልፍልፍ መስመሮችን እየተከተለ የተከተበ ነው ማለት እችላለሁ::

ፈቃዳቸው ከዛፉ ፍሬ ያለመብላት ቢሆን ኖሮ፣ ከዚያ በኋላ ያለው ታሪካቸው:- 'አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ በሰላምና በደስታ ለዘላለም ሲኖሩ፤ አቤልና ቃየል ሲዋደዱና ሲተሳሰቡ፤ ሞት፣ ምቀኝነት፣ ተንኮል፣ ጥላቻ እና የመሳሰሉት ባህሪያት በሰው ልጅ ከነመኖራቸውም ሳይታወቁ..' እንዲህ ያሉ ብዙ የሰላምና የፍቅር ታሪኮችን ልናይም እንችል ነበር::

ከዛፉ ፍሬ ከበሉም በኋላ ቢሆን፣ ቃየል አቤልን ካልተመቀኘ እንዲህ፣ እንዲህ ይሆናል፤ ከተመቀኘ ግን ልክ እንዳነበብነው ይገድለዋል:: ከዚያም ይሄ ከሆነ እንዲህ ይከሰታል፤ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ እንዲያ ይሆናል.. እያለ እልፍ አዕላፍ የሕይወት ፍሰት ጎዳናዎችንና ጥልፍልፍ መስመሮችን ያካተተ የዕጣ-ፈንታ መዝገብ እንደሚሆን አምናለሁ::

ይሄ ጥልፍልፍ የዕጣ-ፈንታ መዝገብ፣ ጥልፍልፍ ጎዳናን ቢሆንና እኛ ደግሞ መኪና ብንሆን፣ ሹፌሩ ፈቃዳችን ነው:: ይሄንን መዝገብ የምንኖረው በፈቃዳችን የመረጠነውን መስመር (ጎዳና) ይዘን በመጓዝ ነው:: በፈቃዳችን ሹፌርነት ከአንዱ ጎዳና ወደሌላው እየተጠማዘዝን ሁሉንም ጎዳናዎች በአንዴ መርገጥ ስለማንችል ከምንጓዝበት ጎዳና (ከመረጥነው መስመር) ውጪ ካሉት ሌሎች እልፍ አዕላፍ የሕይወት ጎዳናዎች (ዕጣ ፈንታዎች) ጋር ስንተዋወቅና ምን ሊመስሉ እንኳ እንደሚችሉ ፍንጣቂ ምስላቸው ሳይኖረን አሊያም ከእነአካቴው መኖራቸውን እንኳ ሳናውቅ ተጀምረን እናበቃለን:: በተከተልነውም ሆነ ባልተከተልናቸው የሕይወት ጎዳናዎች ውስጥ የተለያዩ ገጠመኞች፣



የተለያዩ የዕድሜ ጣሪያዎችና የተለያዩ የሞት መንስዔዎች ተፅፈዋል አላለሁ:: ይሄ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያመንኩበት መደምደሚያ ነው::

እዚህ ላይ "ከእኛ ፈቃድ ውጪ በሌሎች ሰዎች አስገዳጅነት ሳቢያ የሚገጥሙን ብዙ ነገሮች አሉ:: አንድ ሰው መኪና ሲያሽከረክር ፍፁም ጥንቃቄ ቢያደርግም አንዱ ተከለፍልፎ መጥቶ ሊወጣበት ይችላል:: የእኔ እንዲህ ያለውስ ነገር ምን ሊባል ነው?" የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: የእኔ መልስ ግን "አሁንም ቢሆን ያንን ጎዳና ተከትለን የተጓዝነው በፈቃዳችን ነውና በዚያ ጎዳና ውስጥ የሚገጥሙንን መልካምም ሆኑ መጥፎ ነገሮችን ሁሉ እናስተናግዳለን::" የሚል ነው::

ስለዚህ ነገሩን ሳጠቃልልው ነፍሰ ገዳዩም፣ ነፍሰ ገዳይ ከመሆኑ በፊት ላይሆንየሚችልበትብዙአማራጭየሕይወትጎዳናዎችነበሩት::የተከተለው ጎዳና ግን ለዚህ አብቅቶታል:: ሟቹም በሕይወት ሊቆይ የሚችልበት ብዙ መንገዶች ሊኖሩ ይችሉ ነበር፤ ነገር ግን በመረጠው ጎዳና እና በዚያ ጎዳና ውስጥ በተከሰቱት ነገሮች ሳቢያ ያ ሳይሆን ይቀራል:: ከፈቃዳችን ውጭ የሚሆኑ ነገሮች ግን አሉ እላለሁ:: መወለዴ በእኔ ፈቃድ የሆነ አይደለም:: ከማን እንደምወለድ፣ የት ሀገር እንደምወለድ እና መቼ እንደምወለድ እኔ አልወሰንኩም::

ለማንኛውም ዛሬ ሰርግ ነበረብኝ:: አማንና ሊዲያም እንደኔው ታዳሚዎች ነበሩ:: የዕንቁጣጣሽ የአክስት ልጅ ስለምታገባ በአማን መኪና ሆነን ሰርጉን ለማጀብ ሙሽሪት ቤት ተገኘን:: ዕንቁጣጣሽም እዚያው ተቀላቀለችን::

ዓይኖቼ አንድ አጭር ሰው ላይ ተተክለው ቀሩ:: ሰውየው የሚያምር ጥቁር ሱፍ ለብሶ ከወዲያ ወዲህ እየተራወጠ ለሰዎች ትዕዛዝ ይሰጣል:: ሰዎቹም እየታዘዙት ይራወጣሉ:: ዕንቁጣጣሽ መፍዘዜን ተመልክታ "ምነው?.. ምን ሆንክ?" ብላ ጠየቀችኝ::

Scanned with CamScanner

ዓይኖቼን ከሰውዬው ላይ ሳልነቅል በጣቴ ወደ ሰውየው እየጠቆምኳት፡ "ያ ሰውዬ.." አልኳት:: ጥቆማዬን ተከትላ ተመለከተችና፤

"ውይ!.. ታውቀዋለህ እንዴ?" አለችኝ:: ድምጿ ውስጥ መደነቅ ስለሰማሁ ዞሬ ተመለከትኳትና "አዎ አውቀዋለሁ::" አልኳት::

"አባዬ እኮ ነው:: እንደውም ዛሬ በዚህ አጋጣሚ አስተዋውቃችኋለሁ::" አለችኝ እየሳቀች:: "ምን?!" አልኳት ደንግጬ::

"ፈራህ እንዴ?.. ባሌ እንዲሆን የመረጥኩት ፍቅረኛ አለኝ ብዬ ነግሬዋለሁ:: ለትውውቁ ይሄ ሰርግ ጥሩ አጋጣሚ አይመስልህም?"

"የአምላክ ያለህ!" ብዬ አጉተመተምኩኝ::

"ምን አልክ?" አለችኝ ስላልሰማችኝ::

"አይ ምንም" አልኳት መደነቄን ለመደበቅ እየታገልኩ::

"ግን የት ነው የምታውቀው?"

"ሌላ ጊዜ ነው የምነግርሽ::" አልኳት:: 'እንዳሻህ' እንደማለት ትከሻዋን ሰበቀች:: መቼም ሰው ማስጨነቅ አትወድም::

ብዙም ሳትቆይ ትታኝ ከግርግሩ ተቀላቀለች:: ሰውየውን በዓይኔ ፈልጌ አገኘሁትና እመለከተው ገባሁ:: ምንም አልተጠራጠርኩም፤ ራሱ ነው:: ከአማን ጋር በተገናኘሁበት የመጀመሪያ ዕለት፣ በጠዋቱ በባዶ አንጀቴ ያቀመሰኝን ጥፊ መቼም አልረሳውም:: ይሄ ሰውዬ የዕንቁጣጣሽ አባት ሆኖ መገኘቱ እንዴት አይድነቀኝ? ተደንቄ የማላውቀውን ያህል ተደነቅኩ::

"ምን ዓይነት የሚገርም አጋጣሚ ነው?" ብዬ ብቻዬን አወራሁ:: መቼም ይሄ 'አጋጣሚ' የሚለው ቃል በጣም ከመለመዱና ከሱ የተሻለም ቃል ባለማግኘቴ ተሽቀዳድሞ አፌ ላይ ይመጣብኛል:: ከሱ ይልቅ ግን ወንድምየው 'ግጥምጥሞሽ' የተሻለ ነው::

ያ አጭር መላጣ ሰውዬ ባቀመሰኝ ጥፊ ሳቢያ ከአማን ጋር ተገናኘንና ቤተሰብ ለመሆን በቃን፤ ሰላምና እርካታን አግኝቼ መኖርም ጀመርኩ:: የአማን የጀንያ ከሰል ደግሞ አንድ ሰንበት እማማ ቤት ወስዶ ከዕንቁጣጣሽ ጋር አገናኘኝና ፍቅርን አግኝቼ መኖር ቀጠልኩ:: የዚህ ሁሉ በረከት መነሻ ደግሞ በዚያ ሰውዬ አዕምሮ ታስቦ በእጁ ፈፃሚነት የቀመስኩት ጥፊ ነው:: እና... ያ ሰውዬ በገዛ እጁ ልጁ ላይ ሲጥለኝ አይደንቅም?... የሚደንቅ ግጥምጥሞሽ ነው እንጂ!... የዕጣ- ፈንታ ትርጉም እንዲህ የተወሳሰበና ሊረዱትም የሚከብድ ነው:: ኮብላይ ካህን ያኔ የሌሊት ቀማኞችን ምሳሌ አድርጎ የነገረኝ የዕጣ-ፈንታ ምስጢር በእንዲህ መልኩ ተገለፀ::

የዚያን ዕለት በንዴት ተሞልቼ መላጣውን በማጎን ከመሬት ልቀብረው ያሰብኩት ትዝ ሲለኝ ድንጋጤ ተሰማኝ:: በዚያች ሰከንድ ውስጥ ፈዝዤ ከመቆም ይልቅ እንዳሰብኩት ብመታው ኖሮ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ሳስበው ያንን ባለማድረጌ እግዚአብሔርን አመሰገንኩት::ብመታው ኖሮ ግርግር ይነሳል:: ምናልባትም አማን ያን ዕለት እንዳለኝ ልብ ድካሙም ተነስቶ ከፉ ነገር ሊደርስበት ይችላል:: እኔም እስር ቤት እገባለሁ:: የሰውየው ሕይወት ከአደጋው ብትተርፍ እንኳ ዕድሜ ልኩን የማይረሳኝ ጠላቱ ሆኜ ከልቡ እሰፍራለሁ:: የዚያን ዕለት በሰከንድ ዕድሜ ልዩነት ያመለጥኩት የሌላኛው ዕጣ ፈንታዬ መስመር ይሄን ሊመስል እንደሚችል አልተጠራጠርኩም:: በዚያች ሽራፊ ጊዜ ፈዝዤ በመቆሜ ሳቢያ የዕጣ ፈንታዬን መስመር ለወጥኩት:: እልፍ አዕላፍ ጊዜ እግዚአብሔር ይመስገን::

ምናልባት እዚህ ጋር 'ሰውየውን መትተኸው ቢሆንና ከዚያ ድርጊት በኋላ በሚገጥምህ የሕይወት ጎዳና የተሻለ ነገርም ሊገጥምህ ይችል ቢሆንስ?' የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል:: ያንን ማንም አያውቅም:: ግን የተከተልኩት መንገድ ትክክለኛ መሆኑን 'እጁ፣ ልጁ' ላይ በጣለኝ



Scanned with CamScanner

ግጥምጥሞሽ መልስ አግኝቻለሁ:: በውጤቱም ሰለም፣ ፍቅርና እርካታን አግኝቻለሁ::

ግርግሩ ሲረጋጋ ዕንቁጣጣሽ የፈገግታ ሙዳይ መስላ ወደኔ መጣችና እጄን ይዛ እያካለበች ወደ ቤት ውስጥ ይዛኝ ገባች:: ከሰውየው ፊት ስቆም በድንጋጤ ተንቀጠቀጥኩ:: አስተዋወቀችን:: ለሰውየው ከአዘቦት ገጠመኞቹ ውስጥ እንደ አንዱ ነበርኩና ከነመፈጠሬም እንደሚያውቀኝ አላወቀም:: በደስታ ተሞልቶ ተዋወቀኝ:: እንዲያውም አቅፎ ሳመኝ:: ጭራሽ ባለውለታው እንደሆንኩ ነገረኝ::

ዕንቁጣጣሽ የመጨረሻና ብቸኛዋ ሴት ልጁ ናት:: ሁለት ታላላቅ ወንድሞቿ አውሮፓ ነው ያሉት:: እናም እነሱ ጋር ካልሄድኩ ብላ አስቸግራው ነበር:: እሱ ደግሞ የዓይኑ ማረፊያ እና የሟች ሚስቱ አምሳያ የሆነችውንና ከምንም በላይ የሚወዳትን ውድ ልጁን ሩቅ መላከ የማይታለም ሆኖበት ይሄን ይሄን እየነገረ ከአጠገቡ እንዳትርቅ ይማፀናት ነበር::

በመጨረሻም የዕንቁጣጣሽ አውሮፓ የመሄድ ሀሳብ ከእነአካቴው ተለወጠ:: ምክንያቱንም ነግራዋለች:: ለእኔ የአውሮፓ ሀሳቧንም ሆነ፣ ሀሳቧን የለወጠችበትን ምክንያት ነግራኝ አታውቅም:: ለአባቷ ግን ፍቅር እንደያዛትና ቀሪ ዕድሜዋን ፍቅር ካስያዛት ፍቅረኛዋ ጋር ተጋብታ እዚሁ በደስታ ለመኖር እንደወሰነች አበሰረችው:: እሱም ከዚህ በላይ የሚፈልገው ነገር አልነበረምና ተደሰተ:: ዛሬም ይሄን ደስታውን ነገረኝ:: አመሰገነኝም:: ይባስ ብሎ ዛሬ እንደተዳረችው የእህቱ ልጅ ሞቅ ያለ ሰርግ ደግሶ እንደሚያጋባን አበሰረን::

ከዕንቁጣጣሽ አባት ጋር እንደተለያየን ይሄንን አስገራሚ ታሪክ ለአማን ለማጫወት ተጣድፌ ወጣሁና በዓይኖቼ ፈለግኩት::



- 17 -

ሲጳራ ጤናዋ ተመልሶ ስራ ጀመረች:: በሰርጉ ማግስት አማን ለሁለት ቀናት ያህል ከከተማ የሚያወጣው ጉዳይ ገጥሞት ሄደ:: ማታ ሊዲያ ቡና አፍልታ ጨዋታ ጀመርን:: ጨዋታችን ወደ ሰሞኑ ዐብይ ጉዳያችን ተንደርድሮ ገባ:: ይህቺ የምትደንቅ ትሁትና ቅን ሴት ሌላ የሚያስደንቅ ጨዋታ አጫወተችኝ:: ጊዜው ሲጳራ በታመመች በሁለተኛው ምሽት፣ ቦታው በአማንና በሊዲያ መኝታ ቤት ባልና ሚስቱ ተቃቅፈው ተኝተው እየተጨዋወቱ ሳለ ነው::

"አሚ፣ ትናንት የሲጳራን በእኛ ጉዳይ ሳቢያ ብቻ ታማ መተኛት ከሰማሁ ጀምሮ ይሄ ነው የማልለው ህመም እየተሰማኝ ነው:: ሕሊናዬ ከፉኛ እየሞገተኝ ነው:: የፅድቅና ኩነኔ ትርጉም ጠፍቶብኛል:: ከእሷ ጋር ሳለህም ፍቅርህን አላጎደልከብኝም ነበር:: እሷ ግን አንተን እንደምታጣ ባወቀችበት ቅፅበት ታማ ለመተኛት በቃች:: ፍቅርህ ሳይጎድልብኝ ከእሷ ላይ ገፈፍኩህና እርቃን አስቀረኋት:: ይሄ መብቴ መሆኑን አውቃለሁ:: ግን... መብት ጽድቅ ይሆናል እንዴ?... በሞት ጎዳና ላይ በተስፋ ቢስነት እየተራመደች ካለች ሴት ላይ የአጭር ዘመን ደስታዋን፣ ፍቅሯን፣ ብርሃኗን 'የእኔ ነው፤ መብቴ ነው' ብዬ ብነጥቃት፣ ይሄ ጽድቅ ነው ኩነኔ?... ከዚህ በኋላ ያንተን ፍቅር እንደማታገኝ ስትረዳ እንዴት በቅፅበት የአልጋ ቁራኛ እንደሆነች አታይም?... ታዲያ ያደረግኩት ትክክል ነው ማለት እንዴት እችላለሁ?... እና አሚ፣ ይሄንን አጭር ዕድሜዋን ደስታዋ ጨልሞ፣

ተስፋዋ መንምኖ፣ የአልጋ ቁራኛ እየሆነች እንድታሳልፈው መፍረድን ሕሊናዬ አይቀበለውም:: ደስታና ተስፋዋን ልመልስላት ይገባኛልና ከዚህ በፊት እንደነበራችሁት ሁኑ::" አልኩት::

"እሱ ግን በግርምት እያየኝ 'ሊዲ፣ ገር ስለሆንሽ ብቻ ገርነትሽን መጠቀሚያ ላደርገው አልፈልግም:: በምድር ላይ ያለች ማንኛዋም ሴት ባሏን አሳልፋ አትሰጥም:: አንቺም በተፈጠረው ነገር ራስሽን መኮነን አይገባሽም::' አለኝ::

"እስቲ አንድ ነገር ልንገርህ፣ አሚ:: ነገ ተነስተህ ሁለተኛ ሚስት አገባለሁ ብትለኝ ህጋችን ነውና ልቃወምህ አልችልም አይደል እንዴ?... በማግባትህ ፈቃደኛ ባልሆን እንኳ ግፋ ቢል ማድረግ የምችለው ፍቺ መጠየቅ ነው፤ ሊያውም ህጋችንን አፍርሼ:: ካልሆነ ግን መቀበሌ ግድ ነው:: እና በሁለቱም መንገድ ቢሆን ከእኔ ሌላ ሴት አቅፈህ ትተኛለህ:: ከሁለተኛዋ ሚስትህ ጋር ስትተኛ በሃላል ነው ይባልልሃል:: ከሲጻራ ጋር ስትተኛ ደግሞ በሐራም ነው ይባልብሃል:: ለእኔ ለመጀመሪያዋ ሚስትህ ግን በሁለቱም ውስጥ ያለው ድርጊት አንድ ነው- የሌላ ሴት ገላ አቅፈህ ተኝተሃል:: ለሰሚና ተመልካቹም ቢሆን ሁለቱ ድርጊቶች የሚለያዩት በአንዲት ብጣሽ ወረቀት ነው:: ተመልከት እንግዲህ... በሃላሉ እና በሐራሙ መካከል ያለው ልዩነት ብጣሽ ወረቀት ሆነ::... በእርግጥ ሰው ነኝና ከአቅሜ በላይ የሆነን ነገር መሸከም አልችልም:: ከጤንነቷ በስተቀር ስለምታደርጉት ነገር መስማት አልፈልግም:: ሌላም ሰው አምጥቶ እንዳያወራልኝ ሁሉንም ነገር በድብቅና በምስጢር አድርጉት:: የእኔ አቅም እዚህ ድረስ ነው:: እዚህ ድረስ ለመሸከም ዝግጁም ፈቃደኛም ነኝ:: ይሁን በለኝ አሚ::" ብዬ ተማፀንኩት::

" 'ሊዲ የእሷን ሁኔታ ለማስተካከል ሌላ መንገድ እፈልጋለሁ:: ሆ... ሀ! ምን ዓይነት ሴት ነሽ ግን?! አለኝ:: ምን ያህል እንደሚያስብላት አውቃለሁ:: የእሱም ሕሊና ፈተና ውስጥ እንደወደቀም አውቃለሁ:: የእሱም ሕሊና ፈተና ውስጥ እንደወደቀም አውቃለሁ:: ከዚህ በፊት ያደረገውን ሁሉ ያደረገው እኔን ከመጥላት አሊያም የግሉን ደስታ ለማጋበስ ብሎ ሳይሆን እሱ የሚሰጣት ፍቅር ለሷ ትልቅ ትርጉም እንዳለው ስለተገነዘበ መሆኑንም አምናለሁ:: ታዲያ የእኔን ፈቃደኝነት ለምን አልቀበልም አለ?... ከእሷ ጋር ሳለ ይመራ የነበረው በሕሊናው ነበር:: አሁን ከእኔ ጋር ሆኖ ግን በልማድና በምን ትለኛለች መመራቱ አይደል?



"እኔ ግን የሕሊናዬን ቁስል ለማስታመም ስል ወግን ከውስጤ አውጥቼ ጥዬ ነው ፈቃደኝነቴን የገለፅኩለት:: እናደደኝ:: ታዲያ አግባትና ሐራሙን ሃላል አድርገዋ!" ብዬ ጮህኩበት:: ደንግጦ ተመለከተኝ:: ወዲያውኑ ተረጋጋሁና እንደውም እንደዚያ ይሻላል:: ህጋችንም ይፈቅዳል:: ከምንፈራው ሐሜትና ወሬም ይገላግለናል:: ይሄ የእኔ ውሳኔ ነው:: 'እሺ ብላት ትታዘበኛለች' የሚለውን አጉል ሀሳብህን ከልብህ አውጣውና አድርገው:: ስለሷ እያሰብኩ ከምሰቃየው የሚብስ እና የዕድሜ ልክ ቁስል የሚሆንብኝ ሌላ ነገር የለም::" አልኩት::

አሚ እያመነታ "ግን እኮ እሷ ሙስሊም አይደለችም::" አለኝ::

"ፈረስአለኝብዬሜዳውንሁሉአልጋልብበትም::እኔመጋለብየምችለው እዚህ ድረስ ብቻ ነው:: ቀሪው ግልቢያ የእናንተ ነው:: ተመካከሩበትና አሳውቁኝ:: ከተስማማችሁ ደስ እያለኝ ቆሜ አድራችኋለሁ:: ለአሁኑ ግን በዚህ ጉዳይ ላይ ከዚህ በላይ መነጋገር አልፈልግም" አልኩት'' አለችኝና በዝምታ ቡናዋን መቅዳት ጀመረች:: የቀዳችውን ቡና አቀበለችኝ:: ጨዋታዋን ግን አልቀጠለችልኝም::

"እሺ ከዚያስ?" አልኳት ዝምታዋ ሲበረታብኝ ጊዜ መጨረሻውን ለማወቅ ጓጉቼ:: ቀና ብላ አየችኝና እየሳቀች "ከዚያስ?!... ከዚያማ

Scanned with CamScanner

ተቃቅፈን ተኛን፡፡ ቀሪው የባልና ሚስት ጉዳይ ነው፡፡ እሱንም ልትዕፈው ፈለግክ እንዴ?... በእኔ በኩል ያለኝን ሁሉ ተናግገርለሁ፡፡" አለችኝ፡፡

"ግን... የምር በደስታ ቆመሽ ትድሪያቸዋለሽ?"

"አዎዋ! ያጣሁትን የሕሊና ዕረፍት ከማግኘት የሚበልጥብኝ ምን ነገር አለ? የእሷንም ደስታ ቆሜ ለማየት ያበቃኛል፡፡ ደግሞም ህጋችንም ይፈቅዳል፡፡ የእኔም አባት ሦስት ሚስት ነው ያለው፡፡ በእርግጥ በእኛ በወጣቶቹ ዘመን ባልን ሌላ ሴት እንዲያገባ መገፋፋት ሞኝነት መሆኑን አውቃለሁ፡፡ ምናልባት በሌላ ሁኔታ ላይ ቢሆን ኖሮ እንኳን ልገፋፋው ራሱ ላግባ ቢለኝ እንኳ እሺ አልለውም ነበር፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን ከዚህ የተሻለ መፍትሔ ሊኖር አይችልም፡፡ የሁላችንም ሰላምና ደስታ ይመለሳል፡፡ አይመስልህም?"

"ምናልባት ግን... አትሰልምስ ከሆነ?"

"እሱን አላውቅም፡፡ ለፍቅር ስንል መከፈል የሚገባንን መስዋዕትነት በየድርሻችን መክፈል ያለብን ይመስለኛል፡፡ ደግሞም ለዚህ የሚሆን ልብ ታጣለች ብዬ አላስብም፡፡" አለችኝ በልበ ሙሉነት፡፡

ሕይወት በቀናት ጅረት ላይ በፍጥነት መፍሰሷን ቀጠለች፡፡ ይሄ ግልቢያ የት ያደርስ እንደሆን ለማወቅ ሁሉ ነገሬን ዓይንና ጆሮ አድርጌ በፅሞና መከታተሌን ቀጠልኩ፡፡ አንድ ቅዳሜ ዕለት አማን፣ ሲጳራና እኔ በአንድ ተቀምጠን እየተጫዋወትን ሳለ ሲጳራ አንድ ትልቅ ሀሳብ አመጣች፡፡ ባቋቋመችው ድርጅት ውስጥ አብሬያት እንድሰራና፤ የጀመረችውን የበጎ አድራጎት ተልዕኮ እንዳግዛት ጠየቀችኝ፡፡ ባልጠበቅኩት ጥያቄዋ ተደንቄ እያየኋት ሳለ አማን በፈገግታ ተሞልቶ ትከሻዬን ቸብ አደረገና "ምን ዝም ትላለህ? ሱቅ ቆሞ ጨው መስፈር ይሻልሃል?... ያንን ሊሰሩ የሚችሉ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እንደውም እስካሁን ድረስ በእነሱ



እንጀራ ላይ ነው የቆምከው፡፡ ላንተ የሚመጥነው ስራ ይሄ ነው፡፡" አለኝ፡፡

"ኧረ እኔም ዓይኔን አላሽም!... ድንገተኛ ሆኖብኝ ነው ፀጥ ያልኩት፡፡ ታዲያ መቼ ልጀምር?" ብዬ ጠየቅኳት፡፡

"ከነገ ወዲያ ሰኞ ነዋ፡፡ እኔና አንተን የሚያመሳስለን ብዙ ነገር አለን፡፡ በእርግጠኝነት ተተኪዬ መሆን የምትችለው ሰው አንተ ነህ፡፡ ካንተ የምማረው ብዙ ነገር እንዳለ ሁሉ፤ ከእኔ የምትማረውም ብዙ ነገር አለ፡፡ ወገብህን አስረህ መዘጋጀት ነው እንግዲህ" ብላ ሳቀች፡፡

ሰኞም መጣ፡፡ የእኔም የሥራ ቦታ ተቀየረ፡፡ ውሎዬ ሲጳራ ጋር፤ ኑሮዬ አማንና ሊዲያ ጋር ሆነ፡፡ የአዲስ እውቀት መንገዴ ተጀመረ፡፡ ሰኞ ዕለት የተቀየረው የእኔ ሥራ ብቻ አይደለም፡፡ ሲጳራም መስጅድ ተገኝታ እስልምናን ተቀበለች፡፡

"አሽሃዱ አንላ ኢላሃ ኢላ አላህ ወአሽሃዱ አነ ሙሐመዱን ረሱል አላህ፡፡" ብላ ሸሃዳ ያዘች፡፡

በመጀመሪያው እሁድም አማንና ሲጳራ ኒካህ አደረጉ፡፡ ኒካህ የማድረጉ ሥነ-ሥርዓት ላይ የታደምነው ሙሽሮቹ፣ ደጋሽና ዳሪዋ ሊዲ፣ እኔና እንቁጣጣሽ፣ የሲጳራ ጓደኛ ትዝታ፣ እንዲሁም ሦስት ሽማግሌዎች ነበርን፡፡

የዚያን ዕለት ሊዲን ያየ ሰው ተደንቆም አያባራ፡፡ እንዲት ሴት ባሏን በዳረችበት ዕለት እንዴት እንዲህ መደሰት ትችላለች?... እንዴት ይበልጥ የሚያስደነግጥ ውበት ትጎናፀፋለች?.. እንዴት እንዲህ ሊያምርባት ይችላል?... ሌላ ድንቅ ነገር ሆናለች፡፡

ያለነው የሲጳራ ቤት ውስጥ ነው፡፡ ሥነ-ሥርዓቱ ተካሄደ፡፡ ከድግሱ ተቋደስን፡፡ ቤቱ ደስታ ብቻ ሆነ፡፡ የእነ ሃጂ ምርቃትና የእኛ እሜንታ

ተደጋገመ:: በደራው ጨዋታ መሃል ሲዲ "ዛሬ መናገር የምፈልገው ነገር አለኝ::" ብላ የሁላችንንም አትኩሮት ወሰደች::

"ለዛሬው ደስታ ስላበቃን አላህ ለዘለዓለሙ የተመሰገነ ይሁን::"ብላ ጀመረች::

"የዛሬው ደስታችን በዚህ ብቻ አላበቃም:: አላህ ተወርቶ በማይጠገበው መሃሪነቱ ለከት በሌለው ቸርነቱ ልጅ ሰጥቶናል::"እንባዋ መውረድ ጀመረ:: ሳግ ንግግሯን አቋረጣት::

እኛ ግን ምን ማለት እንደፈለገች ሰላልገባን በድንጋጤ አፍጥጠን እያየናት ነው::

"ሁላችሁም እንኳን ደስ አላችሁ:: አርግዣለሁ::" ብላ አስደነገጠችን::

ድንጋጤያችን ግን ያልተጠበቀ ወሬ ሲሰማ እንደሚያደርገው ዓይነት ነበርና ወዲያውኑ ፈነጠዝን:: አማን ተፈናጥሮ ተነስቶ ተጠመጠመባትና ተቃቅፈው ተላቀሱ:: ሲጻራ ፊቷ በደስታ ብርሃን ተጥለቅልቆ ከተቀመጠችበት ተነሳችና ሊዲያን እቅፍ አድርጋ አገላብጣ ሳመቻት:: ስማ የምትጠግባትም አትመስል:: እኔ፣ ዕንቁጣጣሽ እና ትዝታ ከዚያም ሦስቱ ሽማግሌዎች ተከታትለን ደስታችንን አቅፈን በመሳም ገለፅንላት::

ሲዲ፣ አማንን ባገባች በጥቂት ወራት ውስጥ እንደምታረግዝ እርግጠኛ ሆና ጠብቃ ነበር:: ሳይሆን ሲቀር ፍርሃት ተሰማት:: እናም ቁርጡን ለማወቅ ሆስፒታል ሄዳ የመሃንነት ምርመራ አደረገችና መሃን መሆኗን ተረዳች:: ሦስት የተለያዩ ሆስፒታሎች ብትሄድም መልሱ ያው ሆነ:: ዛሬ ግን አረገዝኩ እያለች ነው:: ተደነቅን::

እነ ሃጂ ደጋግመው "አልሃምዱሊላሂ!" ይላሉ:: "ለአላህ ምን የሚሳነው ነገር አለ? የልብሽን ገርነት ተመልከቶ አላህ ልጅ ሰጠሽ::"

ሐድራው ደራ፣ ሳቅ ነገሰ:: የላይኛውና የታችኛው ከንፈር ላይሳሳሙ



ተጣሉ፤ ጥርስ በመሃል ነፃ ወጣ:: ዱዓ ስንቀበል እንኳ በፈገግታ ሆነን ሆነ::

"አሚ" ብላ ተጠራች:: አማን ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ጨዋታችንን አቋርጠን ወደ ሲዱ ዞርን:: "ያኔ፣ ዛሬ እውን ስለሆነው ጉዳይ መጀመሪያ የተነጋገርንበት ቀን ትዝ ይልሃል? አንተና ሲጻራ እንድትጋቡ የጠየቅኩህ ዕለት?"

አማን "አዎ፣ አንድ ወር ሊሆነው ነው መሰል::" አላት የምትናገረውን ነገር ለመስማት በጉጉት ተሞልቶ::

"የዚያን ዕለት ከተኛን በኋላ በጣም የሚገርም ሕልም አይቼ ነበር::"

ሃጂ "ኼር!" አሉ ሕልሙን እንድትነግረን በሚጋብዝ ድምፅ::

"እኔ፣... እኛ ቤት ሳሎን የተቀመጥኩ ይመስለኛል:: የግቢያችን በር በሃይል ይንኳኳል:: ለመከፈት ተነስቼ ልወጣ ስል ሃሰን በሩን ለመከፈት ሲሄድ አየሁትና ቆሜ ተጠባበቅኩ::" 'ሃሰን' ሊዲያ እኔን የምትጠራበት ስም ነው::

"... ሃሰን ትንሿን በር ከፍቶ ከውጭ የቆመውን ሰው ከተመለከተ በኋላ ፈገግ ይልና ትልቁን በር ብርግድ አርጎ ይከፍተዋል:: አንድ ነጭ ጊሙ የተንዠረገገና ልክ እንደ ቄስ ጥምጣም የጠመጠመ ሰውዬ፣ ከፊቱ ሸከም የተጫነ አህያ አስቀድሞ ከሃሰን ጋር እያወሩ ወደ ቆምኩበት መጡ::"

ይሄንን ስሰማ ልቤ ቀጥ ያለች ያህል ደነገጥኩኝ::

'ምንድነው እያወራች ያለችው?' አልኩኝ በልቤ:: ሲዲ ቀጠለች::

"እጠገቤ እንደደረሱ ቀና ብሎ ተመለከተኝና 'አህያው ላይ የተጫነው ወርቅ ነው፤ ያመጣሁትም ላንቺ ነው::... አውርጂና ውሰጂው::' አለኝ::..."

'የአምላክ ያለህ!.. ኮብላይ ካህንና የአህያው ላይ ወርቅ!' በልቤ ውስጥ ጮህኩኝ:: ሲዲ ሕልሟን ቀጠለች:: "ይከብደኛል

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ብዬም አላሰብኩ... ብቻ አንከብከቤ ሳወርደው፣ ሃሰን በግርምት ሲመለከተኝ አየሁት፡፡ ከዚያ... ሰውየውን 'ግባና ምሳ ብላ' አልኩት፡፡ 'ስለጋበዝሸኝ ብቻ እንደበላሁ ነው የቆጠርኩት፡፡ አሁን ልሂድ፣ ብዙ ስራ አለብኝ፡፡ ደህና ከረሚ፡፡ ይሄን ልብሽን ጠብቂው፡፡' ብሎኝ አህያውን ከፊት አስቀድሞ ከሃሰን ጋር እያወሩ ወጡ፡፡ እኔም ከዓይኔ እስኪርቁ ድረስ ቆሜ እየኋቸውና ሽከሙን ይዤ ወደ ቤት ገባሁ፡፡"

አንደኛው ሸማግሌ "እንዲህ ነው እንጂ!.. አላህ ቀድሞ አሳይቶሻል! እውነትም ንፁህ ልብ አለሽ፡፡ የተሰጠሽ ወርቅ እኮ ልጅ ነው፡፡" አሉ እየተደነቁ፡፡ እኔ ግን በድንጋጤ ይሁን በገረሜታ ፈዝዣለሁ፡፡

እዚህ ከተማ ከመግባቴ የሰዓታት ዕድሜ አስቀድሞ ከካህኑ ጋር የተነጋገርነው ነገር ከእነምስሉ ፊቴ መጥቶ ድቅን አለ፡፡

'ለመሆኑ ይሄ አህያ የጫነው ሸከም ምንድን ነው?'

'ወርቅ ነው፡፡'

'መቼም አንተ ይሄን ያህል ሀብት አያስፈልግህም፡፡ የማን ንብረት ቢሆን ነው?'

'ከእኔ ሀብት ጋር ሲወዳደርማ ይሄ ብናኝ ነው፡፡ ከምትገምተው በላይ የገዘፈ ሀብት አለኝ፡፡ ይሄ ንብረት ግን የአንድ መልካም ሰው የአደራ ንብረት ነው፡፡...'

ሲዲያ "አዎ፣ በሕልም ወርቅ ሲታይ ልጅ እንደሆነ እናቴ ስትናገር እሰማለሁ፡፡" ብላ ንግግሯን ስትቀጥል ከሄድኩበት ተመልሼ እሰማት ጀመር፡፡

"በመጀመሪያ እኔም ልጅ አድርጌ ፈታሁት፤ ወዲያው ደግሞ የማይመስል ነገር ሆነብኝና ቸላ አልኩት፡፡ ... የወር አበባዬ በሳምንቱ መምጣት ነበረበት፤ ቀረ፡፡... በሌላኛው ሳምንትም ጠበቅኩት የለም፡፡ ስለ ህልሙ በድጋሚ ማሰብ ጀመርኩ፡፡ ከትናንት ወዲያ ግን ይሄ



ህልም ተዓምር ይሁል ብዬ ደመደምኩና ሆስፒታል ሄጄ ተመረመርኩ፡፡ እውነትም ህልሙ ተዓምር ነበር፡፡ ዶክተሩ ማርገዜን አበሰረኝ፡፡ ማመን ተሳነኝና ትናንትና በድጋሚ ሌላ ሆስፒታል ሄጄ ተመረመርኩ፡፡ በትክክል በተዓምር አርግዣለሁ፡፡ የአንድ ወር ፅንስ በሆዴ ይዣለሁ፡፡

ደስታዬን ከዛሬው ደስታ ጋር አንድ ላይ እንድናከብረው ስለፈለግኩ እንደምንም ጨክኜ ለዛሬ አሳደርኩት፡፡" አለችን ፀሐይ መስላ፡፡

"ሆ... ሆ! አጃኢብ ነው!" አልኩኝ ሳላስበው ድምፄን ከፍ አድርጌ፡፡

"አዎ፡፡ አጃኢብ ያሰኛል እንጂ፡፡ ደግሞ እኮ የዚህ ልጅ በሩን ወ_ ገግ አርጎ መክፈት!... ትልቅ ቀልብ ያለህ ልጅ ነህ፡፡" አሉ ሃጂ ወደኔ ዞረው፡፡

"እኔን በጣም የገረመኝ..." አለች ዕንቁጣጣሽ "ሊዲ፣ ሙስሊም ሆነሽ ሳለ፤ እንዴት ከሸኽ ይልቅ ቄስ ልታይ ቻልሽ?" እውነትም ፊቷ ላይ ታላቅ ገረሜታ ይነበባል፡፡

"እኔ ምን አውቄ ዕንቁ" አለች ሊዲያ በፈገግታ፡፡

"አዬ ልጄ!... የአላህ ሥራ ረቂቅ ነው፡፡ እሱ በመረጠው ረቂቅ መንገድ ነው ተዓምራቱን የሚገልፀው፡፡ ሲያሻው በዲዳ በኩል ሕልም ይልክብሻል፡፡ የሱን ሥራ እኛ ልንመረምረው ሥልጣኑም፣ አቅሙም የለንም፡፡ ነቢያችን ሰለላሁ ወአለይሂ ወሰለም የመጀመሪያዎቹ ተከታዮቻቸው በሀገራቸው ላይ ሲታሰሩና ሲገደሉ፣ ጥቂት ተከታዮቻቸውን ለማትረፍ 'ወደ ሀበሻ ሀገር ሂዱ፤ እዚያ ፍትህ የማያዛባ የእውነት ንጉሥ አለ፡፡' ብለው አይደለ ወደ ኢትዮጵያ የላኳቸው?... ታዲያ ያኔ ኢትዮጵያ እኮ የቄሶች ሀገር ነበረች፡፡ ንጉሱም ክርስቲያን ነበር፡፡ ከነቢያችን፣ ሰለላሁ ወአላይሂ ወሰለም በላይ ለአላህ የቀረበ የለም፡፡ አላህ ለእርሳቸው የገለፀላቸውን ምስጢር እኛም ተረድተን ቢሆን ኖሮማ ይቺ ዓለም መች እንዲህ መያዣ መጨበጫ ታጣ ነበር?...

"እኛ ነን ችግር ፈጣሪዎቹ ልጄ፡፡ ልዩነታችንን ከማጥበብ ይልቅ

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

እያሰፋነው፣ የማንተዋወቅ ያህል የተራራቅነው፣ እኛው ነን:: የአላህ ጥበብማ ብዙ ነው::" ብለው መለሱላት ሃጂ:: እኔ ግን ልጮህ ትንሽ ቀርቶኛል:: የልቤን አንጉርጉሮ ማድመጡ እና እዚህ የሚወራውንም ነገር መስማቱ፣ ሁለት ስራ ሆኖብኝ ከማናቸውም በላይ ተዳከሜያለሁ:: ደግሞም ጭንቅላቴ እየተወጠረ መጥቶ እንዳይፈነዳ ሁሉ ፈራሁ::

"ኧረ ይሄን ተዓምር ልናገረውና ይውጣልኝ::" አልኩኝ ድምጼን ከፍ አድርጌ:: እንዴት እንደተመለከቱኝ ሳይ ያመመኝ እንደመሰላቸው ጠረጠርኩ:: ድምጼን ዝቅ አደረግኩና "አሚ፣... ያኔ መጀመሪያ የተገናኘን ዕለት ከአንድ ካህን ጋር ተጉዤ እንዴት እዚህ እንደደረስኩ ያጫወትኩህ ትዝ ይልሃል?... ከዚያም ቀን በኋላ ስለ ካህኑ በጥቂቱም ቢሆን አጫውቼሃለሁ::" አልኩት:: አማን አናቱን በመነቅነቅ ብቻ እንደሚያስታውስ ነገረኝ::

"... ዕንቁ እንኳ ስለ ካህኑ በደንብ አውርቼልሻለሁ:: ለሌሎቻችሁ ግን እንግዳ ታሪክ ስለሆነ ላጫውታችሁ::" ዕንቁጣጣሽ ፊት ላይ አዲስ ስሜት ታየ:: አሁን ገና የሊዲያን ህልም ከእኔው ኮብላይ ካህን ታሪክ ጋር አያይዛ እንደተረዳችው መደነቋ ላይ አነበብኩት::

የኮብላይ ካህንን ታሪክ በዝርዝር ሳወራቸው ሁሉም ከሊዲያ ህልም ጋር አገጣጥመውት ተደነቁ:: በመጨረሻም "... የሚገርማችሁ ያንን በአህያ የተጫነ ጆንያ ሙሉ ወርቅ የሚያፍስ ሰው ማን ይሆን? ምን ዓይነት ጀብዱ የሰራ ጀግና ይሆን?... እያልኩ ስለዚያ ዕድለኛ ሰው ያላወጣሁ ያላወረድኩበት ጊዜ የለም:: እኔ ሞኙ ያን ጀግና ወንድ አድርጌ ደምድሜያለሁ:: የሚገኘውም ከእኔ ሩቅ የሆነ ሥፍራ ላይ እንደሚሆን ጥርጥር ገብቶኝም አያውቅ:: ወርቁንም ቢሆን እኔ እንደማውቀው ጥሬ ወርቅ አድርጌ ወስጄዋለሁ:: ይኸው ዛሬ... ሊዲ፣ እናንተን ከደነቃችሁ በላይ ያስደነቀኝንና ያስደነገጠኝን ተዓምር አምጥታ ፊቴ ዘረገፈችው::



ለካስ ጀግናዋ ሴት ናት፤ ለካስ ጀግናዋ እዚሁ ጎኔ አለች:: ለካስ እኔም፣ የዚህ ዕጣ ፈንታ ተዋናይና የቅርብ ታዛቢ ነኝ:: አይደንቅም?... እንዴት ያ በእውን ያየሁት ታሪክ ተዓምር ሆኖ በሊዲ ህልም ውስጥ ምስጢሩ ተፈታ?... ሰዎች ይሄ መደነቅ ከምሸከመው በላይ ሆኖብኝ ልፈነዳ ደርሻለሁ:: ከመፈንዳቴ በፊት ይሄንን ተዓምር ልንገራችሁ ብዬ ነው ይሄንን ሁላ ታሪክ ማውራቴ::" አልኳቸው:: ሁሉም በየበኩሉ ተደነቀ፣ ተንጫጫ::

ሊዲያከተቀመጠችበትተነስታወደኔመጣችናፊቴተንበርክካአቀፈችኝ:: ተቃቀፍን::

'ምን ዓይነት ተዓምር ነው?!' ተባባልን- ሁላችንም::

"ይሄስ እውነትም ለመሸከም የከበደ ተዓምር ነው!" አሉ ሃጂ:: ሊዲ ቦታዋ ተመልሳ ተቀመጠች:: ዕንቁ፣ ስለ ኮብላይ ካህን አዲስ እውቀት ለላገኘሁና ምስጢሩም ስለተፈታልኝ ተደስታ፣ አናቷን ትከሻዬ ላይ አጋደመችው:: አማን በአድናቆት ዓይኑን ከእኔ ላይ መንቀል አልቻለም::

"አንተን ቤቴ እንድትኖር ማድረጌ አላህ ቢወደኝ ነው::" አለኝ::

"እናሳ!" አሉ ሌላኛው ሼኽ:: "ይኸው በሩን ወለል አርጎ ከፍቶ መልዕክተኛውን ከነወርቁ አስገባው እኮ!" አሉ የደስታ ሲቃ እያነቃቸው::

"ግን በዚህ ጉዳይ ላይ የእኔ ተሳትፎ ምንም ነው ማለት እችላለሁ:: ጉዳዩ ከእኔ ሳይሆን ከሌላ ሰው ጋር የተያያዘ ነው:: እኔ፣ እግዚአብሔርን ፍቅር፣ ሰላምና እውቀትን እንዲሰጠኝ ዕለምነው ኖሬያለሁ:: ካለሁበት ነቅዬ ካህኑን በመከተል እዚህ ከመጣሁ በኋላ ፍቅርና ሰላምን አግኝቻለሁ:: እውቀትንም መንገዴ ላይ እየገበየሁ ነው የመጣሁት:: እኔን ከእናንተ ጋር ያቆየኝ የዚህን ምስጢር መጨረሻ እንዳውቅና እውቀትን በመጠየቄ ምክንያት እውቀቴን እንዳሰፋ ነው:: የእኔ ተሳትፎ ከዚህ አያልፍም::

Scanned with CamScanner

"እንደተረዳሁት ከሆነ ሊዲ ደግሞ ያጣሽውና አላህን ደጋግመሽ የጠየቅሽው ነገር ነበር:: ያም ልጅ እንደሚሆን አልጠራጠርም:: ህልምሽን ከእኔው እውን ታሪክ ጋር ገጥመን ስናየው ፀሎትሽ የሰመረው አንድ ትልቅ ፈተና በማለፍሽ ነው:: ቅንነትንና ትህትናን የሚፈትን፣ ጀግንነትን የሚጠይቅ ከባድ ፈተና:: ይሄን ፀጋ ላንቺ ያመጣው ሰው ካንቺ የሚፈልገው ትልቅ ነገር አለው፤ ያንን ትልቅ ነገር ደግሞ ልትሰጪው ችለሻልና የተመኘሽውን ፀጋ ተሸለምሽ:: እንግዲህ ያ ሌላ ሰው ማን ነው?... መልስ የሚሻው እንቆቅልሹ ምን ነበር?... በወርቁ ፈንታ የሚፈልገው ሌላ ትልቅ ነገር ምን ነበር?... የሚለው ነው ሌላኛው ምስጢር::

"በእርግጥ ይሄንን አውቃለሁ ብሎ መነሳት ለራስ ከልክ በላይ ግምት መስጠት ይሆናል:: ልቤ ግን አንድ ነገር እንድል ትገፋፋኛለች::" ፊቴን ወደ ሲጳራ መለስኩና::

"ሲጳራ፣ እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅሽ:: ከምንም በላይ አብልጠሽ የምትፈልጊውና እግዚአብሔር እንዲሰጥሽ ከልብሽ የለመንሽው ነገር ምንድን ነው?" አልኳት::

ሲጳራ በፈገግታ ሆና "ፍቅርን ነው:: የምመኘውን ዓይነት ፍቅረኛ እንዲሰጠኝ ነበር ቀን ከሌት ስለምነው የኖርኩት::" ብላ መለሰችልኝ::

"እና አማን የምትመኚው ዓይነት ፍቅረኛ ሆኖ አገኘሽው? የዘወትር ፀሎትሽ ተመልሶልሻል?" አልኳት::

"አዎ:: የማታ የማታ፣ ምድር በጠበበችኝና ሰማይ በተደፋብኝ፣ ጨለማ በዋጠኝ ሰዓት አገኘሁት::" ብላ አማንን በስስት ተመለከተችው::

"ሊዲ፣ አማንን ለሲጳራ የፈቀድሽ ዕለት ነው ይሄንን ህልም ያየሽው:: የፀነሽውም ያን ዕለት ነው:: ታዲያ... አንዳችሁ ለሌላችሁ ፀሎት ምላሽ ለመሆን በቅታችኋል ከማለት ውጪ ምን ማለት ይቻላል?... ይሄ ድንቅ



ተዓምር አስተቃቅፎ ሊያመሰጋግናችሁ ይገባል:: ያለ ስጦታዬ ምስጢር ልግለፅ ብዬም ከሆነ እግዚአብሔር ይቅር ይበለኝ::" ብዬ ንግግሬን ደመደምኩ::

ሊዲያና ሲጳራ በደስታ ተቃቅፈው ተሳሳሙ:: ከዚህ በኋላ በዓለም ላይ ከሚገኙ ጣውንቶች ሁሉ ከሁለቱ የሚልቅ ፍቅር ያለው የሚገኝም አይመስለኝም::

ሐድራው ይበልጥ ደራ:: ዱዓው እንደ ደራሽ ውሃ ተንፏለለ:: ቤቱ ፍቅር ሆነ:: እኔ ግን በሁሉም ነገር ውስጥ ገባ ወጣ እያልኩ ብንሳፈፍም አንድ ያልተመለሰ ጥያቄ ልቤን ሰቅዞ ይዟታልና ነፍሴ ተጨንቃለች::

"ኩብላዩ ካህን ማን ነው?" እያልኩ ማሰላሰል ይገባለሁ:: አሁንማ እንደኔው ስጋ የለበሰ ፍጡር ሁሉ አልመስል አለኝ:: መንፈስ ሆነብኝ::

'ሲጀመር ምስጢሬን ሁሉ ዘርግፎ ነገረኝ:: እንድከተለው ጠየቀኝ:: ራሴን በሚገባ እንድረዳ ብርሃን ሆነኝ:: ከዚያም ከዕንቁ ጋር ቤተ-ክርስቲያን በሄድኩበት ዕለት፣ ቄሱ ስለ መልከ ጼዴቅና አብርሃም ሲያስተምሩ፣ በመልከ ጼዴቅ እና በሙሴ አማች ካህኑ ዮቶር እግር ተተክቶ ከአብርሃም እና ከሙሴ ፊት ቆሞ አየሁት:: ዛሬ ደግሞ በአካል በማታውቀው ሊዲያ ህልም ውስጥ ምኑም ሳይለወጥ መጣ:: ታዲያ ይሄ ሰው ማነው?... ነው ወይንስ ሰው አይደለም? እንደዚህ እንዳልል ደግሞ ለቀናት አብሬው ተጉዣለሁ፤ አብሬው በልቻለሁ፣ ጠጥቻለሁ:: አብሬው አውርቻለሁ:: ማንነቱ ለምን የዚህን ያህል ምስጢር ሆኖ አስቸገረኝ?... ለምን በመልከ ጼዴቅ እግር ተተክቶ ተመለከትኩት? ለምን የምድያሙን ካህን መስሎ ታየኝ?...' ብዬ ደጋግሜ እያሰብኩ ቀና ስል ስድስት ዓይኖች እኔ ላይ ተተክለው ተመለከትኩ:: ደንግጬ እኔም አፍጥጬባቸው ቀረሁ::

የሦስቱ ሽማግሌዎች ስድስት ዓይኖች እንደ ብረት ጠንክረው ንቅንቅ

Scanned with CamScanner

አላሉም:: ጥርሳቸው ቢከደንም የፊታቸው ፀዳል እንደፈገግታ ያበራል:: አስተያየታቸው አንድ ሆነብኝ:: የሆነ ነገር ያዩብኝ ይመስላሉ:: ዓይኔን ሰበር አደረግኩና አፍታ ቆይቼ ተመለከትኳቸው:: አሁንም ያው ናቸው::

‘ምንድነው ጉዱ?’ ብዬ ዓይኔን ወደ እነ አማን ስመልስ እነሱም የእኔንና የሽማግሌዎቹን መፋጠጥ ተመልከተው ሲጠቃቀሱ ደረስኩባቸው:: ተሳሳቅን::

ዕንቁጣጣሽ ወደ ጆሮዬ ቀረብ ብላ “ምን ሆነህ ነው?” አለችኝ::

“ምንም አልሆንኩ:: ይልቅስ በይደር ያቆየሁትን አንድ ታሪክ ልንገርሽ:: ያኔ ሰርጉ ላይ አባትሽን የት እንደማውቀው ጠይቀሽኝ ሌላ ጊዜ እነግርሻለሁ ብዬሽ ነበር::”

“አዎ” አለችና ለመስማት ተመቻቸች:: አጫውትኳት:: እየተገረመች ሰማችኝና ስጨርስ “ወይ አምላኬ!.. እንዴት የሚገርም ታሪክ ነው:: አስቀይሞሃላ?” አለችኝ ጣቶቼን በጣቶቿ እያሻሸች::

“የዚያንዕለትማበጣምተናድጄነበር፡ውሎአያደርግንእንኳንልቀየመው ጭራሽአመሰግነው ጀመር:: የእሱ ጥፊ እኮ ነው ከአማን ያገናኘኝ:: ከአማን ጋር ለእማማ ከሰል ይዘን ስንመጣ ደግሞ አንቺን አገኘሁሽ:: ታዲያ አባትሽን ማመስገን ይነሰኝ እንዴ? ልጄን ለእጅህ ሲል እኮ ነው ጥፊ የለተመ[illegible]::” አልኳትና ተሳሳቅን:: የእሷ ሳቅ ጠንከር ሲልብኝ “ምነው?.. ተንጠራርቶ ሲያቀምሰኝ ታየሽ እንዴ?” ስላት ከሳቋ ጋር እየታገለች “አዎ” አለችኝ::

“ምነው ጨዋታችሁን የግል አደረጋችሁት? ንገሩን እና ሳቁን እናግዛችሁ እንጂ::” አለችን ሊዲ::

“አንድ ምስጢር አጫውቻት ትዝናናብኛለች:: አሚ፣ የ‘ፋዘርን’ ነገር ነግሬያት እኮ ነው::”

“በእሱ ከሆነማ ገና ብዙ ቀን ትስቃለች::” አለ እየሳቀ::



“በነገራችን ላይ አሚ፣ ያንን ከሰል ያመጣልህን ሰውዬ ከዚያ በኋላ አግኝተኸው ታውቃለህ?” አልኩት ድንገት ትዝ ብሎኝ::

“አዎ:: ሦስት አራቴ አግኝቼዋለሁ::”

“እባክህ በድጋሚ ስታገኘው በጣም አመስግንልኝ:: እሱ ያመጣውን ከሰል ትልቅ ዋጋ የሰጡት እማማ ጋር ወስደን በመመንዘራችን ነውኮ ዋጋ የማይተምናትን ይቺን የመሰለች ውብና ውድ ሴት ያስገኘልን::” ብዬ ዕንቁጣጣሽን አቀፍኳት::

“ልክ ነህ:: በደንብ ላመሰግነው ይገባል:: ላንተ ሆነልህ ማለት ለእኔ እንደሆነልኝ ነው:: ከዛሬ ጀምሮ ከዋልኩለት ውለታ በላይ እንደዋለልኝ አድርጌ አስበዋለሁ::” ብሎ መልስ ሰጠኝ::

## - 18 -

ዛሬ ያለሁት አዲስ አበባ ነው፡፡ ከሲጳራ ጋር መስራት ከጀመርኩ ሁለት ወር ሆኖኛል፡፡ ስራዬንም በጣም ወድጄዋለሁ፡፡ ሲጳራ ጥሩ አስተማሪ ሆናኛለች፡፡ ዩኒሴፍ በህፃናት ጉዳይ ላይ የሚሰሩ የተለያዩ ድርጅቶችን ለአስራ አምስት ቀናት ያህል ሥልጠና ይሰጣልና ነው ወደ አዲስ አበባ ከብዙ ወራት በኋላ የተመለስኩት፡፡ አዲስ የገባሁት ትናንት ማምሻውን ሲሆን፤ ሆቴል ነው ያረፍኩት፡፡ እና ዛሬ፣ ከአዲስ ከወጣሁኝ በኋላ በተደጋጋሚ ላደርገው ሳስብና መልሼ ስተወው የቆየሁትን ነገር አደረግኩ፡፡

ዕድላዊት ጋር ደውዬ አገኘኋት፡፡ ከተራራቅን በኋላ ‘እንዴት ሆና ይሆን’ ብዬ ደጋግሜ አስባት ነበር፡፡ ሀሳቤ የመነጨው ለእሷ መልካሙን ሁሉ ከመመኘት እንጂ ከቂምና ከጥላቻ አልነበረም፡፡

ገና ድምጼን ስትሰማ “አንተ!.. በሕይወት አለህ?!” ብላ ጮኸች፡፡ መደንገጧ ያስታውቃል፡፡

“አለሁ ዕድል፡፡ እንዴት ነሽ አንቺ?”

“ለነገሩ የት እንዳለህ ማወቅ አልቻልኩም እንጂ መኖርህንስ በወሬ ሰምቻለሁ፡፡ ግን እንዴት ነህ?”

“በጣም ደህና ነኝ፡፡ አንቺስ እንዴት ነሽ? ጤና ስራ?”

“እኔ በጣም ደህና ነኝ፡፡”



የደወልኩላት አዲስ አበባ ሆኜ መሆኑን ስነግራት እንድንገናኝ ጠየቀችኝና ተገናኝተን ምሳ አብረን በላን፡፡

የማውቃት ዕድላዊት ሳትሆን ሌላ ሴት እስከትመስለኝ ድረስ ተለውጣለች፡፡ ሁኔታዋ ሁሉ አዲስ ሆነብኝ፡፡ ንግግሯ በስሏል፡፡ ያ እኔ የማውቀው ለስላሳ ውበቷ እንኳ ጠንከር ብሎ ብስለት ይታይበታል፡፡ በተለያየንበት ጊዜ የሆነውን ሁሉ አጫወተችኝ፡፡

“ይገርምሃል፡፡ እዚህ ሄድኩ ሳትል ወጥተህ ከቀረህ በኋላ ብዙ ደጋግሜ አሰብኩህ፡፡ ለቀናት ያህል ብቻዬን ሆኜ፣ አንተን ብቻ ሳይሆን ዙሪያዬ ያሉትን ሰዎች ሁሉ እንደ አዲስ መመርመር ጀመርኩኝ፡፡ ከዚህ በፊት ያላስተዋልኳቸውን ብዙ ነገሮች የተገነዘብኩት ያኔ ነው፡፡ አብሬያቸው ስወጣና ስገባ የነበሩት ብዙዎቹን ወዳጆቼን የጊዜ ሰው ሆነው አገኘኋቸው፡፡ ስፈካ እንደሚወሩኝ ንቦች፣ ስጠወልግ ትተውኝ ወደ ሌሎች አበቦች የሚነጉዱ ትሎች እንደሆኑ ተረዳሁ፡፡ ሁሌም በችግሬም በሐዘኔም ጊዜ ከጎኔ ያልጠፋ አንድ ሰው ብቻ አገኘሁ፡፡

“ለእነዚያ ወዳጆቼ የሰጡሁትን ፍቅር፣ ክብርና ምስጋና ግን ለዚያ ሰው ነፍጌው ነበርና በጣም አዘንኩኝ፡፡ ‘ምነው ከመርፈዱ በፊት ይሄንን አስተውዬ በነበር’ ብዬ በጣም ተቆጨሁ፡፡ አንተን መልሼ ማግኘት ባልችል እንኳ እንድሆን ስትመኝልኝ የነበረውን ዓይነት ሴት ሆኜ ለመገኘት ቆረጥኩ፡፡ በቃ.. ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጌ ትቼ ስራዬና የወደፊት ምኞቴ ላይ ብቻ አተኮርኩ፡፡ በሄድኩበት ሁሉ ምርኩዝ ሆነህ፣ ሲደክመኝም ተሸክመህ ታደርሰኝ እንደነበር የተረዳሁት ያለፍኩበትን መንገድ ዞር ብዬ ሳየው ነው፡፡ ያ በቀላሉ ስለደረስኩበት ሜዳ ይመስለኝ የነበረው መንገድ ስንት ዳገትና ቁልቁለት ፣ ስንት አፋፍና ገደል እንደነበረበት ያኔ ነው የታየኝ፡፡

“ወደፊትም ሜዳ ሳይሆን ብዙ ውጣ ውረድ እንደሚጠብቀኝ

ተገለፀልኝ፤ ሲያውም ለብቻዬ ሆኜ፡፡ እናም መንገዴን ቀጠልኩ፡፡ ያለ ጫማ ተራምዶ የማያውቅ እግር መንገድ ሲበዛበት ይላላጥና ይቆስል የለ? ስጀምር እንደዚያ ነው የሆንኩት፡፡ እያረፍኩና ሕመሜን እያስታመምኩ ገፋሁበት፡፡ ለካስ አብረን በነበርንበት ጊዜ ሳላስበው ካንተ ብዙ ተምሬያለሁ፡፡ ዛሬ እንዴት ያለ ጎበዝ ወጥቶኛል መሰለህ፡፡" አለችኝና ፈገገች፡፡

"ይሄን በመስማቴ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ ሁሌም የምመኝልሽ እንዲህ እንድትሆኚ ነው፡፡" አልኳት በሰማሁት ነገር ተደስቼ፡፡

"አንተስ እንዴት ነህ? በጣም እንደተስማማህ ነው የማየው፡፡"

"በምመኘው ዓለም ውስጥ እየኖርኩ ነው፡፡ ለዚያ ነው..." አልኩና ስላለሁበት ሁኔታ አዲስ አበባ ስላመጣኝ ጉዳይ አጫወትኳት፡፡

"ዋው!... በጣም የሚያስቀና ነገር ነው የነገርከኝ፡፡ ከፈቀድክልኝ.. በዚህ የበጎ አድራጎት እንቅስቃሴ ላይ የበኩሌን ለማበርከት ዝግጁ ነኝ፡፡"

"አመሰግናለሁ ዕድል፡፡ እኔም እርዳታሽን ለመቀበል ወደ ኋላ አልልም፡፡"

ትንሽ አመነታችና "አሁን ታዲያ እንዴት ነው?... ሌላ ፍቅረኛ አገኘህ?" ብላ ጠየቀችኝ በፈገግታ፡፡

"አዎ፡፡ በጣም የማፈቅራት ቆንጆ ፍቅረኛ አለችኝ፡፡ እንደውም የሚቀጥለው ሳምንት እዚህ ስለምትመጣ አስተዋውቅሻለሁ፡፡ ጊዜውን አልቆረጥንም እንጂ ከጥቂት ወራት በኋላ ልንጋባ ነው፡፡" ብዬ መለስኩላት፡፡

"በጣም በርትተሃል፡፡ ለማንኛውም ያሰብከው እንዲሳካ እግዚአብሔር ይርዳህ፡፡"

"አሜን" ለአፍታ ዝም ተባባልን፡፡

"ግን ይቅርታ አድርገህልኛል?.. መናገር ከምችለው በላይ በድዬሃለሁ እኮ፡፡"

"ይቅርታ ካደረግኩልሽ ቆይቻለሁ፡፡ እንደውም ከይቅርታም አልፌ



እያመሰገንኩሽ ነው የኖርኩት፡፡ ካንቺ ጋር ያሳለፍኩት ዕድሜ ያኔ ባይመስለኝም ብዙ እውቀት የሸመትኩበት ውድ ጊዜ እንደነበር የኋላ ኋላ ተረድቻለሁ፡፡ አመሰግንሻለሁ፡፡ ባይሆን አንቺ ይቅርታ አድርጊልኝ፡፡"

"እኔ?!... ምን አድርገሽኝ?"

"የሰው ንፁህ የለም፡፡ ሁላችንም እንበድላለን፤ እናጠፋለን፡፡"

"የበደልከኝ ነገር እንደሌለ አውቃለሁ፤ ግን ይቅር መባባሉ ጥሩ ነው፡፡ ሳላውቀው እና ሳታውቀው የበደልከኝ ነገር ካለም ይቅር ብዬሃለሁ፡፡" አለችኝ፡፡

አዲስ በምቆይበት ወቅት በድጋሚ እንደምንገናኝና ከዕንቁጣጣሽም ጋር እንደማስተዋውቃት ቃል ገብቼ ብዙ ተመስጋግነንና ተመካከረን ተለያየን፡፡ ዕድላዊትን ከሸኘሁ በኋላ በአግራሞት ተውጬ አሰላሰልኩ፡፡ ለዓመታት ዛሬ ያገኘኋትን ዓይነት ዕድላዊት ለመፍጠር ብዙ ስክብና ስንድ ብኖርም አልተሳካልኝም ነበር፡፡ ዛሬ ግን እኔ በሌለሁበት ያቺ ዕድላዊት ተገኝታለች፡፡ እሷን ለመለወጥ የሄድኩበት መንገድ ስህተት እንደሆነ ዛሬ ተገለፀልኝ፡፡ ዕድላዊትን ብርቱና አስተዋይ ሊያደርጋት ይችል ከነበረው የሕይወት ውጣ ውረድ ያለመጠን ሸሸጌያት፤ ሸክሙን ሁሉ ራሴ በመሸከሜ የጥንካሬ ምንጯን አድርቄው ነበር፡፡ የሕይወትን ውጣ ውረድ በጫንቃዋ መሸከም በመቻሏ ለዛሬው ብስለት በቅታለችና የእኔ መራቅ ለዕድላዊትም ጭምር ጥቅም እንዳስገኘ ተረዳሁ፡፡ ለዚህ በመብቃቷም ተደሰትኩ፡፡

Scanned with CamScanner

## - 19 -

ጊዜው ይነጉዳል:: ሊዲም መንታ ልጆችን ካረገዘች ዘጠኝ ወር ሆናት:: ሲጻራ ሕመሙ እየፀናባት ስለመጣ የሥራውን ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ ወደ እኔ አዘዋውራዋለች:: በዚህ ጊዜ እሷን ማየት ብቻውን ትልቅ ሕመም ነው:: እሷ ግን ከማናችንም ይልቅ ብርቱ ናት::

"ምኑንም ሳልጨብጠው፣ ሳይጣፍጠኝና ሳያረካኝ ካለፈው ያ የዕድሜ ክምር ይልቅ ምኞቴ ተሳክቶ፣ በፍቅር ተከብቤ ያሳለፍኩት ይሄ አጭር ጊዜ ለእኔ ውድ ነው:: ይቆጨኝ የነበረው ይሄንን ሳላይ ብሞት ነበር:: አሁን ግን ሞትን በሳቂ እቀበለዋለሁ::" ትለናለች::

አሁን ሆስፒታል ተኝታ እንክብካቤ እየተደረገላት ነው:: ሊዲያም ልትወልድ ቀናት እንደቀሯት ሐኪም ነግሯቷል:: ከሰዓት በኋላ ሊዲ፣ ጠዋት አብረን ያየናትን ሲጻራን በድጋሚ ሄደን ካላየናት ብላ አዋከባ ጠራችንና ወደ ሆስፒታል ሄድን:: እንዲህ ደከማ እንኳ ዕረፍት አርጊ ብንላትም እሺ ሳትል ነበር ሲጻራን ስታስታምም የከረመችው::

አማን ፀጉሩም ፂሙም አድጐ ሐዘንተኛ መስሏል:: ሲጻራ አትናገር አትጋገር አፍና አፍንጫዋ ላይ ሰው ሰራሽ መተንፈሻ ተገጥሞላት ተኝታለች:: ለሰዓታት በትካዜ ከተቀመጥን በኋላ ሊዲ ሕመም ተሰማት::

"አባክሽን ሊዲ.... ስለ ራስሽም አስቢ እንጂ:: ቤት ሄደሽ ዕረፍት አድርጊ" ብሎ አማን ተቆጣት:: ሊዲን ወደ ቤት ይዣት ተመለስኩ::

ቤት በገባን በጥቂት ደቂቃ ውስጥ ግን ሕመሟ ይበልጥ ፀና:: ምጧ



ሐኪሙ ከነገረን ጊዜ ቀድሞ እንደመጣ ተጠራጠርኩና በፍጥነት ምርመራ ወደምታደርግበት ሆስፒታል ይዣት በረርኩ:: ምጥ መሆኑን ከማረጋገጤ በፊት አማንን ልረብሸው ስላልፈለግኩ ዕንቁጣጣሽን ፈጥና ሆስፒታል እንድትመጣልኝ ጠየቅኋት::

ሆስፒታል ደርሰን ምርመራ አደረጉላት:: በትክክልም ምጥ ነው የጀመራት:: ዕንቁጣጣሽ ፈጥና ደረሰች:: ሊዲን ማዋለጃ ክፍል ሲያስገቧት እኔ አማን ጋር ደወልኩ:: አማን ስልኩን አንስቶ "ዛሬ ጉድ መሆናችን ነው:: ተስፋ ያላት አይመስለኝም::" አለኝ እያለቀሰ::

"ምነው ምን ተፈጠረ?" አልኩት ደንግጬ::

"እያጣጣረች ነው:: ዶክተሩ ከዛሬ አታልፍም ብሎኛል::"

እንባዬን ታግዬ ገታሁት:: " አሚ፣ ቀድመን ያወቅነው እንጂ አዲስ ነገር አይደለም የሚመጣው:: ራስህን አረጋጋ...:: ሊዲም ምጧ መጥቶ ሆስፒታል ወስጃታለሁ::"

"ምጧ?...ገና ቀናት ይቀሩታል አላሉንም እንዴ?" አለኝ ደንግጦ::

"ብለው ነበር:: አሁን ግን ማዋለጃ ክፍል አስገብተዋታል::"

"ወይ አምላኬ... ታዲያ ምን ይሻለኛል?"

"አትጨነቅ አሚ፣ ለሊዲ እኔና ዕንቁ አለን:: አንተ እዚያው ሁንና በየደቂቃው እደውልልሃለሁ:: በተረፈ ፀልይ:: እንፀልያለን:: ከዚያ በላይ እኛ የምናደርገው ነገር አይኖርም::" ብዬ ላፅናናው ሞከርኩ::

"እሺ እሺ... በየደቂቃው ደውልልኝ:: አጠገቧ ልሆን ይገባኝ ነበር::" አለ በደከመ ድምፅ::

"ሊዲ ትረዳሃለች፣ አሚ:: ቻዎ በቃ::" አልኩትና ስልኩን ዘጋሁት:: ዕንቁጣጣሽ " እንዴት ናት?" ብላ ጠየቀችኝ::

" እንጃ ዕንቁ:: በጣም ታማለች ነው የሚለኝ:: ነይ እስቲ ወደዚያ እንጠጋ::"

ወደ ማዋለጃው ክፍል ተጠጋን:: ከደቂቃዎች በኋላ የሕፃን ልጅ ለቅሶ ሰማንና እፎይ አልን:: ደግሞ አንድ ይቀራል:: ግን ሌላኛው እስኪመጣ ድረስ የቀደመውን እንኳ በማብሰር ሳፅናናው ብዬ አማን ጋር ደወልኩኝ:: ስልኩን እንዳነሳው " አረፈች እኮ::" አለኝ ተንሰቅስቆ እያለቀሰ::

" አ አምላክ!" ብዬ ካለሁበት ክፍል ወጣሁ::

" ምን ነበር እኔን በወሰደና እሷን ባተረፈልኝ::" እያለ ማልቀሱን ቀጠለ::

" አሚ እንደዚህ አይባልም:: ማድረግ የሚገባህን ሁሉ አድርገሃል:: አሁን በሕይወት ስላሉት ቤተሰቦችህ ማሰብ ነው ያለብህ::" እንባዬ ቢወርድም ጨክኜ ማፅናናቱን መረጥኩ::

"ሊዲስ?... ሊዲ እንዴት ናት?" አለኝ ሳግ እየተናነቀው::

" የመጀመሪያዋን ልጅ ተገላግላለች:: እስከመጨረሻው መታገስ አቅቶኝ ነው የደወልኩልህ::"

" አልሃምዱሊላህ " ብሎ አምላከን አመሰገነ::

" አየህ አላህ በሁሉም አላሳዘነህም:: ሲጳራን ቢወስድብህም ልጅ ሰጥቶሃል" እያልኩ ያፅናናዋል ብዬ የማስበውን ሁሉ አወራው ገባሁ:: ዕንቁጣጣሽ እየሮጠች መጣችና ከጀርባዬ ቆማ " ተገላገለች..." ብላ ጮኸች::

" አሚ፣ እንኳን ደስ አለህ:: ሁለተኛውንም ልጅ በሰላም ተገላግላለች እያለችኝ ነው ዕንቁ.."

"አልሃምዱሊላህ አባከህ ላናግራት፤ አገናኘኝ::" አለኝ ተጣድፎ::

"ቆይ እሺ:: ካስገቡን ደውዬ አገናኝሃለሁ::" አልኩና ስልኩን ዘግቼ ስዞር ዕንቁጣጣሽ አፍጥጣ አየችኝ:: ማልቀሴን ስትረዳ ግድግዳውን ተደግፋ መንሰቅሰቅ ጀመረች::

"ዕንቁ፣ እዚህ መለቀስ የለበትም:: የምንቀበለው ወደዚህ ዓለም ገና የመጡ እንግዶችን እኮ ነው::" ብዬ አቅፌ አፅናናኋትና ይሄት ወደ ውስጥ ገባሁ::

ሊዲ ጋር ስንገባ መንታ ልጆቿን አቅፋ በስስት ስትመለከት ደረስን:: እኛን ስታይ "እንኳን ደስ አላችሁ ደስ የሚሉ ልጆች ወለድኩ:: አልሃምዱሊላህ::" አለችን:: ግን ፈገግታዋ ከመቅፅበት ጠፋና አፈጠጠችብን:: ከዚያም ከፍሉ ውስጥ የነበሩትን ሁለት ነርሶች እናቷን በመነቅነቅ ጠርታ ልጆቿን አስታቀፈቻቸውና

"ሲጳራ አረፈች አይደል?" አለችን እንባዋ ቁልቁል እየተንደረደረ::

"ሊዲ፣ አምላክ የሰጠሽን ልጆች እንምባ አትቀበያቸው:: ተረጋጊ::" ብዬ ተጠግቼ አቀፍኳት:: ድምጿን ላለማውጣት ከንፈሯን ነክሳ ተንሰቅስቃ አለቀሰች:: እሷን ካረግጋጋኋት በኋላ አማን ጋር ደውዬ አገናኘኋቸው::

"አሚ፣ አይዞህ እሺ::" አለችው ስልኩን ተቀብላኝ::

"እንዴት ነሽ አንቺ፣ ሊዲ ደህና ነሽ? "

"አልሃምዱሊላህ፣ በሰላም ተገላግያለሁ:: አሁን...ከሀዘናችን የሚያፅናኑን ልጆች አሉን:: ኢና ሊላሂ ወኢናኢለይሂ ለራጂኡን::" ዕምባዋን ጠረገችና፤

"መጀመሪያ ለተወለደችው ልጃችን ስም አዘጋጅቼላት ነበር፣ ልንገርህ?"

"ንገሪኝ ማን አልሻት?"

"አውቄ ደብቄህ እንጂ ሲጳራ ብያታለሁኝ::" አለችው:: እኔና ዕንቁጣጣሽ ተያይተን በገረሜታ ራሳችንን ነቀነቅን::

ሕይወት ትገርማለች:: ሕፃኗ ሲጳራ በተወለደችበት ደቂቃ ትልቋ ሲጳራ አንቀላፋች:: ምናልባትም ደቂቃው ብቻ ሳይሆን ሰከንዱም ተገጣጥሞ ይሆናል፤ የሞትና የሕይወቱ::

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner

ምናልባትም ሁለቱ ሲጻራዎች ቀጠሮ ይኖራቸው ይሆናል፡፡ የሊዲ ሲጻራን ደግሜ ካላየኋት ሞቼ እገኛለሁ ማለት ቁርጥ ቀን መሆኑን ተረድታ ይሆን? ትናንት ቀናት ይቀሩታል የተባለለት ምጧ ዛሬ ተቻኩሎ የመጣው ቀጠሮውን ለማክበር ይሆን? እግዚአብሔር ያውቃል፡፡

እኔ ግን ከኮብላይ ካህን ጋር ያለኝ ጉዞ ገና አላበቃም፡፡ ሊዲም በህልሟ፣ ከካህኑ የተቀበለችውን ጀንያ ወርቅ ይዛ እንደቆመች፣ የደጃፉም በር ተመልሶ ሳይዘጋ እኔም ከኮብላዩ ካህን ጋር እያወጋሁ፣ ከዓይኗ ርቀን ሄደን የለ?... እናም ገና ጉዞ አለብኝ፡፡ ካህኑ እንዳለው፣ ከእርሱ ማንነት ይልቅ የራሴን ማንነት የምቆፍርበትና ወደ ነፍሴ የምጠልቅበት ረጅም ጉዞ ከፊቴ ይጠብቀኛል፡፡

ተፈፀመ

"በእርግጥ የየትኛውም ጉዞ ፍጻሜ፤ የሌላ ጉዞ መነሻ ነው፡፡"

15/02/2001 ዓ.ም.

ዓለምአየሁ ደመቀ

Scanned with CamScanner

Scanned with CamScanner



ዓለማየሁ ደመቀ

ከግጥምና ዜማ ደራሲው ዓለማየሁ ደመቀ ጋር ለአፍታ ማውጋት ጨዋታ ብቻ አይደለም፤ ትላልቅ ሀሳቦችን የያዙ ትናንሽ መጻሕፍትን እንደማንበብም ጭምር እንጂ። ከመጻሕፍትም የፍልስፍና መጻሕፍት። ደራሲው ለዓመታት በዘፈን ግጥሞቹ ሠላምና ፍቅርን ሲሰብከን እንደኖረው ሁሉ አሁን ደግሞ "ዮቶር (ኮብላይ ካህን)" የተባለውን ልቦለድ ለ7 ዓመት ገደማ ጽ[illegible] ካስቀመጠበት አንስቶ "እንካችሁ" ብሎናል። ልቦለዱ እንደሚጠበቀው ታሪክ ነግሮን የሚያበ[illegible] አይደለም። ውስጣችንን ንጦ አንዳች የለውጥ ማዕበል ያስነሳል። ጨርሰን የምናበቃው ታሪ[illegible] አይደለም ያለው ፤ ጨርሰን እንጀምራለን። በእያንዳንዱ ምዕራፍና ገጽ ታሪክን ፣ ሀሳብን ፣ ፍልስፍናን ፣ ሥነልቦናን ፣ እምነትን ፣ ድብቁንና የተጠላለፈውን የእጣ ፈንታን ምሥጢ[illegible] እንፈትሸበታለን። ከኮብላዩ ጋር አብረን በፈቃዳችን እንኮበልላለን። ካህኑ ወደ ነበረበት ሲመለስ የእኛ ጉዞ ግን አያበቃም ፤ ይቀጥላል። ከአንድ ደራሲና ድርሰቱ የሚጠበቀውም ይኸው ነው።

ቴዎድሮስ ተ/አረጋ[illegible]

"መንፈሰዊው ሥልጣኔ የተመሰረተው ፍቅር ላይ ነው። ፍቅር ደግሞ የሰብአዊነት ቁልፍ ነው። ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው ራሱን ለፍቅር ያስገዛል። በዘመናዊው ወይም በቁሳዊ[illegible] ሥልጣኔ ውስጥ ያላችሁ ተዋናይነት ያልገዛላችሁ እርካታ እና ሰላም በመንፈስ ብትሰለጥኑ ኖሮ ሁሌም ከደጃፋችሁ ይኖራል። ወደ ውስጣችሁ፣ ወደ መሰረታችሁ በመመለስ ላይ ትጉ። ትናንት በገነነው ላይ ዛሬ ሌላው ገንኖ፣ የትናንቱን ገናና በሚያስረሳው ዓለም አትወናበዱ። ዛሬ ተጨብጭቦለት ነገ በሌላው ጭብጨባ በሚዋጠው ወረተኛ ዓለም አትታለሉ።

"ዛሬ ምስኪንና ተመፅዋች የሆነችው ኢትዮጵያ ለዚህ ሁሉ ችግር መድኃኒትና የመፍትሔም ምሳሌ ትሆን ዘንድ ነበር ጥንት የተፈጠረችው። ለዚህ በቆዳ ቀለም፣ በዘርና በሃይማኖት ለምትጨረስ ዓለም አንድ የመሆን ምሣሌና መፍትሔ ነበር መሰረቷ። ዛሬ ግን ያን መሆን አልቻለችም። እናንተ ልጆቿ በነፍሳችሁና በማንነታችሁ ላይ በርትታችሁ ስትሰለጥኑ እሷንም ወደ መሰረቷ ትመልሷታላችሁ። ያኔ ዓለም ለኢትዮጵያ ከምትሰጠው በላይ ኢትዮጵያ ለዓለም የምታበረክተው ይበዛል።" አለኝና ወደ ዝምታው ወረደ። እኔም ወደ ዝምታ መንደሬ ተመልሼ ገባሁ።

* * * * *

"በእርግጥ ትምህርት ቤት ሄዶ መማሩ መልካም ነው። ግን የልብን እውቀት ሽሮ በተጣመመ መንገድ መሄድ ነው ትልቁ አደጋ። እናንተ የዘመኑ ወጣቶች ደግሞ ልባችሁ ከሚነግራችሁ ይልቅ መጽሐፍ የነገራችሁን ብቻ አምናችሁ፣ ግራ በተጋባ እውቀት ውስጥ ትዋኛላችሁ።... ትምህርት ቤትም ገብቼ አላውቅ። አንተም የተፈጥሮን ምስጢር ራስህ መርምረውና የአላህን ቋንቋ ትረዳዋለህ። አላህ ስራውን የሚሰራው በብዙ ምስጢራዊ ጥበቦች ውስጥ ነው። የአላህን ቋንቋ ስትረዳ እውነተኛውን ጥበብ ታገኘዋለህ።" ብለው መለሱልኝ።

ከመጽሐፉ የተወሰደ

**ዋጋ:- 150 ብር**

**ከኢትዮጵያ ውጭ:- 10 $**

ከአርስ ፕህትመትና የማስታወቂያ ሥራ ኃ/የተ/የግ/ማ
0911 487152

Scanned with CamScanner